# የተቀበረ መክሊት

ዲ/አግዛቸው ተፈራ

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

«ጥንታውያንና ፍለጋቸውን የተከተሉ የዘመናችን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንዳስተማሩት።»

መጋቢት 1993 ዓ.ም. ታተመ።

የሽፋን ስዕል   ወንደሰን ገ/ትንሳኤ

## አድራሻ

ጥያቄና አስተያየት ካላችሁ ወይም ወደፊት ማካፈል የምትፈልጉ

በመ.ሳ.ቁ.522 አሰላ

ወይም

በመ.ሳ.ቁ.56307 አዲስ አበባ

ብላችሁ ጻፉልን፡፡

# የተቀበረ መክሊት

# ወደፊት የሚታተም
# «ጥላና አካል»

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ይህችን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ በነገሮች ሁሉ የረዳኝን የመጽሐፏን ባለቤት ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ውድ ጊዜአቸውን መሥዋዕት በማድረግ መጽሐፏን አንበው የጠመመውን አቅንተው፥ የጎደለውን ሞልተው በማረም የረዱኝን አባቶች አቶ ሠርጸ ዕጓለ ጽዮንንና አቶ ጸጋዬ ደምሴን፥ በአንዳንድ የትርጉም ሥራዎች ሞያዊ እገዛ ያደረጉልኝን ኤክስፐርት ዮሴፍ መኮንንን፥ በኮምፒውተር ከመጻፍ ጀምሮ እስከ ማሳተም ድረስ ባለው ሂደት በጊዜአቸው፥ በጉልበታቸውና በገንዘባቸው የረዱኝን ወገኖችና መጽሐፏን ሳዘጋጅ ከጎኔ ሆነው ያበረታቱኝን ወንድሞች ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካቸው!

ይህች መጽሐፍ የያዙት እውነተኛ ትምህርት እንደ ስሕተት ተቆጥሮባቸው ያለአግባብ ከእናት ቤተክርስቲያናቸው ለተገፉና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀደመው እውነተኛ መሠረቷ መመለስ ለሚሹ ወገኖች ሁሉ መታሰቢያ ትሁን!

# ምልከታ

ፍሬን የተሸከሙ ዛላዎች ጎንበስ ይላሉ፣ እንደ ፍሬ አልባ ዛላዎች በቀላሉ በነፋስ እየተወዛወዙ ጭንቅላታቸውን አያሳዩም።

ከ16ኛው ምእተ ዓመት ጀምሮ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ሊቃውንት አንገታቸውን ሲሰየፉ፣ ሲወገሩ፣ በእሳት ሲቃጠሉ፣ የከብት አጎዳ ሲነዳባቸው፣ ምላሳቸውን ሲቆረጡ፣ በተለያየ መቃኒተ ስቃይ ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግም የአካልና የሕይወት ቅጣት ሲፈጸምባቸው ኖሮአል። ከዚህ የተረፉትም ተሰደዱ፣ የቀሩትም የዘረጉት የትምህርት ወንበር በዐዋጅ እንዲታጠፍ ተደረገባቸው፤ ለብዙ ምእተ ዓመታትም ሲጠሩበት የነበረውን "ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ" የሚለውን ስማቸውን ሌሎች ነጠቋቸው።

እንግዲህ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት ሙሉና ፍጹም እውነት ይነገርበትና ትክክለኛው የቅዱሳት መጻሕፍት የብሂል ትርጓሜ ይፈክርበት የነበረው የሊቃውንተ ኦርቶዶክሳዊት ጉባኤ ደብዛው ጠፋ። በምትኩም እንዲያው ጉንጭ፣ ከንፈር፣ ምላስና ጉረሮ ማልፊያ የሆነው ስልተ ትርጓሜ ስፍራውን ያዘ ከዚህ የተነሣም ለእናት ልጆች ማፈሪያ የሆኑ አንደበራ (ዲቃላ) ሥነ ጽሑፎች እንደ አሸን በመፍላት ቤተ ክርስቲያናችንን አጥለቀለቋት። በሁኔታውም ያዘኑ ትሩፋን ሊቃውንት "ሑር ሕዝብየ፣ ባእ ቤተከ፣ ወዕጹ ኆኅተከ፣ ወተኀባእ ኅዳጠ ምዕረ እስከ የኀልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር። - ሕዝቤ ሆይ! ወደ ቤትህ ግባ፣ በርህንም ዘግተህ የእግዚአብሔር ቁጣ እስኪያልፍ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ተሸሸግ።" በተባለው መሠረት (ኢሳ. 26፣20) ለጸሎት በዘጋቸው እልፍኞች ውስጥ ሆነው "ወዬት ሄዱና የተዋሕዶ በሮች፣ ፈሩን አጠፉት የእውጣኬ ወይፈኖች። "እያሉ በእንጉርጉሮና በቁዘማ ረጅሙን የጽሙና ጊዜ አሳለፉት።

ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና፣ ይህን "የተቀበረ መክሊት" ረቂቅ ስናነብ፣ ለካስ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች የማኅበረ ጽዮን ሰማያዊትን ጥፋት አታሳየን፣ (ኢታርእየነ ሙሰናሃ) እያሉ የጽዮንን ምርኮኞች መመለስም እየተጠባበቁ አንቀላፉ እንጂ አልሞቱም ኖሯል ለማለት ችለናል። የፍሬ አልባዎቹን ዛላዎች ያህል ጭንቅላታቸው ከሩቅ አለመታየቱ፣ በነፋስም እየተወዛወዙ እዩን፣ እዩን አለማለታቸው፣ አንድም በወንጭፍ ድንጋይ ከመመታት ለመዳን፣ አንድም ከተሸከሙት ፍሬ ክብደት የተነሣ ጎንበስ በማለታቸው ኖሯል።

ቤተ ክርስቲያን በጉድፍድፍ አዋልድ ድርሰቶች የተቀበረውን መክሊቷን እየቆፈረች ታወጣ ዘንድ ትጉሃን ልጆቿ እንደ ደረሱላት፥ የጽዮን ምርኮኞች እየተመለሱ እንደሆነ፥ የቤተመቅደስንም ተሐድሶ ለመጀመር የጉድፍ ድርሰቶች መጠረግ እንደተጀመረ "የተቀበረ መክሊት" ታበሥረናለች።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምን ማለት እንደ ሆነ የማያውቁ "የተቀበረ መክሊት"ን ያንቡ፥ ተኩላዎችም ያጠለቁትን ለምድ ያውልቁ፥ ቀማኞ ችም መልካሙን ስም ለባለ ስሙ ይመልሱ። በማለት እንመክራለን። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው እውነታ ውጪ የሆኑ መናፍቃን እንኳ ቢያነቧት የቀደመችውን መንገድ የትና የት ትተዋት እንደነጎዱ ታስረዳቸዋለች፥ ለንስሓ የታደሉትንም ወደ ቀደመችው መንገድ ልትመልሳቸው እንደምትችል እናምናለን።

እንግዲህ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት የሥነ ጽሑፎች ምዕራፍ ተከፍቷል፥ "አንተ የምትተኛ ንቃ" እንላለን። ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ደራሲውን እንዲያሳድገው፥ መጽሐፏንም ለብዙዎች በረከት እንዲያደርጋት ምኞታችን ነው።

ሠርጸ ዕጓለ ጽዮንና
ጸጋዬ ደምሴ

## ማውጫ

ምዕራፍ 1 የተደፈነ የውሃ ጉድጓድ .......... 9
የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት (ዶግማ) .......... 12
የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት .......... 21
አምላክ ለምን ሰው ሆነ? .......... 25
ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት .......... 33
ምዕራፍ 2 ውሃ መያዝ የማይችሉ ጉድጓዶች .......... 47
ለቅዱስ ሚካኤል የተሰጠ የፈጣሪ ስፍራ .......... 52
ለቅዱስ ገብርኤል የተሰጠ አምላካዊ ስፍራ .......... 61
ለቅድስት ድንግል ማርያም የተሰጠ የፈጣሪ ስፍራ .......... 67
ለሌሎች ቅዱሳን የተሰጠ የአምላክ ስፍራ .......... 80
የቅዱሳን ተግባርና ተጋድሎ ለምን ነበር? .......... 92
ምዕራፍ 3 የስሕተት መግቢያ በር .......... 95
በትርጉም የተቀበሩ እውነቶችና ቦታ ያገኙ ውሸቶች .......... 100
የአብርሃም እንግዶች .......... 102
ያዕቆብ በሕልሙ ያየው መሰላል .......... 104
የታቦት መባዛት ምስጢር .......... 106
ቃል ኪዳን .......... 109
የእግዚአብሔር የእግሮቹ መቆሚያ ስፍራ .......... 115
የቀረልን ዘር .......... 120
የጽዮን ማንነት .......... 122
የመጻተኞችና የጃንደረቦች መታሰቢያ .......... 127
የቀደመችው መንገድ .......... 131
ፍጻሜን ያገኘው ሕግ .......... 137
ወደጥፋት የሚወስደው ደጅ .......... 145
ራስን ለካህን ማሳየት .......... 147
የእግዚአብሔርን ቅዱሳን መቀበል .......... 155
ምስጢራዊቷ ዕለት ስትታወቅ .......... 157
ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ .......... 159
የቅዱሳን ዕውቀት .......... 161
አምስቱ አዕማደ ምስጢር .......... 167
እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት .......... 171
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ .......... 173
ለቅዱሳን የሚደረግ አገልግሎት .......... 177
ፀሐይን የተጐናጸፈችው ሴት .......... 179
ከሞት በኋላ የቅዱሳን ተግባር .......... 182
ጽድቅ በሥራ ወይስ በእምነት .......... 188

# መግቢያ

ሰዎች በየጊዜው እናት ቤተ ክርስቲያናቸው የሆነችውን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን እየተዉ ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ለምን ይፈልሳሉ? ለዚህ ዓይነተኛ ጥያቄ ለገንዘብ ሲሉ ነው፤ ሌላ ጥቅም ስለሚያገኙ ነው፥ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ነው፥ ክደውና ተሳስተው ነው . . . ወዘተ የሚሉ ምላሾች ከውስጥ ከቤተክርስቲያናችን ሰዎች ሊሰጡ ቢችሉም እነዚህ ምላሾች በተለይ በዘመናችን ተቀባይነት የሌላቸው ያረጁና ያፈጁ ናቸው። ከዚህ ይልቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እውነተኛ መሠረት ያላት ቤተ ክርስቲያን ብትሆንም በዘመናት ብዛትና በተለያዩ ተጽዕኖዎች እውነቷ ተቀብሮ ልዩ ልዩ እንግዳ ትምህርቶችና የፈጠራ ድርሰቶች ስለሸፈኑት ትውልዱ የሚፈልገውን እውነቷን ለማግኘት ባለማቻሉ ነው ቢባል ያልተጋነነ ምላሽ ይሆናል።

እርግጥ ለገንዘብና ለተለያዩ ጥቅማ ጥቅም ሲሉ እናት ቤተክርስቲያናቸውን ጥለው የሚሄዱ እንዳሉ ባይካድም የዕድል ጉዳይ ሆኖ ጥቅማ ጥቅሙን እዚያው በቤተ ክርስቲያናችን እንዳሉ ሆነው ያገኙት ደግሞ የጥቅማቸው ምንጭ እንዳይነጥፍ ሲሉ የሚያውቁትን እውነት ገልጠው እንደማይናገሩና የተሸቃቀጠ ወንጌል እንደሚሰብኩ ይታወቃል። ሁለቱም ወገኖች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ጥቅም ስለገዛቸው እንዴት ምስኪኖች ናቸው!

ከእነዚህ ጎራ የማይመደበው ወገን ግን ወደ ሌሎች አብያተክርስቲያናት የሚፈልሰው እውነትን ፈልጎ አሊያም ደግሞ የያዘው እውነተኛ ትምህርት እንደ ኑፋቄ ተቆጥሮበትና "መናፍቅ" የሚል ስም ተሰጥቶት ስለሚሰደድ ነው።

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ይህ ትውልድ የሚፈልገውን እውነት በውስጧ ይዛለች። ነገር ግን እውነቷን ባልተዛባና ትውልዱ በሚፈልገው መንገድ ገልጣ ልታቀርብ አልቻለችም። አብዛኛዎቹ የስብከት መድረኮቿ የተሞሉት ሌላውን በመንቀፍ ወግና ሥርዓትን ታሪክን በመተረክ ላይ በተመሠረቱ ስብከቶች ነው። በማኅበርና በግል ደረጃ በጽሑፍ የሚተላለፉ መልእክቶችም ይኸው ገጽታ ነው ያላቸው።

ያለባትን ችግር በመረዳት በሚፈለገው ሁኔታ ወንጌልን የሚሰብክ አንድ ሰው ቢነሣ እንኳ በጥርጣሬ መንፈስ እየታየ በተለያዩ ውንጀላዎች ከመድረክ የሚወገድበት መንገድ ይፈለጋል።

በዚህ እኩይ አድራጎት ቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ሊጠቅሟት የሚችሉ አገልጋዮቿን ዐጥታለች። ስለዚህ በየጊዜው የገዛ ልጆቿን ወልዳ አሳድጋ ለሌላ ከምትሰጥ "ልጆቼ ምንድነው የሚፈልጉት? ከኔ ፈልገው ያልሰጠኋቸው ነገር ምንድነው? የሚፈልጉትስ ነገር በኔ ዘንድ የለምን? ብላ ራሷን በመጠየቅ ዐቋሟን ልታስተካክል በተገባት ነበር። እውነቱን እንመስክር ካልን ልጆቿ የሚፈልጉት ከድርጅት ወደ ድርጅት መዛወርን ሳይሆን እውነትን ነው። እውነት ደግሞ ሰው ሆኖ በተገለጸው በክርስቶስ ኢየሱስ አለ። (ኤፌ. 4፥21) ስለሆነም ሳትበርዝና ሳትከልስ የሚፈልጉትን እውነት በትክክል ልትሰጣቸው፥ ሁሉን ከኃጢአቱና ከድካሙ የሚያሳርፈውን የክርስቶስን የመስቀል ላይ ፍቅሩን፥ ወሰንና ድንበር የለሽ ምሕረቱንና ቸርነቱን ልታሳያቸው ይገባል። እርሱ መድኃኒታችን የእግዚአብሔር ምስጢር ነውና የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉም በእርሱ ነውና። (ቆላ. 2፥2-3) በእርግጥ ልጆቿ ይህን ካገኙ ወደየትም አይሄዱም።

እውነት ነው፤ ትውልዱ እግዚአብሔርን ይፈልጋል። (መዝ. 23፥6) ፍላጎቱን በቃላት የመግለጽ ተነሣሽነት ባይኖረውም እርሱ ሊያስተውለው የማይችለው የልቡ መሻት ግን "ኢየሱስን ማን ያሳየኝ? በጎውን ማን ይነገረኝ?" የሚል ነው። (መዝ. 4፥6)

በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው የጌታን ዝና በሩቁ ሰምተው የነበሩትና የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት የግሪክ አይሁድ ለሐዋርያው ፊልጶስ ያቀረቡት ጥያቄ ከዚህ ትውልድ ጥያቄ ጋር ይመሳሰላል። (ዮሐ. 12፥21)

ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና በፊልጶስ ቦታ ላይ የሚገኙ አገልጋዮች ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ለሚፈልገው ትውልድ በግልጽ የማሳየትና የማስተዋወቅ ትልቅ የኃላፊነት ድርሻ አለባቸው። ይህ ሁሉ እንዳይሆን ግን ቤተክርስቲያናችን ብዙ መንፈሳዊ ችግሮች አሉባት። በተለይም ደግሞ ያላት እውነት ርቆ ስለተቀበረና ብዙ ስሕተቶች ስለሸፈኑት እውነትን ከመቃብሩ ቆፍሮ አውጥቶ ትንሣኤ ለመስጠት አስቸጋሪ ጉዳይ ነው።

ለዚች አነስተኛ መጽሐፍ "የተቀበረ መክሊት" የሚል ስያሜ የተሰጣት ተቀብሮ ለዘመናት የኖረውን እውነትና ይህን እውነት ሸፍኖ የያዘውን ሐሰተኛ ትምህርት በመጠኑም ቢሆን ጠቋሚ ልትሆን ስለምትችል ነው።

እግዚአብሔር መክሊትን የሚሰጠው ተነግዶ እንዲተረፍበት እንጂ ተቀብሮ ያለትርፍ እንዲቀመጥ አይደለም። እንዲህ ማድረግ ምን ያህል እንደሚያስጠይቅ ከወንጌል መረዳቱ ብቻ በቂ ይሆናል። (ማቴ. 25፥13-30)

ቤተ ክርስቲያናችን ከእግዚአብሔር የተቀበለችውን የእውነት መክሊት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ቀብራ በመኖሯ የተጠቀመችው አንዳች ነገር ወይም ያስገኘችው ትርፍ የለም። ይልቁንም ለትልቅ መንፈሳዊ ክስረት ዳርጓታል።

በዚች መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስቲያናችንን እውነት ለማግኘትና ከተቀበረበት ለማውጣት ሲባል እንኳ ብዙ ተቆፍሯል። ይህ እውነት የተገኘው ከብዙ ውሸቶች መካከል ነው።

ለዚች መጽሐፍ ዝግጅት በዋቢነት ያገለገሉት የቤተክርስቲያናችን መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ተስማሚነት አላቸው ለማለት ባያስደፍርም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታቸውን በመተው ለዓይነት ያህል ከመሀል ጣል ጣል የተደረገውን እውነት ስንመለከት ግን የእውነቱን ዱካ ለማግኘት ለሚባዝኑት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ልጆች በእጅጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል።

ስለዚህ ይህችን መጽሐፍ የምታነቧት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ አስቀድሞ ከሰማሁት ውጪ ሌላ ነገር መስማት አልፈልግም፤ የያዝኩት ብቻ ትክክለኛ ነው ይበቃኛል፤ በሚሉትና በመሳሰሉት ጠባብ አመለካከቶች ሳትያዙ መጽሐፏን በልበ ሰፊነት አንብባችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር እንድትረዷት፥ እውነቷን ከስሕተቷ እንድትለዩና ሕይወታችሁን በእውነቷ መሠረት ላይ እንድታቆሙት ትጋብዛለችሁ።

ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሳሳተ ግምት የነበራችሁ ወገኖችም ብትኖሩ ቤተ ክርስቲያናችን ከጊዜ በኋላ የተነሡ

ሰዎች ቢያበላሻሹትም እውነተኛ መሠረት ያላት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ተረድታችሁ የተሳሳተ ግምታችሁን ከተጨባጩ እውነታ አንጻር እንድታስተካክሉ እጠቁማለሁ።

ከአዘጋጁ

## ምዕራፍ 1
## የተደፈነ የውሃ ጉድጓድ (ዘፍ. 26፥15-22)

ሕይወት ላለው የፍጥረት ወገን እጅግ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል ውሃ ግንባር ቀደሙ ነው። ሕይወት ያላቸው ፍጥረቶች ያለ ውሃ ህልውና አይኖራቸውም። በመሆኑም በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ የሰው ልጆች ኑሮአቸውን ሁሉ የሚመሠርቱት ከውሃ ማግኘት ጋር በተያያዘ መንገድ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታላቁ የእምነት አባት አብርሃም ጌራራ በተባለው ስፍራ በስደት ሲኖር ለእርሱና ለቤተሰቡ እንዲሁም ለእንስሶቹ ፍጆታ የሚውል ውሃን ለማግኘት ሲል በዘመኑ ጥበብ (ዘዴ) ተጠቅሞ በጌራራ ሸለቆ ባስቆፈራቸው ጉድጓዶች ውስጥ በሚገኘው ንጹሕ ውሃ በዘመኑ አብርሃምና መላው ቤተሰቡ እንስሳቱም ጭምር ተጠቅመው ነበር። ታሪክ ተደገመና ከአብርሃም ሞት በኋላ ልጁ ይስሐቅም በራብ ምክንያት ተሰድዶ ወደ ጌራራ መጣ። በዚያ ሲኖር ግን ውሃን ለማግኘት ሌላ ዐዲስ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር አላስፈለገውም። አባቱ አስቆፍሮ በተጠቀመባቸውና እርሱ ከሞተ በኋላ ፍልስጥኤማውያኑ በደፈኑአቸው የውሃ ጉድጓዶች ለመጠቀም ወደደ። ምንም እንኳ በተለያዩ ቆሻሻ ነገሮች የተደፈኑትን የአባቱን የውሃ ጉድጓዶች እንደገና መቆፈር አሰልቺና እልህ አስጨራሽ ቢሆንም አባቱና ቤተሰቡ ከጠጡት ንጹሕ ውሃ ለመጠጣት ጽኑ ፍላጎት ያደረበት ይስሐቅ ይህን አድካሚ ሥራ ለመሥራት ታጥቆ ተነሣ። በተለያዩ ቆሻሻ ነገሮች ተደፍነው የኖሩትን ጉድጓዶችም እንደገና አስቆፈረና አብርሃም ይጠራቸው በነበረው ስም መልሶ ጠራቸው።

ከዚህ ሁሉ ድካም በኋላ ግን ይስሐቅን የገጠመው ችግር አሳዛኝ ነበር። ለብዙ ዘመናት በተለያዩ ቆሻሻዎች ተደፍነው የቆዩት የአብርሃም የውሃ ጉድጓዶች ዳግመኛ ተቆፍረው የአብርሃም ወገን የሆነ ሁሉ እንዲጠቀምባቸው የማይሹት ፍልስጥኤማውያን ሥራውን በመቃወም በጉድጓዶቹ ላይ የይገባናል ጥያቄ አቀረቡ። ይስሐቅም የአባቱን የውሃ ጉድጓዶች ቢፈልጋቸው እንኳ ከጠቡ ለመራቅ ሲል መተውና ሌላ መቆፈር ግድ ሆነበት።

የዚህ ትውልድ ዕጣ ፈንታም ከዚህ ያልተለየ ነው። ትውልዱ አባቶቹ የጠጡትንና መንፈሳቸው የረካበትን ንጹሕ ውሃ በእጅጉ ይፈልጋል። ከዘመናት ብዛትና ወራሽ ከመታጣቱ የተነሣ የአባቶች

የንጹሕ ውሃ መገኛ ያ ጉድጓድ በተለያዩ ቆሻሻ ነገሮች ተደፈነ። የተደፈኑትን ጉድጓዶች እንደገና መቆፈር ለትውልዱ አሰልቺና እልህ አስጨራሽ ስለሚሆንበት፤ እንደገናም ቆሻሻውን ቆፍሮ ለማንሣት ደፋ ቀና ማለት ሲጀምር ጉድጓዱን ለደፈኑት ሰዎች ወገን የሚሆኑ ክፍሎች ስለሚከለክሉት የአባቶቹን ጉድጓድ ትቶ ሌላ ለመቆፈር ይገደዳል።

እግዚአብሔር ለቀደሙት የብሉይ ኪዳን አበው በነቢያቱ አፍ የተናገረውና ተስፋ የተገባለት ዘላለማዊ ዕቅዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ማርያም ተወልዶ ስለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት ቤዛ ሆኖ በመሞቱና በመነሣቱ እውን ሆኗል። በዘመኑ ፍጻሜ ለድኅነታችን የተገለጸውን ይህን እውነት ጌታ ለቀደምት ደቀመዛሙርቱ፥ ደቀመዛሙርቱም በእነርሱ ፍለጋ ለተተኩት የቤተክርስቲያን አበው በትውፊት እያስተላለፋት ከዘመናችን ደርሷል። (2ጢሞ. 2፥2) ሆኖም ተቀብሯል።

በዚህም ምክንያት በተለያዩ የፈጠራ ድርሰቶች ያልደፈረሰውን ንጹሕ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አሁን ካለችው ቤተ ክርስቲያናችን ለማግኘት የማይቻል ሆኗል። ለዚህም ይመስላል ትውልዱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በተከታዮቹ ሐዋርያት የተሰበከውን ወንጌል በእጅጉ የሚሻው። በስም ጥንታዊቷ በተግባር ግን ዐዲሲቷ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስንና የሐዋርያቱን ትምህርት ቀብራ በዐዲስ ልብ ወለድ ትምህርቶች መሞላቷና የእግዚአብሔርን ክብር ለፍጡራን መስጠቷ ፍንትው ብሎ ስለሚታየው የልቡ ደርሶለት መሻቱን ሊፈጽም ባለመቻሉ ትውልዱ እናት ቤተ ክርስቲያኑን እየተወ ወደ ሌላው ለመሄድ ተገድዷል።

ለአንዳንዶች "ዐዲስ ትምህርት" ሲባል አሁን በቅርብ የተገኘ ብቻ ይመስላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ከያዘው እውነት ውጪ የሆነው ሁሉ ዐዲስ ትምህርት ነው። የትክክለኛው ትምህርት መለኪያ የዕድሜ መርዘም ወይም ማጠር ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ብቻ ነው። ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው "ዐዲስ" የሚሰኙ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያናችን ሞልተዋል። ቢሆንም በወንጌል ከተሰበከው ውጪ የሆኑት ልዩ ልዩ ትምህርቶች በሐዋርያት ሥልጣንና ቃል የተወገዙ ናቸው። ". . . ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ።

ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።" (ገላ. 1፥8-9)

ትውልዱ ግን ሊያስተውል የሚገባው ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ጉድጓዱ ውስጥ የተሞላውን ቆሻሻ ነገር ብቻ መሆን የለበትም። ቆሻሻው ቢነሣ ሊገኝ የሚችለውን ያንን ቀደምት አባቶቹ የጠጡትን ንጹሕ ውሃም ጭምር ነው እንጂ።

## የቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት (ዶግማ)

ክርስትና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የተመሠረተና የተደመደመ ሃይማኖት ነው። ይህም ሲባል መሠረተ እምነቱና (ዶግማውና) ሥርዓቱ (ቀኖናው) ሁሉ በአንድም በሌላም መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ማለት ነው።

ከሕዝብም ከአሕዛብም ወገን የሆኑትንና በክርስቶስ አዳኝነት ያመኑትን ወገኖች በማሰባሰብ መንፈሳዊት ጉባኤ የሆነችው አንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ለሐዋርያቱ ያስተላለፈውን እርሱ ካረገ በኋላም መንፈስ ቅዱስ መጥቶ የገለጠውን ትምህርት (ዮሐ. 16፥12-13) ከሐዋርያቱ ተቀብላ ስትመራበት ቆይታለች። ይህም ከጥንት ጀምሮ "የሐዋርያት ትምህርት" ተብሎ ይጠራ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጭ ይሰጣል። (የሐዋ. ሥራ 2፥42) የሐዋርያት ትምህርት መሠረት እምነት በመሆኑም የሃይማኖት መግለጫዎችን ወይም ውሳኔዎችን እንደያዘ የሚጠቁመንን ሌላ ክፍልም እናገኛለን። (ዕብ. 6፥2) በዚህ ትምህርት መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ 4ኛው መቶ ክ/ዘ ድረስ ስትመራ መቆየቷን ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረዳት አያዳግትም።

ዘመነ ሐዋርያትና ዘመነ አርድእት አልፎ ቤተ ክርስቲያንም በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ብቻ መወሰኗ ቀርቶ እየተስፋፋችና አብዛኛውን የዓለም ክፍል እየሸፈነች ስትመጣ ያላትን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅና የቀደሙት ሐዋርያት እንዳደረጉ (የሐዋ. ሥራ 15፥24-29) የትምህርትን ዐረሞች ለማረምና ነቅሎም ለመጣል እንዲረዳት የስብከተ ወንጌል ክልሎችን በአራት አህጉረ ስብከት አመራር ሥር ከፈለች። እነዚህም የአህጉረ ስብከት መናብርት የሚገኙባቸው ከተሞች ሮም፥ እስክንድርያ፥ ኤፌሶንና (በኋላ ቍስጥንጥንያና) አንጾኪያ ሲሆኑ የተቀሩት አገሮች ግን እንደ ቅርበታቸውና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ከአራቱ በአንደኛው ውስጥ እንዲታቀፉ ተደርጓል። አራቱም መናብርት ባሉባቸው ከተሞች በሊቀ ጵጵስና ማዕርግ የሚሾሙ አባቶች ተሠይመው በየአቅራቢያቸው ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት እንዲያስተዳድሩ፥ የወንጌልን ሥርጭት እንዲከታተሉና እንዲያፋጥኑ የስሕተት ትምህርቶችንም እንዲቆጣጠሩ ስምምነት ተደርጓል። (ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ 1ኛ ክፍል አንቀጽ 4፥ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁ.12)

አንዲቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ መዋቅር ዘርግታ ወንጌልን ለማዳረስ በምትፋጠንበት በዚያ ዘመን ከሐዋርያት ተቀብላ ስትመራበት የቆየችውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚያደፈርሱ የኑፋቄ ትምህርቶች ብቅ ብቅ ብለው የአንዲት ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አንድነት ለመከፋፈልና ህልውናዋንም ለማናጋት በመሞከራቸው ቤተ ክርስቲያን የወከለችው ጉባኤ በየጊዜው ተሰብስቦ የመናፍቃንን ትምህርተ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ቃል እየመረመረ እውነቱን በመግለጽና ስሕተታቸውን ዐርመው እንዲኖሩ ዕድል በመስጠት ፍትሐዊ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። ነገር ግን መናፍቃኑ ነፋቄያቸውን ጥለው በቀናው መንገድ ለመጓዝ እንቢተኞች በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን እነርሱንም ትምህርታቸውንም ከአንድነቷ አውግዛ ስትለያቸው ለራሷ ደግሞ በኑፋቄያቸው አንጻር መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የሃይማኖት መግለጫ አውጥታ የእምነቷ ደንብ አድርጋ እየተጠቀመችበት ትገኛለች። በኒቅያ በ325 ዓ/ም የአርዮስን፥ በቁስጥንጥንያ በ381 ዓ/ም የመቅዶንዮስን ትምህርተ ሃይማኖት ለመመርመር የተሰበሰቡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሁለቱ ጉባኤዎች መጨረሻ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ ዛሬ ጸሎተ ሃይማኖት በመባል የሚታወቀው ነው።

ጸሎተ ሃይማኖት የተሰኘው የሃይማኖት መግለጫ 12 አንቀጾች ያሉት ሲሆን ሰባቱ በኒቅያ ጉባኤ፥ አምስቱ ደግሞ በቊስጥንጥንያ ጉባኤ የተረቀቁ ናቸው። ሁሉም ልብ ይላቸው ዘንድ አሥራ ሁለቱም አንቀጾች በግእዝና በአማርኛ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

<u>የኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት በግእዝ</u>

1. ነአምን በአሐዱ አምላክ አብ አኀዜ ኲሉ ገባሬ ኲሉ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ
2. ወበአሐዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ባሕቲቱ ዘተወልደ እምአብ ወውእቱ እምባሕርየ አብ አምላክ ዘእም አምላክ ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘበአማን እም አምላክ ዘበአማን ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዋሕድ ምስለ አብ በመለኮቱ ዘቦቱ ኲሉ ተፈጥረ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ
3. ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ ተሠገወ ወተሰብአ
4. ሐመ ወሞተ ወተቀብረ
5. ወተንሥአ ዳግመ በሣልስት ዕለት
6. ዐርገ ውስተ ሰማያት

7. ወይመጽእ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወበመንፈስ ቅዱስ

አማርኛው፥

1. በአንድ አምላክ እናምናለን ሁሉን የያዘ አባት ሁሉን የፈጠረ የሚታየውንም የማይታየውንም
2. በእግዚአብሔር ልጅ በአንድ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፥ ብቻውን ከአብ የተወለደ ይኸውም ከአባቱ ባሕርይ ከአምላክ የተወለደ አምላክ፥ ከብርሃን የተወለደ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተወለደ እውነተኛ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮት ከአባቱ ጋር አንድ የሚሆን፥ ሁሉ በእርሱ የሆነ በሰማይም በምድርም
3. ስለእኛ ስለሰዎች ስለመዳናችንም የወረደ፥ ሥጋ የሆነ፥ ሰውም የሆነ
4. የታመመ (መከራን የተቀበለ) የሞተ የተቀበረ
5. በ3ኛው ቀን ዳግመኛ የተነሣ
6. ወደ ሰማያት የወጣ
7. ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ፤ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን።

የቍስጥንጥንያ አንቀጸ ሃይማኖት በግእዝ

8. ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት
9. ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት
10. ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት
11. ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን
12. ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም

አማርኛው፥

8. በጌታ፥ በአዳኝ፥ ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ እንስገድለት እናመስግነው
9. በሁሉ ባለች በሐዋርያት ጉባኤ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን
10. ለኃጢአት ማስተስረያ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን
11. የሙታን ትንሣኤን ተስፋ እናደርጋለን

12. የሚመጣውን ሕይወት እንጠባበቃለን ለዘለዓለሙ አሜን!

በቍስጥንጥንያው ጉባኤ የመጨረሻዎቹን አምስቱን አንቀጾች ከማርቀቅ ባሻገር በኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ውስጥ ተጨማሪ (ሥርዋጽ) ቃላትን የመጨመር ሥራ ተከናውኗል። በተጨማሪ ሆነው በሥርዋጽ የገቡት ቃላት 3ኛው አንቀጽ ላይ "እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም ድንግል" 4ኛው አንቀጽ ላይ "ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ" 5ኛው አንቀጽ ላይ "በከመ ጽሑፍ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት" 6ኛው አንቀጽ ላይ "በስብሐት" "ወነበረ በየማነ አቡሁ" በ7ኛው አንቀጽ ላይ ደግሞ "ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ" የሚሉት ናቸው።
(የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ከአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 113-114፤ 130-131)

እነዚህ የሃይማኖት ውሳኔዎች የተላለፉት በሌሎች ስብሰባዎች እንደሚደረገው ሌሎችን ጎድቶ የራስን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በድምፅ ብልጫ በዚህ እናምናለን፤ በዚህ ደግሞ አናምንም በሚል ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል በሚለው መሠረት ተጠንተው ነው። ምንም እንኳ ውሳኔው ቃል በቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ የተቀዳ ባይሆንም የያዛቸው መልእክቶች ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ይኸው የእምነት መግለጫ (ጸሎተ ሃይማኖት) ነው። ከዚህ ውጪና ተጨማሪ የሆነ መሠረተ እምነት ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን ድረስ የላትም፤ ለወደፊቱም አይኖራትም። በአባ መልከጼዴቅ የተጻፈው ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 3 ይህንኑ ይመሰክራል፣ "ይህ ተአምኖ ሃይማኖት ለትምህርት ለምስክርነት በቂ ስለሆነ ማንኛውም ሊቅ ስለዶክትሪን ሰፋ አድርጎ እጽፋለሁ ቢል ከዚህ ውጪ ሊሄድ ከቶ አይችልም፤ እንዲሁም በመጠኑ ቢጽፍም ከዚህ ውስጥ የሚቀንሰው የሚተወው የለም። ምክንያቱም መጀመሪያውኑ በጥሩ መልክ የተዘጋጀ ስለሆነ ያለምንም ለውጥ ለመኖር ይችላልና"

በተጨማሪም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረተ እምነት በአጠቃላይ በ6 እንደሚከፈል እኚሁ አባት በሌላው መጽሐፋቸው ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል:- "የቤተ ክርስቲያን ዶግማ በአጠቃላይ በ6 ክፍል ይከፈላል ይኸውም:-

1. የእግዚአብሔርን ህልውና ማወቅና ማመን፤ ይህም ማለት እግዚአብሔር አምላክ የነበረ፥ ያለ፥ የሚኖር አምላክ እንደሆነ፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ፥ ያለ እርሱ አንድም የሆነ የሌለ አምላክ እንደሆ ማመን፤
2. እግዚአብሔር በሦስትነት፤ እግዚአብሔር በአንድነቱም በሦስትነቱም ጸንቶ ያለ አምላክ ስለሆነ ሦስትነቱ ሳይጠፋ በሦስትነቱም ርባኤን ሳያመጣ የሚኖር አምላክ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅና ማመን፤
3. ዓለም በጠቅላላ፤ ሰማይና ምድር በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ የሚታየውም የማይታየውም የራቀውም የቀረበውም ሁሉ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ለተቀደሰ ዓላማ መፈጠሩን ማመን፤
4. ድኅነተ ዓለም፤ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ በሰው በደል ምክንያት ለጥፋት ተዳርጎ መኖሩ፤ የታወቀ ነው፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ነውና ስለታረቀው ቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን እንደላከ ግልጥ የሆነ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነው። የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተገለጠው በዚህ ዓለም ድኅነት ነው። የዘላለም ተስፋቸውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ መሆኑን ማወቅ፤
5. ምስጢረ ተዋሕዶ፤ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ አምላክ ወሰብእነቱ በተዋሕዶ መሆኑን ማመን ተገቢ ነው፤ ይኸውም መለኮት ከሥጋ አካልና ከሥጋ ባሕርይ ጋር ሥጋም ከመለኮት አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ አምላክ ወሰብእ መባሉ ረቂቅ ምስጢር እውነተኛም ሃይማኖት መሆኑን ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ምክንያት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየተባለች የምትጠራ መሆኗን መረዳት፤
6. ምስጢረ ምጽአት፤ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ይህንም ዓለም አሳልፎ ሌላ ዐዲስ ዓለም እንደሚተካ ኦርቶዶክሳዊ እምነታችን ነው። (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረተ እምነትና የካህናት ተልእኮ ከአባ መልከ ጼዴቅ ገጽ 104 - 105)

ይሁን እንጂ ለዘመናት ቤተ ክርስቲያናችንን ከመሪዋ ከመንፈስ ቅዱስ ለይተው ያስኮበለሏትና ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ እንደ ገዛ ፈቃዳቸው እያሽከረከሩ በመምራት ስተው ያሳቷት ጊዜ የሰጣቸው ጣልቃ ገብ ነገሥታትና አቀንቃኞቻቸው ናቸው። ለራሳቸው ክብርና ዝና እንዲሁም የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘምና ኑሯቸውን ለማደላደል ሲሉ ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት የሃይማኖት ውሳኔዎች ውጪ የሆኑትንና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚቃረኑትን ኑፋቄዎች ሌላ አውጋዥና ከልካይ በሌለበት የሥልጣን ዘመናቸው

ወደቤተ ክርስቲያን በዐዋጅ በማስገባት የተከሉብን ክፉ መርዝ ሥር ሰድዶ የአንዲቱን ቤተ ክርስቲያን ልጆች በመከፋፈል የጎሪጥ እንዲተያዩ አድርጓል። በተጨማሪም ራሱን እውነተኛ አድርጎ በማስቀመጡ አማኙንና ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ልጅ መናፍቅ፥ በእስተምህሮው መናፍቅ የሆነውን ደግሞ አማኝ ሲያሰኝ፥ ሲያስወጣና ሲያስገባ ቆይቷል።

የስሕተት ትምህርትን በስፋት ይዘው ከሚያራግቡት መካከል ፈሊጠኞች የሆኑት ደግሞ በጊዜው በለስ ቀንቶት ተቀባይ ያገኘው አስተምህሮአቸው የእውነትን ካባ ካልደረበ በቀር ወደፊት ዕርቃኑን እንደሚቀር ቀድመው ስለተረዱ ስሕተታቸውን ይዘው ወደ እውነት መጠጋትን እንደ አማራጭ በመውሰድ ከጸሎተ ሃይማኖትም ሆነ ከስድስቱ የቤተ ክርስቲያን ዶግማዎች ላይ ቅርንጫፍ አበጅተው ኑፋቄአቸውን በማዳቀል ከእውነት ግንድ የወጣ ቅርንጫፍ ለማስመሰል ቢደክሙም የነርሱ ቅርንጫፍ ተቀጽላ እንጂ የግንዱ ትክክለኛ ቅርንጫፍ አለመሆኑን መንፈሳዊ ዐይኑ የበራለት ሁሉ ይለየዋል።

መሠረተ እምነት (ዶግማ) በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የቆመ፥ የሚጨመርበትና የሚቀነስለት ወይም እንደ ሁኔታው ታይቶ የሚሻሻል ነገር የሌለበት ዘላለማዊ ነው። ቀኖና ደግሞ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማካሄድ፥ ወንጌልን ለማሠራጨትና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተግባራት ለማከናወን ሲባል የሚወጣ ሥርዓት ነው። ቀኖና ሥርዓት በመሆኑ እንደጊዜው ሁኔታ ታይቶ መሻሻል የሚደረግበት ነው። ቢሆንም ሥርዓትን የማሻሻልና ያለማሻሻል መብቱ የሁሉም ሳይሆን የቤተ ክርስቲያናችን የበላይ አካል የሆነው የቅ/ሲኖዶስ ነው። አንዳንድ ጠባቦች ግን በዶግማና በቀኖና መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ካለመረዳታቸውና ለመረዳትም ጥረት ካለማድረጋቸው የተነሣ ሁለቱንም አደበላልቀው በመመልከት ሥርዓት አይሻሻልም ወደሚል አቅጣጫ እያመሩና ቤተ ክርስቲያንንም እያወኩ ይገኛሉ። እነርሱ እንዲህ ቢሉም ሥርዓት በባሕርዩ ቋሚነት የሌለው በመሆኑ ከሕዝቡ የኑሮ ደረጃና የአስተሳሰብ እድገት ከዓለም ሥልጣኔም አንጻር እየተሻሻለ፥ እያደገና እየተለወጠ መሄዱ አልቀረም።

ከመሠረተ እምነትና ከሥርዓት ውጪ የሆኑ ብዙ ልምዶችና ባህሎችም በቤተ ክርስቲያን መኖራቸው ይታወቃል። ነገር ግን ተገቢ የሆነ ስፍራቸውን አልያዙም። እንደውም የዶግማውንና የሥርዓቱን ስፍራ አስለቅቀው መሠረተ እምነት መስለው ተቀምጠዋል። ከዚህ

የተነሣ አብዛኛው ሰው ሕገ እግዚአብሔር ቢጣስ ያን ያህል ግድ የለውም፤ ከልማዶቹ ወይም ከሥርዓቱ ጥቂቱ እንኳ ዝንፍ ቢል ዱላ ያነሣል እንጂ በቸልታ አያልፍም። ይህም ከትምህርት ጉድለት የመጣ እንጂ የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ይህ እንዲሆን የሚፈቅድ ስለሆነ አይደለም።

ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አገራችን ፈልሰው የመጡት አይሁድ አምልኮአቸውን፥ ሥርዓታቸውን፥ ባህላቸውንና ልማዳቸውን ጭምር ይዘው መጥተዋል። እነዚህም ሁኔታዎች በሕዝባችን አኗኗር ውስጥ ሠርጸው ስለገቡና የመሠረተ እምነት ያህል ስፍራ ስለተሰጣቸው ሕዝባችን ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዳይል መጋረጃ ሆነዋል። (2ቆሮ. 3፥14-16)

ሁሉም የዓለማችን ማኅበረሰብ ለራሱ የሚወደድ መልካም የሆነ ባህል፥ ሥርዓት፥ ልማድ አለው። ከእግዚአብሔር ውጪ መኩራት ተገቢ አይደለም እንጂ የእኛም የኢትዮጵያውያን ባህል ለራሳችን የሚያኮራን መልካም ባህል ነው። ወደ እምነት ጉዳይ ሲመጣ ግን ሃይማኖትና ባህል ተነጣጥለውና የየራሳቸው ስፍራ ተሰጥቷቸው እንደየደረጃቸው ሊታዩ ይገባል። መቼም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ባህል ስለሌለ ባህልና ልማድን በእምነት ስፍራ ማስቀመጡ ትልቅ ስሕተት ነው። ዛሬ ሕዝባችን ባለማወቅ ዶግማ ወይም ቀኖና አድርጎ የሚወስዳቸው ልማዶች ከቀጥተኛው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አንጻር ሲታዩ ከዶግማ ወይም ከቀኖና ቁጥር የማይገቡ እንዲሁ ልማዶች ብቻ መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህንም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደሚከተለው ገልጸውታል፡- ". . . የብሉይ ኪዳን ልማዶችና ባህሎች ባሁኑ ጊዜ በክርስትና ሃይማኖታችን ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆን እንደ ልማድ ሁነው የሚጠበቁ ናቸው" ካሉ በኋላ በምሳሌነት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክላቸውን እንስሳትና አዕዋፍ አለመመገብን፥ ግዝረትን፥ በአጠቃላይ በሕዝቡ የኑሮ ሥርዓትና ሃይማኖታዊ ስሜት፥ በኀዘን በደስታ ጊዜ ያለው ሁኔታ፥ የበዓላት አከባበር፥ የሴቶችና የሕፃናት ጌጣጌጥ ሁሉ ከአይሁድ የተወረሰ ልማድ መሆኑን ገልጸው ሲያበቁ "በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የማሕሌት ሥርዓት፥ የካህናቱ ልብሰ-ተክህኖ፥ ካባው፥ ድርቡ፥ ጸናጽሉ፥ ከበሮው፥ ኩፋሩ፥ መጠምጠሚያው የታቦቱ ክብርና ሌላውም ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር

ይመሳሰላል።" ሲሉ ጽፈዋል። (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 16-17)

በስተመጨረሻው ላይ ያሰፈሩትና አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩት አረታዊ ሥርዓቶችና ልማዶች ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል ያሉት ግን ነገሮችን አቻችሎ ለማቅረብ ታስቦ ይመስላል እንጂ ብዙ እውነትነት የለውም። እንዲያውም "ይመስላል" ከማለት ይልቅ "ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት የተወረሰ ነው" ቢባል ለተናጋሪውም ለሰሚውም ይመቻል።

በቤተ ክርስቲያናችን ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆኑትንና አሁንም እየተሠራባቸው ያሉትን ትምህርቶችና ሥርዓቶች ምንነት ያለፉትም ሆኑ አሁን ያሉት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አሳምረው የሚያውቁት ቢሆንም ለማስተካከልና ቤተ ክርስቲያናችንን ወደጥንቱ እውነተኛ መሠረቷ ለመመለስ የሚያደርጉት ጥረት እጅግ አናሳ ነው። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ይኖሯቸዋል። ከነዚህም ውስጥ ለማስተካከል እንነሣ ብንል ስሕተቶች ዘመናትን ያስቆጠሩና ሥር የሰደዱ፥ በሕዝቡም ልብ ውስጥ የእውነትን ያህል የሚታዩ በመሆናቸው ሰሚ አናገኝም፥ እውነትን በሚቃወሙ ክፍሎች "መናፍቅ" የሚል ስም ተሰጥቶን እንደተሰደዱት ወንድሞቻችንና ልጆቻችን መሰደድ፥ ከእንጀራችን መፈናቀል ሌላም ሌላም መከራ ይገጥመናል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጽሑፍ አሳባቸውን ለመግለጽ ቢፈልጉ እንኳን የእግዚአብሔር ቃል ምስጢር ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቀድቶ ያለቀ ይመስል አንባቢው ወገናችን እስኪሰለች ድረስ መልሰው መላልሰው የሚጽፉት ያንኑ ተቃዋሚዎች ሁሉ የሚያብጠለጥሉትን አንድ ዓይነት ነገር ነው። ከሺህ አንድ እውነት ለመናገር ደፍረው እንኳ በመካከል አንድን እውነት ጣል ቢያደርጉበት ተቃዋሚዎች በጆሌዎቻቸው ታጅበው ለውግዘት ይነሡባቸዋል። እውነትን የሚያወግዙ መናፍቃን የመብዛታቸውን ያህል ውሸትን በብዕራቸው ጫፍ እንኳ ለመንካት የሚደፍሩ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መታጣታቸው ያሳዝናል። ቤተ ክርስቲያናችን ያሉባትን መንፈሳዊ ችግሮች ሊቃውንቱ የሚያውቁትን ባያህልም ምእመናንም በበኩላቸው የሚያውቁት ብዙ ጉዳይ እንዳለ ግልጽ ነው። ሌላው ሁሉ ይቅርና በአብዛኛው ምእመን ልብ እንኳ ቢያንስ ቢያንስ "ይህስ ትክክል አይደለም" የሚባል አንዳንድ ነገር መኖሩ ሳይጠቀስ አይታለፍም።

እንግዲህ የቀደሙት ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ያስቀመጧቸው አስተምህሮዎች፣ ስርዓቶችና ልማዶች ከቤተ ክርስቲያናችን ትክክለኛ ትምህርት ጋር በመደበላለቃቸው ምክንያት አብዛኛው ሕዝባችን የእግዚአብሔርን ቃል ከሰዎች ወግና ሥርዓት ለይቶ ለማወቅ አልቻለም። የእግዚአብሔርን ቃል ከሌሎች ነገሮች ጋር ሳይቀላቅል ከሚሰብከው ይልቅ የሰው ወግና ሥርዓትን የሚሰብከው ቁጥር በርካታ በመሆኑም ከአምላካዊው ሕግና ሥርዓት ይልቅ የሰውን ሥርዓት አስበልጦ ይመለከታል። ይህ ሁሉ ከንቱ አምልኮ ነው። (ማቴ. 15፥9) ከዚህ ሁሉ ጥፋት ለመዳን የሰው የሆኑትን ነገሮች ከትክክለኛው የቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ውሳኔና ዶግማ አንጻር መመርመርና መልካሙን ሁሉ ይዞ በሃይማኖት ጸንቶ መኖር የያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ወገን ኃላፊነት ይሆናል። (ኤፌ. 5፥10፤ 1ተሰ. 5፥21፤ 1ዮሐ 4፥1)

# የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት

ለብዙዎች መሳሳት እንደዋነኛ ምክንያት የሚቀርበው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ጠንቅቆ አለመረዳት ነው።

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ታላቅ ስፍራ ይሰጠዋል። የዘመን መቀዳደምና የክብር መበላለጥ በሌለበት በክበበ ሥላሴ ከሚገኙት ሦስት አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን የምታምነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዋ ነው። (ዮሐ. 1፥14፤ የሐዋ. ሥራ 20፥28 ፤ ሮሜ 5፥9፤ ቲቶ 2፥13፤ 2ጴጥ. 1፥1፤ 1ዮሐ. 5፥20)

ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮታዊ ባሕርዩ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የማያንስ፥ ትክክል የሆነ፥ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ፥ ሁሉ በእርሱ የተፈጠረበት የአብ አካላዊ ቃል ነው። (ዮሐ.10፥30፤ 14፥9-11፤1፥3፤ቆላ.1፤15-16)

በዘላለማዊ ልደቱ ከአብ የተወለደው የእግዚአብሔር ቃል (ወልድ ዋሕድ) በኋለኛው ዘመን ዓለምን ለማዳን ያለዘርዐ ብእሲ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። (መዝ.2፥7፤ 2ሳሙ.7፥14፤ ሉቃ. 1፥30-35)

ይህም ሲሆን አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይከፋፈል በመለኮቱ የእግዚአብሔር ልጅ ያለዘርዐ ብእሲ ሥጋንና ነፍስን መንፈስንም ነሥቶ በሥጋ ሥርዓት ከድንግል ማርያም በመወለዱ ደግሞ የማርያም ልጅ ነው። "አኮ ውእቱ ወልደ ማርያም በመለኮት አላ ዘከመ ሥርዓተ ትስብእት" "በመለኮት የማርያም ልጅ አይደለም፤ ሰው በሆነበት ሥርዓት ነው እንጂ" (ሃይ. አበ ዘቴዎዶስዮስ ምዕራፍ 82 ክፍል 2 ቁ. 20)

የቃል ሥጋ መሆን ምስጢር የተከናወነው በተዋሕዶ ሲሆን ይህም ተዋሕዶ ከመቀላቀል፥ ከመጠፋፋት ወዘተ . . . የውሕደት ዓይነቶች ፈጽሞ የተለየ፥ እግዚአብሔር ቃልና ሥጋ የባሕርይ መደባለቅና መለወጥ እንዲሁም የአቀዋም ሽረትና ፍልሰት ሳይኖርባቸው ፈጽመው ሳይለያዩና ሳይከፋፈሉ ምንታዌን አጥፍተው በአንዱ የአካል ተዋሕዶ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው የተሰኘበት ምስጢራዊ መገናዘብ ነው። በዚህ ተዋሕዶ የቃል የሆነው ነገር ሁሉ

ለሥጋ፥ ከኃጢአት በቀር የሥጋ የሆነው ነገር ሁሉ ለቃል ገንዘቡ (ንብረቱ) ሆኗል። "ወእንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" "የቃል የሆነው ነገር ሁሉ ለሥጋ ሆኗል፤ የሥጋ የሆነው ነገር ሁሉ ደግሞ ለቃል ሆኗል።" እንዲል

ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ባለመቀበል የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት ክዶ "ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው" ያለውን አርዮስንና የተረገመች ትምህርቱን፥ የተዋሕዶ ምስጢር በመለወጥ እንደተፈጸመ ቆጥሮ የክርስቶስ ሰውነት ወደ አምላክነቱ ተለወጠ የሚለውን የአውጣኬን የውላጤ ትምህርት፥ እንዲሁም ከተዋሕዶ በኋላ በክርስቶስ ሁለት ህላዌና ሁለት ገጻት አለ የሚለውን የንስጥሮስን ክሕደትና የሌሎችንም በተዋሕዶ ትምህርት ላይ ኑፋቄ ያመጡትን ሁሉ ቤተክርስቲያን ከአንድነቷ ለይታለች።

በመለየት ብቻ ሳትወሰን የተዋሕዶን ምስጢር በማደላደል አምልታና አስፍታ አስተምራለች። እንዲህ በማለት:- "ተዋሕዶተ እሳት ምስለ ዕፅ ልምልምት እንተ ርእየ ሙሴ በኮሬብ ያጤይቅ ተዋሕዶተ መለኮት ወትስብእት፤ እሳት አምሳለ መለኮት ውእቱ ዕፅኒ አምሳለ ትስብእት ውእቱ። ወኢመጽልዎቱ ለልምላሜ ዕፅ በተዋሕዶተ እሳት ያጤይቅ ከመ ኢጠፍአ ህላዌ ትእብእት ወአካለ ትስብእት በተዋህዶተ መለኮት ወኢጠፊኦቱ ለእሳት በተዋሕዶተ ዕፅ ልምልምት ያጤይቅ ከመ ኢጠፍአ ህላዌ መለኮት ወአካለ መለኮት በተዋሕዶተ ትስብእት. . ዝንቱ ምሳሌ አስተጻደለ ራእዮ ለፍና ትስብእት"

ትርጓሜ:- "ሙሴ በኮሬብ ያየው የእሳትና የቁጥቋጦ መዋሐድ የአምላክነትንና የሰውነትን መዋሐድ ያስረዳል። እሳት የመለኮት ምሳሌ ነው። ቍጥቋጦውም የትስብእት ምሳሌ ነው። እሳት የተዋሐደው የቍጥቋጦው ልምላሜ አለመጠውለጉ የሰውነት ህላዌና አካል መለኮትን በመዋሓድ አለመጥፋቱን ያስረዳል። የቍጥቋጦው ልምላሜ የተዋሐደው እሳትም አለመጥፋቱ የመለኮት ህላዌና አካል በሰውነት መዋሐድ አለመጥፋቱን ያስረዳልና . . . ይህ ምሳሌ የመዋሐድ ስልት ራእይን አብራርቷል።" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 77)

የቃልና የሥጋ ዘላለማዊ የተዋሕዶ ምስጢር እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ ብቻ የሚመስላቸው፥ ከትንሣኤውና ከዕርገቱ በኋላ ግን ሰው መሆኑ እንደቀረ የሚያስቡ የአውጣኬ ተከታዮች ዛሬም አይታጡም። ቤተክርስቲያን ግን የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ከትንሣኤ

በኋላም እንዳልቀረና ዘላለማዊ መሆኑን ታምናለች። "ሰው በመሆኑ መከራን ተቀበለ እንጂ ለዘለዓለሙ ሥጋን ተዋሕዶ ይኖራል" እንዳለ ቅ/አትናቴዎስ (ሃይ. አበ ምዕራፍ 26 ክፍል 7 ቁ.7)

ስለዚህ ሞትን ድል ነሥቶ በአብ ቀኝ የተቀመጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ለዛላለምም የማይለወጥ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። (ዕብ. 13፥8)

ዛሬ ዛሬ ግን በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ በብዛት የሚሰበከው የክርስቶስ አምላክነት ለብቻው ተነጥሎ ነው። አምላክነቱን ብቻ የሚሰብኩት ክፍሎች ሰው መሆኑን አልካድንም ቢሉም ከትንሣኤው በኋላ ያለውርደት በክብር የሆነውን የሰውነቱን ሥራ እንዳቆመ አድርገው ያስባሉ፤ ያስተምራሉም።

ሠኔ 21 ቀን 1982 ዓ.ም. በታተመውና "የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ" በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 28 ላይ " . . . ስለዚህ ነቢረ የማን (በአብ ቀኝ መቀመጥ) ክርስቶስ ግብረ ትስብእት ከፈጸመ በኋላ እንደገና የሰውነትን ሥራ የማይሠራ ነገር ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር መለኮታዊ ሥራውን እየሠራ የሚኖር መሆኑን የሚያስረዳ ቃል ነው።" የሚለው አባባል ይህንኑ የስሕተት ትምህርት ይደግፋል።

እንዲህ ማለት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ እስኪቀመጥ ድረስ መለኮት ሥራውን ለሥጋ ትቶ ሥጋ ብቻ ይሠራ ነበር፥ ሥጋ ደግሞ አሁን በተራው የሥራ ጊዜውን ስለፈጸመ ሥራውን ለመለኮት ተወ አያሰኝብንምን? ነገሩ እንዲህ ከሆነማ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖ ያዳነንን እርሱን ዕሩቅ ብእሲ፥ የእኛንም ድኅነት ከንቱ ማድረግ ይሆናል።

እኒህ ወገኖች የሰውነቱ ሥራ በመለኮቱ ሥራ እንዲዋጥ ያደረጉት ምናልባት አምላክነቱ እንዳይዋረድ በማሰብ ከሆነ "መጻሕፍት ግን ስለ አምላክነቱ የሚናገሩት አለ። ሰው ስለመሆኑም የተናገሩት አለ። እርሱ ሰው የሆነ አምላክ ሲሆን ስለአምላክነቱ ሰው ስለመሆኑም አንድ አድርገው የተናገሩት አለ። እኔም ከእነዚህ ቃላት ለመለኮት የሚገባ ዳግመኛም ለትስብእት የሚገባ እንዳለ ይህንን እናገራለሁ" ይላል እንላቸዋለን። (ሃይ. አበ ምዕራፍ 74 ክፍል 21 ቁ. 37፤ ዮሐ. 1፥1-14)

አዎን፤ ጥንታውያን አባቶቻችን በተዋሕዶ ትምህርታቸው ከትንሣኤው በኋላ ሰውነቱም ሆነ የሰውነቱ ግብር እንዳልቀረ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ጽፈዋል። ለምሳሌ ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ራሱን በክርስቶስ ቦታ ተክቶ የሰጠውን ምስክርነት እንመልከት:- "ይብል እስመ አነ አምላክ ወሰብእ ኀቡረ ወአነ አሐዱ ውእቱ፣ አነ እብል ዘንተ ወዘክተሂ እስመ ተወከፈኩ ኵሎ ዘዕጓለ እመሕያው ዘአልቦቱ ኃጢአት። ይብል አንሰ ነሣእኩ ዘበአማን ትስብእተ ወከመዝ ጸዋዕክዎ ለአቡየ አምላኪየ ዘከመ ይደሉ ለሥርዓተ ትስብእት ዘረሰይክዎ አሐደ ምስሌየ"

ትርጓሜ:- "እኔ ሰው የሆንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና፤ ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል። የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጌአለሁና። ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኔ ነፍስን ሥጋን በእውነት ተዋሕጄአለሁና ከእኔ ጋር አንድ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን "አምላኬ" ብዬ ጠራሁት ይላል" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 68 ክፍል 19 ቁ. 13)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን አምላኬ ብሎ የጠራው ሰውነቱ ወይም የሰውነቱ ግብር ቀርቷል፤ አሁን አምላክ ብቻ ነው ብለው ከሚናገሩለት ከትንሣኤው በኋላ እንደሆነ አስተውል። (ዮሐ. 20፥17)

ምናልባት በግልጽ ለተቀመጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትና የአባቶች ምስክርነት ሌላ አንድምታ በመስጠት "ይህማ ሰው መሆኑን ለማጠየቅ ነው።" በሚል እውነትን ለማድበስበስ ይሞከር ይሆናል። አምላክ ሰው የመሆኑ ምስጢር በእንደዚህ ያለ ቀላል አንድምታ የሚታለፍ አይደለም። ይህ ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው (1ጢሞ. 3፥17) የምስጢሩን ታላቅነት ለመረዳት አምላክ ሰው ሆኖ ለምን እንደመጣ ማወቁ አስፈላጊነት ይኖረዋል።

# አምላክ ለምን ሰው ሆነ?

ይህን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ከቻልን የመዳናችን መንገድ ሲጠፋን ከቶ አይችልም። አሲያ "አምላክነቱ እንዳይዋረድ" በሚል ሽፋን ልብ ያላልነውን (ሳናጤን ያለፍነውን) የትሥጉቱን ምስጢር የአምላክነቱን ያህል ልንረዳው ሳንችል ብንቀር ከአምላክነቱ ጋር በተዋሐደው ትሥጉቱ የምናገኘውን ድኅነት ማስተዋል አንችልም።

የሰው ልጅ ከውድቀቱ በኋላ በተሰጠው ሕግ ተመርቶም ይሁን በሌላ እድንበታለሁ ብሎ ባሰበው መንገድ ከኃጢአት ሞትና ከዘላለማዊ ኩነኔ ሊድን ፈጽሞ አልተቻለውም። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ጽድቅም ቢሆን እንኳን ለሌሎች ተርፎ ከዘላለም ኩነኔ ለማዳን ይቅርና ለራሳቸውም እንደመርገም ጨርቅ ሆኖባቸው ነበር። (ኢሳ. 64፥6) ምናልባት እግዚአብሔርን በመፍራታቸውና በትእዛዙ በመሄዳቸው በሰው ሚዛን ሲመዘኑ ቅዱሳንና ጻድቃን ተብለው ቢጠሩም ሕግን ሁሉ ስላልፈጸሙና የአዳም ልጆች በመሆናቸው ምክንያት አዳማዊ ኃጢአት ስላለባቸው ከተጠያቂነት ነጻ አልነበሩም። (ኢዮ. 15፥7፤ 10፤ 25፥4-6፤ ማቴ.12፥34፤ መዝ. 50፥5፤ ሮሜ. 3፥11፤ 23፤ 5፥12፤ ኢሳ.48፥8)

ሊቁ አቡሊዲስም እንዲህ ብሏል፡- "ብእሲ ኢይክል ያድኅን ዓለመ ወሞቱ ለብእሲ ኢያንጽሖ . . . ወኢይክል መኑሂ እምሰብእ ያብጥል መዊተ ወያብርሃ ለሕይወት በከመ ይቤ ዳዊት መኑ ውእቱ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት ወመኑ ዘያድኅና ለነፍሱ እም እደ ሲኦል ወዘኢክህለ ያድኅን ነፍሶ እፎኑመ ይክል ያድኅን ኩሎ ዓለመ እስመ ኃጢአት የኀድር ውስተ ሰብእ ወሞተ ይተልዎ። . . . ወሶበ አበሰ አዳም ወለደ ዘከመ አምሳሊሁ"

ትርጓሜ፡- "ሰው ዓለምን ለማዳን አይችልም፤ የሰው መሞትም ከኃጢአት አያነጻም። . . . ዳዊት "ሕያው ሆኖ የሚኖር ሞትንም የማያይ ሰው ማነው? ከሲኦል እጅስ ነፍሱን የሚያድን ማነው?" ሲል እንደተናገረ ሞትን ያጠፋ ዘንድ ሕይወትንም ያበራ ዘንድ የሚቻለው ከሰዎች ይገኛልን? ነፍሱን ለማዳን ያልቻለ ከሆነማ ሌላውን ለማዳን እንዴት ይችላል? አንዱን ለማዳን ካልቻለስ መላውን ዓለም እንዴት ሊያድን ይችላል? ኃጢአት በሰው ውስጥ አድሮአልና። ሞትም ይከተለዋል። . . . አዳም በበደለ ጊዜ ሰውን የወለደው በራሱ አምሳል ነው።" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 42 ክፍል 8 ቁ. 5፤7-8፤ ዘፍ. 5፥3፤ ኤር. 3፥24-25)

የሰው ዘር በሙሉ በኃጢአት መበከሉንና ከዚህም የኃጢአት ብክለት በራሱም ሆነ በሌላ ነጻ መሆን እንደማይችል የተረዳው ደራሲ እንኳ። "አድኅኖ ነፍሶሙ እምኵነኔ ነቢያት ኢክህሉ" "ከኩነኔ ነፍሳቸውን ማዳን ነቢያት እንኳ አልቻሉም" በማለት በሰው አመለካከት ብቁ መስለው የሚታዩት ነቢያት ሌላውን ቀርቶ ራሳቸውን እንዳላዳኑ ተናግሯል።

ወደፊት ለሚመጣው ፍጹም አዳኝ እንደጥላና ምሳሌ ሆኖ ያገለገለው የአሪት ካህናት ምልጃና ጸሎት እንዲሁም መሥዋዕት ኅሊናን ሊያነጻ፤ ጊዜያዊ ስርየት ከማስጠትም በቀር በኃጢአት ምክንያት የተቋረጠውን የእግዚአብሔርና የሰው ግንኙነት እንደገና እንዲቀጥል ሊያደርግ አልተቻለውም። (ዕብ. 9፥13-14)

በዕርቅ ላይ የሁለቱም ጥለኞች ወገኖች መገኘታቸው የግድ ነው፤ አሊያ ግን እውነተኛ ዕርቅ አይወርድም። ቅዱሳን አበው፥ ካህናትና ነቢያት ሰው ብቻ ናቸው። ፍጹምነት ይጎድላቸዋል። ይህም ሆኖ ሊወክሉ የሚችሉት እንደ እነርሱ ኃጢአተኛ የሆነውን ሰውን ብቻ እንጂ እግዚአብሔርን የሚወክሉ ስላልሆነ የሰውና የእግዚአብሔር ዕርቅ በሰው አስታራቂነት በኩል የማይሞከር ሆነ።

ቅዱሳን መላእክትን ብንመለከት ደግሞ እግዚአብሔርንም ሰውንም የመወከል ወገናዊነት የሌላቸው ረቂቃን መናፍስት ስለሆኑ ለማስታረቅ አልበቁም። እግዚአብሔርም እነርሱን አስታራቂ አድርጎ አልሾመልንም። የዮሐንስ አፈወርቅንና የጵርቅሎስን ምስክርነት እንጥቀስ:- "እስመ ለሊሁ ነጸረነ ወናሁ ኮነ አፅራረ ለእግዚአብሔር ወአልብነ ምንትኒ ግሙራ ዘይክል ያቅርበነ ኀቤሁ ለዐቂበ ሀብቱ ኢኪዳን፥ ወኢመሥዋዕት ወበእንተ ዝንቱ ተሣሃለነ ወኢያንሥአ ለነ ሊቀ ካህናት እመላእክት ወኢእምኀይላት እለ እሙንቱ ይቀውሙ ዐውደ መንበሩ"

ትርጓሜ:- "እርሱ ተመልክቶን እነሆ ለእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ተገኘን። ሀብቱን ለማግኘት ኪዳንም ቢሆን፤ መሥዋዕትም ቢሆን፥ ወደ እርሱ ያቀርበን ዘንድ የሚችል ፈጽሞ አልነበረንም፤ ስለዚህ ይቅር አለን። ዙፋኑን ከብበው ከሚቆሙ ከመላእክት ከኃይላትም ወገን አስታራቂ አልሾመልንም" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 62 ክፍል 2 ቁ. 15) በዚህ ክፍል ግእዙን ወደ አማርኛ የመለሱት ክፍሎች የፈጸሙት ስውር ደባ አለ። በግእዙ "ሊቀ ካህናት" ያለውን ወደ አማርኛ ሲመልሱ

አልተረጎሙትም። እንደ ግእዙ "ሊቀ ካህናት" ነው ያሉት። በሌላ ስፍራ ላይ ግን "ሊቀ ካህናት" የሚለውን ግእዙን ወደአማርኛ ሲመልሱ "አስታራቂ" ብለው ተርጉመውታል። ለዚህም በዚሁ ክፍል ቁ. 14 ላይ በግእዙ "መኑ ውእቱ ሊቀካህናት ወምእመን ዘእንበሌሁ" ያለውን ወደ አማርኛ የመለሰው "ከእርሱ በቀር . . የታመነ አስታራቂ ማነው? ማለቱ ምስክር ሊሆነን ይችላል። ከላይ ስለመላእክት በተነገረበት ስፍራ ግን በግእዙ "ሊቀካህናት" ያለውን "አስታራቂ" ብለው መተርጎመን ለምን ፈሩ? መቼም ምክንያታቸው ሌላ ሳይሆን ዐዲስ ያቋቋሙትን ትምህርት የሚያፈራርስባቸው ስለሆነ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

የጵርቅሎስ ምስክርነት ደግሞ እንዲህ ይላል:- "ብእሲስ ትሑት አድኅኖ እምኢክህለ እስመ ውእቱሂ ይፈዲ ምስሌነ ዕዳ ወመልአክሂ ኢክህለ ተሣይጦተነ እስመ አልቦቱ ቤዛ ሥጋ በዘይትቤዘወነ"

ትርጓሜ:- "ወራዳው ሰው የገዛ ራሱ ከእኛ ጋር ዕዳን ስለሚከፍል ሊያድነን ባልቻለም፤ መልአክም ቢሆን ስለእኛ ቤዛ የሚሆንበት ሥጋ ስለማይኖረው ሊዋጀን አልቻለም" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 150)

አንባቢ ሆይ፤ ሰውስ በድሏልና ሊያስታርቅ አልቻለም። ቅዱሳን መላእክት ግን አልበደሉም ነበር። ነገር ግን ለማስታረቅ ያለመቻላቸው ምስጢር ግልጽ ሆነልህን?

ከላይ በተመለከትነው መሠረት ማንኛውም ፍጡር ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን አለመቻሉ የተረጋገጠ ነገር በመሆኑ ከዚህ በኋላ ድኅነታችን በፍጡር አማላጅ ወይም በመልእክተኛ (መልአክ) መሆኑ ቀርቶ በራሱ በሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ይከናወን ዘንድ የግድ ሆነ። ይህን ሲያስረግጥ ቄርሎስ እንዲህ ብሏል:-" ወኢሳይያስኒ ነቢይ ይቤ አኮ ውእቱ መተንብል ወኢመልአክ አላ ለሊሁ እግዚእ ዘመጽአ ወአድኀነነ ወኢያድኅነነ በደመ ነኪር ወኢበሞተ ብእሲ አላ በደሙ በሕቲቱ"

ትርጓሜ:- "ነቢይ ኢሳይያስ ሰው ሆኖ ያዳነን እርሱ ራሱ ጌታ ነው እንጂ ሌላ አማላጅ ወይም መልአክ አይደለም። በባዕድ ደም በዕሩቅ ብእሲም ሞት አላዳነንም። ራሱ በደሙ አዳነን እንጂ" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 77 ክፍል 46 ቁ. 13፤ ኢሳ. 63፥ 9ን ግእዙን ተመልከት)

ስለዚህ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅና ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ሰው ሆኖ የመጣው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት ንጹሕ የሆነ፥ በሰውነቱ ሰውን በአምላክነቱ ደግሞ እግዚአብሔርን ሊወክል የቻለ፥ እንደ አሪት ካህናት አስታራቂነቱ በሞት የማይሻር ሕያውና ዘላማዊ ሊቀካህናት ሆነ። (ኤፌ. 2፥12-13፤ ዕብ. 7፥23-25)

አንዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርና ሰው ስለሆነ ተበድያለሁ የሚል እግዚአብሔርና በድያለሁ የሚል ሰው በእርሱ ተገናኙ። ይህም በመካከላችን የነበረውን ጥል አስወግዶ ዕርቃችንን ፍጹም አድርጎታል። በመጽሐፈ ምዕላድ የሚከተለው ተጽፎአል:- "እምቅድመ ይሠጎ ተንጥአ ንጹሐ ዐራቂ እምክልኤ ጾታ እምይእዜስ ይደልዎ ይስረይ ኃጢአተ ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ በመለኮቱ እስመ ተረከበ ንጹሐ ዐራቂ ወመተንብለ በትሰብእቱ"

ትርጓሜ:- "ሥጋ ከመልበሱ በፊት በሁለቱም ወገን ንጹሕ የሆነ አስታራቂ ታጥቶ ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ ግን በመለኮቱ ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኖ ኃጢአትን ይሰርይ ዘንድ ተገብቶታል። በሰውነቱ ንጹሕ አስታራቂና የሚጸልይ ሆኗልና።" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 112)

ኃጢአትን ሳይቀጣ እንዲሁ ማለፍ ለጻድቅ ባሕርዩ የማይስማማው ቅዱስ እግዚአብሔር የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ በቤዛነት የሚሞትና የቁጣውን ትኩሳት የሚያበርድበት በእግዚአብሔር በግ የተመሰለው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውና ስለኃጢአታችን አሳልፎ ሰጠው። (ዮሐ. 1፥29፤ 1ቆሮ. 5፥7፤ ኢሳ. 53፥7፤ ራእ. 7፥14፤ 14፥1፥ ኢሳ. 53፥10)

እኛን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ጣልቃ መግባት ያስፈለገው በፍጡራን ለመታረቅ ስላልተቻለ ነው። (ኢሳ. 59፥16፤ 2ቆሮ. 5፥19) ስለዚህም ኤፍሬም ሶርያዊ " ወኮነ ዐራቂ ለሐዲስ ኪዳን' "የዐዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነ" ብሎ እንደመሰከረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ አስታራቂ ነው። (ውዳሴ ማር ዘእሑድ)

ዐዲስ ኪዳን አንድ ዕለት ብቻ አይደለም። በጌታችን መገለጥ ተወጥኖ በፈሰሰው ደሙ የጸናና እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ አስታራቂ መሆኑን ሲገልጽ ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ:-"መኑ ውእቱ ሊቀ ካህናት ወምእመን ዘእንበሌሁ ዘይክል ለሊሁ ባሕቲቱ ሰራዬ ኃጢአት ወምንት ውእቱ መሥዋዕት ዘአዕረገ በእንተ ዝንቱ ሥርዓት ዘእንበለ ሥጋሁ ባሕቲቱ ዘነሥአ በእንተ ዝንቱ ግብር'

ትርጓሜ:- "ከእርሱ በቀር ራሱ ብቻውን ኃጢአትን ማስተስረይ የሚቻለው የታመነ አስታራቂ ማነው? ለማስታረቅ ኃጢአትን ለማስተስረይ ያቀረበው መሥዋዕትስ ምንድነው? መሥዋዕት ለመሆን የነሣው ሥጋው ብቻ ነው እንጂ." ብሏል። (ሃይ. አበ ምዕራፍ 62 ክፍል 2 ቁ. 14)

አስቀድሞ በፍጡራን በኩል ዕርቅ ስላለተገኘ የእርሱ ጣልቃ ገብነት እንዳስፈለገ ሁሉ ከእርሱ በኋላ ደግሞ በእርሱ ያልተፈጸመና የቀረ ነገር ኖሮ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የሚገባ ሌላ ጣልቃ ገብ አይኖርም። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሰከሩ። (ዮሐ. 14፥6፤ 1ጢሞ. 2፥5-6፤ ዕብ. 10፥19-22፤ ኤፌ. 2፥18)

ስለሌላው የሚጸልዩ ቅዱሳን ቢሆኑ እንኳ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡት በክርስቶስ በኩል ነው። ምክንያቱም ሰው በራሱ ብቁ ሊሆን አይችልም፤ የሰው ብቃት ክርስቶስ ብቻ ነውና። (2ኛ ቆሮ. 3፥5፤ 1ኛ ቆሮ. 15፥10)

በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል በ1963 ዓ.ም. በታተመውና "ጽድቀ ሃይማኖት የቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ውሳኔዎች" በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 35 ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አለ:- ". . . እንዲሁም የሞቱ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ የሚያርቁን አይደሉም። ከኛ ጋር አንድ ማኅበር ሆነው በክርስቶስ ፍቅርና በክርስቶስ ጸሎት የተያያዙ ናቸው እንጂ። ምእመናን ሁሉ በዓለምም ሆነ በሰማይ ቢኖሩ ወደ ሌላ ሳይሄዱ በቀጥታ በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ ይችላሉ። እስመ ሐደሰ ለነ ፍኖተ ሕይወት . . . ንቅረብ እንከ ይላል (የሕይወትን መንገድ ስላደሰልን እንግዲህ እንቅረብ) (ዕብ. 10፥19-23)

አንዳንዶች የክርስቶስን የአዳኝነት ሥራ እንዳለፈ ድርጊት ብቻ ስለሚቆጥሩት ዘላለማዊ አገልግሎቱን አምኖ የሚቀበል ዝግጁ ልብ የላቸውም። እነርሱ ጌታ ሰው ሆኖ የመጣው የአዳምንና የሔዋንን ኃጢአት (የኛን የውርስ ኃጢአት) ለማስተስረይ ብቻ ይመስላቸዋል። ስለሆነም ይህንን ሥራ ፈጽሞ በአብ ቀኝ በመቀመጥ አሁን የአምላክነቱን ሥራ ብቻ እየሠራ ነው ብለው በመናገር በክብሩ ሆኖ የሚሠራውን የሰውነቱን ሥራ ይክዳሉ።

ለዚህ አሳባቸው ግን ድጋፍ የሚሆናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የላቸውም፤ የክርስቶስን ስፍራ ለሌሎች ያወረሱበት የፈጠራ ድርስታቸው ካልሆነ በቀር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳምና ለሔዋን ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ስለምንሠራው ኃጢአት ሁሉ ነው የሞተው። በሌላ አነጋገር ክርስቶስ ዋጋ ያልከፈለበት ኃጢአት የለም። ስለዚህ ዛሬም በቤዛነቱ መታረቂያችንና የኃጢአታችን ማስተስረያ ነው። (1ዮሐ. 1፥7፤ 2፥2፤ ቆላ. 1፥19-22)

መጽሐፍ ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር በቀደሙት ዘመናት በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት እንደተናገረና በዘመኑ መጨረሻ ግን ዓለማትን በፈጠረበት፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው በልጁ እንደተናገረ ይመሰክራል እንጂ በልጁ ከተናገረ በኋላ ሌላ የተናገረበት መንገድ ወይም ልጁን ከላከ በኋላ የላከው ሌላ አዳኝ እንዳለ አይናገርም። (ዕብ. 1፥1-3፤ ማቴ. 21፥30-41)

በልጁ በመድኃኒታችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የወደደውን ሁሉ አድርጓል። ከዚህ በኋላም ሊያደርግ ያሰበው አሳቡ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው። (ኤፌ. 1፥9-10)

ይህን ባለመረዳት ሰው የሆነበትን ዓላማ ዘንግተው ስለቀድሞው ኃጢአታችን ከሞተልን በኋላ አሁን ለምንሠራው ኃጢአት በክርስቶስ ሳይሆን በሌሎች ነው የምንታረቀው ብለው ሌላ ዐዲስ መሠረት መሥርተዋል። ነገር ግን ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (1ኛ ቆሮ. 3÷11 )

እነዚህ ወገኖች የተሳሳተ አመለካከታቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል የእግዚአብሔርን ቃል ላልተነገረበትና ላልተጻፈበት ዓላማ እንዳሻቸው ይጠቅሳሉ። የተመሠረተውን አፍርሰው እነርሱ ላኖሩዋቸው ዐዳዲስ መሠረቶች ድጋፍ እንዲሆኑአቸው ከሚጠቅሱአቸው መካከል፡- "የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው። . . . በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ" የሚለው ይገኝበታል። (2ኛ ቆሮ. 5÷18 - 19 ) ከዚህ ቃል የምንረዳው ሐዋርያት ወንጌልን በመስበካቸው ምክንያት ስለተከናወነውና ዛሬም በሕይወተ ሥጋ ባሉት ሐዋርያትና ሰባኪያነ ወንጌል እየተከናወነ ስላለው የሰውና የእግዚአብሔር ዕርቅ ነው። ሐዋርያቱ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ባኖረው የማስታረቅ ቃል ለሰው ወንጌልን በመስበክ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምኖ ንስሐ በመግባት በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ የሚያደርጉት ይህ የማስታረቅ አገልግሎት ትርጉሙ ይኸው ብቻ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ቁ. 20 ላይ "እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ" የሚለውን "በእኛ እንደሚማለድ" በሚለው በመተካት የእግዚአብሔርን አሳብ ወደ ራሳቸው ፍላጎት ለማምጣት ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ ሁኔታ የቱንም ያህል ጥረት ቢደረግ የመልእክቱን ትክክለኛ አሳብ ማዛባት አይቻልም። ይህ ክፍል ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያቀርቡት የምልጃ ጸሎት አለመናገሩን በግልጽ የምንረዳው "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን" በሚለው ቃል ነው። ይህ ልመና የቀረበው ለእግዚአብሔር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ መታረቅ ለሚገባቸው ኃጢአተኞች ነው። (የሐዋ. ሥራ 13÷46 )

ይህን የማስታረቅ አገልግሎት በሚመለከት ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ግን ቅዱሳን ሐዋርያት ጳውሎስና ሲላስ ለወኅኒ ቤቱ ጠባቂ ያደረጉትን እንመልከት፤ ሐዋርያቱ ታስረው በመንፈቀ ሌሊት በዜማ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሲጸልዩ በተደረገው ተአምራት ተደንቆ " ጌቶች ሆይ! እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" የሚል ጥያቄ ባቀረበላቸው ጊዜ በውስጣቸው በተቀመጠው የማስታረቅ ቃል "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ" በማለት ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በማመን በኩል እንዲታረቅና ዘላለማዊ ድኅነትን እንዲያገኝ አደረጉት። (የሐዋ. ሥራ 16÷ 25 - 34 ) የዕርቅ ውጤት ደስታ ነውና ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቁ ምክንያት ከመላው ቤተሰቡ ጋር

ተደሰተ። በሰማይም ይህ ደስታ እንደሚደረግ እሙን ነው። (ሉቃ. 15፥ 10 )

አንባቢ ሆይ! በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅንና ከዳንን በኋላ ኃጢአት ሠ ርተን ብንገኝ ስለኃጢአታችን ከክርስቶስ በቀር ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድም ሆነ የሚቀርብልን መሥዋዕት አለመኖሩን አስተውል! (ዕብ. 10፥ 26) ብዙዎች ይህንን እውነት የማይቀበሉት የክርስቶስ አምላክነት የሚዋረድ ስለሚመስላቸው ነው። እነርሱ እንደሚያስቡት በዚህ ምክንያት የክርስቶስ አምላክነት አይዋረድም። ይልቁንም ሰው መሆኑ ይገለጣል። እርሱ ለዘለዓለም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው። በክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆን ቀድሞ የተከናወነውንና ዛሬም እስከ መጨረሻው የሚከናወነውን ቀጥሎ እንመለከታለን።

# ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት

እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ ውስጥ እንደገለጸው ለዐዲስ ኪዳን ጥላና ምሳሌ ሆኖ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕዝቡን ሲያስተዳድርና ሲመራ የኖረው በሕዝቡና በእርሱ መካከል መካከለኛ አድርጎ ባቆማቸው ተቀብተው በተሾሙ ካህናት፥ ነቢያትና ነገሥታት አማካኝነት ነበር።

በዐዲስ ኪዳን ግን ለተለያዩ ነገዶችና ግለሰቦች ተሰጥተው የነበሩትን እነዚህን ሦስቱን ሹመቶች ሊቀካህንነትን፥ ነቢይነትንና ንጉሥነትን ሰው ሆኖ የተገለጸው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠቅልሎ ይዟቸዋል።

"ክርስቶስ" የሚለው የግሪክ ቃል የጌታችን የሹመት ስሙ ነው። ትርጉሙም በዕብራይስጥ መሲሕ በአማርኛ የተቀባ፥ ቅቡዕ እንደ አሮንና እንደ ዳዊት ተመርጦ የተሾመና የነገሠ ማለት ሲሆን መቀባትም ለሦስቱ ሹመት ነው። ካህን ነቢይና ንጉሥ ለመሆን። (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 549-550)

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ሰውነቱ ካህንነትን ነቢይነትንና ንጉሥነትን ገንዘብ ማድረጉን ሊቃውንተ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው አስተምረዋል።

አባ መልከ ጼዴቅ በ1984 ዓ.ም ባሳተሙት "ትምህርተ ክርስትና" 2ኛ መጽሐፍ ላይ ያሰፈሩትን እንመልከት:- "ሦስቱ የድኅነት መዓሪያዎች በሦስቱ መዓርጋት የተፈጸሙትን የድኅነት ሥራዎች የሚገልጡ ናቸው። ሦስቱ መዓርጋት የተባሉትም ነቢይነት፥ ሊቀ ካህንነትና ንጉሥነት ናቸው። እነዚህንም ሦስቱን የማዕርግ ስሞች ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የፈጸመባቸው ስለሆኑ የእርሱ መጠሪያ ስሞች ሆነዋል።

የክርስቶስ የነቢይነቱ መዓርግ ዞሮ ማስተማሩን ሕዝቡን ለድኅነት ማዘጋጀቱን ያመለክታል። ስለዚህም ራሱ "ናሁ ነዐርግ ኢየሩሳሌም ወይእኅዝዎ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው" እያለ ትንቢት ተናግሯል (ማቴ. 20÷18)

ኢየሱስ ነቢይነት ገንዘቡ እንደሆነ ነቢይም እንደሚባል "ኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍአ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም" ሲል ራሱ ተናግሯል። (ሉቃ. 13÷33)

ሊቀ ካህንነቱ ደግሞ በሥራ ተገልጧል ማለት ክርስቶስ ዐቢይ ሊቀ ካህናት ሆኖ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለአባቱ አቅርቧልና . . . ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባቀረበልን መሥዋዕት ድነናል። እርሱ ቤዛ ሆኖ ተለውጦ አድኖናል።

ንጉሡ ነገሥትነቱም ክርስቶስ ማለት የተቀባ፣ የከበረ፣ የነገሠ ማለት እንደመሆኑ የጠፋውን ልጅነት መለሰ፣ ፍዳን ደመሰሰ፣ ምርኮን መለሰ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለን ጌታችንን ስንጠራው የዳንን ወገኖች መድኀንም ያለን ሕዝቦች ነን። ስለዚህ ኢየሱስ →ክርስቶስ እንደሆነ አምነን እንቀበላለን" (ገጽ 36-37 እንዲሁም የቤ/ክ ታሪክ በዓለም መድረክ ከአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 51)

ከላይ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገውን የአባቶችን ምስክርነት እንደተመለከትነው ካህንነት፣ ነቢይነትና ንጉሥነት የክርስቶስ ገንዘቦቹ ናቸው። እኛንም ያዳነንና ለዘላለምም የሚያድነን በነዚህ በሦስቱ ሹመቶቹ አማካይነት ነው። በዚህ ክፍል ግን ስፍራ ሰጥተን በስፋት የምንመለከተው ሊቀ ካህንነቱን ነው።

ሊቁ ቄርሎስ (በሃይማኖተ አበው ም. 81 ክፍል 52 ቁ.8 ላይ) እንደመሰከረው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው በመሆኑ:- ብእሲ፣ መሲሕ፣ ኢየሱስ፣ ታቦት፣ አስታራቂ፣ ለሙታን በኩር፣ ከሙታን ወገን ለሚነሣም በኩር የቤተ ክርስቲያን (የምእመናን) ራስ ተብሏል። በነዚህ ስሞችም ይጠራል።

እርሱ ፍጹም አምላክ ብቻ ሳይሆን ፍጹም ሰውም ነውና ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እኛን ቢመስልም (ዕብ. 4÷15) የአምላክነቱ ክብር ለቅጽበት እንኳ አልተቀነሰም። ክቡር አምላክ ሲሆን በፈቃዱ ራሱን ስለእኛ ዝቅ አደረገ እንጂ። በተዋሕዶ ምስጢር አንድ የሆነው እርሱ የአምላክነቱንም የሰውነቱንም ሥራ ሠርቷል። ይሠራልም። ለምሳሌ መሞት ለአምላክ የማይስማማ ባሕርይ ነው። ከሙታን ተለይቶ መነሣትም አምላክ ካላስቻለ በቀር ለሰው አይቻለውም። ነገር ግን ክርስቶስ አምላክም ሰውም በመሆኑ በሰውነቱ ሞቶ በአምላክነቱ ኃይል ተነሣ። (1ጴጥ. 3÷18)

"አንስ አአምን ከመ ውእቱ ሞተ በሥጋ ወሐይወ በኃይለ እግዚአብሔር" "እኔ በሥጋ እንደሞተ በእግዚአብሔርነቱ ኃይልም እንደተነሣ አምናለሁ" እንዳለ ቄርሎስ (ሃይ አበ ም 80 ቁ. 9)

እንደዚሁም በአምላክነቱ ኃጢአትን ሁሉ የሚያስተሰርይ ሲሆን ሰው በመሆኑ ደግሞ የዐዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆኗል።

"ወውእቱ መዋዔ ኩሉ ኃጢአት በመለኮቱ ኮነ ሊቀ ካህናት በትስብእቱ" "በመለኮቱም ኃጢአትን ሁሉ የሚያጠፋ እርሱ ሰው በመሆኑ አስታራቂ ሆነን" (ሃይ. አበ ምዕ. 79 ክፍ. 50 ቁ. 68)

በፍጹም ሰውነቱ የክርስቶስ የአስታራቂነቱ ግብር የተገለጸው በሊቀ ካህንነቱ ነው። የሊቀ ካህንነቱን ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ተጽፎ የምናገኘው በዐዲስ ኪዳን ክፍል በተለይ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ነው።

መልእክቱ በመጀመሪያ የተጻፈላቸው ዕብራውያን በሥጋ የአብርሃም ዘሮች የሆኑ፥ ከሁሉ አስቀድሞ ልጅነትና ክብር፥ ኪዳንም፥ ሕግም የተሰጣቸው የምድራዊ መቅደስ ሥርዓት የነበራቸው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የሚፈጸመውንና ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል የተቀበሉ ነበሩ። (ሮሜ. 9፥4-5)

ለዕብራውያን ተሰጥተው የነበሩት እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለሚመጣው ዕዲስ ነገር ጥላና ምሳሌ ነበሩ። (ዕብ. 10፥1፤ 9፥9-10፤ ቆላ. 2፥17)

አሁን በዐዲስ ኪዳን በተስፋ ሲጠበቅ የቆየው የጥላው አካል ስለተገለጠ ብሉይ ኪዳን የአገልግሎት ዘመኑን ፈጽሞ ለተተኪውና እስከመጨረሻ ለሚጸናው ለዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ስፍራውን ለቅቋል። (ዕብ. 8፥1-13፤ 9፥1-10፤ 2ቆሮ. 3፥7-18)

የዕብራውያን መልእክት ጥላውን ከአካሉ፥ ምሳሌውን ከአማናዊው ነገር ጋር በማነጻጸር የተሻለውና ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበትን ዐዲስ መንገድ ይጠቁመናል። መልእክቱ ለዕብራውያን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነውና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በየድርሳናቸው ውስጥ ከሐዋርያት እንደተቀበሉት የክርስቶስን ሊቀ ካህናትነት

ጽፈውልን ዐልፈዋል። ይሁን እንጂ የመዳናችን ዋስትና የቆመበት የክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት ትምህርት ከመቃብር በታች ውሎ ብዙ ነገር ከተጫነበት ዘመናት ተቆጥረዋል።

ከውድቀት በኋላ ምንጊዜም ቢሆን ያለመካከለኛ በራሱ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የማይሆንለት የሰው ልጅ የመቅረቢያው መንገድ ስለጠፋበት ሌላ መንገድ ለመፈለግ ተገድዷል።

በጉዞው መጨረሻ ሊገጥመው የሚችለውን ለማያውቅ የሰው ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት በኩል ሳይሆን በሌላ ወደ አብ እደርስበታለሁ ብሎ ባሰበው መንገድ ሁሉ ላይ መጓዙ ለጊዜው ዝም ብሎ ከመቆምና ግራ ከመጋባት አማራጭ መስሎ ቢታየውም እግዚአብሔር ያላዘጋጀው መንገድ ወደ እግዚአብሔር የማያደርስ መሆኑ ግን በእጅጉ ያሳዝናል። (ዮሐ. 14÷6፤ ዕብ. 10÷19-20)

ከብሉይ ኪዳን አገልግሎት እንደምንረዳው የካህን አገልግሎት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ሲሆን ካህኑ የማስታረቁን አገልግሎት የሚፈጽመው ለኃጢአተኛው ሰው መሥዋዕት በማቅረብና በመጸለይ ነው (ዘሌዋ. 4÷1-35)

ክርስቶስ ካህን ሆኖ ለኃጢአት ሁሉ የሚበቃውን መሥዋዕት ራሱን በማቅረቡ የአሮንን ክህነት አስቀርቷል። (ዕብ. 7÷11-28) የክህነቱን ሥራ የፈጸመው በምድራዊ ሳይሆን በሰማያዊ መቅደስ፥ በእንስሳት ደም ሳይሆን በራሱ ደም ነው። (ዕብ. 9÷11)

ክርስቶስ ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ከማቅረቡ ባሻገርም በሊቀ ካህንነቱ ጸሎትንና ምልጃን አቅርቧል። ይህም የሆነው:-

1. በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከመሞቱ በፊት በነበረው ጊዜ (ዮሐ. 17፤ ሉቃ. 22÷31-32)
   "አንቃዕደወ ሰማየ ኀበ አቡሁ ወአስተምሐረ ወላዲሁ ወአማኅጸነ አርዳኢሁ ከመ ይዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ"

   ትርጓሜ:- "ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ቀና ብሎ አየ፤ ወላጅ አባቱንም ማለደ፤ ደቀ መዛሙርቱንም ከክፉው ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ አደራ አስጠበቀ" (ቅዳ. ማር. ቁ 113)

2. በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ (ኢሳ. 53÷12፤ ሉቃ. 23÷34፤ ዕብ. 5÷7)

"ወሰአሎ ለአብ ያኅልፍ እምኔነ መዓተ ዘረከበነ እምቅድም ከመ ዘለሊሁ ይኃልቀ ስእለተ ሎቱ እስመ ውእቱ ነሥአ አምሳሊነ ከመ ይስአሎ ለአብ በእንቲአነ ከመ ምዕረ ዳግመ ይዝክረነ ወኢይኅድገነ እምኔሁ"

ትርጓሜ:- "እርሱ ለራሱ ልመናን የሚሻ መስሎ ከጥንት ጀምሮ ያገኘንን ፍዳ ከእኛ ያርቅ ዘንድ አብን ማለደው። እንደገና ደግሞ እንዲያስበን ከእርሱም እንዳይለየን ስለእኛ አብን ይማልደው ዘንድ ባሕርያችንን ነሥቷልና" (ሃይ. አበ ም. 79 ክፍል 50 ቁ. 38)

3. ከትንሣኤውና ከዕርገቱ በኋላ (ሮሜ 8÷34፤ ዕብ. 7÷25፤ 1ዮሐ. 2÷1)

"ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አዐርግ ኀበ አቡየ ወእስእሎ በእንቲአክሙ" "ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ አባቴ ዐርጋለሁ ስለእናንተም እለምነዋለሁ አላቸው።" (የፋሲካ ድጓ ገጽ 291 3ኛው ዓምድ ላይ)

"ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አዐርግ ሰማየ ኀበ አቡየ ኀበ እስእል ምሕረተ በእንተ እሊአየ" "ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የኔ ስለሆኑት ምሕረትን ወደምለምንበት ወደ አባቴ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ አላቸው" (የሠኔ ሚካኤል ዚቅ (ዓራራይ))

"ወልድ ሆይ እንደታመመ ሰው አስምተህ ተናገር። ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ በል። በአፋቸውም ውስጥ ሳለ አባ አባቴም ሆይ፤ ሥጋዬን የበሉትን ደሜን የጠጡትን ማራቸው ይቅር በላቸው በል" (ቅዳ. አትናቴዎስ ቁ. 144)

ቀደምት አባቶቻችን በዚህ መልክ የክርስቶስን ዘላለማዊ ሊቀ ካህንነት ቢመሰክሩም በኋላ የተነሡት አንዳንዶቹ ግን አስተባብለውታል። ደግሞም የጌታ ሊቀ ካህንነት ያለፈ ድርጊት ብቻ እንጂ ቀጣይነት እንዳለው አይናገሩም። ይህም ዘላለማዊ ሊቀ ካህንነቱን የሚቃወም አመለካከት ነው። (ዕብ. 5÷7) ይህን እውነት ለማጣመም

የተጠቀሙበት ዘዴ የተለያየ ሲሆን ዋናው ግን የግእዝ መጻሕፍትን ሲተረጉሙ ለንባቡ የማይስማማ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ ተደርሶበታል። ለምሳሌ ያህልም በሃይማኖተ አበው ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውንና በግእዙ " እስመ ውእቱ ይተነብል በእንቲአነ" "እርሱ ስለእኛ ይማልድልናል።" የሚለውን በቀጣይ ድርጊት የተገለጸውን ገጸ ንባብ ያለ አንቀጹ በኃላፊ ድርጊት "ማልዶልናል" ብለው ተረጉመውታል። (ሃይ. አበ. ም. 63 ክፍል 2 ቁ. 26)

በሮሜ 8÷34 የግእዙ ዐዲስ ኪዳን "ወይትዋቀሥ በእንቲአነ" " ስለእኛ ይከራከራል" የሚለውን ያለፍቺው "ስለእኛ ይፈርዳል" ብለው ተርጉመውታል። " ተዋቀሠ" ስለሚለው ግስ የኪዳን ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት የሚሰጠው ፍቺ "በቁሙ (ተዋቀሠ) ተሟገተ፣ ተከራከረ" የሚል ነው እንጂ ፈረደ አይልም። (ገጽ 401) ስለጌታ ፈራጅነት በሌላው ስፍራ ሲናገር የግእዙ ዐዲስ ኪዳን የሚጠቀመው ግስ "ኰነነ" የሚለውን ነው። (ዮሐ. 5÷27 ግእዙን ተመልከት)

መቼም ለጥቂት ጊዜ ካልሆነ በቀር ሁልጊዜ መዋሸት አይቻልም። አሁን አሁን ከየአቅጣጫው ጫናው እየበዛና እውነቱ እየተገለጠ ሲመጣ ሮሜ 8÷34ን በፊት "ይፈርዳል" እያሉ የተረጎሙ ሁሉ "ይከራከራል" ወደሚለው ሐቅ እየመጡ ነው። ለዚህ አለቃ አያሌው ታምሩ ተጠቃሽ ናቸው። በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ እንዲህ ብለዋል:- "እንግዲህ ቅ/ጳውሎስ "ለእመ ለሊሁ ያጸድቅ መኑ ዘይኴንን ክርስቶስ ኢየሱስ ዘሞተ ወተንሥአ እምዉታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር ወይትዋቀሥ በእንቲአነ" "እርሱ ቢያጸድቅ የሚኮንን ማነው? ሞቶ የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በአብ ቀኝ ተቀምጦአል ስለኛ ይከራከራል" (ሮሜ 8÷34) (ምልጃ ዕርቅና ሰላም 1992 ዓ.ም ገጽ 27)

በ1ኛ ዮሐ. 2÷1 ላይ "ወእመኒ በ ዘአበሰ ጰራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ" ይህም ማለት "የበደለ ሰው ቢኖር ከአብ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠበቃ አለን" ማለት ነው። ነገር ግን የግእዙ "ጰራቅሊጦስ ብነ" ያለውን በአማርኛ ዐዲስ ኪዳን ትርጉማቸው ላይ "ጰራቅሊጦስ አለን" በማለት የክርስቶስን ጠበቃነት ለማስካድ ተሞክሯል። የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት "ጰራቅሊጦስ" የሚለው ቃል በግሪኩ (ፓራክሊቶስ) እንደሆነና ትርጉሙም:- አማላጅ፣ አስታራቂ፣ አፍ፣ ጠበቃ . . . እንደሆነ ይናገራል። (ገጽ 907) የግእዙ ዐዲስ ኪዳን የግሪኩን ቃል ወደ ግእዝ ሳይተረጉም እንዳለ ነው

የተጠቀመበት አማርኛው ዐዲስ ኪዳን ግን በመተርጎም "ጠበቃ" ብሎት እናነባለን።

ለአብነት ያህል እነዚህ ብቻ ተጠቀሱ እንጂ በዚህ መንገድ ትርጉማቸው የተለወጠ ብዙ ናቸው። የትርጉም ለውጥ ከተደረገ በኋላ ደግሞ የአስተምህሮቱ ይዘት መለወጡ አይቀርምና ቀጣይነት ያለውን የሊቀ ካህንነቱን አገልግሎት ጠቅሰው ገለጻ ሲሰጡ "የዕለተ ዐርቡን ይዞ ይከራከራል፥ ይለምናል አለ እንጂ አሁን የባሕርይ አምላክ ነው" ይላሉ።

ከዚህ ዐልፈው ደግሞ ሁሉም የማያስኬዳቸው ሆኖ በጥያቄ አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ "እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ ወደ ማነው የሚማልደው?" የሚል ከተጠያቂነት የማያድን ጥያቄ ያነሣሉ። ጥያቄያቸው የሥላሴን ትምህርት ገደል ይጨምራል። በአውጣኬ የትምህርት ስልት ሥጋን በመለኮት እንዲዋጥም ያደርጋል። ይህ እንዳይሆን እግዚአብሔር ሦስትነት ያለው አንድ አምላክ ነው። ሦስትነቱ በአንድነቱ ተጠቅልሎ አንድ አካል አይሆንም፤ አንድነቱም በሦስትነቱ ተከፋፍሎ ሦስት አማልክት አይሆንም። በተጨማሪም ክርስቶስ ለዘለዓለም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

መቼም ቢሆን ይህን ኑፋቄ የሚያስተምሩት ወገኖች ክርስቶስ በሥጋው እስከ መስቀል ሞት መማለዱን አይክዱም ተብሎ ይታመናል። እስኪ ይጠየቁና ጌታ ከመሞቱና ከመነሣቱ በፊት የማለደው አምላክነት ስለጎደለው ነውን? እንዲህ ማሰብ ትልቅ ክህደት። ስለዚህ "እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው ወደማነው የሚማልደው? ለሚለው ተጠያቂ ጥያቄአቸው ዐጭሩ መልስ ቀድሞ ወደ ማለደበት" የሚል ይሆናል።

ከላይ እንዳየነው በአንድ ወገን ሦስትነቱን በመጠቅለል ሲጠይቁ በሌላ ወገን ደግሞ አንድነቱን በመከፋፈል "አብ እንደማለደ በኤር. 7÷25 ወልድ እንደሚማልድ በሮሜ 8÷34፥ መንፈስ ቅዱስም እንደሚማልድ በሮሜ 8÷27 ይናገራልና ሦስቱም ወደማነው የሚማልዱት?" በማለት የተለያየ መልእክት ባላቸው ጥያቄዎች ለማደነጋገር ይሞክራሉ። የሦስቱንም ጥቅሶች መልእክት ለመረዳት በየክፍል በየክፍላቸው ማጤን ያስፈልጋል።

ስለአብ የሚጠቅሱትና "አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ <u>በየዕለቱ እየማለድሁ</u> ባሪያዎቼን ነቢያትን

ሁሉ ልኬባችሁ ነበር" ተብሎ የተጻፈው ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እያከታተለ በላካቸው ነቢያት አማካይነት ወደ እርሱ እንዲመጡ በየጊዜው የጠራቸው መሆኑን ይገልጻል። ዛሬም በዐዲስ ኪዳን በሐዋርያትና በሌሎቹም አገልጋዮች እየማለደ ድኅነት የሚገባቸውን ሁሉ እንደሚጠራ ማለት ነው። (2ቆሮ. 5÷20)

በጥሪው የተገኘው ውጤት "ነገር ግን አንገታቸውን አደነደኑ እንጂ አልሰሙኝም ጆሮአቸውንም አላዘነበሉም። አባቶቻቸውም ካደረጉት ይልቅ የባሰ አደረጉ" (ኤር. 7÷26) የሚል ሲሆን "በየዕለቱ እየማለድሁ" ለሚለው ቃል ሙሉ ትርጉም ይሰጣል። እግዚአብሔር በነቢያቱ ኑ! ብሎ የለመናቸውና እንቢተኛ የሆኑት እነርሱ ናቸው ማለት ነው እንጂ አብ ወደ ሌላ አምላክ ማለደ አያሰኝም።

ስለመንፈስ ቅዱስ በሮሜ 8÷26-27 " እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል። ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለቅዱሳን ይማልዳልና" የተባለው በጸሎታቸው ጊዜ ክርስቶስን በማመን ቅዱሳን የሆኑትን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸውና በድካማቸው እንደሚያግዛቸው ያመለክታል። ቅዱሳን በመንፈስ ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ሆኖ መንፈሳዊ ነገርን ማለትም ምስጋናን፥ ስለሌሎች ምልጃን፥ ልመናን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከመስጠት ጀምሮ ኃጢአታቸውንም እያሳሰበ እንዲናዘዙበትና ከዲያብሎስ ክስ ነጻ እስከማድረግ ድረስ የሚያደርግላቸው እገዛ ነው እንደ ምልጃ የተቆጠረው።

በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ልብ ውስጥ ለውጥንና መታደስን ያመጣል። (ሮሜ 8÷9፤ ቲቶ 3÷5-7) ለአማኙ የእግዚአብሔር ልጅነቱን እየመሰከረ ወራሽነቱን ያረጋግጣል። (ሮሜ 8÷ 16፤ 2ቆር. 1÷22፤ ገላ. 4÷6፤ ኤፌ. 1÷13-14) መንፈስ ቅዱስ የወረደው ምእመናንን በዚህ መንገድ ለመረዳትና እውነት ወደሆነው ሁሉ ለመምራት ነውና። (ዮሐ. 16÷13)

ወደ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ጉዳይ ስንመለስ በተሳሳተ የአተረጓጎም ስልታቸው ንጹሐን የትምህርት ምንጭ እያደፈረሱና የድኅነታችንን አድራሻ እያጠፉ ሰውና እግዚአብሔርን ለማለያየት

ጥረት ቢያደርጉም አባቶች በግእዙ ቋንቋ ያስፈሩት ጽሑፋቸው ግን እንደፈለጉ የሚያስፈነጭ አይደለም።

ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያንን መልእክት በተረጎመበት 13ኛ ደርሳኑ ቁ 156 ላይ "ወጊዜ ፈቀደ ይተነብል ሎሙ አኮ በዝንቱ ጊዜ ባሕቲቱ አላ በእንተ ዘትመጽእ ሕይወት ዘለዓለም"

ትርጓሜ:- "በወደደ ጊዜ ይለምንላቸዋል በዚህ ጊዜ (በዕለተ ዐርብ) ብቻም አይደለም። ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ ለዘላለም ነው እንጂ" በማለት የካቡትን የስሕተት ካብ በትክክለኛ ትምህርቱ ይንዳል።

ትክክለኛውን አስተምህሮ እየበረዙ እየከለሱ ያሉት ወገኖች አምላክነቱ እንዳይዋረድ ሠግተው ከሆነ ቀድሞም ቢሆን ይህ የሊቀ ካህንነቱ አገልግሎት የተከናወነው በሰውነቱ ነው። ስለሆነም በዚህ ምክንያት አምላክነቱ እንዳልተዋረደ ሁሉ አሁንም የሚሆነው ይኸው ነውና አይሥጉ እንላለን።

ለዚህ የከበረ እውነት ጠንቃቆች የነበሩት አባቶቻችን (2ጴጥ. 1÷19) ክርስቶስ በሊቀ ካህንነቱ "ስለኛ ይማልድልናል" ካሉ በኋላ "ወኢተናገረ በዝየ በእንተ ህላዌ መለኮት አላ ተናገረ በእንተ ሥርዓተ ትስብእቱ እስመ ትስብእቱ ግቡር ውእቱ"

ትርጓሜ:- "በዚህ አንቀጽ ስለ ባሕርየ መለኮት አልተናገረም አምላክ ሰው ስለመሆኑ ሥርዓት ተናገረ እንጂ ሥጋ ፍጡር ነውና" (ሃይ. አበ. ምዕራፍ 63 ክፍል 2 ቁ.28)

እንዲሁም ቄርሎስ:- "ይህ ነገር ፍጡር የሚል እንደሚመስል ነገሩ ግልጽ ነው። ይህም ሰው ስለመሆኑ እንጂ ለሌላ አልተነገረም። እሱ የባሕርይ አምላክ ሲሆን ሰው በመሆኑ ከአብ ክብርን ይቀበላል።" (ሃይ. አበ ም. 79 ክፍል 50 ቁ 74)

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን አንድ ነገር አለ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁላችን በመሞቱ አንድና ሕያው መሥዋዕት አድርጎ ራሱን አንድ ጊዜ ለዛለለም አቅርቧል። በተጨማሪም "በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አልለምንም" (ዮሐ. 17÷21) በማለቱ ስለሁላችን አንድ ጊዜ ምልጃን አቅርቧል። ይህን ሁሉ ፈጽሞ በአብ ቀኝ

ከተቀመጠ በኋላ ዛሬም እንደቀድሞው በመውደቅ፣ በመነሣት፣ ከዳኛ ፊት እንደሚከራከር ጠበቃ በአብ ፊት ስለኛ ይከራከራል ወይም አብን ስለኛ ዘወትር ይለምነዋል ማለት አይደለም። በቀደመው ጸሎቱና መሥዋዕቱ ለዘወትር አስታራቂያችን ነው እንጂ።

ክርስቶስ ከትንሣኤው አስቀድሞ በነበረበት የውርደትና የዝቅተኛነት ሁኔታ አሁን አይታይም። አሁን ያለው ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ሆኖ በታላቅ ክብር ውስጥ ነው። (2ኛ ቆሮ. 5÷16፤ ፊልጵ. 2÷9-11፤ ዕብ. 2÷9)

ነገር ግን በቀደመው አገልግሎቱ ዛሬም አስታራቂያችን እሱ ብቻ በመሆኑ በስሙ ስንጸልይና ስንለምን የቀድሞው ጸሎቱና መሥዋዕቱ ስለእኛ ጽድቅ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ይታይልንና (ይቆጠርልንና) ተቀባይነት እናገኛለን። ሐዋርያው እንደመሰከረ ቤዛነቱን ተረድተው በስሙ አምነው በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ ለማዳን የዘላለም ምክንያተ ድኂን ሆኖ በሰማያዊቱ መቅደስ እነሆ አለ። በእርሱ መካከለኛነት በኩል ለሚመጡትም ጽድቃቸው ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ስለእነርሱ ይታይላቸዋል። እርሱ የዐዲስ ኪዳን ዋስ ነውና። (ዕብ. 5÷9-10፤ 7÷25፤ 9÷24፤ 7÷22)

ዛሬ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅ ሆኖ ያለኃጢአት የሚታየው በመስቀል ላይ ሥራው ጠላቶች የሆኑትንና በእርሱ አምነው በአስታራቂነቱ በኩል የመጡትን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ መሆኑን ቄርሎስ እንዲህ ሲል ይገልጠዋል:-

"ዛሬስ በምን ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት ተገለጠ (ታየ)? አምላክ የሆነ ቃል እንደኛ ሰው ሆኖ በዐዲስ ሥራ ታየ። <u>ዛሬ ስለኛ በእግዚአብሔር ፊት በእኛ ባሕርይ በአስታራቂነት ታየ</u>። . . . ዛሬ ስለኛ በእግዚአብሔር ፊት እንደታየ የምንናገረው ነገር ይህ ነው። በአዳም ትእዛዝ ማፍረስ ምክንያት ተዋርዶ የነበረ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ በአባቱ በእግዚአብሔር ፊት ገልጦታልና በገንዘቡ ግብር በእግዚአብሔር አብ ፊት አቆመው ቀድሞ እንደነበረው አይደለም። ሰው ሆኖ ታየ እንጂ ዳግመኛ ወደ አባቱ ያስገባን ዘንድ" (ሃይ. አበ ምዕ. 79 ክፍ. 50 ቁ 72-73)

ክርስቶስ ምትክ የሌለው የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ አስታራቂ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሕያውና የማይሞት መሆኑ

ነው። ሌሎቹ ቅዱሳን ሰዎችን ስንመለከት የማስታረቅ አገልግሎታቸውን የሚያከናውኑት እስኪሞቱ ድረስ ነው። ከሞቱ በኋላ ግን አይችሉም ነበር። የብሉይ ኪዳን ካህናት በቁጥር የበዙበት ምክንያትም ይኸው ነው። ካህኑ አሮን ከሞተ በኋላ ማስታረቅ ቢችል ኖሮ ሌላ ካህን ልጁ አልዓዛር መተካት አያስፈልገውም ነበር። (ዘኁ. 20÷22፤ ዕብ. 7÷23)

የማስታረቅ አገልግሎታቸው በሞት የመገደቡ ነገር ቁጥራቸውን አበራክቶታል። ሕያው ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ግን ለዘለዓለም አይሞትምና የሚተካው አላስፈለገውም።

"ወእመሰ ኢኮነ አሐደ ውእቱ እምኢኮነ ዘኢይመውት ወእልከቱሰ ካህናት ኮኑ ብዙኃነ፥ መዋትያን እሙንቱ ከማሁኬ ዝንቱ አሐዱ በእንተ ዘኮነ ዘኢይመውት ይቤ እስመ ይክል አድኅኖቶሙ ለዝሉፉ እለ ይቀርቡ ኀበ እግዚአብሔር እንተ መንገሌሁ እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይተነብል ሎሙ። ጠየቀኑ አ፤ ፍቁር ከመ ብሂሎቱ ኮነ በእንተ ሥጋዊሁ . . . እመሰኬ ካህን ውእቱ አሜሃ ይተነብል። . . . ይቤ እስመ ይክል አድኅኖቶሙ ለዝሉፋ እስመ ሕያው ውእቱ ለዓለም ወአልቦ ተውላጥ እምድኅሬሁ"

ትርጓሜ:- "እርሱ አንድ ባይሆን ኖሮ የማይሞት ባልሆነም ነበር። የኦሪቱ ካህናት ግን የሚሞቱ ስለሆኑ ብዙ ናቸው። እንደዚሁም ሁሉ ይህ አንድ የሆነው የማይሞት ስለሆነ ነው። ሐዋርያው በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ዘወትር ሊያድናቸው ይችላልና ለዘላለም የማይሞት ሕያው ስለሆነ፤ ስለእነርሱም ይማልድላቸዋል። ወዳጅ ሆይ፤ ይማልድላቸዋል ብሎ ያለው ሰው ስለመሆኑ እንደሆነ ተረዳህን? ሊቀ ካህናት በመሆኑ ያን ጊዜ ይማልድላቸዋል አለ . . . ለዘላለም ሕያው ስለሆነ ለዘወትር ያድናቸው ዘንድ ይችላልና አለ። <u>ከእርሱ በኋላም የሚተካ የለም"</u> (የዮሐንስ አፈወርቅ 13ኛ ድርሳን ቁ. 129-131፤ 135-136)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሊቀ ካህንነቱ የዐዲስ ኪዳን ብቸኛና ብቁ የሆነ አስታራቂ መሆኑን ስናስብ ብቃቱ የተለካባቸውን መስፈርቶች ማስተዋል ይጠበቅብናል። እግዚአብሔር ከእኛ ከሰዎች ፈልጎ ያጣውን ነገር ያገኘው ፍጹም ሰው ከሆነው ከክርስቶስ ብቻ ነው። ይህም ተፈልጎ የታጣብን ነገር ሕግን ሁሉ መፈጸም ነው። በመሆኑም አንድስ እንኳ ጻድቅ የለም ተባለ። (ሮሜ. 3÷11-12)

እንደተጻፈው "ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ነው::" (ያዕ. 2÷10)

ካሁን በፊት እንዳየነው የአንዳንድ ቅዱሳን ሰዎች የተወሰነው መልካም ሥራ እነርሱን አስመስግኖ ጻድቅ ቢያሰኛቸው እንኳ የጽድቅ ሥራቸው ከኃጢአት ነጻ የሆነ ነበር ለማለት አያስደፍርም። ኖኅንና ሙሴን ብንወስድ እንኳ ስለእነርሱ ሲናገር የእግዚአብሔር ቃል ቅዱሳን መሆናቸውን ይመሰክራል (ዘፍ. 6÷9፤ ዘኁ. 12÷3፤ 6-8፤ ዘዳግ. 34÷10) ይህ ማለት ግን ኖኅና ሙሴ ሕግን ሁሉ ጠብቀዋል፣ ኃጢአትንም አላደረጉም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በጻድቅነቱ የተመከረለት ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ በወይን ጠጅ ሰክሮ ይታያል። ስካር ኃጢአት ነው። (ዘፍ. 9÷21) ሙሴም በበኩሉ በቃዴስ በረሃ ለተጠማው ሕዝበ እስራኤል ውኃን ከዐለት ሲያፈልቅ እግዚአብሔርን ያለመቀደስ ኃጢአት ሠርቶ ነበር። በዚህም ምክንያት ወደ ተስፋይቱ ምድር አልገባም (ዘኁ. 20÷11-13) እንዲህ ዓይነቱ ኃጢአት ያልተለየው የሰው ጽድቅ በመርገም ደም ከተበከለ ጨርቅ ተለይቶ አይታይም። የኛ የምንለው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ምንኛ አስጸያፊ ነው! (ኢሳ. 64÷6)

ክርስቶስ ግን በሰውነቱ ኃጢአትን ባለማድረጉና ሕግን በሙሉ በመፈጸሙ የሕግ ፍጻሜ ከመሰኘቱም በላይ በሕግ ፈጻሚነቱ እግዚአብሔር ደስ ተሰኝቶበታል። (ሮሜ 10÷4፤ማቴ. 12÷18 -21፤ 3÷15)

በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሊመለከተው የሚችል ፍጹምና ጻድቅ ሰው ክርስቶስ ብቻ ሆኗል። ስለዚህም እግዚአብሔር በክርስቶስ ጽድቅ ብቻ ተሸፍነው በክርስቶስ በኩል የሚመጡትን ሁሉ ይቀበላል። ያለክርስቶስ ሰው በራሱ ነገር ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ፈጽሞ አይችልም። ( ሮሜ . 3÷21-24፤ኤፌ. 2÷13፤18፤ ገላ.2÷15-16)

እኛ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ቤዛችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኛን ኃጢአት በሥጋው ተሸክሞ በመስቀል ዕዳችንን ለመክፈል ኃጢአተኛ ሳይሆን ኃጢአት ሆኖ ነበር። (2ቆሮ. 5 ÷21)

ኃጢአትን ማየት ለጻድቅ ባሕርዩ የማይስማማው አምላካችን እግዚአብሔር ልጁን ክርስቶስን ኃጢአት ሆኖ በተመለከተው ጊዜ ፊቱን ከእርሱ መለሰ። ሰዎችም በበኩላቸው የኃጢአታችን ቅጣት

ያጎሳቁለውን መልኩን እንኳ የመመልከት ድፍረት ስላልነበራቸው በመሰቀቅ ፊታቸውን ሰውረውበታል። በዚህን ጊዜ ነበር "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ" ያለው (ማቴ. 27÷46፤ ኢሳ. 53÷1-6)

እርሱ በእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ የኃጢአታችንን ተገቢ ቅጣት በሥጋው ከተቀበለ በኋላ ኃጢአታችን ይቅር ስለተባለ፥ ዕዳችን ስለተከፈለ ከዚህ በኋላ ያድናቸው ዘንድ በእምነት ለሚጠባበቁት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ያለኃጢአት ይታይላቸዋል። (ዕብ. 9÷22)

ስለዚህ በአዳኝነቱ አምነን በስሙ ስንጸልይና ስንለምን የእርሱ የጽድቅ ሥራ ለኛ በእምነት ተቆጥሮልን እንጸድቃለን። በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደሙም ዛሬም ሕያው ነውና ኃጢአታችንን ያስተሰርይልናል (ዮሐ. 14÷13፤ 15÷16፤ 16÷23-24፤ ቆላ. 3÷17፤ ሮሜ. 3÷25፤ ዕብ. 12÷24፤ 1ዮሐ. 1÷7)

በጽሑፍ የሰፈሩ ብዙ የቤተ ክርስቲያናችን ጸሎቶች ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጸለይ ብቻ መሆኑን ያስገነዝቡናል። ለምሳሌ እንደሊጦን፥ መስተበቍዕ፥ ዘይነግሥ እንዲሁም በቅዳሴ ላይ እንደ ጎዳፌ ነፍስና መስተብቍዕ ያሉት ጸሎቶች በስተ መጨረሻቸው ላይ "በአሐዱ ወልድከ" "በአንድ ልጅህ" በሚል ተማጽኖ ይደመደማሉ።

በመጽሐፈ ሰዓታት:- "ኦ! አብ በእንተ ኢየሱስ ርድአነ ክርስቶስ ኀበ አቡከ ኄር አማኅጽነነ" ትርጓሜ "አብ ሆይ ስለኢየሱስ ብለህ እርዳን ክርስቶስም በቸር አባትህ ዘንድ አደራ አስጠብቀን" የሚልና በኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት የቀረበ ጸሎት አለ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የመጸለይን ተገቢነት አባ መልከጼዴቅ በትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፋቸው ሲገልጹ:- "ጸሎታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ እንዲሆንና ተቀባይነትም እንዲኖረው በግድ ያስፈልጋል። ያለዚያማ ጻማ ከናፍር ብቻ ሁኖ ይቀራል። ሰማያዊ አባታችን ክብሩ በግልጥ እንዲታወቅ የኛም ደኅንነት እንዲጸድቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ ሊጸልይ የሚፈልግ ሁሉ እንዴት መጸለይ እንዲገባው ማወቅ አለበት። ማለት በጌታችን ስም እንዲጸልይ እንዲለምን ያስፈልጋል።" (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 189)

በአጠቃላይ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። "አልቦ መኑሂ ዘይክል በጺሐ ኀበ እግዚአብሔር ዘእንበለ ወልድ" "ያለወልድ ወደ እግዚአብሔር መድረስ የሚቻለው ማንም የለም" (ሃይ. አበ. ም. 76 ክፍል 36 ቁ.8)

ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም በ33ኛ ድርሳኑ ከቁ. 209-218 ባለው ክፍል እንዲህ ብሏል፡- "ይቤ ወናቀርብ ሎቱ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር እመንገለ ዐራቅይናሁ መሥዋዕት ዘይቤ ፍሬ ከናፍር ውእቱ እለ ይትአመኑ በስሙ ወእሉሰ አቅረቡ አባግዐ ወአልህምተ ወንሕነኒ ኢናበውእ ምንተኒ እምእሉ ግብራት አላ አኰቴተ... እስመ እግዚአብሔር ይሠምር በዘከመዝ መሥዋዕት መፍትው ለነ ናብእ ሎቱ ዘከመዝ መሥዋዕተ ከመ ያብእ ውእቱኒ ለአብ ወኢይትከሀል ያቅርቡ ምንተኒ ዘእንበለ በዐራቅይናሁ ለወልድ"

ትርጓሜ፡- "በወልድ አስታራቂነት በኩል ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን እናቅርብ አለ። መሥዋዕት የሚለው ስለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮች ፍሬ ነው። እነርሱም (የኦሪት ካህናት) ላሞችንና በጎችን ሠዉ። እኛ ግን ከእነዚህ መካከል ምንም ምን አናቀርብም፥ ምስጋናን እንሠዋለን እንጂ። እንዲህ ባለው መሥዋዕት እግዚአብሔር ደስ ይሰኛልና። እንደዚህ ያለውን መሥዋዕት እናቀርብ ዘንድ ይገባናል። እሱም (ወልድ) ለአብ ያቀርብ ዘንድ፤ ያለወልድ አስታራቂነት ምንም ምን ያቀርቡ ዘንድ አይቻልም"

# ምዕራፍ 2

# ውሃ መያዝ የማይችሉ ጉድጓዶች (ኤር. 2÷13)

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለርስቱ የመረጣቸውና ሕዝቤ የሚላቸው እስራኤላውያን እሱ በብርቱ ክንድና በተዘረጋች እጅ በድንቅና በተአምራት አባቶቻቸውን ከባርነት ነጻ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ማስገባቱን በመዘንጋት የሕይወት ውሃ ምንጭ እሱን ትተው ውሃ መያዝ የማይችሉትን ጉድጓዶች በመቆፈራቸው ሁለት ክፉ ነገሮች አደረጉ። የመጀመሪያው ክፋታቸው የሕያው ውሃ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን መተዋቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተውት የውሃ ምንጭ ምትክ ሌሎች ጉድጓዶችን መቆፈራቸው ነው። ይህም ሁለተኛው ክፉ ነገር የሚያመለክተው የተፈጠሩትንና ማዳን የማይችሉ ጣዖታትን በመከተል ለእግዚአብሔር ይሰጡ የነበረውን አምልኮና ክብር ለጣዖታቱ መሰጠታቸውን ነው። (ኤር. 2÷13)

ቤተ ክርስቲያናችን እስራኤላውያን እንዳደረጉት አምልኮተ እግዚአብሔርን በመተው ሙሉ በሙሉ አምልኮተ ጣዖትን የተከተለች ባይሆንም በሌላ አቅጣጫ ግን ከዚህ ያልተለየ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ቀጥተኛ መንገድ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አገልግሎቱን እንዳይሰጥ ለምእመናን ዝግ ከሆነ በኋላ ሌሎች አቀራራጭ የሚመስሉ ነገር ግን ዙሪያ ጥምጥም የሆኑ፥ ይህም ሆኖ ከቶ ወደ አብ የማያደርሱ ብዙ ዐዳዲስ መንገዶች ተጠርገዋል።

በዓለም ታሪክ ውስጥ ሮም በሥልጣኔዋ ገናና አገር በነበረችበት ዘመን "መንገዶች ሁሉ ወደሮም ይወስዳሉ" ተብሎላት እንደነበር የዓለም ታሪክ ይዘክራል። ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት መንገድ ግን ወደሮም እንደሚወስዱት መንገዶች ያለ አይደለም። ሰዎች በኋላ ተነሥተው የጠረጓቸው መንገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር አያደርሱም። እግዚአብሔር ያዘጋጀው መንገድ ብቻ እንጂ፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በመጽሐፈ ሰዓታት "ፍኖት ለኀበ አቡሁ አንቀጽ ዘመንገለ ወላዲሁ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ " ወደ አባቱ ለመድረስ መንገድ ወደወለደው ለመግባት የሚሆን በር እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" እንደተባለው ማለት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድነት

በመዝጋት በምትኩ ሌሎች መንገዶችን ያዘጋጁ ወገኖች የእግዚአብሔርን ትክክለኛ አድራሻ በማጥፋት ያደረሱት በደል ይህ ነው አይባልም። በጥቅሉ ሲታይ ግን እንደ ሕዝበ እስራኤል አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ክፉ ነገሮችን አድርገዋል። የኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛ መንገድነት መዝጋት የመጀመሪያው ጥፋት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለዐዳዲሶቹ መንገዶች የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ፥ የእሱነቱ ብቻ መጠሪያ የሆኑ ስሞቹንና ለእርሱ ብቻ ሊቀርብ የሚገባውን ምስጋናና አምልኮ በመስጠት የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ማክበር ሳይሆን ወደ ማምለክ መሸጋገር ነው።

"ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" (ዘጸ. 20÷3) የሚለውንና " እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው። ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም" (ኢሳ. 42÷8) የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ያልተከተለው ይህ አካሄድ ከእግዚአብሔር አሳብ ውጪ ነው።

በቃላት መዋጋትንና ክርክርን እንደበሽተኛ የሚናፍቁት የዚህ ዐዲስ ትምህርት አራማጆች መሠረታዊ የሆነ ስሕተታቸውን ትክክለኛ ለማስመሰል የእግዚአብሔርን ቃል እንደሸፋን መጠቀማቸው በአንዳንድ መድረኮች ይደመጣል።

ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱት እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ምድረ ግብጽ ወርዶ ወገኖቹን ነጻ እንዲያወጣ ሊልከው በፈለገ ጊዜ ሙሴ በተደጋጋሚ ፈቃደኛ ባለመሆኑ "እኔ ከንፈረ ቈላፍ ሰው ነኝ። ስለዚህ ሌላ ሰው ላክ " ብሎ ስለነበር እግዚአብሐር "...እይ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ። ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል" (ዘጸ. 7÷1) ያለውን ነው።

ይህን መለኮታዊ ቃል በእግዚአብሔር መንፈስ ለመረመረው ሰው ሙሴ በፈርዖን ዘንድ እንደ አምላክ ይመሰካል ወይም ደረጃው ዝቅ ያለ ትንሽ አምላክ ይሆናል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ቃሉ የሚያመለክተው ሙሴ በፈርዖን ላይ የሚኖረውን የበላይነት ነው። ስለ አፈ ኰልታፋነቱ "አሮን ነቢይ ይሆንልሃል" ወይም አፍ ይሆንሃል ተባለለት። ይህም በተግባር ታይቷል። (ዘጸ. 8÷5-9)

ሌላው ከዚሁ ጋር አብሮ የሚጠቀሰው (መዝ. 81÷6) ላይ "እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ" ተብሎ

የተጻፈው ነው። ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ስለመጣላቸው የእስራኤል አለቆችና መሪዎች የተነገረ ቢሆንም (ዮሐ. 10÷35) እንደ እግዚአብሔር አምላክ መሆንን ወይም መመለክን ከቶ አያሳይም። ይልቁንም "አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ" የተባለላቸውን "ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ" በማለት ትክክለኛ ማንነታቸውን እዚያው ላይ ይገልጻል (ቁ.7)

እኛ ግን የማይሞትና ሕያው የሆነ፥ የሁሉ ፈጣሪ፥ የሁሉ ገዥ፥ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ውስጥ የሚኖር በሦስትነት ራሱን የገለጸ አንድ አምላክ እርሱም እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ እናምናለን። (ዘዳ. 6፥4፤ ሚል. 2፥10፤ 1ጢሞ. 2፥16፤ ዘዳ. 32፥39-40) ለእርሱ ክብር ይሁን አሜን!

የሁሉም አስተዋይ ኅሊና ሊቀበለው በማይችል ሁኔታ በቤተክርስቲያናችን የአምላክ ክብርና ስፍራ በተለያዩ ልብ ወለድ ድርሰቶች ለፍጡራን ተሰጥቷል። ሆኖም ይህ ከብዙኀኑ የተሰወረ ምስጢር ነው። በየዐውደ ምሕረቱ "ለቅዱሳን የሚገባቸውን ክብር እንሰጣለን እንጂ አናመልካቸውም" ተብሎ የሚነገረው ትክክለኛ አባባል ቢሆንም ወደ ተግባራዊነቱ ስንመጣ ግን ጉዳዩን የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን።

ኢትዮጵያዊው የዜማ ደራሲ ቅ/ያሬድ በብሉያትና በሐዲሳት መጻሕፍት መሠረት ለእግዚአብሔርና ሥጋን ለብሶ ለመጣው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲስማማ አድርጎ የዘመራቸውና የጸጋ ክብር ሳይሆን አምላክነት፥ ፈጣሪነት፥ ቤዛነትና አዳኝነት እንዲሁም ገዥነት የሚንጸባረቅባቸውን መዝሙራት ከያሬድ በኋላ የተነሡና በድካሙ የገቡ የዜማ ሊቃውንት በመበረዝና በመከለስ እንዲሁም ስምን በማፋለስና ጾታን በመለወጥ ለቅድስት ማርያም፥ ለቅዱሳን መላእክት፥ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሰጥተው እናገኛለን።

ሌሎቹም ደራሲዎች በየድርሰቶቻቸው ትክክለኛውን ነገር ዐልፎ ዐልፎ ቢያስቀምጡም ይበልጥ ግን የፈጣሪን የሥራ ድርሻና ክብር ለፍጡራን ያለ አግባብ በመስጠት ፍጡራንን እያስመለኩ ይገኛሉ። ለዚህም ባንቀላፋ ቅዱሳንና መላእክት ስም የተደረሱ መልክአ መልኮች ድርሳናትና ገድላትን መመልከቱ ብቻ በቂ ነው።

መቼም ቢሆን የእግዚአብሔር ቅዱሳን በውሸት አይከብሩም። ያልሆኑትን ናችሁ፥ ያልሠሩትን ሠርታችኋል፥ ያልተናገሩትን ተናግራችኋል ብንላቸው ፈጽሞ አይቀበሉንም። ነገሩ እንዲያውም እንደ ሽሙጥ ይቆጠርብናል። ቅዱሳን በእነርሱ ውርደት እግዚአብሔር ሲከብር፥ በእነርሱ ዝቅታ የእግዚአብሔር ከፍታ ሲታይ ከማየት በቀር ራሳቸውን በማክበር እግዚአብሔርን ሊጋርዱ ወይም ሊሸፍኑ አይሹም። የቅዱሳን ሕይወት ይህ አይደለምና።

መጥምቁ ዮሐንስ የእስራኤል ልጆች በዘመኑ እንደ ታላቅ ነቢይ የተቀበሉት ሰው ነበር። (ማቴ. 14፥15፤ 21፥26)

በእጅጉ ከእርሱ የሚልቀውና የባሕርይ አምላክ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ግን የክብሩን ስፍራ ለእርሱ በመልቀቁ "ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው። ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል" ሲል ሙሽራይቱን ምእመንን ለሙሽራው ለክርስቶስ የሚያቀርብ ሚዜ መሆኑን መሰከረ (ዮሐ. 3፥29-30)

ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራን ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነና ፈጽሞ ሄዶ የማያውቀውን ሰው በተአምራት በፈወሱት ጊዜ የአገሩ ሰዎች በተደረገው ድንቅ ነገር ተገርመው "አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል" በማለት ለሐዋርያቱ ዐዲስ ስም ሰይመውላቸው በነበሩአቸው አማልክት ላይ እነርሱን እንደ ዐዳዲስ ሌሎች አማልክት ለመቀበል በማሰብ የቤተ ጣዖቱ ካህን ሊሠዋላቸው ኮርማዎችን ስቦ፥ ሊያቀዳጃቸው ደግሞ አበባ በመጎንጎን አክሊሎችን ሠርቶ ወደ እነርሱ መጣ። በዚህ ጊዜ ይህ ሁሉ ብቻውን አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ በመሆኑ፥ ካህኑ ሊያደርግላቸው የፈለገውን ሁሉ በደስታ ሳይቀበሉ አድራጎቱን ተቃውመው ልብሳቸውን በመቀደድ ወደ ሕዝቡ ሮጡ። ከዚያም እነርሱ አማልክት ሳይሆኑ ሰው ብቻ መሆናቸውን ገልጸው ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ነገሩአቸው። (የሐዋ. ሥራ 14፥8-12)

ሰማዕቱ ቅ/ጊዮርጊስን ስንመለከት ደግሞ በጌታ ስም ያደረገላትን ድንቅ ነገር ተመልክታ መበለቲቱ ሴት "አምላከ ገሊላውያን ተመሲሎ ሰብአ ወረደ እምሰማይ ወቦአ ውስተ ቤትየ" "የገሊላውያን አምላክ ሰውን መስሎ ከሰማይ ወረደ ወደ ቤቴም ገባ" በማለት ስትሰግድለት

ቅ/ጊዮርጊስ ግን መልሶ "ተንሥኢ ብእሲቶ አንሰ ኢኮንኩ አምላከ ገሊላውያን አላ ገብሩ ሎቱ" "አንቺ ሆይ ተነሽ! እኔ የገሊላውያን አምላክ አይደለሁም። ለእርሱ ባሪያ (አገልጋይ) ነኝ እንጂ" በማለት እሱነቱን እንደገለጸላት መጽሐፈ ገድሉ ይተርካል (ገድ. ጊዮ. ገጽ 92 ም. 6 ቁ 12)

"ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክም" (2ቆሮ. 4፥5) እንደተባለው ቅዱሳን አንድም ጊዜ ቢሆን የክርስቶስን ጌትነት ብቻ እንጂ ለእርሱ የሚሰጠው ክብር ለእኛም ይገባናል ብለው አልሰበኩም። ታዲያ በትሕትና ሕይወት ጌታን አገልግለው ወደ አገለገሉት ጌታ በክብር ከሄዱ በኋላ ማስተዋላቸው የተወሰደባቸው ሰዎች ቅዱሳኑ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት የለቀቁትን መድረክ ከሞቱ በኋላ ስማቸው እንዲረከበው በማድረግ አምልኮ ባዕድን ያስፋፋሉ። ሲላቸውም ስም በማፈራረቅ በአንዱ ስም አንድ ሰሞን ጉድ ያሰኙና ወረቱ ሲያልቅ ደግሞ ሌላውን ተረኛ ስም ይዘው ይነሣሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ክብሩን የሚወስደው ያው አንዱ ሌላው መንፈስ እንጂ የእግዚአብሔር ቅዱሳን አለመሆናቸውን ማስተዋል ይገባል።

በቀጣዩ ክፍል በመጽሐፈ ዚቅ ከተጻፈው ውስጥ የአምላክ ክብር ለፍጡራን መስጠቱን የሚጠቁመውን ጥቂቱን ብቻ እናቀርባለን። ይህም ጥቂቱ የተቀረውን ሁሉ አንባቢው ድርሰቶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር መርምሮ የሚጠቅመውን በመያዝ ረብ የለሹን እንዲጥል አመላካች ይሆናል ተብሎ ይታሰባል።

## ለቅዱስ ሚካኤል የተሰጠ የፈጣሪ ስፍራ

ስለዚህ ጉዳይ ከመመልከታችን በፊት ስለመላእክት ጥቂት ግንዛቤ መጨበጡ ተገቢ ነው።

መላእክት በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ረቂቃን መናፍስት ሲሆኑ የተፈጠሩበትም ዓላማ እግዚአብሔርን እያገለገሉ ፈቃዱን ለመፈጸም እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። (ዕብ. 1፥7፤ 10፤ መዝ.102፥20)

የሚሰጡትም አገልግሎት የተለያየ ነው። ይኸውም:-

- እግዚአብሔርን ዘወትር ያለ ዕረፍት በምስጋናና በስግደት ያመልኩታል (ኢሳ. 6፥2-3፤ ዳን. 7፥9-10፤ ሉቃ. 2፥13፤ ራእ. 5፥11-14፤ 7፥11-12፤ ዕብ. 1፥6)
- የእግዚአብሔርን መልእክት ለሚመለከታቸው ሰዎች ያስተላልፋሉ። ወደ ቅዱሳን ሰዎች የሚመጡት ግን ከእግዚአብሔር ሲላኩ ብቻ ነው። (ሉቃ. 1፥11-20፤ 26-38፤ ዳን. 9፥23፤ 10፤12)
- እያንዳንዱን ምእመን ይረዳሉ፤ ክፉውንም ተከላክለው ያድናሉ (መዝ. 33፥7፤ 90፥12፤ ዕብ. 1፥14)
- የሕፃናትን ነፍስ ይጠብቃሉ (ማቴ. 2፥13፤ 20፤ 18፤10)
- በዓለም የእግዚአብሔርን ፍርድ ያከናውናሉ፤ ኃጢአተኞችንም ይቀጣሉ። (2ሳሙ. 24፥16፤ የሐዋ. ሥራ 12፤23፤ ዘፍ. 19፥2፤ 2ነገ. 19፥35)
- ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ በብዛት ሆነው ያጅቡታል (ማር. 8፥38፤ 2ተሰ. 1፥7)
- የተፈረደባቸውን ወደ ዘላለም ኩነኔ በመጣል የተመረጡትን ደግሞ ይሰበስባሉ። (ማቴ. 13፥39፤ 49)
- ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋትን ይመለከታሉ (የሐዋ. ሥራ 5፥19፤ 8፥26፤ 1ጢሞ. 5፥21)
- ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ደስ ይላቸዋል (ሉቃ. 15፥10)
- በክርስቶስ ለሰዎች የተደረገውን ጥበብ ሊመለከቱ ይሻሉ። (ኤፌ. 3፥10፤ 1ጴጥ. 1፥12)

ይህን ተግባር ከሚያከናውኑት መካከል አንዱና በመላእክት ላይ አለቅነት ያለው መልአክ ቅ/ሚካኤል ነው። የመላእክት ማንነትና አገልግሎት ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ሳለ ለቅ/ሚካኤል የአምላክን

ስፍራና ክብር መስጠት በሌላም በኩል ሚካኤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያላደረገውን ነገር ሁሉ አድርጓል በማለት መዋሸት በእውነት ሚዛን ላይ ተመዝኖ ቀልሎ መገኘት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገውን ነገር ሲናገር ስሙን ጭምር ይጠቅሳል። (ዳን. 10፡13-21፤ 12፡1፤ ይሁ. 9፤ ራእ. 12፡7)

ሚካኤል በተጻፈው መሠረት እንጂ በውሸት የፈጠራ ድርሰት አይከብርም። እስቲ በመጽሐፈ ዚቅ ለእርሱ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ስፍራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማነጻጸር እንመልከት:-

ሀ/ "ቦኑ ኢትክል አድኅኖ እዴየ ወቦኑ ዘኢይሰምዕ በእዝንየ አክብሩ በዓልየ ወሑሩ በሕግየ ትበልዑ ከራሜ፣ ከራሜ፣ ከራሜ እምበረከትየ ወእምፍሬ ተግባርየ ይቤ ሚካኤል"

ትርጓሜ:- "ሚካኤል አለ፣ በውኑ እጄ ማዳን አትችልምን? በጆሮዬስ የማልሰማ ነኝን? በዓሌን አክብሩ፣ ሕጌንም ጠብቁ፣ ከሥራዬ ፍሬ ከበረከቴም የከረመውን ትበላላችሁ" (የመስከረም ሚካኤል ዚቅ)

እንደ ደራሲዎቹ የሐሰት ምስክርነት ይህን ቃል የተናገረው ሚካኤል ሳይሆን የሚካኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔር ነው። (ዘሌዋ. 24፡ 18-22፤ ኢሳ. 59፡1) "በዓሌን አክብሩ፤ ሕጌንም ጠብቁ፤ ከሥራዬ ፍሬ ከበረከቴም ትበላላችሁ።" ለማለት የተገባው ከአንዱ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር በቀር ማነው? (መዝ. 103፡13)

"ሚካኤል በዓሌን አክብሩ" አለ ብለው እየዋሹ እውነቱን እንድንመሰክር ካነሳሡን የሚካኤል በዓል አከባበር በተለይም የኅዳር ሚካኤል እንዴት መከበር እንደጀመረ ታሪካዊ የት መጣውን ከቤተክርስቲያን መጻሕፍት ማስረጃ በማቅረብ መመልከት እንችላለን።

"በግብጽ አገር "ዙሐል" ተብሎ የሚጠራ ጣዖት ነበር፤ የግብጽ ሰዎች ከሌሎች ጣዖታት አጅግ አድርገው ያከብሩታልና ያመልኩት ነበር። ሐዋርያው ቅ/ማርቆስ የግብጽን ጣዖቶች ሁሉ ሲደመስሳቸው ዙሐልን ሳይደመስሰው ቀርቶ ነበር። ከማርቆስ ቀጥለው የተሾሙ ብፁዓን ጳጳሳትና ቅዱሳን አበውም ሁሉ የዙሐልን ተመላኪነትና ተከባሪነት ማስቀረት ሳይቻላቸው እስከ 320 ዓ.ም. ያህል የግብጽ ሰዎች ሲሰግዱለትና ሲያመልኩት ኖረዋል።

ዙሐል ከቀሩት ጣዖታት የበለጠ ተአምራታዊ ኃይል ወይም የተለየ ምትሐት ኑሮት ሳይሆን የቀሩት ጣዖቶች አንድ በአንድ ሲወድቁና ሲደመሰሱ የግብጽ ሕዝብ አልተጋፋም ነበር። ዙሐልን የደፈርን እንደሆነ ግን ሕዝብ ይነሣብናል በማለት ፈርተው ነበር። በተጠቀሰው ዓ/ም ግን የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባ እለእስክንድሮስ እንደምንም ብሎ ሕዝቡን እያግባባና እያስተባበረ እያባበለም ብዙዎችን በማስረዳትና በማሳመን "ዙሐል" ከምኩራብ ጣዖትነቱ ተነሥቶ በምትኩ የቅ/ሚካኤልን ታቦት እንዲገባበት አድርጎ የዙሐል በዓል በየዓመቱ ኅዳር 12 ቀን ይከበር ስለነበረ ኅዲገ ልማድ ጽኑዕ ውእቱ ነውና ሕዝቡን ለማስደሰት ሲል በዚያው በተለመደው ኅዳር 12 ቀን ይከበር ብሎ ዐዋጅ አስነግሮ ዐዋጁም ጸደቀ" (መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 152-153)

የእግዚአብሔር እውነተኛና ታማኝ አገልጋይ ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ለማስደሰት ሲል አይኖርም። አሊያማ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊባል አይችልም። "ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።" (ገላ. 1፥10፤ 1ተሰ. 2፥4)

የኅዳር ሚካኤል በዓል አከባበር የት መጣው እንዲህ ሆኖ ሳለ ዛሬ ግን በዕለቱ የሚነገረው የዙሐልን በዓል ለማስቀረት ባለመቻሉ በምትክነት የተሠራ በዓል መሆኑ ሳይሆን "ሚካኤል ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣበት ቀን" ተብሎ ነው የሚከበረው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሚካኤል ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ማውጣቱን አይናገርም። እርግጥ እግዚአብሔር ሚካኤልን ልኮ ሕዝቡን ከግብጻውያን እጅ ሊያድናቸው ይችላል። እንዲያውም በዘመኑ መጨረሻ በክርስቶስ አዳኝነት አምነው ለሚድኑት የእስራኤል ቅሬታዎች ሚካኤል እንደሚቆም የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። (ዳን. 12፥1፤ ራእ. 12፥7) ነገር ግን ሕዝበ እስራኤል ከምድረ ግብጽ ሲወጡ በፊታቸው የወጣው መልአክ ሚካኤል ነው አይልም። (ዘጸ. 3፥2-6፤ 23፥20-23፤ የሐዋ. ሥራ 7፥30-34) ስሙ በግልጽ ያልተጠቀሰው ይህ የጌታ መልአክ ፍጡር የሆነ መልአክ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር በአርአያ መልአክ ተገልጾ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ስፍራ

ያስተምረናል። (ዘዳ. 32፥12፤ መሳ. 2፥1-5፤ 6፥8-9፤ መዝ. 135፥16፤ 104፥43፤ ኤር. 32፥21፤ ሆሴ. 12፥14)

ሰይፈ ሥላሴ የተሰኘው የቤተ ክርስቲያኒቱ የጸሎት መጽሐፍ ገና በምድረ በዳ በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ለሙሴ የታየውና ሕዝቡን የመራ የእግዚአብሔር መልአክ የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጾታል፡- "ስብሐት ለመልአከ እግዚአብሔር ዘአስተርአየ ለሙሴ በነደ እሳት በኀበ ዕፀ ጳጦስ መልአክኒ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ"

ትርጓሜ፡- "በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ሙሴን ለታየው ለእግዚአብሔር መልአክ ክብር ይሁን። መልአክ የተባለውም የእግዚአብሔር ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው።" (ሰይፈ ሥላሴ ዘረቡዕ)

ሙሴና ሕዝበ እስራኤል ፍጡር መልአክ (ሚካኤል) ሳይሆን ጌታ ራሱ ነጻ እንዳወጣቸውና የሚመራቸውም እርሱ ራሱ መሆኑን ተረድተዋል። በጣዖት አመልኮ እስካሳዘኑት ጊዜ ድረስም አብሮአቸው የተጓዘው እግዚአብሔር እንደነበር፥ ከዚህ በኋላ ግን እርሱ አብሮአቸው እንደማይወጣና ሌላ ፍጡር የሆነ መልአክ እንደሚልክላቸው መናገሩ ብቻ እንኳ በቂ ማስረጃ ሲሆን ይህን ሁኔታ የሰሙት ሙሴና ወገኖቹ በፍጡር መልአክ በመመራትና በራሱ በእግዚአብሔር በመመራት መካከል ታላቅ ልዩነት አለና በሰሙት ክፉ ወሬ ማዘናቸው የነገሩን እውነተኛነት ያረጋግጥልናል። (ዘጸ. 33፥1-4)

ሙሴ እግዚአብሔር የተናገረውን ከሰማ በኋላ "አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ ከዚህ አታውጣን" በማለት መለሰ። እግዚአብሔርም የሙሴን ጥያቄ ተቀብሎ ራሱ አብሯቸው ለመውጣት ተስማማ። (ዘጸ. 33፥ 14-17)

እርሱም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በተለየ ግብሩ ልጅ ነውና ልጅነቱን ለአባቱ የሚታዘዝ፥ የሚላክ፥ ጻድቅ ባሪያ፥ ቅን አገልጋይ፥ ፈቃድ ፈጻሚ በመሆን አስመስክሯል። (ኢሳ. 42፥1፤ 52፥13-15፤ 53፥11፤ዮሐ. 17፥ 1-5፤ ዕብ. 5፥8)

ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም ተብሎ እንደተጻፈ (መዝ. 106፤20) እግዚአብሔር በአርአያ መልአክ ወደ ሕዝቡ የላከው አካላዊ ቃሉን

ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። እርሱም በዘመነ ሥጋዌው አይሁድ "አንተ ማነህ?" በማለት ላቀረቡለት ጥያቄ ሲመልስ "ከመጀመሪያ ለእናንተ የተናገርሁት ነኝ" በማለቱ እርሱነቱን ገልጿል። (ዮሐ. 8፥25) በዚህም ሕዝቡን በክርስቶስ ያሉ የክርስቶስ ሕዝብ አሰኝቷል። (ኤፌ. 2፥12፤ ዕብ. 11፥25-26)

መላክ የልጅነት ግብሩ መሆኑንም በቃሉ አረጋግጦአል (ዮሐ. 7፥28-29፤ 8፥26) በሌላም አኳኋን ቅ/ጳውሎስ ሕዝበ እስራኤልን በምድረ በዳ እየተከተለ ውሃ ያጠጣቸው ዐለት ክርስቶስ መሆኑን መስክሯል። (1ቆሮ. 10፥4)

ይህም ብቻ አይደለም ሙሴ "እባክህን ክብርህን አሳየኝ" ሲል ላቀረበው ጥያቄ "ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም . . . እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ። በዐለቱም ላይ ትቆማለህ፥ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዐለት አኖርሃለሁ። እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ። እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ። ጀርባዬንም ታያለህ ፊቴን ግን አታይም" የሚል መልስ ከእግዚአብሔር ተሰጠው። (ዘጸ. 33፥18-23)

እግዚአብሔር በመለኮታዊ ባሕርዩ ለመታየት ባይችልም የክርስቶስ አምሳል በነበረው ዐለት ለሙሴ ክብሩን አሳይቷል።፥ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔርን ለማየት የሚችል የለም። ለሙሴ በምሳሌው ዐለት ላይ ክብሩን እንዳሳየ ሁሉ በአማናዊው፥ በእቅፉ ባለውና የመለኮቱ ሙላት በተገለጸበት የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ በሆነው ሥጋን ለብሶ በመጣው በክርስቶስ እግዚአብሔር ተገልጧል። (ዮሐ. 1፥18፤ ቈላ. 2፥9፤ ዕብ. 1፥3፤ ዮሐ. 14፥9፤ 1፥14)

እዚህ ላይ መጠንቀቅ ያለብን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአርአያ መልአክ በአርአያ ኵኵሕ ተገለጸ ማለት እርሱ ፍጡር መልአክ ነው፥ ወይም ደግሞ የዘመኑ አርዮሳውያን አፋቸውን ሞልተው እንደሚናገሩት "ኢየሱስ ሚካኤል ነው" ማለት አይደለም። (ሎቱ ስብሐት! ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁን!) ነገር ግን በመልአክ አምሳል ተገልጾ ሕዝቡን መራ እኛንም ሰው ሆኖ አዳነን እንጂ:- "ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ውስተ መጻሕፍት ወልደ ዕጓለ እመሕያው በእንተ ሥርዓተ ትስብእቱ ወዓዲ ተሰምየ እግዚአብሔር፥ ወልደ እግዚአብሔር፥ ወመልአከ፥ ወመዝራእተ፥ ወነቢየ፥ ብዙኀ ጊዜያተ የዐውቆ ከመ ውእቱ አምላክ ወዓዲ ብዙኀ ጊዜያተ የዐውቆ ከመ ውእቱ ሰብእ"

ትርጓሜ:- "ስለዚህም ሰው ስለሆነ በመጻሕፍት ውስጥ የሰው ልጅ ተባለ። ዳግመኛም እግዚአብሔር፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ መልአክ፥ ክንድ፥ ነቢይ፥ ተባለ። አምላክ እንደሆነ መላልሶ መጽሐፍ ያስረዳል። ሰውም እንደሆነ መላልሶ ያስረዳል" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 83 ቁ. 12፤ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 6 እና 7)

ለ) "መፍትው እንከ አኀውየ ንግበር በዓለነ በኵለሄ በታሕተ ሰማይ ንፌኑ ስብሐተ ፍሬ ከናፍሪነ እስመ ሚካኤል እግዚእነ"

ትርጓሜ:- "ወንድሞቼ! ከሰማይ በታች በሁሉ ስፍራ በዓላችንን እናከብር ዘንድ (እናደርግ ዘንድ) ይገባናል። የከንፈራችንን ፍሬ ምስጋናን እንላክ ሚካኤል ጌታችን ነውና።" (የመስከረም ሚካኤል ዚቅ)

ከሰማይ በታችም ይሁን በሌላው ስፍራ ያለው ጌታ አንድ ብቻ ነው (ኤፌ. 4፥5፤ 1ቆሮ. 8፥7) በምድር ላይ በተሰጣቸው ምድራዊ በረከት በሥጋ ላይ ጌቶች የሆኑ ቢኖሩም የሁሉ ጌታ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ዓይነት ንጽጽር የላቸውም። ይልቁንም በሥጋ ጌቶች የተባሉቱ ራሳቸው ለጌቶች ጌታ እንደ አገልጋይ ሆነው ይገዛሉ። (ኤፌ. 6፥9)

ስለዚህ በእግዚአብሔር ቃል እንደታዘዝነው የከንፈራችን ፍሬ የሆነውን የምስጋና መሥዋዕት የምንሠዋው በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ለአንዱ ጌታ ብቻ ነው። "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ (በኢየሱስ ክርስቶስ) እናቅርብለት።" (ዕብ. 13፥15)

ሐ) "ሚካኤልኒ የሀበነ ምሕረቶ ወምድርኒ ተሀበነ ፍሬሃ"

ትርጓሜ:- "ሚካኤል ምሕረቱን ይስጠን ምድርም ፍሬዋን ትስጠን" (የመስከረም ሚካኤል ዚቅ)

የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም በሚካኤል በመተካት ለሚካኤል ተስማሚ ያልሆነ የአምላክነትን ሥራ የሰጡበትን ይህን ቃል (በመዝ. 84፤ 12) ዘማሪው በተገቢው መንገድ ለእግዚአብሔር ዘምሮታል። በግእዙ መዝሙረ ዳዊት "ወእግዚአብሔርኒ ይሁብ (የሀበነ) ምሕረቶ ወምድርኒ ትሁብ (ተሀበነ) ፍሬሃ" የሚል ሲሆን በአማርኛ መጽሐፍ

ቅዱስ ላይ ደግሞ:- "እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች" ይላል።

እውነት ነው ከእግዚአብሔር በቀር በጎ ነገርን በመስጠት ምድራችን ፍሬ እንድታፈራ የሚያደርግ የዚች ዓለም ሠራዒና መጋቢ እንደሌለ የታመነ ነው። (መዝ. 15፥2) ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር አምላክነት ያላረካቸው ስሑታን ሚካኤልም እንደ እግዚአብሔር ምሕረት ሰጪ የሆነ ሌላ አምላክ ነው እያሉን ነው።

መ) "ስማዕ ጸሎተነ ወስእለተነ ወስረይ ኩሎ ኃጢአተነ ኖላዊነ ኄር ዐቃቤ ነፍሳቲነ በዕለተ ምንዳቤነ ስፋሕ ክነፊከ ለረድኤትነ ነዓ ኀቤነ"

ትርጓሜ:- "ጸሎታችንንና ልመናችንን ስማ፤ ኃጢአታችንንም ይቅር በል። ነፍሶቻችንን የምትጠብቅ ቸር እረኛችን ሚካኤል ሆይ! በችግራችን ቀን ክንፍህን ዘርጋ እኛን ለመርዳትም ወደእኛ ና!" (የኅዳር ሚካኤል ዚቅ)

በዚህ ድርሰት ውስጥ የተነገሩት ነገሮች:- ጸሎትንና ልመናን መስማት፥ ሰምቶም ኃጢአትን ይቅር ማለት፥ በቸር እረኝነቱም መጠበቅ ማስጠበቅ የአገሩን ስፋት ሁሉ በሚሸፍነው ክንፉ መጋረድና ማዳን የእግዚአብሔር ብቻ የሥራ ድርሻ ነው። (መዝ. 64፥1-3፤ ማር. 2፥5-12፤ መዝ. 120፥3-8፤ ዮሐ. 10፥11፤ መዝ. 101፥1-2፤ ኢሳ. 8፥8፤ ዘዳ. 32፥11)

መላእክት ረቂቃን መናፍስት ቢሆኑም በቦታ የሚወሰኑ ናቸውና በሁሉ ስፍራ የመገኘት ባሕርይ የላቸውም። ስለዚህ ምሉዕ በኩለሄ የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ካላካቸው በስተቀር የእኛን የድረሱልን ጥሪ ሰምተው ሊመጡ ፈጽሞ አይችሉም። በስፍራ የሚወሰኑና በሁሉ ቦታ የመገኘት ብቃት የሌላቸው መሆኑን ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ ዕብ. 1፥14ን ሲተረጉም የወልደ እግዚአብሔርን ተልኮ መምጣት ከእነርሱ መላክ ጋር አነጻጽሮ እንዲህ ብሏል:- "ወእኮ ዘፈለሰ ሶበ ተፈነወ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት እስመ ይትኀጥኡ እመካኖሙ ሶበ ይትፌነዉ"

ትርጓሜ:- "ወልድ በተላከ ጊዜ እንደ መላእክት ቦታውን ለቆ የሄደ አይደለም። መላእክት ሲላኩ የነበሩበትን ቦታ ለቀው ይሄዳሉ ወደ ተላኩበትም ስፍራ ይደርሳሉ" (ድርሳን 3 ቁ. 155-156)

ስለዚህ የእግዚአብሔር እርዳታ በሚያስፈልገን ሰዓት በቅዱሳን መላእክቱም ሆነ እርሱ በወደደው መንገድ እንዲያድነን ሊሰማን ወደሚችል ወደ እሱ በሙሉ ኃይላችን መጸለይ አለብን። በምድር ሆነን የጸለይነውን በሰማይ ሆኖ የሚሰማ እግዚአብሔር ብቻ ነው። (1ነገ. 8፥28-53)

ሠ/ "ይቤ ሚካኤል ሰባሕኩከ በዮርዳኖስ በቅድመ ዮሐንስ መጥምቅ ሰባሕኩከ በደብር በቅድመ ሙሴ ወኤልያስ ነቢያት ምእመናኒከ ሰባሕኩከ ሰባሕኩከ ወዓዲ እሴብሐከ"

ትርጓሜ:- "ሚካኤል አለ በመጥምቁ ዮሐንስ ፊት አከበርኩህ፤ በተራራ ላይ ታማኞች በሆኑት ነቢያት በሙሴና በኤልያስ ፊት ፈጽሞ አከበርኩህ፤ ዳግመኛም አከብርሃለሁ።" (የጥር ሚካኤል ዚቅ)

በዚህ ድርሰት ውስጥ ሚካኤል የአብን ስፍራ ተክቶ ጌታውን ኢየሱስ ክርስቶስን "አከበርኩህ" በማለት በእውነት ላይ የቀልድ ድራማ እንደሚሠራ ተዋናይ ተደርጎ ቀርቧል።

ሚካኤል ከዲያብሎስ የትዕቢት አሳብ የራቀ ቅዱስ መልአክ እንደመሆኑ የአብን ስፍራ የመያዙ ድፍረት ፈጽሞ የለውም። እሱ ዘወትር የጌታውን ፈቃድ ለማድረግ የሚተጋ አገልጋይ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅም ሆነ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ተራራ ላይ (እንደ ቤተክርስቲያናችን ትምህርት ደብረ ታቦር) "የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት በማለት ልጁን የገለጠውና ያከበረው እግዚአብሔር ነው። (ማቴ. 3፥7፤ 17፥5) ስለሆነም ክርስቶስ ስለ መሲሕነቱ ምስክርነትንም ሆነ ክብርን ከአባቱ እንጂ ከሌላው እንደማይሻ ተናግሯል። (ዮሐ. 5፥31-34፤ 37፤ 8፥18፤ 17፥5)

መቼም በእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ አይደረግም ይሆናል እንጂ ሚካኤል ያላለውን "ብሏል" ያሉትን ክፍሎች በስም አጥፊነት ከሶ ሊያስቀጣቸው በቻለ ነበር። ሆኖም ክብሩን

ለሌላ የሰጡበትን ሰዎች ጌታ ይበቀላቸዋል። (ዘዳ. 4፡23-24፤ 6፡14-15፤ 1ቆሮ. 10፡22)

## ለቅዱስ ገብርኤል የተሰጠ አምላካዊ ስፍራ

ሀ) "ከመ ጽጌ ደንጐላት ናርዶስ ወሀበ መዓዛሁ መላትሒሁ ድጉኃን ገብርኤል እኁየ ይትሜሰል ከመ ወይጠል"

ትርጓሜ:- "እንደሱፍ አበባ ናርዶስ መዓዛውን ሰጠ። ጉንጮቹ የጸኑ ወንድሜ ገብርኤል እንደሚዳቋ ይመስላል" (የጥቅምት ገብርኤል ዚቅ)

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንዲሚያስተምሩት በማሕልየ መሓልይ ዘሰሎሞን በሁለቱ ፍቅረኛሞች መካከል የተገለጸው የፍቅር ግንኙነት በብሉይ ኪዳን መንፈሳዊ ፍቺው የእግዚአብሔርንና የቤተ እስራኤልን ግንኙነት ሲያሳይ በዐዲስ ኪዳን ደግሞ የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት የሚያሳይ ነው።

የዐዲስ ኪዳኑን ፍቺ ቅ/ያሬድ ሲገልጸው:- "በማሕልየ መሓልይ ትነግር ቤተ ክርስቲያን እንዘ ትብል ወልድ እኁየ ወረደ ውስተ ገነት ወአነሂ ምስሌሁ ዘልፈ" "በማሕልየ መሓልይ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ወንድሜ (ክርስቶስ) ወደገነት ወረደ። እኔም ለዘወትር ከእርሱ ጋር ነኝ እያለች ትናገራለች' ብሏል። (የጥቅምት መርቆሬዎስ ዚቅ አቡን)

በመሆኑም የማሕልየ መሓልይ ትርጉም በዐዲስ ኪዳን ከክርስቶስና ከቤተ ክርስቲያን (ከምእመናን) ዐልፎ ተርፎ ከጊዜ በኋላ ለተፈጠረ እንግዳ ትምህርት መሸፈኛነት በተናጠል፣ ስምና ጾታ በመለወጥና በአንድምታ ጋጋታ ለሌላ ሊሰጥ ፈጽሞ አይችልም። እንደዚሁም ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ወንድሜ ብላ ስለውዷ ስለ ክርስቶስ የተናገረችውን ለገብርኤል መስጠቱም በዚሁ ሚዛን የሚመዘን ነው።

ገብርኤል በሥጋና በደም የተካፈለ ባለመሆኑና ከቅዱሳን መናፍስት አንዱ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ወንድም ሊባል፣ ጎንጮች አሉት ተብሎ ሊነገርለት አይገባም። ይነገርለት ቢባል እንኳ ስለ ጉንጮቹ ሊሰጥ የሚችል መንፈሳዊ ትርጉም ባልተገኘ ነበር። ክርስቶስ ግን በሥጋና በደም በመካፈሉ ምክንያት ወንድምነትን ገንዘቡ አድርጓልና ቤተ ክርስቲያንን እህቴ ብሎ ሊጠራት እንደተገባው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ልጅ ወንድሜ ብላ ልትጠራው ተገብቷታል። (ማሕ. 5፥1፤ ዕብ. 2፥10-17፤ ሮሜ 8፥29፤ ዮሐ. 20፥17)

መንፈሳዊ ምንዝርና የተጠናወታቸው ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ስም ለማጉደፍ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ውዶች እንዳሏት አስመስለው ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል። የእሷ ውድ ግን ከአእላፍ የተመረጠና እሷ ብቻ የምታውቀውን ምልክት የያዘ አንድ ብቻ ነው። (ማሕ. 5፥10-16)

ለ) "መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን መልአከ ሥረዊሆሙ ለመላእክት ገብርኤል አሠርገዋ ለምድር በስነ ጽጌያት፣ ሰማየ በከዋክብት"

ትርጓሜ:- "የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ የመላእክት ጭፍራ አለቃ የሆነ ገብርኤል ሰማይን በከዋክብት፣ ምድርን በአበቦች አስጌጠ"

ሐ) "መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን መልአከ ሥረዊሆሙ ለመላእክት ገብርኤል ለነገሥት ዕበይ ወስን አሆ፤ ብሂሎ ተአዛዜ ከዊኖ ወረደ ወመጽአ ለአድኅኖ"

ትርጓሜ:- "የቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋ የመላእክት ጭፍራ አለቃ ገብርኤል ለነገሥታት ክብርና ሞገስ ነው። እሺ ብሎ ታዛዥ በመሆን ከሰማይ ወረደ፤ ለማዳንም መጣ" (የታኅሣሥ ገብርኤል ዚቅ)

የጋብቻን ቅዱስ ሕግ በሠራ በእግዚአብሔር ዘንድ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ብቻ እንደምትሆን ምስክር አያሻውም። ከታጨችለት ከአንዱ ወንድ ውጪ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች።

ሙሽራዋ ክርስቶስ ብቻ የሆነላት ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ናት። በዚህ አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን የተባለችው ሕንፃ ሳትሆን በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን አንድነት ናት።

ምእመንን በንስሐ ሕይወት አዘጋጅቶ ወደ ሙሽራዋ ወደ ክርስቶስ በማቅረቡ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስተያን ሙሽርነት ሚዜ የተሰኘው መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ነበር ሁኔታውን የገለጸው:- "ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው። ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል" (ዮሐ. 3፥29)

በየዘመናቱ የተነሡ የወንጌል አገልጋዮችም በዘመናቸው ያሉትን ምእመናን በሙሽርነት ያጩት በመዝሙር መጽሐፍ:- "እርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል እንደ አርበኛ በመንገዱ ለመሮጥ ደስ

ይለዋል አወጣጡ ከሰማያት ዳርቻ ነው። ዙረቱም እስከ ዳርቻቸው ነው። ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም" ለተባለለት ለአንድ ወንድ ለክርስቶስ ብቻ ነው። (መዝ. 18፥5-6፤ 2ቆሮ. 11፥2)

ቤተ ክርስቲያን የምታውቀውና የኔ የምትለው ሙሽራዋ ስለእርስዋ ራሱን አሳልፎ በመስጠት የወደዳትን ክርስቶስን ብቻ ነው። እስከ ሞት ድረስ ለወደዳት ለእርሱ ብቻም ትገዛለች። (ኤፌ. 5፥23-32)

"ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ቤተ ክርስቲያንህ ትሰግድልሃለች። ሙሽራህም ከፍ ከፍ ታደርግሃለች" (ቅዱ. ቄርሎስ ቁ. 49)

ቤተ ክርስቲያን በበጉ የሠርግ ቀን ራሷን በማዘጋጀት የእርሷ የአካል ብልቶች በሆኑት በቅዱሳን የጽድቅ ሥራ በተመሰለው ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ተጐናጽፋ እንደምትታይ በተስፋ ይጠበቃል። (ራእ. 19፥7-8)

ይህን ሁሉ እውነተኛ ነገር ወደ ጎን በመተው ቤተ ክርስቲያንን ለሌሎች ለማጨት ማሰብ ጌታ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ለራሱ ብቻ ሊያቀርብ የፈለጋትን ክብርት ቤተ ክርስቲያንን እንደ አመንዝራ መቁጠር ነው። (ኤፌ. 5፥27)

ቤተ ክርስቲያንም እንዲህ አድርጋ ብትገኝ በቀደመው ዘመን ቤተ እስራኤል ሙሽራዋ እግዚአብሔርን ትታ ሌሎች አማልክትን በዘማዊነት በመያዟ ምክንያት ሙሽራዋ እግዚአብሔር ቀንቶ እንደተቆጣትና እንደፈረደባት የቤተ ክርስቲያንም ዕጣ ፈንታዋ ከዚህ የበለጠ እንጂ ያነሰ አይሆንም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ስሐተቷን አስተካክላ በይቅርታ በመመለስ በሌሎች ያስቀናችውን ውዷን፦ "ይቅርታ አድርግልኝ ከእንግዲህ በኋላ ግን ያንተ ብቻ ነኝ" በማለት ልትታረቀው ይገባታል። (ኤር። 3፥1-11፤ ሕዝ. 16፥1-63)

ለገብርኤል ከክርስቶስ የሙሽርነት ስፍራ ሌላ የፈጣሪነት፥ የክርስቶስ የአዳኝነት ስፍራም ተሰጥቶታል። ይህም የተደረገው ለገብርኤል ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹም ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ጭምር ነው። ለምሳሌ ያህል እንኳ ለሰማዕቱ መርቆሬዎስና ለቅድስት ማርያም የተሰጠውን መመልከቱ ይበቃል፦

"ዕገኒ ለስምከ ወእሴብሕ በኃይልከ ሰማዕ ጸሎተ ኩሉ ዘሥጋ ዘመጽአ ኀቤከ፤ ኢታጕንዲ እግዚአ መርቆሬዎስ ሣህለከ፤ በከዋክብት ሰማየ ዘከለልከ፤ ወበጽጌያት ምድረ አሠርጐከ፤ ፌት ብርሃንከ፤ ወጽድቀከ፥ እማንቱ ይምርሐኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ"

ትርጓሜ:- "ለስምህ እገዛለሁ፥ በኃይልህም አመሰግናለሁ፥ ወዳንተ የሚቀርብ የሥጋ ለባሽን ሁሉ ጸሎት ስማ! መርቆሬዎስ ሆይ! አቤቱ ይቅርታህን አታዘግይ! ሰማይን በከዋክብት የጋረድህ ምድርን በአበቦች ያስጌጥክ ነህ። ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፥ እነርሱም ይምሩኝ ወደ ቅድስናህ ተራራም ይውሰዱኝ።" (የጥቅምት መርቆሬዎስ ዚቅ)

"ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ ለመድኃኒትነ ማርያም ድንግል ለዘገብረት ብርሃናተ ዐበይተ ባሕቲታ"

ትርጓሜ:- "ታላላቅ ብርሃናትን ብቻዋን ለፈጠረች ለመድኃኒታችን ለድንግል ማርያም ኑ! እንስገድ እንገዛላትም" (የየካቲት ኪዳነ ምሕረት ዚቅ)

ለሦስቱም የተሰጣቸው ስፍራ፥ ምስጋና፥ ክብርና የሥራ ድርሻ ለእነርሱ የሚገባ አለመሆኑ የሚታወቅ ሲሆን የስም መፋለስና የጾታ ለውጥ የተደረገበት ድርሰት መሆኑም ግልጽ ነው። ይህን ስሕተት፥ ስሕተት ነው ለማለት ማስረጃ ማቅረብ ባያስፈልግም ማስረጃ ሰጥቶ ማለፉ አግባብነት ያለው በመሆኑ የሰዎችን ውሸት በእግዚአብሔር እውነት እናፈርሳለን። (2ቆሮ. 10፥5)

ታላላቅ ብርሃናት የተባሉ ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብትን እንዲሁም የምድር አበቦችን ያለማንም እርዳታ ብቻውን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። (ዘፍ. 1፥11-19፤ መዝ. 135፥7-9፤ 146፤ 4፤ 8፤ ኢሳ. 40፥ 26፤ 45፥7)

"እርሱ ብቻ አምላክ ነው። እርሱ ብቻ ጌታ ነው። ፈጣሪም እርሱ ብቻ ነው። ሠሪም እርሱ ብቻ ነው። ስላሰበው ጥበብ ረዳት አይሻም፤ ስለወደደውም ሥራ መካር አይሻም።" ቅዳ. ኤጲፋንዮስ ቁ. 11-12)

ደራሲዎቹ በሐሰት ድንግል ማርያም ያልፈጠረችውን ፈጥራለች፥ ያልሆነችውን ነች በማለት ያጭበረበሩትን ሊቁ ጎርጎርዮስ በቅዳሴው "ብርሃናትን የፈጠረ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።" በማለት እውነቱን አፍረጥርጦ ይናገርባቸዋል። (ቅዳ. ጎርጎርዮስ ካልእ ቁ. 58)

ደግሞም "ለርሱ ብቻ እንሰግድ ዘንድ ኑ!" በማለት ፍጥረቱን ሁሉ ለእርሱ ብቻ ይሰግዱ ዘንድ ይጋብዛል (ቅዳ. ጎርጎርዮስ ቁ. 42፤ መዝ. 94፥6)

በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር ሳይቆጥር ዓለምን ለማዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ እስከ መስቀል ሞት ድረስ እሺ ባይ ታዛዥ በመሆን ከሰማያት የወረደውና ወደኛ የመጣው ገብርኤል ሳይሆን ክርስቶስ ነው። (ፊልጵ. 2፥10-11፤ ኢሳ. 45፥23፤ ራእ. 5፥13)

መዝሙረኛው ዳዊትም "ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፣ እነርሱ ይምሩኝ ወደቅድስናህ ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ" በማለት የለመነው መርቆሬዎስን ሳይሆን አምላኩን እግዚአብሔርን ብቻ ነው። (መዝ. 42፥3)

መዳንም ቢሆን በሌላ በማንም የለም። እንድንበት ዘንድ የተሰጠን ብቸኛ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (የሐዋ. ሥራ 4፥12፤ ማቴ 1፥21፤ ኢሳ. 43፥11፤ ሆሴ. 13፥4)

የኢየሱስን መድኃኒትነት አቃልሎ ወይም ብቻውን ያለተጨማሪ መድኃኒቶች እንደማይጠቅም ቆጥሮ መድኃኒት ማብዛቱ ግን "መድኃኒት ያበዛሽው በከንቱ ነው። መዳንም የለሽም" እንደተባለችዋ መሆን ነው እንጂ ሌላ ትርፍ የለውም። (ኢሳ. 47፥11)

ቅድስት ማርያምን ከፍጥረታት አልቀን በማየት የምንወዳትና የምናከብራት የመድኃኒታችን እናት በመሆኗ እንጂ ራሷ መድኃኒት ነች ብለን አይደለም። እንዲህ ቢሆንማ ከእርስዋ መድኅን ክርስቶስ መወለድ ሳያስፈልገው ድኅነታችን በእርሷ በኩል ይፈጸም ነበር። ግን አልሆነም፤ ስለዚህ እርሷ ራሷ "መድኃኒቴ" ብላ በመጥራቷ መድኃኒት እርሱ ብቻ መሆኑን አመለከተች። (ሉቃ. 1፥47)

የእግዚአብሔርን የሥራ ድርሻና ክብሩን ለፍጡራን መስጠት የእግዚአብሔር አሳብ አይደለም። በክርስቶስ አምነው የዳኑ ቅዱሳን የዘላለም ሕይወት ከማግኘታቸው ባሻገር በክርስቶስ ኖረው በሚያፈሩት መልካም ፍሬ ታላቅ ሽልማት (የሕይወት አክሊል) የሚሰጣቸው ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር ግን ይመለካሉ፣ ፈጣሪ

ይባላሉ ማለት አይደለም። ምንም ቢኮን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እስከ መመለክ የሚደረስበት መንፈሳዊ የደረጃ እድገት የለም።

## ለቅድስት ድንግል ማርያም የተሰጠ የፈጣሪ ስፍራ

ቅድስት ድንግል ማርያም ከሴቶች መካከል ተለይታ የተባረከችና የተመረጠች፥ ሰው ሆኖ ያዳነንን አምላክ በሥጋ የወለደች፥ ከዚህ ታላቅ ዕድል የተነሣ ከፍጥረት ሁሉ ከፍ ያለችና የከበረች እንደሆነች የታመነ እውነት ነው። (ሉቃ. 1፥28፤ 30-35፤ 42-43)

"ማርያም ሆይ! ስለዚህ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛ የጽድቅ መብልንና እውነተኛ የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና" (ቅዳ. ማርያም ቁ.9፤ ዮሐ. 6፥35)

ብዙዎች ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጣትን ይህን ታላቅ ክብር መነሻ በማድረግ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በሆነ መንገድ እርሷን ከፍ ከፍ አድርገው ከልጇ ከክርስቶስና በአጠቃላይም ከእግዚአብሔር ጋር ወደማስተካከል ብሎም የእግዚአብሔርን ስፍራ ለእርሷ ወደመስጠት ደርሰዋል።

ሰዎች እንዲህ ቢያደርጉም አምላክ፥ ጌታና መድኃኒት አንድ ብቻ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ የተረዳችው ቅድስት ማርያም እኔ ሁሉንም ነኝ ሳትል አስቀድማ ጌታዋን አምላኳንና መድኃኒቷን "ጌታ አምላኬ መድኃኒቴ" ብላ ጠርታዋለች። (ሉቃ. 1፥47)

ጌታ በቅዱስ ወንጌል"እውነት እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል። ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" (ዮሐ. 14፥12) ያለውን ቀጥተኛ ቃል በማጣመም ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር ለማስተካከል ከተሳካላቸውም ለማስበለጥ የሚጠቅሱ እንዳሉ ይታወቃል።

ቃሉ የሚናገረው ክርስቲያን ሁሉ በእምነት ስለሚሠራው ተአምራታዊ ሥራ ነው እንጂ ፍጡራን ከፈጣሪ እኩል ስለሚሆኑበት አሊያም ስለሚበልጡበት ሁኔታ አይናገርም።

ማንኛችንም ብንሆን ለቅድስት ማርያም የተሰጣትን ክብር ቅንጣት ታህል መቀነስ እንደማንችል ሁሉ ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው በቀር ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልምና (ዮሐ. 3፥27) ያልተሰጣትን ክብር እኛ በፈቃዳችን ሰጥተን በውሸት ልናከብራት አንችልም።

እርሷን አከብርናት እንጂ መቼ አመለክናት? ይባል ይሆናል እንዲህ ከተደረገ መልካም ነው። አንዳንድ አላዋቂዎች በተሳሳተ ድርሰታቸው እግዚአብሔር ባከበራት ክብር ከመከበር አልፋ እንደትመለክ አድርገዋል። ይህን ምስጢራዊ አሠራር ሁሉም ቢያውቀው "ለካስ ነገሩ እንዲህ ነውን?" ብሎ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ አሳብ ከሰዎች የተሳሳተ አሳብ ለመለየት ይችላልና ጥቂቱን ብቻ እንመልከት፥

ሀ) "ኢፈለጠ ወኢሌለየ አልቦ አይሁዳዊ ወአልቦ አረማዊ ኵሉ ዘአምነ ወጸውዐ ስማ ለማርያም ውእቱ ይድኅን ወይረክብ ሕይወተ።"

ትርጓሜ:- "ፈጽሞ ልዩነት አላደረገም አይሁዳዊ የለም አሕዛብም የለም ያመነና የማርያምን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል የዘላለም ሕይወትንም ያገኛል።" (የኅዳር ኪዳነ ምሕረት ዚቅ)

ከላይ የድንግል ማርያምን ስፍራና ክብር ተመልክተናል ከዚያ አንጻር ይህ ቃል ለእርሷ አልተነገረም። በአስተምህሮ የድጓ ክፍል በገጽ 144 3ኛው ዓምድ ላይ ቅ/ያሬድ ይህን ስለክርስቶስ ዘምሮታል። "ኢፈለጠ ወኢሌለየ አልቦ አይሁዳዊ ወአልቦ አረማዊ ኵሉ ዘአምነ ወጸውዐ ስሞ ውእቱ ይድኅነ ወይረክብ ሕይወተ" በማለት። ሰዎቹ ግን ጾታና ስም ለውጠው "ዘአምነ ወጸውዐ ስማ ለማርያም" ብለው እውነትን ከመስመሩ አወጡት።

ይህ የያሬድ ድርሰት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው። (ሮሜ 10፥11-13፤ 1ቆሮ. 12፥13፤ ገላ. 3፥26-28፤ የሐዋ. ሥራ 2፥21)

እንደ አባባለቸው የእርሷን ስም በመጥራት መዳንና ዘላለማዊ ሕይወት ቢገኝ ኖሮ ሐዋርያት ጽፈውልን ጌታም አስተምሮን ባለፈ ነበር። "እነርሱ ይህን ያልጻፉት በወቅቱ አንገብጋቢው ጉዳይ የኢየሱስ ክርስቶስ ነገር በመሆኑ ነው" የሚል ምክንያት ቢቀርብ እንኳ ተቀባይ አያገኝም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰው ስላይደለ "ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ቶሎ ይጻፍ ያ ግን በኋላ ይደርሳል" በሚል እውነቱን ከእውነት አበላልጦ አላቀዳደመም። ዘላለማዊ ሕይወት የሚገኝበት ቃሉን ሁሉ በበቂ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጿል። (ዮሐ. 20፥31)

መጽሐፍ ቅዱስ በእምነት ጠርተን የምንድንበት ስም "ኢየሱስ" ብቻ እንደሆነና ከእርሱ ውጪ ለመዳን የምንጠራው ስም አለመኖሩን አስረግጦ ይናገራል። "መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (የሐዋ. ሥራ 4፡12)

ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት "ኢየሱስ" ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም መሆኑን በመረዳታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና እርሱን ለማመስገን ለመለመንና ለመጸለይ በመሰላልነት ተጠቅመውበታል። "አቤቱ በተወደደው ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ እናመሰግንሃለን።" (ቅዳ. ሐዋርያት ቁ. 4፤ ሮሜ 7፡25፤ ኤፌ. 5፡20፤ ቆላ.3፡17)

"ኢየሱስ" እግዚአብሔር ለእኛ ኃይሉንና ብርታቱን በረከቱንም የሚገልጥበት ስም ነው። የጠላት ዲያብሎስን ሥራ ለማፈራረስ ከኢየሱስ በቀር በሰማይም ሆነ በምድር የሚጠራ ሌላ ስም ባለመኖሩ ጠላትን በዚህ ስም ገሥጸዋል፥ ተቃውመዋል ሥራውንም ሁሉ አፈራርሰዋል።

"የሚፈታተነንን አጥፋው ከእኛም አርቀው። በእኛ ላይ የተከለውን ሁከቱንም ገሥጽ ወደ ኃጢአት የምትወስደንንም ምክንያት ከእኛ ቁረጥ። ጽኑ በሚሆን ኃይልህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አድነን" (ቅዳ. ጎርጎርዮስ ቁ. 85)

"ያንተን ስም ሰምቶ ሞት ይደንግጥ፤ ቀላያትም ይሰንጠቁ፤ ጠላትም ይረገጥ፤ የጥፋት መንፈስም ይንቀጥቀጥ ከይሲም ይወገድ አለማመንም ይራቅ" (ቅዳ. እግዚእ ቁ. 53፤ 1ዮሐ. 3፡8፤ ማር. 16፡17፤ ሉቃ. 10፡17፤ የሐዋ. ሥራ 16፡18፤ መዝ. 43፡5)

በሌላውም መንፈሳዊ ጉዳይ ቢሆን ከኢየሱስ በቀር የሚጠራ ሌላ ስም አለመኖሩን በተግባር አሳይተዋል። (ያዕ 5፡ 14፤ ማር. 9፡41፤ ቆላ. 3፡17)

"በሚፈተት በዚህ ኅብስት ላይ የምንጠራው ስም ምን ስም ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ማኅየዊ መድኃኒት ከሚሆን ስምህ ብቻ በቀር" (ቅዳ. ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቁ. 118)

በእውነትም ኢየሱስ የሚለው ስም ለሁሉም የሚሆን ለሁሉም የሚበቃ ብቸኛና ፍቱን መድኃኒት ነው። ክብር ለስሙ ይሁን! አሜን !

ለ) "እንዘ እግዝእትነ ማርያም ምስሌነ አልቦ ዘይክለነ ወአልቦ ዘይብለነ ኪያሃ ንሰብክ መድኃኒትነ"

ትርጓሜ:- "እመቤታችን ማርያም ከእኛ ጋር ሳለች የሚችለን የለም የሚናገረንም የለም መድኃኒታችንን እሷን እንሰብካለን" (የየካቲት በአታ ዚቅ)

ሐዋርያው በእግዚአብሔር ላይ ስላለው ትምክሕትና የተሰቀለውን መድኅን ክርስቶስን ስለመስበኩ የተናገረውን በመኮረጅና ለማርያም በመስጠት የተጻፈ ነው። (ሮሜ 8፥31፤ 1ቆሮ. 1፥23)

መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስመካው በእግዚአብሔር ብቻ እንድንመካ ሲያስተምረን ከእግዚአብሔር ውጪ ባለው ነገር ወይም በዕሩቅ ብእሲ ወይም በፍጡራን በአጠቃላይ መመካት ከንቱና ከእርግማን በታች መሆን እንደሆነ ይነግረናል። (መዝ. 59፥11፤ 117፥8፤ 145፥3፤ ኤር. 17፥5፤ 9፥23-24፤ ኢሳ. 31፥1-3፤ 1ቆሮ. 1፥30፤ 3፥20-21)

ሊቁ ኤጲፋንዮስም እንዲህ ብሏል:- "አለኝታችንም በዕሩቅ ብእሲ (በሰው) አይደለም። በእግዚአብሔር ነው እንጂ ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር በሌላ የሚያምን ርጉም ነው የሚል ጽሑፍ አለና። እንደ እርሱ ባለ ሰው የሚያምን ሁሉ እንደ ደረቀ እንጨት ይሆናል" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 57 ክፍል 9 ቁ 9-10)

በእውነትም ሲታይ ከእግዚአብሔር የሚበረታ ማን አለ? ቅድስት ድንግል ማርያም እንኳ ሳትቀር የተመካችው በሌላው ነገራቸው የሚመኩ ትዕቢተኞችን አዋርዶ እንደ እርሷ ሳሉ ትሑታን ክብርን በሚሰጠው ጌታ ነው። ትሕትናዋን ተመልክቶ ያከበራትን ጌታ "ነፍሴ ታከብረዋለች" ስትል ተመካችበት (ሉቃ. 1፥47)

ሌሎች ቅዱሳን ሁሉ የተመኩት በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ቅ/ዳዊት:- "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው። የሚያስፈራኝ ማነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው። የሚያስደነግጠኝ ማነው? ክፉዎች አስጨናቂዎቼ ጠላቶቼም ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ

በቀረቡ ጊዜ እነርሱ ተሰነካከሉና ወደቁ። ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም። ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ" (መዝ. 26፥1-3)

ቅ/ያሬድም በበኩሉ እንደ ዳዊት "ክርስቶስ ምእመና ለሕይወትየ ምንትኑ ያደንግፀኒ እመኒ ጸብአኒ ተአይን ኢይፈርሀኒ ልብየ ወእመኒ ሮዱኒ ጸባኢት አንስ ቦቱ ተወከልኩ"

ትርጓሜ:- "ክርስቶስ የሕይወቴ መታመኛዋ ነው ምን ያስደነግጠኛል? ሰልፍ ቢነሣብኝ ልቤ አይፈራም ሰራዊት ቢከብቡኝ በእርሱ ታመንኩበት" ብሏል። (የፋሲካ ድጓ ገጽ 267 3ኛ ዓምድ (አቡን ))

በእግዘአብሔር ብቻ የሚተማመን ሰው እምነቱ ፍጹም ነው። የተማመነበት አምላኩ እግዚአብሔርም ያድነዋል ያከብረዋልም። (መዝ. 90፥14-16)

እምነተ ጎደሎው ግን የማያድነው የለም እንጂ በብዙ ነገሮች ይታመናል። ሌላው መመኪያ ሁሉ ተሰባሪ ሸምበቆ በመሆኑ ቢደገፉት ይሰበራል፤ ጦሱ ለራሱ ብቻ ስለማይሆን ለተደገፈውም ተርፎ ስንጣሪው ተመልሶ ያቆስላልና (ኢሳ. 36፥6፤ 2ነገ. 18፥21) የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ።

የምንሰብከው መድኃኒት ደግሞ አንድ ብቻ እርሱም በሥጋ ልደት የቅድስት ድንግል ልጅ ክርስቶስ ነው። በመሠረቱ ስብከት ኃጢአተኛውን ሰው በወንጌል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምናመጣበት መንገድ ነው። (2ቆሮ. 5፥19-20)

ኃጢአተኛ ሰው በሥጋው ጤነኛ ሆኖ ቆሞ ቢሄድም ከእግዚአብሔር ተለይቷልና መንፈሳዊ ምዉት ነው። (ኤፌ. 2፥1-2፤ ዮሐ 5፥25) ከኃጢአት ሞት ሊያድን የሚችል መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ብቻ በመሆኑ በእርሱ የሚያምን ኃጢአተኛ ይድናል። (ዮሐ. 3፥16-18፤ 36፤ 1ዮሐ. 5፥12)

ስለዚህ ለኃጢአተኛው ሰው ክርስቶስን "መድኃኒትህ ነው። እርሱ ስለ ኃጢአትህ ሞቷል። አንተን ለማጽደቅም ተነሥቷል። ብታምነበት ትድናለህ ባታምንበት ግን ይፈረድብሃል።" ብለን እንሰብክለታለን። ለመዳን የተዘጋጀ ሁሉ "ኢየሱስ ሞተ ተነሣ" የሚለውን ወንጌል አምኖ

በመቀበል ይድናል። የሚጠፋው ግን ይህንን ማመን እንደሞኝነት ይቆጥረዋልና አይቀበለውም። (ሮሜ 1፥3-4፤ 1ቆሮ. 15፥3-4፤ 1ቆሮ. 1፥21)

"መድኃኒታችንን እሷን እንሰብካለን" በሚለው የሰዎች ፈጠራ ከመተካቱ በፊት መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የቤተ ክርስቲያን አባቶች "መድኃኒት የሆነውን ክርስቶስን እንሰብካለን" ብለው መስክረዋል። (1ቆሮ. 1፥23፤ 2ቆሮ. 4፥5)

ቅ/ያሬድ:- "ነህነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተንሥአ እሙታን . . . ' " "እኛ ግን ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ክርስቶስን እንሰብካለን።" (የፋሲካ ድጓ ገጽ 269 1ኛ ዓምድ)

"ንሰብክ ወልደ እምዘርዐ ዳዊት ዘመጽአ ወተወልደ በሥጋ ሰብእ" ከዳዊት ዘር የመጣውንና በሰው ሥጋ የተወለደውን ወልድን (ክርስቶስን) እንሰብካለን። (የአስተምህሮ ድጓ ገጽ 176 2ኛ ዓምድ)

እንዲሁም በስብከት መዝሙር ላይ "ወልደ መድኅነ ንሰብክ ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ" "ዓለም ሳይፈጠር የነበረውን አዳኝ ልጁን (ክርስቶስን) እንሰብካለን" ይላል (መጽሐፈ ዚቅ ወመዝሙር ገጽ17)

ስብከት ቅሉ በየትኛው ርእስ እንነሣ ስለአዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር ማለት ነው።

በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (አቡነ መልከ ጼዴቅ) በ1980 ዓ.ም የታተመው "የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የስብከት ዘዴ" መጽሐፍ የሚለውን እንመልከት:- "የእግዚአብሔር ቅዱስ ዓላማ ሰው ሁሉ እንዲድን ሰው ሁሉ የመንግሥቱ ወራሽ እንዲሆን የታለመ ነው። ለዚህም ሁሉ መምህር ሁኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመጣ የስብከቱ ጠባይ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ የሚከተል ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል አድርጎ የሚሄድ ይሆናል። ስለሰው ድኅነት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞቷል። እንግዲያውስ የስብከቱ ይዘት የስብከቱም ጠባይ የተሰቀለውን ኢየሱስን የሚመለከት መሆን አለበት። ሰባኪው በፈቀደው ርእስ ሊናገር ይችላል። ሆኖም ዋናው ዓላማ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ለመናገር መሆን አለበት።

ምንም የስብከት ምንጩ ቅዱስ መጽሐፍ ቢሆንም፣ ጥቅሱም ከእርሱው ቢወጣም ሐተታውና አገላለጡ ስለአዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆን አለበት። "ኢየሱስን ማዕከል ያላደረገ የእርሱንም አዳኝነት የማይገልጥ ስብከት ስብከት ሊሆን ሊባልም አይችልም" (ገጽ 64፤ 67)

ሐ) "ኃይለ ጽልመት ተሰደ በማርያም" "የጨለማው ኃይል በማርያም ጠፋ።" (የሚያዝያ ኪዳነ ምሕረት ዚቅ)

ሌላው ለድንግል ማርያም የተሰጠው የክርስቶስ የብርሃንነት ስፍራ ነው። ከነቢያት ጀምሮ ሰለክርስቶስ ብርሃንነት በስፋት ተነግሮአል። (መዝ. 42፥3፤ ኢሳ. 9፥1-2፤ ሉቃ. 2፥32)

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጨለማን ለማስወገድ የመጣ ብርሃን መሆኑን ገልጿል። (ዮሐ. 8፥12፤ 12፥46)

ሐዋርያቱም በነቢያቱ የተነገረውንና ከጌታም የሰሙትን ተቀብለው ለእኛ አስተላልፈውታል። (1ዮሐ. 1፥5፤ ዮሐ. 1፥4-9፤ 1ጢሞ. 6፥16፤ ኤፌ. 5፥14)

የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትም በበኩላቸው ይህንን እውነት አስተጋብተዋል። "ብርሃን ዘበአማን ዘያበርህ ለኩሉ ሰብእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ዓለም በእንተ ፍቅረ ሰብእ መጻእከ ውስተ ዓለም ወኩሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽአትከ"

ትርጓሜ፦ "በዓለም ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ስለሰው ፍቅር ወደ ዓለም መጥተሃልና ፍጥረት ሁሉ በመምጣትህ ደስ አለው" (ውዳሴ ማርያም)

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን "ብርሃን" ስትለው በሥጋ የወለደችውን እናቱን ደግሞ "እመ ብርሃን" (የብርሃን እናት) ብላ ትጠራታለች። ደግሞም "ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች። ፈውስም በክንፎቿ ውስጥ ይሆናል" (ሚል. 4፥2) እንደተባለው ቤተ ክርስቲያናችን ይህን መሠረት አድርጋ "አንቲ ምሥራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ" "አንቺ ምሥራቅ (የፀሐይ መውጫ)ነሽ ልጅሽ ደግሞ የጽድቅ ፀሐይ ነው" ብላ እውነተኛውን ነገር ትመሰክራለች።

እርግጥ ክርስቶስ ብርሃን ሆኖ ወደ ጨለማው ዓለም በመምጣቱ አምነው የተከተሉት ቅዱሳን "የዓለም ብርሃን" ተብለው ተጠርተዋል። (ማቴ. 5፥14-16) ብርሃንነታቸው ግን የእግዚአብሔርን ቃል በመፈጸማቸውና ስሌላውም በመመስከራቸው ምክንያት ነው። (ፊልጵ. 2፥14፥16)

ስለ ክርስቶስ ብርሃንነት ለመመስከር ከጌታ 6 ወራት ቀደም ብሎ ለእስራኤል የተገለጠው መጥምቁ ዮሐንስ በሰጠው አገልግሎት "የሚነድና የሚያበራ መብራት" ተብሎ ቢጠራም ብርሃንነቱ ለክርስቶስ ተከታዮች በተሰጠው ስያሜ አንጻር ነው እንጂ እሱ ራሱ ለሰው ሁሉ የሚያበራው ብርሃን አልነበረም። (ዮሐ. 5፥35፤ 1፥ 6-8)

የእመ ብርሃን ማርያም ብርሃንነትም በዚሁ መሠረት የሚታይ ነው። ከላይ እንዳየነው እሷ ምሥራቅ ልጇ የጽድቅ ፀሐይ ነው። ፀሐይ ካልወጣ በቀር የፀሐይ መውጫ ( ምሥራቅ) በራሱ ብርሃን ሊሆን አይችልም። እንደዚሁም ሁሉ እሷ የክርስቶስን የብርሃንነት ስፍራ ልትተካ አትችልም።

ስለዚህ ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ክርስቶስ ብቻ ነው። እርሱ ብርሃን ሆኖ ከመምጣቱ በፊት በዓለም ሰፍኖ የነበረው የጨለማው ገዢ ሥልጣን ነው። ሥልጣኑን በብርሃንነቱ ገፍፎና ድል ነሥቶ በጨለማ ለሚኖሩት የተደነቀ ብርሃን በመሆን ወደ ራሱ መንግሥት አፍልሷል። እኛም በብርሃኑ ብርሃንን አይተናል። (ቈላ. 1፥13-14፤ 2፥15፤ 1ጴጥ. 2፥9፤ መዝ. 35፥9)

መ) "ይትባረክ እግዚአብሔር ወይትአኰት ስሙ ኪያኪ ሠናይተ ዘፈጠረ ለቤዛ ብዙኃን እስመ መሠረት አንቲ ለሕይወተ ኩሉ ዓለም።"

ትርጓሜ:- "መልካም የሆንሽ አንቺን ለብዙዎች ቤዛ እንድትሆኝ የፈጠረ እግዚአብሔር ይባረክ ስሙም ይመስገን አንቺ ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት መሠረት ነሽና።" (የግንቦት ልደታ ዚቅ)

ይህ ዐዲስ ድርሰት ከእግዚአብሔር ቃልና አሠራር ጋር በእጅጉ ይቃረናል። ስለ ሰው ልጆች ድኅነት ቤዛ ሆኖ የሚሞትና ሊቤዥ የሚችል ፍጡር ከሰውም ከመላእክትም ባለመገኘቱ አምላክ በተዋሕዶ ምስጢር ሰው ሆኖ እንደመጣ እናውቃለን።

"ከዚህ በኋላ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ ቤዛ መድኃኒት የሚሆን ልጁን ሰደደልን። ፈጽሞ ያድን ዘንድ በፊቱ የሕያዋንንና የሙታንን መታሰቢያ ያገባ ዘንድ" (ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ቁ. 43)

"ቤዛ" የሚለው የግእዝ ቃል የሚያመለክተው በሌላ ወገን የተያዘን ወይም የተወሰደን አንድ ነገር ለመመለስ የሚከፈለውን ዋጋ፥ ካሣ ለውጥ፥ ምትክ፥ መድን፥ . . ወዘተ ነው። (የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 265-266)

በዚህም መሠረት እኛን ባሮች አድርጎ ከሚገዛን እጅ ከዲያብሎስ የተቤዠን፥ ስለእኛ ምትክ ሆኖ በመሞት የመቤዠታችንን ውድ ዋጋ የሚሆን ክቡር ደሙን ካሣ የከፈለልንና ከባርነት ወደ ልጅነት የመለሰን ቤዛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። (ማር. 1፥45፤ ዮሐ. 10፥34፤ ኤፌ. 1፥7፤ 1ጢሞ. 2፥ 5-6፤ ቲቶ 2፥14፤ ዕብ. 9፥12፤ 1ጴጥ. 1፥18-19)

ታዲያ አንድ ጊዜ በመሞቱ የዘላለም ቤዛነትን አግኝቶ በገዛ ደሙ ወደ ቅድስት የገባ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ያልጠቀመ ሆኖ ነውን ሌላ ቤዛ መጨመር ያስፈለገው? በእውነት ይህ ቤዛችንን እርሱን መርገጥ፥ የተቀደስንበትን የኪዳኑን ደም እንደርኩስ ነገር መቁጠርና የጸጋውንም መንፈስ ማክፋፋት በመሆኑ ከምንም በላይ የባሰውን ቅጣት ያመጣብናል። (ዕብ. 10፥29)

በሌላ በኩል ደግሞ ሕንፃው የሚገጣጠምበትና የሚያድግበት ጽኑ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በብልሃተኛ የአናጺ አለቃ ተመሥርቷል። ሌላ መሠረት መመሥረት ሳያስፈልግ ምእመናን በዚሁ መሠረት ላይ በጥንቃቄ ታንጸው ሥራቸውንም እያነጹ ሕንፃውንም በማሳደግ ወደ ፍጻሜው መራመድ ይሆናል። (1ቆሮ. 3፥10-11፤ ኤፌ. 3፥20-22፤ 1ጴጥ. 2፥4-6)

ቅድስት ማርያም አምላክን በሥጋ በመውለድ ከሴቶች መካከል የተባረከችና የተመረጠች ቢሆንም በሕንፃው ውስጥ የእርሷ ድርሻ መሠረትነት ሳይሆን የሕንፃው አንድ ክፍል መሆን ነው። የሌሎቹ

ቅዱሳን ድርሻም ቢሆን እንዲሁ ተመሳሳይ ነው። (1ቆሮ.12፥20-27) መቼም አንድ ቤት ለመሥራት ሁለት መሠረት አይጣል!

ሠ) "በዛቲ ድንግል ኪዳነ ምሕረት እንተ ባቲ ተሞዐ ሞት ወተቀጥቀጠ ኃይሉ ለጸላኢ ዘመጠነዝ አርአየ እግዚአብሔር ምሕረቶ በላዕሌነ ፍጹመ ፍቅረ አፍቀረነ"

ትርጓሜ:- "በዚች ድንግል በኪዳነ ምሕረት ሞት የተሸነፈባት ሆነ። የጠላት ኃይልም ተቀጥቅጦ እግዚአብሔር እንደዚህ ያለ ምሕረቱን በእኛ ላይ አሳየ። በፍጹም ፍቅርም አፈቀረን" (የግንቦት ኪዳነ ምሕረት ዚቅ)

ከአዳም ጀምሮ የሰውን ዘር በሙሉ ሲገዛና ከሥልጣኑ በታች ሲያደርግ የኖረው ሞት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሙታን ትንሣኤ ድል በመነሣት እንደሚዋጥ በተስፋ የሚጠበቅ ዐቢይ ጉዳይ ቢሆንም ለክርስቲያኖች ሁሉ ድል መንሣትን በሰጠ በክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ ድል ሆኗል። (ሮሜ. 5፥12-14፤ 1ቆሮ. 15፥51-57፤ ራእ.1፥17-18)

እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ በኩል ይህን በማድረጉ እጅግ የበዛውንና በአእምሮ ከመታሰብ የሚያልፈውን ምሕረቱን በእኛ ላይ ሲያሳይ ለሚወደው አንድ ልጁ እንዳይራራ ያስጨከነውን ድንቅ ፍቅርም ገልጿል። (ኤፌ. 2፥4-5፤ ሮሜ 8፥32፤ 5፥8 ዮሐ.3፥16)

ይህ ሁሉ የሚያውቀው ሐቅ "እውነት ነው? አይደለም "ለሚል ድርድር ቀርቦ ማስተማመኛ መስጠቱ ባያስፈልግም ሐሰተኞች ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትና በአባቶችም:- "እርሱም በመዋቲ ሥጋ ይነሣ ዘንድ በፈቃዱ ሞተ። ከተነሣም በኋላ ዳግመኛ አይሞትም፤ከትንሣኤው በኋላ ግን ጌታ ይህን አልተናገረም። ከሰውም ወገን ማንንም ተነሥ ከመቃብር ውጣ አላለም። ዳግመኛ እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ለሰዎች ሁሉ አንድ ሆነው በሚነሡበት ቀን ሙታን ይነሣሉ አላቸው። ከሙታንም ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ከሞቱት ሁሉ ማንንም በሥጋ እንዳላስነሣ አስተውል።" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 59 ቁ. 49-50 )

"አብ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ከሰጠው ከምእመናን አንዱንስ እንኳን አላጠፋም፤ ፈጽሞ አዳናቸው፤ በኋለኛይቱ ቀን

አስነሣቸው እንጂ እንደምን ያስነሣቸዋል? ከሙታን ተለይቶ እርሱ ብቻ ስለተነሣ ነው እንጂ። . . . ከሰማይ የመጣ የእግዚአብሔርን ቃል በሥጋው ብቻውን ከሙታን ቀድሞ እንደተነሣ እናውቃለን በተነሣ ጊዜ አባቱ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ለርሱ የሰጣቸው ምእመናን በትንሣኤ ይመስሉት ዘንድ እንግዲህ ወዲህም በቀድሞው ሰው አዳም ትእዛዝ በማፍረስ ምክንያት ፈርሰው በስብሰው አይቀሩም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እሺ በጀ ብሎ እስከ ሞት በመድረሱ እነርሱ ፈጽመው ይድናሉ እንጂ " ( ሃይ. አበ ምዕራፍ 7 ክፍል 50 ቁ. 51 እና 52) በማለት በመንፈሳዊ አካል ካሁን ቀደም የተነሣ ክርስቶስ ብቻ መሆኑንና የተቀረው የሰው ዘር በሙሉ በመጨረሻው ቀን እንደሚነሣ የተጻፈውን ማስተባበላቸው ሳያንሳቸው በሞትና በጠላት ኃይል ላይ የተገኘውን የክርስቶስን ድል ለቅድስት እናቱ በመስጠት ሌላ ስሕተት መድገማቸው ሐሰትን ለእውነት መቅበሪያነት በተሰናዳው ጉድጓድ መልሶ ቀብሮ እውነትን ከድል ወደ ድል ማሸጋገር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። (ዮሐ. 3፥13፤ ኤፌ. 4፥8-10፤ ሮሜ. 10፥6-7፤ ራእ. 5፥5)

"ሟች ሥጋን የተዋሐደው ያስነሣው ወደ ሰማይ ያወጣው ሞትን በሥጋ ድል የነሣው ለረጅም ዘመን (አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን) ነግሦና ሠልጥኖ የነበረ ዲያብሎስን ያጠፋው እርሱ ነው። ኃይሉ የሚገለጥበት ኃጢአትን ፍዳን አጥፍቶ ቁራኝነትን ቀጥቅጦ ፊቱ በጨለማ የተሸፈነ ዲያብሎስ በልደት ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ከድንግል ሥጋን ተዋሕዶ ወደ ሲኦል ወርዶ ባየው ጊዜ ፈራ ደነገጠ " (ሃይ. አበ ምዕራፍ 2 ቁ. 6-8)

መንፈስ ቅዱስ ገልጾላቸው የትንሣኤው ጉልበትና ኃይል የተሰማቸው ጥንታውያን አባቶቻችን ሞትና በሞት ላይ ሥልጣን የነበረው ዲያብሎስ የተሸነፉት ሥጋን ለብሶ በመሞት ከቁጥጥራቸው በላይ የሆነ ኃይልና ሥልጣን ባለው ድል አድራጊ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሞትና ዲያብሎስን በወርቃማው ድርሰታቸው አናዝዘዋቸዋል:- "ከሕጌ የተለየ ይህ ማነው? ከኔ ዘንድ የነበሩ አሕዛብን ከወገኖቼ ለይቶ የሚማረካቸው ይህ ማነው? ... ወገኖቼን እንዳላጠፋ ከሹመቴ የሻረኝ ይህ ማነው? ይኸውም የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ሲኦልን ረግጦ በሞቱ ሞትን አጠፋው። "(ሃይ. አበ. ም. 4 ቁ. 14፤ 18-19፤ ም. 5 ቁ. 1)

እውነቱ እንዲህ ተቀምጦ ተመልካች በማጣቱ ምክንያት "በቅድስት ማርያም ሞትና የጠላት ኃይል ተሸነፈ" የሚለው ዐዲስ

ትምህርት ተፈለሰፈ። ይህም የዲያብሎስን ሥራ ያፈረሰውን ኃያሉን ጌታ ደካማ አድርጎ በሞት ላይ የተገለጸውን ታላቅ ኃይሉን መካድ ይሆናል። (1ዮሐ.3፥8፤ ኤፌ. 1፥19-21)

ለማንኛውም በእውነት ላይ መዋሸት ሐሰተኞችን ትዝብት ላይ ቢጥል እንጂ እውነትን ከእውነትነቱ ፈቀቅ አያደርገውም።

ረ) "ማርያምሃ እሁበክሙ ወጸጋሃ አኀድግ ለክሙ ይቤሎሙ ዐርገ እምገጸሙ መንፈስ ቅዱስ አስተጋብኦሙ ጰራቅሊጦስ መጽአ ኀቤሆሙ"

ትርጓሜ:- "ማርያምን እሰጣችኋለሁ ጸጋዋንም እተውላችኋለሁ ብሏቸው በፊታቸው ዐረገ። የእውነት መንፈስ ሰበሰባቸው ጰራቅሊጦስም ወደ እነርሱ መጣ " (የጰራቅሊጦስ ዚቅ)

በዚህ ድርሰት ለቅድስት ማርያም የመንፈስ ቅዱስና የጸጋው ስፍራ ተሰጥቷታል። ይህም ጌታችን በቅዱስ ወንጌል "ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ሰላሜን እተውላችኋለሁ" ብሎ ስለመንፈስ ቅዱስ መምጣት፥ ለሐዋርያቱና ለአማኞች ሁሉ ስለመስጠቱ የተነገረውን በእርሷ በመተካት የተከናወነ ነው። (ዮሐ. 14፥27)

እርሷ መቼ ከእነርሱ ተለየችና ነው እርሷን እሰጣችኋለሁ ያላቸው? የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በተስፋ እየጠበቁ ከሚተጉት መካከል አንዷ እርሷ እንደነበረች ተገልጿልና። (የሐዋ. ሥራ 1፥14)

የሚገርመው ደግሞ እዚህ ድርሰት ላይ "እሰጣችኋለሁ አለ" የተባለው ማርያምን ሆኖ ሳለ የመጣው ግን መንፈስ ቅዱስ መሆኑ ሩቅ ሳንሄድ የድርሰቱን ውሸትነት እንረዳለን።

በዘመናችን ሌላ አስገራሚ ነገር ደግሞ ይሰማ ጀምሯል። ይኸውም "ሐዋርያት ድንግል ማርያምን ይዘው ስለጸለዩ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን ድንግል ማርያም በሌለችበት ጉባኤ መንፈስ ቅዱስ አይወርድም" የሚል ነው። የሚደንቀው ግን መንፈስ ቅዱስ በዚህ መንገድ እንደሚሰጥ የሚሰብኩት ክፍሎች ስለመንፈስ ቅዱስ ያላቸው አመለካከትም ሆነ ስሜት በእጅጉ የሞተ መሆኑ ነው። ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ስፍራ

ሥጋና ደም (ሰው) ስለያዘው ቤተ ክርስቲያናችን ከመንፈሳዊ ሕይወት ርቃና በሥጋዊ ነገሮች ተጠላልፋ ትታያለች።

ይሁንና የደራሲዎቹ አባባል ለእነርሱ ቀኝ ቢሆንም ለሰሚው ግን ግራ ነው። የነገሩትን ሁሉ በይውህና አሜን! ብሎ የሚቀበለው ምእመን ይህ ሲሰበክለት ዐዲስ ምስጢር እንደተገለጠለት ቆጥሮ ልቡ ቢነሆልልም ሁሉን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ለሚቀበል አስተዋይ ግን ፈጽሞ አይዋጥም።

በሕይወተ ሥጋ ያሉት ቅዱሳን ምእመናን ሞተው ወደ አገለገሉት ጌታ ከሄዱት ቅዱሳን ምእመናን ጋር ቅድስት ድንግል ማርያምን ጨምሮ በክርስቶስ በኩል መንፈሳዊ ኅብረት ያላቸውና በክርስቶስ ፍቅር የተያያዙ ናቸው። ይህ በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ እውነት ነው። (ዕብ. 12፥22-24)

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው እርሷ በምትገኝበት ጉባኤ ብቻ መሆኑን የሚጠቁም ፍንጭ ግን ፈጽሞ የለም። ለመንፈስ ቅዱስ መውረድ ምክንያቱ የጌታ የተስፋ ቃል እንጂ የእርሷም ሆነ የሌሎቹ በዚያ መገኘት አልነበረም። የሐዋ. ሥራ 1፥14 የሚናገረው እርሷ ከሐዋርያትና ከተቀሩት ሴቶች ጋር አብራ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ተስፋ በማድረግ ለጸሎት መትጋቷን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ይወርድ ዘንድ በጸሎተኞቹ መካከል መገኘቷን አይደለም።

እርግጥ እርሷ በአካል ባልተገኘችበትና የክርስቶስ አዳኝነት ብቻ በተመሰከረበት ጉባኤ መካከል መንፈስ ቅዱስ መውረዱን የሐዋርያት ሥራ ሲያስነብበን ይህ መሠረት የለሽ ትምህርት ውድቅ ይሆናል። (የሐዋ. ሥራ 10፥44፤ 19፥6)

## ለሌሎች ቅዱሳን የተሰጠ የአምላክ ስፍራ

በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች ግንዛቤ አንድ ሰው ቅዱስ የሚሆነው በገዛ ራሱ ጥረትና ተጋድሎ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል። በተጋድሎና በብዙ መከራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደምንገባ ቢታወቅም ይህ በእምነት ብቻ መጽደቅን ተከትሎ የሚመጣና ሁሉን የሚያስችለን ጸጋ እግዚአብሔር በውስጣችን በመሆኑ ብቻ የምናከናውነው ይሆናል። ከዚህ ውጪ የሆነው የሰው ተጋድሎና አለኝ የሚለው መልካም ሥራው ሰውን ለቅድስና አያበቃውም (የሐዋ. ሥራ 14፥21-22፤ ኢዮ.14፥4 15፥14-16፤ 25፥4 ሮሜ 5፥11፤ 13 ቲቶ 2፥11-13)

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው ቅዱሳን፥ ሰማዕታት በቅድሚያ የክርስቶስን የአዳኝነት ሥራ አምነው በእምነት የጸደቁ፥ በግንዱ ላይ እንደተጣበቀ ቅርንጫፍ በክርስቶስና በጸጋው ላይ ብቻ በመደገፍ የቅድስናን ኑሮ የኖሩ፥ መልካም ፍሬን ያፈሩ የእግዚአብሔር ምርጦች (ኅሩያን እግዚአብሔር) ናቸው። (ሮሜ. 4፥3፤ ገላ.2፥16፤ ዮሐ.15፥4-5፤ 1፥17፤ ሮሜ 8፥29-30)

በተለይም ደግሞ ሰማዕታት በቃል ብቻ ሳይሆን የተለየዩ ጸዋትወ መከራዎችን እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት ድረስ በመቀበል ወንጌልን የመሰከሩ የክርስቶስ ታማኝ ምስክሮች ናቸው። (2ቆሮ.11፥23-28፤ 6፥3-10፤ የሐዋ.ሥራ 1፥8፤ 2ጢሞ. 2፥8 -10)

ከቅዱሳን መካከል ሩጫቸውን በድል ፈጽመው የአገልግሎት ዋጋቸውን ወደፊት ጻድቅ ፈራጅ ከሆነው ጌታ ለመቀበል ወደዚያው የሄዱ እንዳሉ ሁሉ ዛሬም በሕይወተ ሥጋ ያሉት ደግሞ ወደ ፍጻሜው ለመድረስ እየተጋደሉ ይገኛሉ። (2ጢሞ. 4፥6-8፤ ራእ. 2 ፥10)

ነገር ግን ቅዱሳን የአምላክ አገልጋዮች እንጂ አምላክ አለመሆናቸው በግልጽ እየታወቀ የአምላክን ክብርና ስፍራ ሰዎች በድርሰታቸው ለጋስነት ችረዋቸዋል።

ሀ) "አንዊከ ሰማዕታት ያሌዕሉከ በክብር፥ ማኅበረ መላእክት ይሴምትከ በፍቅር፥ ወልደ ኢየሉጣ ቅድስት ቃልከ እስመ ለዓለም ምሕረቱ።"

ትርጓሜ:- "ወንድሞችህ ሰማዕታት በክብር ከፍ ከፍ ያደርጉሃል። የመላእክት አንድነትም በፍቅር ሰላምታ ያቀርቡልሃል። የቅድስት ኢየሉጣ ልጅ (ቂርቆስ ሆይ!) ቃልህ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና" (የኅዳር ቂርቆስ ዚቅ)

የመላእክትና የቅዱሳን ተግባር በሰማያት እግዚአብሔርንና የታረደውን በግ በምስጋናና በክብር ከፍ ከፍ ማድረግ ነው። (መዝ. 144÷1፤ ራእ. 5÷13፤ 7÷12፤ 15÷2-4) ከዚህ ውጪ ፍጡራንን እንደ እግዚአብሔር ቆጥረው ለእግዚአብሔር በሚገባ ምስጋና ያመሰገኑበት ጊዜ ፈጽሞ አይገኝም። በዚህ ድርሰት ውስጥ እንደሚታየው መላእክትና ሰማዕታት ቂርቆስን በክብር ከፍ ከፍ ያደረጉበት ምክንያት የቂርቆስ ቃል ልክ እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ምሕረት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ነው። ለመሆኑ እንደ እግዚአብሔር "ቃልህ ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ተብሎ የተነገረለት ማነው? አንዳንዶች "እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጽማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ።" ተብሎ የተጻፈውን እንዲህ ላለው ስሕተታቸው መሸፈኛ አድርገው ይጠቅሱ ይሆናል። (ዮሐ. 17÷ 22) ጌታ ላመኑበት ቅዱሳን ሁሉ የሰጠው ይህ ክብሩ በእግዚአብሔር ልጅነት የተገኘውን መብትና ሥልጣን ያሳያል እንጂ ሰዎች ለቂርቆስ እንዳደረጉት የእግዚአብሔርን ክብር ለራስ መውሰድን ወይም በእግዚአብሔር ቦታ መሆንን አያመለክትም። ስለዚህ እያስተዋልን የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ልናስረክብ ይገባናል።

ለ) "ክሥት ሊተ እግዚኦ ከመ አእምር ሕጋ ለሐና ኵሉ ዘጌሠ ወመጽአ ኀቤሃ ኢይጸመሙ እስመ መፍቀሪተ ነግድ።"

ትርጓሜ:- "አቤቱ የሐናን ሕግ አውቅ ዘንድ ግለጥልኝ። ወደ እርሷ ገሥግሦ የመጣ ሁሉ አይደክምም እርሷ እንግዳ ወዳጅ (ተቀባይ) ናትና።" (የኅዳር ሐና ዚቅ)

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ሐና የድንግል ማርያም እናት መሆኗ ይታወቃል። ሐና የደነገገችውና ክርስቲያኖች የሚመሩበት የሐና ሕግ ተብሎ የተሰየመ ሕግ ስለመኖሩ ግን የሚታወቅ ነገር የለም። ደግሞም ሊኖር አይችልም። ክርስቲያኖች ሁሉ የሚመሩት በእግዚአብሔር ሕግ ብቻ ነው። ሰው ላወጣው

ሕግና ሥርዓት እንኳ ተገዢ የሚሆኑት የእግዚአብሔርን ሕግ በመፈጸም ነው። (ሮሜ 13÷1-2፤ 1ጴጥ. 2÷13)

በሌላም በኩል በኃጢአት የደከመውን ሰው ከድካሙ ለማሳረፍ ከፍጡራን ወገን በመታጣቱ ብቸኛው ማረፊያ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኗል። ስለሆነም የኃጢአት ሸክም ያደከማቸውን ሁሉ ". . . ወደኔ ኑ! እኔም አሳርፋችኋለሁ" ብሎ ወደሱ ለመጥራት ተገብቶታል። (ማቴ.11÷28) ታዲያ እሱን ትቶ ሌላ ማረፊያ መፈለጉ ሌላ ድካም ማትረፍ እንጂ ዕረፍት አያስገኝም።

በድርሰቱ ውስጥ የስም ለውጥ ያደረጉት ክፍሎች ቢያንስ ይህን ለሐና ብንሰጥ ከሐና ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላልን? ብለው ማገናዘብ ነበረባቸው። ምክንያቱም ሐና ምን ሕግ ልትደነግግ ትችላለች?

ትክክለኛው ድርሰት ለሐና ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን የተነገረ መሆኑን ከያሬድ ድርሰት ማመሳከር ይቻላል። (ጾመ ድጓ ዘምኩራብ የሰኞ ዕዝል ገጽ 58 2ኛ ዓምድ ላይ ያለውን አቡን ተመልከት)

ሐ) "ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ ደነነ ሥዕል ከመ አሆ! ዘይብል ሰምየሙ ጸሎቶሙ ወቀተለ ጸሮሙ"

ትርጓሜ:- "ባስልዮስና ጎርጎርዮስ ወደ ቅ/መርቆሬዎስ ሥዕል ጸለዩ፤ ሥዕሉም እሺ እንደሚል ሰው ጎነበስ አለ፤ ጸሎታቸውንም ሰምቶ ጠላታቸውን ገደለ።"

"ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅ/መርቆሬዎስ ሰአሉ ወይቤሉ "ቀተልኮኑ ለዑልያኖስ" ደነነ ሥዕል ከመ አሆ! ዘይብል ወተፈሥሑ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ"

ትርጓሜ:-"ባስልዮስና ጎርጎርዮስ ወደ ቅ/መርቆሬዎስ ሥዕል ጸለዩ፤ እንዲህ ብለውም ጠየቁ ዑልያኖስን ገደልኸውን? ሥዕሉም እሺ እንደሚል ሰው ጎንበስ አለ፤ጎርጎርዮስና ባስልዮስም ደስ አላቸው።" (የኅዳር መርቆሬዎስ ዚቅና ዐራራይ)

ዑልያኖስ የሚባል አንድ ዐላዊ ንጉሥ (360-363 ዓ.ም) በጠላትነት ተነሥቶ በመርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ የተባሉ ቅዱሳንን ሊያጠፋና ቤተ ክርስቲያኑንም

(ሕንፃውን) ሊያፈራርስ እንደመጣ ሁለቱ ቅዱሳን ባወቁ ጊዜ በመርቆሬዎስ ሥዕል ፊት እንደጸለዩና ሥዕሉ ከስፍራው ተነሥቶ በመሄድ ዑልያኖስን በጦር ወግቶ በመግደል ተመልሶ በቦታው እንደተቀመጠ በቤተ ክርስቲያን የሚተረክ ታሪክ አለ። ከላይ በመጽሐፈ ዚቅ የተጠቀሱት ሁለቱም ድርሰቶች ይህንኑ ያንጸባርቃሉ።

ትረካውን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ብንመረምረው የማይመስልና ከእግዚአብሔር አሠራር ውጪ በመሆኑ "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" በሚለው ጥቅስ እንኳ ሊሸፈን የማይችል ትረካ ነው።

ሥዕል መሣል የተጀመረው በካታኮምብ (ግበበ ምድር) ውስጥ እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። በዘመኑ የሮም ቄሳሮች በክርስቲያኖች ላይ ይፈጽሙት ከነበረው አሰቃቂ መከራ አምልጠው በካታኮምብ ዋሻ ውስጥ በብዙ መከራ ሕይወታቸውን ይገፉ የነበሩት ክርስቲያኖች ባለው ሁኔታ እግዚአብሔርን ማምለክ አላቋረጡም ነበር። በዚሁ ውስጥ ብዙ አማኞች እየመጡ የማኅበራቸው አባል መሆን ጀመሩ። ከመከራው ጽናትና በክርስትና ላይ ከነበረው ስደት የተነሣ ትምህርተ ክርስትናን አስፋፍቶ ለመስጠት በቂ መጻሕፍት ስላልነበሩ ፥ እንደልብ ከዋሻው ወጥቶ ለመፈለግና ለማዘጋጀትም ቢሆን ነጻነቱ ስላልነበረ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ታሪኮችንና ምሳሌዎችን እንዲገልጹ አድርገው በዋሻው ግድግዳ ላይ በከሰልና በዐመድ ሥዕል በመሣል ማስተማር ጀመሩ። ሥዕሎቹም የሚሣሉት ትክክለኛ ናቸው ተብለው ሳይሆን በምሳሌነት ነበር።

በወቅቱ ከነበረው ችግርና የመጻሕፍት እጥረት አኳያ የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪኮች ማንበብ ለማይችሉ ሰዎችም ለማስረዳት ሥዕል ጠቀሜታ ነበረው።

በዚህ ዓላማ የተጀመረው ሥዕል እየቆየ ሲመጣና ብዙ ዘመናትን ሲያሳልፍ ዓላማውን ስቶ ማስተማሪያነቱ ቀረና በአፍቃሪዎቹ ዘንድ እንደ ጣዖት ወደ መመለክ ተሸጋገረ። ሥዕላት እንደ አማልክት ስለተቆጠሩም ጸሎትና ተማጽኖ ይቀርብላቸው ጀመር። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት በሚያመልኩትና በሥዕል አምላኪዎች መካከል ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጥሮ ለብዙ ዓመታት ቆየ። እስከ 787 ዓ/ም ድረስ የተነሡ የሮም ነገሥታትና ጳጳሳት

በክልበላም ሆነ በሀዋድ አምልኮተ ሥዕላትን ለማስቀረት ጥረት አድርገዋል።

ቈስጠንጢኖስ 5ኛ በ787 ዓ/ም ጠቡ በተነሣበት አካባቢ የነበሩ የአብያተ ክርስትያናት መሪዎችን ጠርቶ "የኒቅያ 2ኛ ጉባኤ" ተብሎ የሚጠራውን ሲኖዶስ ሰብስቦ ሥዕላት በቤተ ክርስቲያን እንዲሰቀሉ÷ ሰላምታ÷ ክብር÷ ስግደት እንዲሰጣቸው ÷ መልካም መዓዛ ያላቸው ሽቱዎች እንዲረበረብላቸው ÷ ዕጣን እንዲታጠንላቸው÷ መብራት እንዲበራላቸው÷ ቀኖና እንዲደነገግ አደረገ። አምልኮተ ሥዕልን ማረም ሲገባ ጭራሽ ሕግ ስለተደነገገለት ይኸው እስካሁን ድረስ እየተሠራበት ይገኛል። በእግዚአብሐር ቃል ግን የተደገፈ ነገር አይደለም። (ዘጸ. 20፡4፡ 34፡17፤ ዘዳ.4፡15-19፤ 27÷15፤ ኢሳ.40፡18-19 )

እንደ ሥዕል ሁሉ በሌላ መልካም ዓላማ ተጀምረው ወደ አልተፈለገ ሁኔቷና ወደ ስሕተት አሠራር የተሸጋገሩ ሲወርዱና ሲዋረዱ መጥተው ዛሬ ትክክለኛ ነገር መስለው የተቀመጡ አያሌ ከንቱ ነገሮች አሉ። (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 111፤ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁ. 12)

እንግዲህ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ በሥዕል አምላኪዎች መሥመር ውስጥ የገቡ በመሆናቸው በችግራቸው ሰዓት የጸለዩት ከላይ እንደተመለከትነው ወደ መርቆሬዎስ ሥዕል ነው። ጸሎታቸውንም ተቀብሎ ጠላታቸውን በመግደል የጸሎት መልስ ሰጣቸው የተባለው የመርቆሬዎስ ሥዕል ነው። ይህች የአምልኮተ ሥዕል አስፋፊዎች ተረት ናት እንጂ ሌላ ምንም አትባልም። ዑልያኖስ የነገሠው ከ360-363 ሲሆን ÷ የሥዕል አምልኮ የተደነገገው ከዚያ በኋላ 400 ዓመት ቈይቶ በ787 ዓ.ም መሆኑን ያስታውሷል።

የእግዚአብሔር ሰዎች ለሚደርስባቸው ማንኛውም ነገር የሚጸልዩት ወደ እግዚአብሔር ሲሆን ብዙ ጊዜ በቅዱሳን መላእክቱ አማካኝነት የሚፈሩትን ሰዎች ከማንኛውም ክፉ ነገር ይታደጋል። (መዝ.33÷7፤ዕብ.1÷14፤ዳን.6÷22፤የሐዋ. ሥራ 12÷11)

የሞቱ ቅዱሳን ሰዎች እንደመላእክት ተልከው በሕይወት ያሉ ቅዱሳንን ከችግራቸው አድነዋል ወይም ያድናሉ የሚል ጽሑፍ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም። እንደዚህ ባለው ተረታ ተረት ውስጥ ግን ሞልቷል።

ባይሆን እንኳ በሕይወተ ሥጋ ያሉ ቅዱሳንን ተጠቅሞ በችግር ውስጥ ያሉ ቅዱሳንን ሊታደጋቸው ይችላል። (ኤር.38÷7-13)

እንግዲህ በዚህ ድርሰት ውስጥ የመርቆሬዎስ ሥዕል በጥቅሉ ጸሎት ሰምቶ መልስ ሰጠ በመባሉ የእግዚአብሔርን ስፍራ÷ የቅዱሳንን ጠላት አጥፍቶ ቅዱሳኑን አዳነ በመባሉ የመላእክትን የሥራ ድርሻ ወስዷል።

መ) "ተወልደ መድኅን ክብረ ቅዱሳን አብ ወእም ዘይከውን ለኩሉ ዓለም፤ በእንተ ልደቱ ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕጣነ ያበውኡ በእንተ ክህነቱ፤ ወርቀ ያመጽኡ በእንተ መንግሥቱ፤ እስመ ንጉሥ ዐቢይ፤ ውእቱ ወአልቦ ማኅለቅት ለስላሙ።"

ትርጓሜ: -"ለዓለም ሁሉ አባትና እናት የሚሆን የቅዱሳን ክብር የሆነ መድኅን ተወለደ። ስለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ልደት ስለክህነቱ ዕጣንን ያቀርባሉ። ወርቅን ስለመንግሥቱ ያመጣሉ። እርሱ ታላቅ ንጉሥ ነውና። ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም።" (ታኅሣሥ 29 ዚቅ)

ቅዱስ ያሬድ ይህን የዘመረው የክርስቶስን ልደት በማስመልከት እንደሆነ በአስተምህሮ ድጓ ላይ በገጽ 195 3ኛው ዓምድ ላይ ያለውን "ሰላም" በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል። ድርሰቱ ውስጥ የተገለጹት ቃላትና ሁኔታዎችም ጭምር ለክርስቶስ ብቻ የሚስማሙና ስለእርሱም የተነገሩ ናቸው።

የክርስቶስን ስም በገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም መተካት ለስም ለዋጮች ቀላል ነገር ቢሆንም ታላቅ የሆነ የምስጢር ተፋልሶ አስከትሏል። ለዓለም ሁሉ አባትና እናት የሆነ÷ የቅዱሳን ክብራቸው÷ ዓለምን ሁሉ ለማዳን ሰው ሆኖ የተወለደው መድኅን÷ ሲወለድም ከሰብአ ሰገል የወርቅና ዕጣን ስጦታ የተበረከተለት÷ ለመንግሥቱና ለሰላሙ መጨረሻ እንደሌለው የተነገረለት ክርስቶስ ብቻ እንጂ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። (ሚል. 2÷10፤ ሉቃ. 2÷11፤ ማቴ. 2÷11፤ ሉቃ. 1÷33፤ ኢሳ.9÷7)

ስለዚህ ብሂሉም "የሰው ወርቅ አያደምቅ" ነውና በክርስቶስ ምስጋና ክርስቶስ ብቻ ይመስገን።

ሠ) "ሰላም ለኪ አ! ደብረ ሊባኖስ ዘአስተርአየ ላዕሌኪ ተክለ ሃይማኖት፤ ህየ ንሰግድ ኩልነ ኀበ ቆመ እግረ ተክለ ሃይማኖት"

ትርጓሜ:- "ተክለ ሃይማኖት ባንቺ ላይ የተገለጠብሽ ደብረ ሊባኖስ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል። ሁላችንም የተክለ ሃይማኖት እግር በቆመበት በዚያ እንሰግዳለን። (የጥር ተ/ሃይማኖት ዚቅ)

በዚህ ድርሰት ደግሞ ተ/ሃይማኖትን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተካከል የታሰበ ይመስላል። ዳዊት "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን። (መዝ. 131÷17) በማለት ስለእግዚአብሔር የዘመረውን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ግድ የሌላቸው ክፍሎች የስምና የቃላት ለውጥ በማድረግ ለተ/ሃይማኖት ሰጡ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ኢየሩሳሌም ብቻ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሆና ብትቆጠር÷ ሰግደትና ሌላውም የአምልኮ ሥርዓት በዚያው እንዲደረግ ቢታዘዝ÷ በዐዲስ ኪዳን ግን ጌታ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ባደረገው ውይይት ላይ እንደገለጸው መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በተወሰነ ቦታ መመለኩ ቀርቶ በሁሉም ስፍራ በእውነትና በመንፈስ የሚሰገድለትና የሚመለክ ሆኗል። (ዮሐ. 4፥21-24)

ይህ በታወጀበት በዐዲስ ኪዳን ዘመን ደብረ ሊባኖስን እንደ ኢየሩሳሌም መቁጠር እግዚአብሔር በስፍራ ሳይወሰን በመንፈስ በሁሉ ስፍራ ለመመለክ ካቀደው ዕቅድ ጋር አይጣጣምም።

ረ) "ይቤ ጊዮርጊስ ኀበ መኑ እኔጽር? ዘእንበለ ኀበ የዋህ ወትሑት ዘየዓቅብ ትእዛዝየ ወያከብር በዓልየ ያዕርፍ ሰላምየ ላዕሌሁ።"

ትርጓሜ:- "ጊዮርጊስ አለ ወደማን እመለከታለሁ? ሰላሜ በእርሱ ላይ ያርፍ ዘንድ በዓላቴን የሚያከብር ትእዛዜን የሚጠብቅ ትሑትና የዋህ ወደሆነው ካልሆነ በስተቀር።" (የየካቲትና የሚያዝያ ጊዮርጊስ ዚቅ)

እንዲህ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣን ላይ የሚዘባበቱት ዘባቾች አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን የሚቀበሉ አይመስልም። በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ጊዮርጊስ ለመበለቲቱ "እኔ አምላክ አይደለሁም የአምላክ ባሪያ እንጂ" ማለቱ ተጠቅሶ ነበር። እዚህ ላይ ግን ሰዎች

በግድ አምላክ ሁን እያሉት ነው። ለመሆኑ ጊዮርጊስ እንደ አምላክ ሆኖ "ወደማን እመለከታለሁ" ብሎ የተናገረው በየትኛው መጽሐፍ ላይ ነው? በእውነት ይህን የተናገረ ጌታ እግዚአብሔር ነው። (ኢሳ.66፥20)

የሰላም አለቃ ክርስቶስ የሰጠን ሰላም ዓለም ከሚሰጠው የተለየና ከእኛ የማይወሰድ እንደሚሆን ተጽፏል። (ዮሐ.14፥27) የጊዮርጊስ የሰላም ምንጭም ክርስቶስ ነው። ነገር ግን ደራሲዎቹ በጊዮርጊስ ስም ሰላም ሊሰጡን የከጀሉት የክርስቶስ ሰላም ስለደፈረስ ነውን? ወይስ ሌላ ምክንያት አላቸው?

በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሕዝበ እስራኤል በዓላትንና ሕግን የሠራ፥ እንዲጠብቁትና እንዲያከብሯቸውም ያዘዘ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሌላ ማንም የለም። (ዘሌዋ. 23፥1-21፤ ዘጸ. 20፥1-17፤ ዘዳ. 5-1-21) ታዲያ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ አክብሩ ያለው በዓሉና ጠብቁ ያለው ትእዛዙ የትኛው ይሆን?

በብሉይ ኪዳን ይከበሩ የነበሩት በዓላት በዐዲስ ኪዳን ይከበሩ የሚል ትእዛዝ የላቸውም። ስለዚህ ክርስቲያኖችን በአይሁድ ሥርዓት የሚኖር ሰው ተነሥቶ "ለምን በዓላትን አታከብሩም?" ቢል ተቀባይ እንደማይኖረው ተጽፎአል። (ቈላ. 2፥16)

የዐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች በዓል ዘወትር በየዕለቱ ክርስቶስን ማሰብና በፍቅሩ መኖር ነው። ይህንን የተረዳው ደራሲ በብሉይ ኪዳን ሰዎችና በእኛ መካከል ያለውን የበዓል ቀንና ያከባበር ሁኔታውን እንዲህ በማለት ገልጿል:- "በመንፈቀ ሳብዕ ወርኅ በዓለ መጸለት ይገብሩ ተድላ ንብረቶሙ በገዳም እስራኤል እንዘ ይዜክሩ። ንሕነሰ ክርስቶስ ንዜክር ለለአሚሩ"

ትርጓሜ:- "እስራኤላውያን በሰባተኛው ወር አጋማሽ ላይ በምድረ በዳ በደስታ መኖራቸውን እያሰቡ የቂጣ በዓልን ያደርጋሉ። እኛ ግን ክርስቶስን በየዕለቱ እናስባለን። "(መልአክ ቍርባን)

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ጌታ ታላላቅ ሥራዎችን የሠራባቸው ዕለታት ለምሳሌ:- የተወለደበት፥ የተጠመቀበት፥ የተሰቀለበት፥ የተነሣበት... ወዘተ እንዲከበሩ የበዓላት ሥርዓት ተሠርቷል።

ከዚህ ሌላ የቅዱሳን መላእክትና የቅዱሳን ሰዎች በዓላት እንዴት ማክበር እንደተጀመረ እኛን ከደሙ ንጹሕ ያስደረገ በሚመስል ሁኔታ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጽሐፋቸው ያሰፈሩት አለ።

"ሊቃውንቱና መምህራኑ (የሌሎቹ) የሕዝቡን የረጅም ዘመን ፍቅረ ጣዖት ለማስተው ስላቃታቸው በጣዖታቱ ተሠይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳን ስም እየለወጡ ያከብሩታል። ለምሳሌ በጣዖታዊነት በነበሩበት ጊዜ "ፓሲዶን" የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነበር። በክርስትና ዘመናቸው ግን ሊቃውንቱ "ኒኮላዎስ" የሚባለውን ቅዱስ "የባሕር ጠባቂ" ብለው በየዓመቱ ያከብሩታል። የመርከበኞች በዓል ነው። "አሬስ" ወይም "ማርስ" የጦር አምላክ ተብሎ ሲመለክ የኖረ ጣዖት ነው። በእርሱ ምትክ ዛሬ ቅ/ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በያመቱ ያከብራሉ።

በአጠቃላይ አረማውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት (ፍጥረት) አምላክ መድበውለት ስለነበር ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሠይመዋል።" (ገጽ 124)

ከአረማዊነት የተመለሱትን የአምልኮ ጣዖት ልማዳቸውን ለማስቀረት ባለመቻሉ በ "አልሸሹም ዘወር አሉ" መንገድ የጣዖታቱ በዓላት በቅዱሳን ሰዎችና መላእክት እንዲተካ በቤተ ክርስቲያናቸው ሥርዓት ተሠራ ተባለ። ታዲያ ወደ ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ይህ ልማድ እውነት መስሎ እንዴትና ለምን ሊገባ ቻለ? ወይስ ደግሞ ጣዖት ያመልኩ እንደነበሩት አረማውያን አልተው ያልነው ምን መጥፎ ልማድ ነበረን? ጉዳዩ በብዙ መንገድ ያጠያይቃል። ልማደ ጣዖትን ለማስቀረት ስላልተቻለ አረማውያን ለነበሩት የተሠራው ሥርዓት በኛ ቤተ ክርስቲያን እንደ ትክክለኛ ነገር ተቆጥሮ ሕጋዊነትን ማግኘቱና አሳቡ ተስፋፍቶ የወሩ 30 ቀናት በሙሉ በዓላት ሆነውና ቀናት በ30 በመመወሰናቸው ምክንያት የበዓል ቀን ያጡትን ስሞች አንዱን በአንደኛው ላይ በመደራረብ እንዲከበር መደረጉ ይገርማል።

የሚያሳዝነው ግን መንፈሳዊ ቅኝ ገዥዎቻችን የነበሩት ግብጻውያን ቤተ ክርስቲያናችንን የጉድፋቸው መጣያ ማድረጋቸው ነው።

ሰ) " ኮከብ ብርሃን ጽባሐዊ ፥ ፀሐየ ጽድቅ አርያማዊ፥ ዘበንጽሕ መርዓዊ ውእቱ ተ/ሃይማኖት።"

ትርጓሜ:- "ምሥራቃዊ የብርሃን ኮከብ፥ ሰማያዊ የሆነ የጽድቅ ፀሐይ፣ በንጽሕና ያለ ሙሽራ ተ/ሃይማኖት ነው።" (የየካቲት ተ/ሃይማኖት ዚቅ)

በመጽሐፈ ሰዓታት ላይ በዚህ ድርሰት መመስገን የሚገባው ክርስቶስ ጌታ የተመሰገነበት ሲሆን እዚህ ስፍራ ላይ ደግሞ ስሙ ተፍቆ በቦታው የተ/ሃይማኖት ስም ተጽፏል። የስሙን ለውጥ ተከትሎ ስለ ክርስቶስ የተነገሩት የብቻው የማንነቱ መግለጫዎች ሁሉ የተ/ሃይማኖት ገንዘብ ሆነዋል። ይህ ታላቅ የሆነ ጥፋት ነው። ሆነም ቀረ ምሥራቃዊ የብርሃን ኮከብ ፥ ሰማያዊ የሆነ የጽድቅ ፀሐይና በንጽሕና ያለ ሙሽራ መባል ለምድራዊው ተ/ሃይማኖት ሳይሆን ለሰማያዊው ክርስቶስ ብቻ ይገባል። (ራእ. 22፥16፤ ሚል.4፥6፤ ማቴ.25 ፥6፤ ዮሐ. 3 ፥31 )

ሸ) "ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ ጊዮርጊስ ተወልደ ነዋ!"

ትርጓሜ:- " ጊዮርጊስ እነሆ! ተወልዷልና አሁንም ሰላምን እንከተላት። " (የጥር 2 ዚቅ)

በመወለዱ ሰላምን ያመጣው ክርስቶስ ለመሆኑ ምስክር ባያሻም ጌታ በተወለደበት ሌሊት መላእክቱ ያሰሙት የሰላም መዝሙር ሳይጠቀስ አይታለፍም። (ሉቃ.2 ፥10)

እንደ ሌሎቹ ሁሉ በዚህ ድርሰትም የስም ለውጥ ተካሂዶበታል። የመጀመሪያው"ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ መድኃኒ ተወልደ ነዋ!" የሚል ነው። (የልደት ሰላም ምልጣን)

ቀ) "ንዜኑ ዘመርቆሬዎስ ኂሩተ ትሕትና ወየዋሀተ ዘተዐገሠ በእንተ አፍቅሮተ ሰብእ፤ ዘሰቀሎ ለሰማይ ከመ ቀመር ዲበ ዕፅ ተሰቅለ፤ዘከለሎ ለሰማይ በከዋክብት አክሊለ ዘሦክ ተቀጸለ።"

ትርጓሜ:- " የመርቆሬዎስን ቸርነት ትሕትናና የዋህነት እንናገራለን። ስለሰው ፍቅር መከራን የታገሠ፥ ሰማይን እንደመጋረጃ የሰቀለው

በእንጨት ላይ ተሰቀለ። ሰማይን በከዋክብት የሸፈነ የሾህ አክሊልን ተቀዳጀ። (የሚያዝያ 25 ዚቅ)

ከእግዚአብሔር ሌላ አምላክ ፥ ከክርስቶስ በቀር ሌላ ቤዛ እንዳለ የሚያምን ሰው " ስለሰው ፍቅር ሲል መከራን የታገሠ ፥በእንጨት ላይ የተሰቀለ ፥ የሾህ አክሊል የደፋ ፥ እንዲሁም ሰማይን እንደ መጋረጃ የሰቀለውና በከዋክብት ያስጌጠው እኮ መርቆሬዎስ ነው።" ቢሉት አምኖ ለመቀበል አያንገራግርም፤በምእመናን ዘንድ ግን ይህ ሊታመን ቀርቶ አይታሰብም። ምእመናንም አምላካቸውና አዳኛቸው ማን እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከእርሱም በቀር ሌላ የሚያውቁት የለም። (1ቆሮ. 2፥2) እርሱም ከላይ የተነገሩትን ሁሉ ስለሰው ፍቅር የተቀበለና የፈጠረም ነው። (ዕብ. 12፥2፤ ዮሐ.19፥2፤ 17-18፤ ኢሳ. 40፥22)

በእንዲህ ዓይነቱ ድርሰታቸው የእምነታቸው ዐቋም የተገለጸው ወገኖች አምላካቸውና መድኃኒታቸው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስካሁን እንደተመለከትነው ፍጡራንና የራሳቸው የፈጠራ ውጤትም ጭምር ነው።

ለዚህ ሁሉ ስሕተት የዳረጋቸው ዋናው ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስን ከአዳኝነቱ ስፍራ ላይ ማንሣታቸው ሲሆን የእርሱን ስፍራ ለሌሎች ፍጡራን ሲሰጡ ለእርሱ ብቻ መቅረብ የነበረበትን አምልኮና ክብር፥ የእርሱ ፈጣሪነትና አምላክነት፥ አዳኝነትና የመሳሰሉት ገንዘቦቹ የተገለጸባቸውን ርስቶች ሁሉ ጨምረው ለመስጠት ተገድደዋል።

እስካሁን በጥቂቱ የተመለከትነው ሁሉ አሳዛኝና የእግዚአብሔርን ቅንዓት በውስጣችን የሚያነሣሣ ነው።

በዘመናችን አንዱ ደራሲ የደረሰውን ሌላ እንዲህ መበራረዝና ማበላሸት ቀርቶ ያለደራሲው ፈቃድ በከፊልም ይሁን በሙሉ ቢያሳትም ወንጀለኛ ሆኖ በሕግ ይጠየቃል። ለዚህም ነው በየመጻሕፍቱ የመጀመሪያ ገጽ ላይ "መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው" የሚል ማስጠንቀቂያ የሚጻፈው"

የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ ደራሲ ያሬድና ሌሎቹም አባቶቻችን ስላንቀላፉና ለእውነተኛ ድርሰታቸው ጥብቅና የሚቆም ወገን ስለጠፋ በተለይም ቅ/ የሬድ ለአምላኩ ብቻ ያቀረበውን ምስጋና

የድርሰትን ጣዕምና ድካም ያላዩ አላዋቂዎች ጾታ በመለወጥና ስም በመተካት ፍጡራንን ያለአግባብ አወዳደሱበት፤ አመለኩበት።

ያሬድ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ቢኖር ድርሰቱን ያለፈቃድ ገልብጦ ያበለሻሸበትን ትውልድ በሕግ እንደሚፋረድ አይጠረጠርም። ሆኖም ያሬድ ይህን ማድረግ ባይችል ለክብሩ ቀናተኛ የሆነው አምላክ ዝም አይልም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እስካሁን ያየነውንና ለፍጡራን የተሰጠውን የፈጣሪ ስፍራና ክብር ያላስተዋለ ምእመን ሁሉ "ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ብላ አታምንም!" ብሎ ሊከራከር ይችል ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ይህን ማድረግ እንደሌለባት መረዳቱ ነውና ይህ መልካም ግንዛቤ ነው። ነገር ግን ሁሉም ሰው ባያምንበትም በየበዓላቱ ቀን ማሕሌት ሲቆም ይህ ሁሉ በደባትሩ ክፍል ያላንዳች ቅሬታ ተመላልሶ እየተጸነጸለ በፈጣሪ ምስጋና ፍጡር ይመለካል።

ይህን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ሲሠራበት የቆየውን ስሕተት አስተካክሎ ትክክለኛውን አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባል የሚሉ ብዙ መምህራን ቢኖሩም፥ ሕገ እግዚአብሔርን እንደ ተላለፉ በመቁጠር ስደት እየታወጀባቸው ነው። ነገሩ በአበው ምሳሌ" ሞኝ የተከለውን ብልህ አይነቅለውም" እንደተባለው ያለ ሆኖብናል።

ቢሆንም ግን በእግዚአብሔር ዐይን ይህን ማስተካከል ኢምንት ነውና የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት እግዚአብሔርን ማስከበር፥ ስሕተቶችን ማስተካከል ቤተ ክርስቲያንን ከነቀፌታና ከትችት መከላከል ይጠበቅበታል።

## የቅዱሳን ተግባርና ተጋድሎ ለምን ነበር ?

ለእግዚአብሔር አምላክነት ደንታ ቢስ የሆኑት ክፍሎች ቅዱሳንን ሁሉ ከልባቸው ባነቁት የተሳሳተ ትምህርት በፈጣሪ ስፍራ አስቀምጠው ማምለክ ማስመለክ እንደያዙ ባለፈው ክፍል ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ስተው ያለፉትን እውነት የቅዱሳን ተግባርና ተጋድሎአቸው ለምን እንደ ነበር እናያለን።

ቅዱሳን በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ የዳኑ÷ በእምነት በደሙ የጸደቁ በክርስቶስ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀው ሰላምን ያገኙ የሰማያዊ መንግሥት ዜጎች ናቸው። (ሮሜ. 5÷1፤ 9-10፤ኤፌ.2÷13-19፤ ፊልጵ. 3÷20)

ድቅድቅ ጨለማ ከሆነው ዓለም ወደሚደነቀው ብርሃኑ የጠራቸውን የእርሱን በጎነት መመስከር ÷ በነጻ ያገኙትን ሰላም ለሰላም ፈላጊዋቹ ሁሉ መስጠት የቅዱሳን ተቀዳሚና ዋነኛው ተግባር ሲሆን ይህም በታላቅ ተጋድሎ የታጀበ ነበር። (የሐዋ. ሥራ 1÷8፤ 1ጴጥ. 2÷9፤ ማቴ. 10÷8፤10-13፤ የሐዋ ሥራ 4÷18-20፤5÷40-42)

በእርግጥ የእግዚአብሔር ቅዱሳን (የቀደሙት) ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ቢኖሩና ወደ እነርሱ ብንሄድ ሊሰጡን የሚችሉት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስን። (የሐዋ. ሥራ 3÷6) ወደ ቀደሙት ነቢያት ሄደን ምስክርነታቸውን ብንጠይቅ በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንደሚቀበል ከመመስከር በቀር ሌላ አማራጭ አይሰጡንም። (የሐዋ.ሥራ 10÷43 ፤3÷24) ወደ ጌታ እናት ብንሄድ በእጇ ያለውና ልትሰጠን የምትችለው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፤ ወይም ደግሞ የምትመራን ወደ እርሱ ነው። (ሉቃ. 2÷28፤ ዮሐ. 2፤5) ይህን ውድ ስጦታ ለሁላችን ለማበርከት እርሱን ከሄሮድስ ሰይፍ ታተርፍ ዘንድ ድንግል ስደተኛ ሆናለች። (ማቴ. 2 ÷14-15)

ለሰው ልጆች በክርስቶስ የተደረገውን የማዳን ጥበብ ለማወቅ ወደ ሚመኙት ቅ/መላእክት ብንሄድ ራሳቸውን ወይም ሌላውን ሳይሆን በበረት የተወለደውን መድኅንና ሞትን ድል የነሣውን ጌታ ነው የሚያሳዩን። (ኤፌ. 3÷10፤ 1ጴጥ. 1÷12፤ ሉቃ.2÷10፤ ማቴ. 28÷5-7)

ወደ ቅዱሳን ሰዎችም ብንሄድ ለዘመናት የእግዚአብሔር ምስጢር ሆኖ የቆየውንና አሁን የተገለጸውን፥ በእግዚአብሔር በግነቱ ሰለመዳናችን የተሰቀለውንና የታረደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ያሳዩናል። (ቈላ. 2፥2-3፤ ዮሐ. 12፥21-22፤1፥36 ፤ የሐዋ. ሥራ 14፥15፤2ቆሮ. 4፥5)

እግዚአብሔር አብም ሰው በክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር ወደእርሱ ሊመጣ የማይችል በመሆኑ:- "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት።" ብሎ ወደ ልጁ መራን። (ማቴ. 17፥5) ወደ መንፈስ ቅዱስም ብንሄድ እርሱን አክብሮ ስለእርሱ ነው የሚመሰክረው። (ዮሐ. 16፥14፤ 15፥27፤የሐዋ. ሥራ 5፥32)

መጽሐፍ ቅዱስንም ገልጠን ብናነብ አዳኝነቱን በመመስከር ወደ እርሱ ነው የሚያሳየን። (ዮሐ. 5፥39)

ይህ በጥቅሉ በፈጣሪም በፍጡራንም በቃሉም ምስክርነት የጸና እውነት በመሆኑ ሁሉም እርሱን ሲሰጡን፥ ወደ እርሱ ሲመሩን ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የሁሉንም መልእክት በማጠቃለል"ወደ እኔ ኑ! " አለን። (ማቴ. 11፥28) ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን !

እንግዲህ የቅዱሳን ዋና ተግባራቸው ሰውን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማምጣት ወይም ለሰው ኢየሱስ ክርስቶስን መስጠት ነበር ማለት ነው። የተጋደሉትም ይህንኑ ዐቢይ ተግባር ለማከናወን ነው።"ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ" እንዳለ ሐዋርያው (ቈላ. 2፥2)

ከዚህ ሌላ ቅዱሳን ያከናወኑት ተግባር ወይም የተጋደሉለት ሌላ እውነት የለም። የተቀረው ሁሉ በዚህ ውስጥ ይጠቃለላል። እኛም ይህንኑ አውቀን ለማድረግ በፍለጋቸው እንከተላቸው። (2ጢሞ. 1፥3፤ 2፥1-10)

እውነት ነው፤ እኛም በእምነት ተቀብለን ለሌላው የምንሰጠው ቅዱሳን በእምነት ተቀብለው የሰጡንን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነው። (ማቴ. 10፥40፤ ዮሐ. 1፥12-13፤ ቈላ. 2፥6)

"ያ ቃል ቀድሞ የነበረ ነው። ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው። ያ ቃል ሥጋ ሆነ። በእኛም አደረ። ለአባቱ አንዳንድያ ልጅ ክብር የሚሆን ክብሩን አየን። ያ ቃል ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም የተቀበልነው እኛ 318ቱ ነን" (ቅዳ. ሠለስቱ ምእት ቁ. 143-144)

" ... ኢየሱስ ክርስቶስ ብለን ጌታችንን ስንጠራው የዳንን ወገኖች መድኀንም ያለን ሕዝቦች ነን። ስለዚህ ኢየሱስ→ ክርስቶስ እንደሆነ አምነን እንቀበላለን " (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ከአባ መልከ ጼዴቅ ገጽ 37)

ይህን ሐቅ በማስተባበል የአምልኮ መልክ ይዘው እኛን ከሕይወታችን ከክርስቶስ በመለየት ወደራሳቸው ስሕተት ሊስቡን የሚከጅሉትን ሁሉ ግን በክርስቶስ ሆነን ስለክርስቶስ እንቃወማቸዋለን።

# ምዕራፍ 3
# የስሕተት መግቢያ በር

በቤተ ክርስቲያናችን እውነት ለሐሰትስፍራውን እንዲለቅ የረዱ ብዙ ምክንያቶች መኖራቸው ይታወቃል። ከነዚህም ውስጥ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ለ1500 ዓመታት ያህል " ማርቆስ አባቴ እስክንድርያ እናቴ" በሚለው ፈሊጥ ተይዘን በግብጻውያን ሥር መቆየታችን ነው። ይህም ዘመን ክፉና ደጉን ሳንለይ ሁሉን በአወንታ እንድንቀበል አድርጎናል። ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ያሉት አብዛኛዎቹ ልማዶችና ወጎች ከግብጻውያን የተወረሱ ናቸው። የበዓላትን አከባበር አመጣጥ ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ያየነው እንኳ ለዚህ በቂ ምስክር ነው።

ስሕተቶች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በሌሎችም በተለያዩ ምክንያቶች ገብተዋል። በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የምንሰጠው ለስሕተቶች ማጠናከሪያ የሰጠውንና ሌሎች ተጨማሪ ስሕተቶችን ለማስገባት ሰፊ በር የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ችግር ነው።

በቤተ ክርስቲያን የሚታወቀውና " አንድምታ" የተሰኘው የትርጓሜ ስልት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቃራኒ የሚመስሉ ገጸ ንባቦችን በማስታረቅና በመሳሰለው ሁኔታ አስተዋጽኦ ቢኖረውም እውነትን አፍኖ ስሕተትን በማራመድ ረገድ ብዙ ረድቷል።

አንድምታ በአንድ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተለያዩና ፊተኛው ትርጉም በኋለኛው የሚፈርስበት ብዙ ትርጉሞችን ስለሚሰጥ ሰው አንድ ተጨባጭ የሆነ ቁም ነገር እንዲይዝ አያስችለውም በዮሐ. 1÷49 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለናትናኤል "ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ " ብሎ የተናገረው ግልጽ የሆነ ቃል በባለ አንድምታዎች ዘንድ ሌላ ድብቅ ምስጢር እንዳለው ተቆጥሮ ስድስት አንድምታዊ ትርጓሜዎች መስጠታቸውን በምሳሌነት እንመልከት:-

1. ሄሮድስ ሕፃናትን በገደለ ጊዜ ወላጅ እናቱ በቀፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ሰውራው ነበርና ያን ጊዜ ያዳንኩህ እኔ ነኝ ሲል፤
2. አንድም ሰው ገድሎ ከበለስ ሥር አስቀብሮ ነበርና አውቅብሃለሁ ሲለው፤
3. አንድም የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ ከበለሱ ሥር የማይረባ ሥራ ሲሠራ ነበርና አውቅብሃለሁ ሲለው፤

4. ባለ ጸጋ ነው ከበለስ ሥር ሆኖ ወይፈኑን ሲያስፈትን፥ ፈረስ በቅሎ ሲያስገራ ይውል ነበርና ያን ማወቁን ሲነግረው፤
5. ምሁረ ኦሪት ነውና ከበለስ ሥር ሆኖ ትንቢት ደረሰ ሱባኤ ሞላ እያለ ይውል ነበርና አውቅልሃለሁ ሲለው፤
6. አንድም የበለስ ቅጠሉ ሰፊ ስለሆነ ኃጢአት ሰፍኖብሃል ሲለው።

በዚህ መልክ የሌለውን ድብቅ ምስጢር ለማውጣት ሲባል የእግዚአብሔርን ቃል ማስጨነቅ ትርፉ የፈጠራ ድርሰትና ታሪክ መፈልሰፍ ሲሆን ኪሳራው ደግሞ ከእግዚአብሔር አሳብ ርቆ መሳሳት ነው።

ስድስቱም አንድምታዎች ሁሉ ናትናኤል ክፋውንም ደጉንም ለመሥራት ከበለሱ ዛፍ ጋር የተማማለ አስመስሎታል። ከአንድምታዎቹ መካከል ምሁረ ኦሪትነቱን የሚገልጸው 5ኛው በግልጽ ከተቀመጠው ቃል ጋር ይጣላል። ፊልጶስ ለናትናኤል " ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለእርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል" ብሎ ሲነግረው ናትናኤል በምሁርነቱ በነቢያት " ናዝራዊ" ይባላል የተባለውን ሊያስተውል ሲገባው እንዳልተማረ ተራ ሰው " ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?" ብሎ መጠየቁ ጥሬው ንባብ ከተሰጠው አንድምታ ጋር አለመስማማቱን ያሳያል። (ዮሐ.1፥46-47፤ማቴ. 2፥23)

" ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ " የሚለው ገጸ ንባብ ያለው ግልጽና አንድ መልእክት ሲሆን ይኸውም ፊልጶስ ናትናኤልን ሳይጠራው በፊት ናትናኤል ተቀምጦም ይሁን ቆሞ ብቻ ከበለሱ ዛፍ ሥር ይገኝ ነበርና ይህንን ሁኔታ አስቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያወቀ መሆኑን ያመለክታል።

አንድምታ ተዘጋጅቶ ከቀረበው ውጪ ሌላ የማይጨመርበትና የማይቀነስለት ሆኖ ስለቀረበ ዕለት ዕለት ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ዐዲስ ድንቅ ነገር ለማየት እንዳይቻል ዕንቅፋት ሆኗል። (መዝ.118፥18)

ይህን በማስመልከት ሊቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ (ብፅዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ) እንዲህ ብለዋል፦ "ይህም አንድም ትርጉም አንድ ጊዜ የተወሰነ ስለሆነ ሊሻሻል፥ ሊለወጥ ወይም ሊጨመርበት የማይችል ሆኖ እስካሁን የቆየ ስለሆነ ደቀመዝሙሩ ምንም መርማሪና አስተዋይ ቢሆን በዚሁ ብቻ መወሰን ግድ ይሆንበታል። በአንዳንድ ቦታ

ላይ እንኳን ያሻሻለ እንደሆነ የኤታ እገሌ ትርጓሜውን ዘንግተውታል፤ አማርኛውን ረስተውታል፤ እየተባለ ብዙ ይነገርበታል። እንዲያውም ዋና ደቀመዝሙር የሚባለው መምህሩ ከሚተነፍሱበት የተነፈሰ÷ ከሚያርፉበት ያረፈ÷ በቀጥታ ያለምንም ለውጥ ወይም አስተያየት ያንኑ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ነው። እንደዚህ ያለው ብቻ ለአብነት ሲፈለግ እንደትልቅም ሆኖ ሲቆጠር በመምሩም እግር ሲተካ ቆይቷል። " (ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ገጽ 217-218)

አንድምታ በሹመት ተዋረድ ሳይሆን በሥራው ፍሬ ሁሉም የሚለይበትን ክፍል በሹመት ተዋረድ በማደላደል በብዙ ስፍራ የአምላክን አሠራር ኢፍትሐዊና አድልዎ የተሞላበት አድርጎታል አንዱን እንመልከት:-

በማቴ 25÷ 14-30 ለመክሊቱ ምሳሌ ከተሰጡት የተለያዩ አንድምታዎች መካከል ባለአምስቱ ሊቀጳጳስ÷ ባለሁለቱ ቄስ÷ ባለአንዱ ዲያቆን ነው የሚል ይገኝበታል። ተርጓሚዎቹ ባለአንዱ መክሊት ነግዶ ባለመትረፉ ተፈርዶበት ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ጨለማ መጣሉን ያገናዘቡ አይመስልም። አሊያም ደግሞ በዲያቆን ላይ ፈርደዋል።

አንድምታው እንዲህ ባለ የሹመት ተዋረድ ሄዶ ነው እንጂ በሥራ ፍሬ ቢላካ በተለይ ባለንበት ዘመን ድልድሉ የተገላቢጦሽ መሆን ይገባው ነበር።

ከብዙው በጥቂቱ እንግዲህ አንድምታ እንዲህ ዓይነት ገጽታ አለው። ሊቃውንት የእኛ በሚሉት ዕውቀት ከተረጎሙ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው እንደ ተረጎሙት በማስመሰል ሰው ለአንድምታቸው ልዩ ከበሬታ እንዲሰጥ አድርገዋል። የምስጢር ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ በእነርሱ እጅ ብቻ እንደሚገኝም በማወጅ የአብዛኛውን የዋህ ሰው ልብ ሰርቀዋል። ስለዚህ ብዙዎች "ያለ እነርሱ አይሆንም÷ እነርሱ አይሳሳቱም" ብለው ያምናሉ። በእነርሱ ለመመራት ራሳቸውን አሳልፈው ስለሰጡም ሁሉን ፈትኖ መልካሙን የመያዝ መብታቸውን ራሳቸው በራሳቸው ጥለዋል።

በዘመናችን ደግሞ ከአንዳንድ ማኅበራት የወጡ ወጣት ሰባኪያን የራሳቸውን ዐዳዲስ ትርጓሜዎች ይዘው ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። አንድ ወጣት ሰባኪ በአቅራቢያዬ ባለው የኦርቶዶክስ

ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲሰብክ የሰማሁትን ልጥቀስ:- በሐዋ. ሥራ 3÷4 ላይ ያለውን ቃል በመጥቀስ እንዲህ አለ "ጴጥሮስና ዮሐንስ ያን አንካሳ የነበረውን ሰው ወደኛ ተመልከት አሉት። የአሁኑ ትውልድ ግን ወደ ሐዋርያት አትመልከቱ ወደ ኢየሱስ ብቻ ተመልከቱ ይላል። " ስብከቱ የአሳቡን ተጋሪዎች ይበል የሚያሰኝ ቢመስልም ትክክለኛ አይደለም፤ ሰባኪው ይህን ቃል የተጠቀመበት የራሱን አሳብ ለማንጸባረቅ እንጂ የቃሉን ቀጥተኛ መልእክት ለማስተላለፍ አይደለም። አንካሳው ሰው በመቅደሱ ደጅ ተቀምጦ ወደ መቅደስ ከሚወጡና ከሚገቡ ምጽዋት ይለምን ነበር። በመሆኑም ትኩረቱን ከሌላ አቅጣጫ ወደ እነርሱ ለመመለስ ሲል:-"ወደኛ ተመልከት" በማለት ጴጥሮስ ተናገረው። ሰወዬውም ወደ እነርሱ ተመለከተ። በጌታ በኢየሱስ ስምም ፈወሱት።

ሰባኪው በምን መንገድ ሐዋርያቱን ተመልከቱ እንዳለ የሚረዳ ይረዳዋል። እርሱ ለማንጸባረቅ የፈለገውን ምልከታማ በወቅቱ ተአምሩ ሲሠራ በአቅራቢያው የነበሩት ሰዎች ወደነጴጥሮስ አተኩረው በመመልከት አሳይተው ነበር። ይህም ምልከታቸው ስሕተት ሆኖ በመገኘቱ ከጴጥሮስ ዘንድ " ... ስለምን ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ?" የሚል ማስተካከያ በወቅቱ ተሰጥቶበታል። (ቁ.12) ሰባኪው ግን ዝቅ ብሎ ቁ. 12ን ሳላየም መሰል በዚህ መንገድ በመመልከት ያን ስሕተት በዚህ ዘመን የምንገኝ እኛ ደግመን እንድንፈጽም ወደ ሐዋርያቱ ተመልከቱ ይለናል። እርሱ በተናገረው መንገድ ሳይሆን በአግባቡ ከመልካም ሕይወታቸው ለመማር የቀደሙትንም ሆነ አሁን ያሉትን ቅዱሳን ሐዋርያት እንመለከታለን። (1ቆሮ. 4÷16፤ 11÷1፤ ፊልጵ.3÷17፤ ዕብ.13÷7)

ከማንም በላይ ደግሞ በሁሉም ነገር የእምነታችንን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንመለከታለን (1ጴጥ.2÷21፤ ዕብ.3÷1፤ 12÷1-2)

ሰዎች በቤተ ክርስቲያናችን በአተረጓጎም ስሕተት ምን ያህል እየጠፉ እንደሆነ አስተውሉ። ይህ ሰባኪ ስሕተት ውስጥ የወደቀው የራሱን አሳብ ይዞ መጽሐፍ ቅዱሳን ለማንበብ በመሞከሩና ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ "ወደኛ ተመልከት" ያሉበትን ምክንያት ምዕራፉን ከላይ እስከታች አንብቦ መረዳት ሲገባው ጥራዝ ነጠቅ በመሆኑ ነው።

"ፊደል ይገድላል ትርጓሜ ያድናል" የሚል መርሕ ቃል በቤተ ክርስቲያን ተዘውትሮ ሲነገር ይደመጣል። ይህም "ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል" የሚለው ቃል ተለውጦ ነው። (2ቆሮ. 3÷6፤ ግእዙንም ተመልከት)

የተደረገው ለውጥ በመልእክቱ ላይ የትርጉም መፋለስን ስለሚያመጣ ስሕተት ቢሆንም መመሪያው በመመሪያነቱ ባልከፋም ነበር። ነገር ግን መመሪያው ከመመሪያነቱ ሳያልፍ ይልቁንም በተቃራኒ መንገድ ሥራ ላይ በመዋሉ ዛሬ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ፊደል ከገደላቸው ይልቅ ትርጉም የፈጃቸው በዝተዋል።

ሌላው ችግር ደግሞ የብሉይ ኪዳንን አሳብ÷ ሥርዓትና ትእዛዝ ወደ ዐዲስ ኪዳን በቀጥታ አምጥቶ ጥቅም ላይ የማዋሉ ጉዳይ ነው፤ ብዙዎች ብሉይ ኪዳን ለዐዲስ ኪዳን ጥላና ምሳሌ መሆኑን ይዘነጉና የብሉይ ኪዳንን ሥርዓትና መመሪያ በዐዲስ ኪዳንም ይመሩበታል። ለምሳሌ ያህል የሚበሉና የማይበሉትን እንስሳት አስመልክቶ በብሉይ ኪዳን የተደነገገ አለ። (ዘሌዋ. 11÷1-47) በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ግን ይህን ድንጋጌ የሚደግፍ ወይም የሚያጸና ሌላ ድንጋጌ የለም። እንዲያውም ድንጋጌውን የሚያፈርስ እንጂ። በዐዲስ ኪዳን ዘመን ሁሉ የተፈቀደልን ቢሆንም ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሆኖም ርኩስ የሆነ ነገር ፈጽሞ የለም። ስለዚህ ሁሉም ሳይነቃቀፍና ሌላውን ሳያሰናክል ሁሉን እንደፍላጎቱ በእምነት እየተጠቀመ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያውል ታዝዟል። (የሐዋ.ሥራ 10÷15፤ ሮሜ 10÷1-3፤ 14፤ 1ቆሮ. 6፥12-13፤10÷23-33፤ ቈላ. 2÷16)

እንግዲህ ይህ ሁሉ ስሕተት ተደማምሮ ሕዝባችን ከማስተዋል መንገድ ወጥቷል። የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድና አሳብም ስቷል።

# በትርጉም የተቀበሩ እውነቶችና ቦታ ያገኙ ውሸቶች

በመጽሐፍ ለተገለጹት እውነቶች የተሳሳተ ትርጉም ከተሰጣቸው ምክንያቶች መካከል ዋናው ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ሰርገው ለገቡት የስሕተት ትምህርቶች ሕጋዊነት ለመስጠት ሲባል መሆኑ ምስክር አያሻውም።

ብዙ የስሕተት ትምህርቶች በማስመሰል መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንዲኖራቸው የሚደረገው መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ስለ ሚስማማበት ነገሩ ተቀባይነት እንዲኖረው ነው። " መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" እንዲሉ አበው።

" የዋህ ቃልን ሁሉ ያምናል ብልህ ግን አካሄዱን ይመለከታል" ተብሎ የተጻፈውን ቃል በማስተዋልና " ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ" በሚለው ቃል መሠረት ማንኛውም ምእመን የሃይማኖቱን ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሊመረምርና መልካሙን ከመጥፎው ለይቶ ሊይዝ ተገቢው ነው። (ምሳ. 14÷15፤ 1ተሰ. 5÷20)

የቤርያ አይሁድ አመለካከት "ከተቀበልነው ውጪ ሌላ መስማት አንፈልግም" በሚል ጠባብነት ያልተሞላና ከላይ ባየነው የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተደገፈ በመሆኑ እውነትን ከሐሰት÷ ትክክለኛን ነገር ከተሳሳተው ለይቶ ለመረዳት ቀና መንገድ ሆኖላቸዋል። (የሐዋ. ሥራ 17÷11)

ስንቶቻችን የሃይማኖታችንን ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል መርምረናል? "መመራመር መጥፎ ነው" የሚለው የሰነፎች ብሂል አስሮ የያዘንስ ስንቶች ነን? በተገለጠው ነገር ላይ መልካሙን ከመጥፎው ለመለየት የሚደረገው ምርመር ምንም መጥፎ ጎን የለውም። እንዲያውም ወደ እውነት ያደርሳል። ከተገለጠልን ውጪ እግዚአብሔር ራሱ ምስጢር ያደረገውን ነገር ለመግለጥ መፍጨርጨሩ ግን ወደ አልተፈለገ ስሕተት ይመራናል። ብዙዎች ከሃይማኖት ወጥተው በትዕቢት ተነፍተው የወደቁት ከዚህ የተነሣ ነው። ለሁሉም ግን " ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ" የተባለው በተገለጠው እውነት ላይ ሁሉን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መርምረን እንደቤርያ አይሁድ ወደ እውነት እንድንደርስ መሆኑን አንዘንጋ።

አንዱንም በትክክል ሳንረዳ እኛ እናውቅላችኋለን በሚሉን ሰዎች ስንመራ ኖረናል። የእግዚአብሔርን እውነት አግኝተን ግን አላረፍንም። ለነገሩማ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡ ÷ ተማሩ ÷ አስተምሩ ብለው ሰጥተውን ነበር። እኛም ገልጠን ማንበብ ÷ መማር ÷ ማስተማር ጀመርን። በዚህ ጊዜ የተረዳነው እውነት ከእነርሱ አስተምህሮ ጋር ሳይስማማ ቀረ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ብልጭ ብሎልን ጥያቄ ስናቀርብ እንኳን ዘመናትን ካስቆጠረው ስሕተት ጋር ጥያቄአችን ስለሚጋጭ "ይህ የመናፍቃን ጥያቄ ነው።" ተብለን እንነቀፋለን። መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ የሚሆኑ ቢገኙም ለህልውናቸው ሲሉ በማቻቻልና አገም ጠቀም በሆነ መንገድ የማያረካ መልስ ይሰጣሉ። እግዚአብሔር ይመስገን! አሁን ግን የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን ተረድተናል። (1ዮሐ.5÷20)

እውነት እንዲዛባ ያደረገው በአተረጓጎም ላይ የተፈጠረው ስሕተት ነው። ከዚህ ቀጥሎ በቤተ ክርስቲያናችን የተሳሳተ ትርጓሜ ከተሰጣቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መካከል ዐለፍ ዐለፍ ብለን ጥቂቶቹን እንቃኛለን።

# የአብርሃም እንግዶች

በዘፍ. 18÷ 1-15 ክፍል ውስጥ ያለው ታሪክ "አብርሃም ሥላሴን እንግድነት ተቀበለ" የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ይገኛል።

አባታችን አብርሃም ከሚታወቅባቸው መልካም ሥራዎች መካከል አንዱ እንግዳ ተቀባይነቱ ነው። በዘፍ. 18 እንደተጻፈው "በቀትርም ጊዜ እርሱ (አብርሃም) በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዘፍ ተገለጠለት። ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ።" አብርሃም የተመለከታቸውን ሰዎች አንድ ጊዜ አንድን ሰው እንደሚያናግር "አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ" በማለቱና ሰዎቹ ሦስት በመሆናቸው "ጥቂት ውኃ ላምጣላችሁ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ" ብሎ መግለጹ መተርጉማኖቻችንን "አንድነቱንና ሦስትነቱን ሲያጠይቅ ነው።" ለማለት ተመችቷቸዋል። ከቁ. 9-10 ባለው ውስጥም መጀመሪያ "እነርሱ" ቀጥሎ ደግሞ "እርሱ" ስለተባለ ለዚህም ተመሳሳይ አንድምታ ተሰጥቶታል።

በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር በሦስትነት አለመገለጹ "ሰዎቹም ከዚያ ተነሥተው ወደ ሰዶም አቀኑ" ተብሎ በተደጋጋሚ በመነገሩና ወደ ሰዶም አቀኑ የተባሉት ሁለት መላእክት መሆናቸው በመረጋገጡ ይታወቃል። (ዘፍ.18÷16፤22፤19÷1)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ እግዚአብሔርን በአንድነትና በሦስትነቱ ያወቀው አልነበረም። ሕዝበ እስራኤል እንኳ ያወቁት በአንድነቱ ብቻ ነበር። (ዘዳ. 6÷4) በአንዳንድ ስፍራ ሦስትነቱን ሊያመለክቱ የሚችሉ ቃሎች ቢገለጹም አገላለጹ ድብቅ ነው። (ዘፍ.1÷26፤ 3÷24፤ 11÷7፤ ኢሳ. 6÷8)

ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ "ወአልቦ ዘአእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት እሙ" "ሥሉስ ቅዱስን (ሥላሴን) ወልድ ዋሕድ ከቅድስት እናቱ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ያወቃቸው ሰው የለም" ሲል መስክሯል።

ከብዙ ውሸቶች መካከል አንድ እውነት አይታጣምና ድርሳነ ሚካኤል እንኳ ለአብርሃም የተገለጹት መላእክት እንደነበሩና የይስሐቅን መወለድ እንዳበሠሩት እውነትን ይዞ ውሸት አክሎበት

ይመሰክራል። " ዳግመኛም መላእክት ወደ አብርሃም ዘንድ መጥተው ይስሐቅ እንዲወለድ ነገሩት።" (ድርሳነ ሚካኤል ዘሚያዝያ ቁ. 11)

የይስሐቅን መወለድ የተናገረው ከሁለቱ መላእክት ጋር ሦስተኛ የነበረው እግዚአብሔር ነው እንጂ ሁለቱ መላእክት አይደሉም። (ዘፍ.18÷10)

በዕብራውያን መልእክት " እንግዶችን ለመቀበል አትርሱ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና" ተብሎ የተገለጸው የአብርሃምና የሎጥ እንግዳ ተቀባይነት መላእክትን እስከመቀበል እንዳደረሳቸው ያመለክታል። አብርሃም የተቀበለው እግዚአብሔርን በሦስትነቱ ቢሆን ኖሮ ይህ ታላቅ ነገር ነውና በዚህ ክፍል ውስጥ ሊገለጥ በተገባው ነበር። (ዕብ.13÷2)

እግዚአብሔር በሦስትነቱ ተገልጾለት አብርሃም ሥላሴን እንግድነት ቢቀበል ምንም ክፋት የለውም። በዚህ ቅር የሚሰኝ አይኖርም፤ አርዮሳዊ ሰባልዮሳዊ ካልሆነ በቀር። እግዚአብሔር ሦስትነት ያለው አንድ አምላክ ነውና። ነገር ግን እግዚአብሔር ከሁለት መላእክት ጋር መገለጹ በግልጽ ተጽፎ ሳለ እግዚአብሔር በሦስትነቱ ተገለጸ ማለት የልተጻፈ አንባቢ ያሰኛል።

# ያዕቆብ በሕልሙ ያየው መሰላል

"ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ። ወደ አንድ ስፍራም ደረሰ። ፀሐይም ጠልቃ ነበርና ከዚያ አደረ። በዚያም ስፍራ ድንጋይ አነሣ። ከራሱም በታች ተንተርሶ በዚያ ስፍራ ተኛ ሕልምም አለመ። እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር። እነሆም እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር።" (ዘፍ 28÷10-13)

ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ፊት ሸሽቶ በጉዞ ላይ ሳለ ካደረበት ቦታ ሌሊት ተኝቶ በሕልሙ ያየው ይህ መሰላል ማርያም ናት ብለው ብዙዎች ያምናሉ÷ ያስተምራሉም። በድርሰቶቻቸውም ውስጥ አስረግጠው በስፋት ጽፈዋል። ይህም የክርስቶስን ስፍራ ለእርሷ ለመስጠት ብለው ያደረጉት ነው።

ያዕቆብ በምድር ተተክሎ÷ ራሱን ወደሰማይ ደርሶ ያየው መሰላል በምድር የሚኖሩ ሰዎች በሰማይ ካለው አምላክ ጋር የተገናኙበት ሰው የሆነው አምላክ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ለያዕቆብ በምሳሌነት የታየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሲመጣ መላእክት በመሰላል ላይ ሳይሆን የሰው ልጅ በተባለው በክርስቶስ ላይ እንደሚወጡና እንደሚወርዱ ራሱ ጌታችን ተናግሯል:- "እውነት እውነት እላችኋለሁ። ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወረዱ ታያላችሁ።" (ዮሐ1÷52)

ያዕቆብ ስለመሰላሉ ያየው ራእይ በክርስቶስ መፈጸሙን ሊቃውንተ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በየድርሳኖቻቸው አስቀምጠውልናል።

"ወሶበሂ ርእይዎ ዓዲ እንዘ የዓርግ ሰማየ ተፈሥሑ ወተሐሠዩ ጥቀ ወዐርጉ ምስሌሁ ውስተ ሰማይ ወበእንተዝ እምአመ ዕለተ ዐርገ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ኮነ ራእይ ዘነጸሮ ያዕቆብ እሙነ እንዘ መላእክት የዐርጉ ወይወርዱ ኀበ አብ ወዝ ውእቱ ርእይ ሐዲስ ዘኮኑ ይትሜነዩ ይርአይዎ እምቅድመ ዮም ወናሁ ይእዜ ርእይዎ"

ትርጓሜ:- "ዳግመኛ ወደ ሰማይ ሲያርግ ባዩት ጊዜ ፈጽሞ ደስ አላቸው። ወደ ሰማይም ተከትለውት ወጡ ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገበት ቀን ጀምሮ መላእክት ወደ አብ ሲወጡ ሲወርዱ ያዕቆብ ያየው ራእይ ደረሰ ተፈጸመ። ከዛሬ አስቀድሞ ሊያዩት

ይመኙት የነበረ እንግዳ ማየት ይህ ነው። እነሆ አሁንም ዛሬ አዩት።" (ሃይ. አበ ዘዮሐ. አፈ ም. 68 ክፍል 25 ቁ. 34)

"ያዕቆብኒ ይቤ ርኢኩ ሰዋስወ ዘሰማይ፤ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ፤ አንተ ይእቲ ሰዋስወ ኢየሱስ ይነብር በየማነ አቡሁ አእላፍ መላእክት ይትለአክዎ።"

ትረጓሜ :- "ያዕቆብም ወደሰማይ የደረሰ መሰላልን አየሁ አለ። የእግዚአብሔር መላእክትም ይወጡበታል ይወርዱበታል። ይህችም በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ አእላፍ መላእክት የሚያገለግሉት የኢየሱስ መሰላልነት ናት።" (የዮሐንስ ድጓ ገጽ 88 3ኛ ዓምድ)

# የታቦት መባዛት ምስጢር

"እግዚአብሔርም ሙሴን አለው። ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ። በሰበርኻቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ።" (ዘጸ.34÷1)

ሙሴ አሥሩ ትእዛዛት የተጻፈባቸውን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ከተራራው ሲወርድ ሕዝበ እስራኤል የሙሴን መዘግየት ምክንያት አድርገው የእግዚአብሔርን ድንቅ ተአምራት ፈጥነው በመርሳት የጥጃ ምስል አቁመው ሲያመልኩት በተመለከተ ጊዜ በእጁ የነበሩትን ጽላቶች መስበሩ ይታወቃል። (ዘጸ. 32÷19)

እንደገና ግን በሰበራቸው ምትክ ሁለት ጽላቶችን ጠርቦ እንዲያመጣና እግዚአብሔር ራሱ ሕጎቹን እንዲጽፍባቸው ነገረው። (ዘጸ. 34÷1)

አሁን ቤተ ክርስቲያናችን አራብታ የምትገለገልባቸው የተለያዩ ጽላቶች (ታቦታት) የት መጣቸው ከዚህ እንደሚጀምር የሚያስተምሩ አሉ። በመሆኑም "ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ የሚለው ትእዛዝ ጽላትን ሰው እንዲሠራና አሁን በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚታየው በብዛት እንዲራባ አመላካች ነው" ይላሉ።

ነገር ግን ይህ ትርጉም ተግባራዊ የሆነው የዘጸ. 34÷1 ቃል ታቦትን ስለማራባት እንደሚገልጽ በሚታመንባት በኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በሌላ የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ግን ተግባራዊ አልሆነም።

እስራኤላውያን ከሙሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ የነበራቸው አንድ ቤተ መቅደስና ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን የያዘ አንድ ታቦት ብቻ ነው። ታቦትን ማራባት የታዘዘ ወይም የተፈቀደ ቢሆን በእስራኤል አውራጃዎች ሁሉ ቤተ መቅደሶችን እያነጹ ጽላቶችን እየቀረጹ ይጠቀሙ ነበር። ሌላው ቀርቶ ክብረ ነገሥት በተሰኘው መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድም ይሁን በስርቆት እንደመጣ በሚተረክለት ታቦታቸው ምትክ ሌላ ታቦት ሊሠሩ ይገባቸው ነበር። ሁሉም ግን አልሆነም። ለነገሩማ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ በክብረ ነገሥት መጽሐፍ

የተተረከለት ታቦት ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በኋላ ብዙ ዓመታት ቆይቶ በ16ኛው የይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ዘመን እዚያው ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ መታየቱ የክብረ ነገሥት ትረካ ተአማኒነትን እንዲያጣ ያደርገዋል። (2ዜና 35÷3)

ስለታቦቱ ከተነሣ ሳይዳሰስ የማይታለፍ ጉዳይ አለ። ታቦት የተሰጠው ለሕዝበ እስራኤል ብቻ ነው። የተሰጠበት ዓላማም እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ተገልጾ የእስራኤልን ልጆች በመሪዎቻቸው አማካኝነት ለማነጋገርና ረድኤትን ለመስጠት ነው። (ዘጸ.25÷22)

እነዚህም ተግባሮች በታቦቱ አማካኝነት የታቦት አገልግሎት እስካበቃበት ጊዜ ድረስ ተከናውነዋል።(ዘኍ. 7÷89፤ ኢያ.3÷8-17፤ 6÷6-21፤ መሳ. 20÷ 27- 28፤ 1ሳሙ. 5÷1-6÷21)

ታቦቱ በውስጡ በድንጋይ ጽላት ላይ የተቀረጹትን በእግዚአብሔርና በእስራኤል ልጆች መካከል ምስክር የሆኑትን ቃል ኪዳኖች ስለያዘ የቃል ኪዳኑ ታቦት እየተባለ ተጠርቷል። (ዘዳ. 10÷8፤ 31÷26)

የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳኑን በማፍረሳቸው እግዚአብሔር ሌላ ዐዲስ ኪዳን እንደሚገባና ዐዲሱ ቃል ኪዳን ከብሉይ ቃል ኪዳን በተለየ መንገድ እንደሚሰጥ ተናገረ። (ኤር. 31÷31-34)

የቀደመው ቃል ኪዳን ከሕዝቡ ሕይወት ውጪ በሆነ የድንጋይ ጽላት ተቀርጾ ነበር። በብዙ መንገድ ከውስጣዊ ሕይወታቸው የራቀ መሆኑ ደግሞ እነርሱ እንዳይፈጽሙት የሚያደርገው ተጽዕኖ ቀላል አልነበረም። ዐዲስ ኪዳን ግን ሕጉ ወደ ውስጣቸው የሚገባበት÷ የድንጋይ ጽላት በልብ ጽላት የሚተካበትና አገልግሎቱ በፊደል መሆኑ ቀርቶ በመንፈስ የሚከናወንበት በመሆኑ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ተምሮ እግዚአብሔርን የሚያውቅበት ኪዳን ነው። በዚህም ኪዳን እግዚአብሔር በደልንና ኃጢአትን ደግሜ አላስብም ሲል ቃል ኪዳን ገብቷል። (ዕብ. 8÷6-13፤ 2ቆሮ.3÷3)

"በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ ይላል እግዚአብሔር በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፤ አያስቡትምም፤ አይሹትምም፤ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም።" ተብሎ በኤርምያስ

እንደተነገረው የእስራኤል ልጆች ከምርኮ ተመልሰው በአገራቸው መኖር ሲጀምሩ ዘሩባቤል ባነጻው ቤተ መቅደስ ውስጥ ታቦት ማኖር አላስፈለጋቸውም። እግዚአብሔር እንደተናገረው የአገልግሎቱ ዘመን አብቅቷልና። (ኤር. 3÷16፤ ዕዝ. 1÷9-11)

እግዚአብሔር እየደጋገመ በአጽንዖት የተናገረውን የኤር. 3÷16ን ቃል ለውጠው "ትንቢቱ የተነገረው ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ስለመጣ ነው" ለማለት የሚዳዳቸው ደፋሮችም አልታጡም።

አሁን በምንገኝበት ዘመን በዐዲስ ኪዳን የታቦቱ አገልግሎት በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ስለተተካ እግዚአብጤርን ለማነጋገርም ሆነ እርዳታውን ለመፈለግ ወደ ታቦት አንሄድም። ያኔ በታቦት ላይ ተገልጾ ሕዝቡን ያነጋግር የነበረው እግዚአብሔር አሁን ራሱን በአንድያ ልጁ በኩል ገልጾ አነጋግሮናል። (ዮሐ.1÷18፤ 14÷8-9፤ ቆላ. 1÷15፤ ዕብ. 1÷1-3) በልጁም ሁሉን ነገር እንዲያው ሰጥቶናል። (ሮሜ. 8÷32፤ 6÷23፤ 5÷17፤)

ከዚህ እውነታ ተነሥተው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የዐዲስ ኪዳን አማናዊ ታቦት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑንና የታቦት ምሳሌነት በክርስቶስ መምጣት መፈጸሙን መስክረዋል። ኤፍሬም ሶርያዊ በውዳሴ ማርያም:- "ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኩለሄ ዘግቡር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ "

ትርጓሜ:- " በውስጥና በውጭ በወርቅ የተለበጠ ታቦት ያለመለወጥና ያለመለየት ሰው የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይመስልልናል" ሲል ቄርሎስም በበኩል " ወእምድኅረዝ ኮነ ሰብአ ተሰምየ ብእሴ÷ ወመሲሐ÷ ወኢየሱስሃ ÷ ወታቦተ÷ ወዐራቄ÷ ወበኩረ ለዘሰከቡ÷ ወበኩረ ለዘይትነሣእ እሙታን÷ ወርእሰ ሥጋሃ ለቤተ ክርስቲያን "

ትርጓሜ:- "ሰው ከሆነ በኋላም በእሲ÷ የተቀባ÷ ኢየሱስ÷ ታቦት÷ አስታራቂ÷ ለሙታን በኩር÷ ከሙታን ወገን ለሚነሣም በኩር የቤተ ክርስቲያን ራስ ተባለ።" (ሃይ. አበ ም. 81 ክፍል 51 ቁ. 8)

# ቃል ኪዳን

"ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ" (መዝ.88÷3)

በዚህ ቃል ሽፋንነት የገባው የስሕተት ትምህርት የክርስቶስን የመካከለኛነት ስፍራ ለፍጡራን ያሰጠ ነው። እግዚአብሔር በተለይም በብሉይ ኪዳን ዘመን ከተለያዩ ቅዱሳን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መነሻ በማድረግና " ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ" የሚለውን ቃል በመታከክ በዐዲስ ኪዳን ዘመንም ኃጢአተኞች ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡበትን የተለያየ ቃል ኪዳን ሰጥቷል የሚሉ አሉ።

በቅዱሳን ስም በተደረሱት ገድላትና ድርሳናት ውስጥ ከራስ ዐልፌው ሰባትና ከዚያም በላይ ትውልድ ድረስ መንግሥተ ሰማያትን የሚያስወርሱ ቃል ኪዳኖች እንዳሉ ተገልጿል። ቃል ኪዳኖቹ የተመሠረቱትም በቅዱሳን ስም የተለየዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ነው። ሌላው ቀርቶ የአንዱን ቅዱስ ገድል የጻፈ÷ያጻፈ÷ ያነበበ÷ የተረጎመ÷ የሰማ÷ ያሰማ እንኳ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚወርስ ተስፋ የሚሰጡት ገድላት አያሌ ናቸው። በራእ. 1÷3 ላይ "ዘመኑ ቀርቧልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው" ከሚለው የተኮረጀ ሊሆን ይችላል።

በመዝ. 88÷3 ላይ የተገለጸው እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንጂ ሌሎችን አይወክልም። በቁ.4 "ለባሪያዬ ለዳዊት ማልሁ ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፤ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ።" ማለቱ ይህንኑ ያስረዳል። ቃል ኪዳን የገባው የማይዋሽ እግዚአብሔር በመሆኑ:- "ኪዳኔንም አላረክስም ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም። ዳዊትን እንዳልዋሸው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ። ዘሩ ለዘለዓለም ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል። ለዘለዓለም እንደ ጨረቃ ይጸናል። ምስክርነቱ በሰማይ የታመነ ነው።" ብሎ ነገሩን እንዳጸናለት ይናገራል። (ቁ. 34-37)

ይህ የዙፋኑ መጽናት ቃል ኪዳን ለጊዜው ጥላነቱ በሰሎሞን ሲታይ በክርስቶስ ግን ተፈጽሟል። (2ሳሙ.7÷12-16፤ ሉቃ.1÷32፤ ዕብ. 1÷5፤ 8፤ ራእ. 22÷11 )

እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ በመሆኑ ዳዊት ከሞተ በኋላ ልጁ ሰሎሞን በቃል ኪዳኑ ውስጥ የነበረውን ውል አፍርሶ በመገኘቱ መንግሥቱ መቀደድ ቢኖርበትም ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን አስቦ ይህን በሰሎሞን ዘመን አላደረገበትም። (ዳን. 9÷4፤ 1ነገ.9÷5-7፤ 11÷1-13)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (በብሉይ ኪዳን) ቃል ኪዳን ከተገባላቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ አዳም÷ ኖኅ÷ አብርሃም÷ ሙሴና ዳዊት ናቸው።

ለአዳም የተሰጠው ቃል ኪዳን መልካሙንና ክፉውን በሚያስታውቀው ዛፍ ምልክትነት ዘላለማዊ ሕይወትን የሚያስገኝ ተስፋን የያዘ ነበር። የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች አዳምና ሔዋን በኪዳኑ ስላልጸኑ ሞት ገዛቸው። (ዘፍ. 2÷8-17፤ ሆሴ.6÷7)

ከአዳም ቀጥሎ ቃል ኪዳን የተሰጠው ኖኅ ሲሆን ምድር ዳግመኛ በጥፋት ውሃ እንዳትጠፋ የቆመ ኪዳን ነው። ይህ በምድር ላይ የመኖር ተስፋን የያዘው ኪዳን በቀስተ ደመና ምልክትነት ተገልጦ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ያገለግላል። (ዘፍ. 9÷1-17)

ሌላው ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን በብሉይ ኪዳን ጎላ ያለ ስፍራ ከተሰጣቸውና በዐዲስ ኪዳን ፍጻሜ ካገኙት መካከል ይጠቀሳል። የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች ለጊዜው ምድራዊቷን ከነዓንን የወረሱት አብርሃምና በይስሐቅ በኩል የተቆጠሩት ዘሮቹ ሁሉ ሲሆኑ በፍጻሜ እይታው ግን አይሁድ አሕዛብ ሳይለዩበት አብርሃምን በእምነት በመምሰላቸው የአብርሃም ልጆች የሆኑት ሁሉ ናቸው። (ገላ. 3÷7-9፤ 29 ፤ ሮሜ 4÷11-12፤ 9÷7-8)

የዚህ ቃል ኪዳን ምልክት ግዝረት፥ የቃል ኪዳኑ ተስፋ ደግሞ በዘሩ የአሕዛብ መባረክና ከነዓንን መውረስ ነው። (ዘፍ. 17÷1-21፤ ሮሜ 4÷11)

የምድር አሕዛብ ሁሉ የተባረኩበት ዘሩ ክርስቶስ የምድራዊት ከነዓን አማናዊት ምሳሌ የሆነችውን ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን የሚያወርስ በመሆኑ ለቃል ኪዳኑ ፍጻሜን ሰጥቷል። (ገላ. 3÷16) እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገው ሁሉ ለአብርሃም ከገባው ቃል ኪዳን አንጻር መሆኑንም ቅዱሳን መስክረዋል። (ሉቃ. 1÷54፤ 73)

በመቀጠል ደግሞ ለሙሴ የተሰጠውን ቃል ኪዳን እናገኛለን። (ዘጸ. 19፥5-6፤ 24፥7-8) የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች የሆኑት ሕዝበ እስራኤል የአብርሃምን የቃል ኪዳን ምልክት ተከትለው ሰንበታቱን መጠበቃቸው ለዚህ ቃል ኪዳን ምልክት ሆኗል። (ዘጸ. 31፥13፤ ሕዝ. 20፥10-17)

በቃል ኪዳኑ የተሰጣቸው ተስፋ በአገራቸው ሕይወትን ማግኘት ነው። ይህንንም ገና ከምድረ ግብጽ ሳይወጡ በነበረው ዕለት ምሽት ላይ ያረዱት የፋሲካ መታሰቢያ በግ ደም አረጋግጦላቸዋል። (ዘጸ. 12፥21-28) ከግብጽ ምድር ወጥተው ወደ ሲና ተራራ ሲደርሱ ሕጉን በድንጋይ ጽላት ጽፎ ይጠብቁትና በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ቃል ኪዳን ይሆን ዘንድ ለሙሴ ሰጠው። ይህም ብሉይ ኪዳን ተብሎ የተጠራው ነው። (ዘጸ. 19፥20፤ 31፥18፤ 20፥1-17፤ 34፥28፤ ዘዳ. 4፥13)

በእንስሳት ደም የቆመው ብሉይ ኪዳን ወደፊት ለሚመጣው ዐዲስ ኪዳን መንገድ ጠራጊ እንጂ በራሱ ቋሚነት አልነበረውም። የጽላቶቹ ተሰብሮ መተካት፥ የማደሪያው ድንኳን ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ መተካቱ፥ የመሥዋዕት መደጋገምና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ለጊዜያዊነቱ ምልክቶች ነበሩ። ይበልጥ ደግሞ ትንቢቱ ይህን አረጋግጧል። (ዘዳ. 18፥15፤ ኤር. 31፥31)

ቃል ኪዳን የሚጸናው ሁለቱም ወገኖች ሲጠብቁት ብቻ ነው። ከሁለቱ አንደኛው ጠብቆ ሌላው ቢያፈርሰው ፈርሷልና ቃል ኪዳን መሆኑ ይቀራል። ብሉይ ኪዳን ጊዜያዊነቱ ሳያንሰው ሕዝቡ ሊጠብቀው ባለመቻሉ ቃል ኪዳንነቱ ቀረ። እግዚአብሔርም ከዚህ በብዙ መንገድ የተሻለውን ቃል ኪዳን እንደሚገባ ተናገረ። (ኤር. 31፥31-34) ይህም ስለ ዐዲስ ኪዳን የተነገረ ትንቢት በመሆኑ በዕብራውያን 8 ላይ ተፈጻሚ ሆኖ ተጠቀሰ። ዐዲስ ኪዳን የተሻለና የበለጠ ኪዳን በመሆኑ ብሉይ ኪዳን ከነጓዙ ፍጻሜ አግኝቶ እንደሚቀርና የሚጠቀምበት ቀርቶ የሚያስበው እንኳ እንደማይኖር እግዚአብሔር በአጽንዖት ተናገረ። (ኤር. 3፥16)

እግዚአብሔር እስከዚህ ድረስ ለተለያዩ ቅዱሳንና ለአጠቃላዩ የእስራኤል ሕዝብ ገብቶ የነበረውን ቃል ኪዳን ሁሉ በመጠቅለል በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ዐዲስና ለዘላለም የማይፈርስ ቃል ኪዳን ገባ። እርሱም በገዛ ደሙ የተመሠረተው ነው። (ሉቃ. 22፥19-20፤ ኢሳ. 42፥6-7)

ዐዲስ ኪዳን በክርስቶስ በኩል በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ ሲሆን የዘላለም ሕይወትን ተስፋ የያዘ ቃል ኪዳን ነው። የተስፋው ምልክቶችም ጥምቀትና ቅ/ቊርባን ናቸው። (ማር. 16÷16፤ 1ቆሮ. 11÷23-26፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 1972 ዓ/ም የታተመ ገጽ 80)

ዐዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ተክቷል። ዐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምክሩ የጸናበት÷ ሁሉ የተፈጸመበት ታላቅ ቃል ኪዳን መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍትም መስክረዋል:- "ወበምክረ ዚአከ ወልድከ ዋሕድ ኢየሱስ ዘተሰቅለ በእንተ መድኃኒትነ ዘበቃለ ኪዳንከ ቦቱ ገበርከ ሠሚረከ ቦቱ"

ትርጓሜ:- "ለድኅነታችን በተሰቀለው በአንድያ ልጅህ በኢየሱስ በባሕርይህ ምክር ደስ ተሰኝተህበት ቃል ኪዳንህን ሁሉ በእርሱ አድርገሃል።" (ቅዳ. እግዚእ ቁ 27-28)

እንዲሁም በእልመስጦአግያ :- "ከመ ታእምሩ ፈቃዶ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወትሌብዉ ምስጢረ መድኃኒትክሙ አ! አንትሙ እደው ወአንስት ቅዱሳት እለ ሀሎክሙ ውስተ ተመክሖ በክርስቶስ ወኩኑ አሐደ ምስለ ብእሲ ዘውስጥ አንትሙኬ እለ አጽንዓ እግዚአብሔር ኪዳኖ ምስሌክሙ ወሤመ መንፈሶ ውስቴትክሙ።"

ትርጓሜ:- "የኢየሱስ ክርስቶስን ፈቃድ ታውቁ ዘንድና የደኅንነታችሁን ምስጢር ታስተውሉ ዘንድ በክርስቶስ ትምክሕት ያላችሁ እናንተ ወንዶችና ቅዱሳት ሴቶች ሆይ! ከውስጣዊ ሰውነት ጋር አንድ ሁኑ፤ እግዚአብሔር ኪዳኑን ከእናንተ ጋር ያጸና መንፈሱንም በውስጣችሁ ያሳደረ እናንተ ናችሁ።" (ሃይ. አበ ምዕራፍ 4 ቁ. 6-7)

የእግዚአብሔር የባሕርይ ምክርና አሳቡ ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም በክርስቶስ በኩል በገባው ዐዲስ ኪዳን ተፈጽሞአል። እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ባለው ታሪክ የገባው የመጨረሻው ቃል ኪዳን ቢኖር ዐዲስ ኪዳን ነው። በዚህ ኪዳን ያልተፈጸመለት ወይም የቀረው ነገር ኖሮ በሌላ ቃል ኪዳን ለመፈጸም በማሰብ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ሌላ ቃል ኪዳን ገብቷል የሚለው ትምህርት ልብወለድ ነው። ምክንያቱም የዘመን ፍጻሜ በሚሰኘው

ባለንበት ዘመን እግዚአብሔር ለማድረግ ያሰበው ነገሮችን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል እንጂ ሌላ መንገድ ለመቀየስ አይደለም። (ኤፌ. 1፥10)

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ለቀደሙት የብሉይ ኪዳን አበው የገባው ቃል ኪዳን እንኳ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መንገድ ወይም ስለወደፊቱ ተስፋ ነበር እንጂ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ቃል ኪዳን ከማንም ፍጡር ጋር አልገባም። ምናልባት ለአዳም የገባው ቃል ኪዳን በአዳም ባይፈርስ ኖሮ ለዘላለም በሕይወት መኖርን የሚያስገኝ ቃል ኪዳን ይሆን ይሆናል። ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ ወደመንግሥተ ሰማያት የምንገባበትን ቃል ኪዳን የገባው ግን በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው።

በሐሰት ለቅዱሳን በዐዲስ ኪዳን ተገባ በሚባለው ቃል ኪዳን መሠረት እንዲህና እንዲያ ያደረገ ይህንንና ያንን ያገኛል የሚል ተስፋ በብዙ አዋልድ መጻሕፍት በስፋት ተጽፎ እናነባለን። አብዛኛው ቃል ኪዳን ተሰጠ ተብሎ የሚተረከው ቅዱሳኑ ሲሞቱ ሲሉ በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ ነው። እንዲህ ከሆነ ታዲያ በዐዲስ ኪዳን መጥምቁ ዮሐንስ፥ ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስና ያዕቆብ በግፍ የተገደሉ ቅዱሳን ናቸው። ሲሞቱ ሲሉም ሆነ ከዚያን በፊት ቃል ኪዳን እንደተገባላቸው በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አናገኝም። (ማቴ. 14÷10-12፤ የሐዋ. ሥራ 7÷6፤ 12÷2)

ለነዚህ ቅዱሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈላቸው ውጪ ሰዎች ከልባቸው አንቅተው በደረሱላቸው ድርሳናትና ገድላት ውስጥ ግን የተለያዩ ቃል ኪዳኖችን ጻጽፈው ሊያስነብቡን ቢከጅሉም አንድም እውነትነት የሌለው ነው።

ዛሬ ብዙዎች ከእግዚአብሔር ባልተገባ ቃል ኪዳን ተሸንግለዋል። ስለዚህ በክርስቶስ አዳኝነት አምነው ከመጽደቅና በእርሱ ኖረው መልካም የሥራ ፍሬን ከማፍራት ይልቅ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን በመጨመር ከእግዚአብሔር ባልሆነው ቃል ኪዳን እየተኩራሩ "በእገሌ ቃል ኪዳን መሠረት እንዲህ ካደረግሁ አልኮነንም።" ብለው ራሳቸውን ያታልላሉ።

"ለዓመፀኞች ልጆች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር ከእኔ ዘንድ ያልሆነውን ምክር ይመክራሉ። ኃጢአትንም በኃጢአት ላይ

ይጨምሩ ዘንድ ከመንፈሴ ዘንድ ያልሆነውን ቃል ኪዳን ያደርጋሉ።"
(ኢሳ. 30÷1)

## የእግዚአብሔር የእግሮቹ መቆሚያ ስፍራ

"እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።" (መዝ. 131÷7)

ክርስቶስ ስለተሰቀለበት መስቀል በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት የሚከታተል ሁሉ ይህ ቃል ለመስቀል ስለመስገድ እንደሚጠቀስ ያውቃል።

መስቀል ሁለት ፍቺ አለው። የመጀመሪያው ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ ሆኖ የተሰቀለበት የተመሳቀለ ዕንጨት ሲሆን (ዮሐ. 19÷17፤ 1ጴጥ. 2÷24) ሁለተኛው ደግሞ በዚህ የተመሳቀለ ዕንጨት ላይ ክርስቶስ የተቀበለው መከራና ሞት በጥቅሉም የቤዛነቱ ሥራ ሁሉ ነው። (ኤፌ. 2÷16፤ ቆላ. 2÷14)

ዓለም ሁሉ በእምነት የሚድንበትና የሚመካበት መስቀል በሁለተኛው ፍቺ ውስጥ ነው የሚገኘው። በተለይም በዐዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ ስለመስቀል የተነገሩት ሁሉ የክርስቶስን ቤዛነት የሚያመለክቱ ናቸው። (1ቆሮ. 1÷18፤ ገላ. 6÷14፤ ፊልጵ. 3÷18)

በቤተ ክርስቲያናችን እነዚህ የተጠቀሱትና የተቀሩትም ሁሉ "መስቀል" የሚል ቃል ይዘው ስለተገኙ ብቻ ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀል ተሰጥተው ይተረጎማሉ። ስለዚህ የብዙ ምእመናን ዐይኖች የመስቀልን ቅርጽ እንጂ የተሰቀለውን ክርስቶስን ለማየት አልታደሉም። (ገላ. 3÷1) እዚህ ላይ አንድ ወንድም ነገሮችን ሁሉ አጢኖ በአንድ ወቅት የተናገረውን ብጠቅስ ተገቢ ይሆናል። "ቤተ ክርስቲያናችን እየሰበከች ያለችው በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ክርስቶስን ሳይሆን ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ነው።"

እርግጥ ዛሬ ጎልቶ የሚታየው÷ የሚሰማው÷ የሚነገረው÷ ይህ ቢሆንም ተቀብሮ ያለው የቤተ ክርስቲያኒቱ እውነት ግን ስለመስቀል ዕፁብ ድንቅ ምስጢርን ይናገራል። "ወበእላ ከናፍር ጾታ ነጊር አይትከሀል ጥንቁቀ፤ ዘእምትካት ኅቡእ ኮነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ ለምእመናን። አኮ ከመ ይትረአይ አላ ከመ ይትኀለይ ውእቱ ዝንቱ መስቀል ወቦቱ ንትመካሕ ከመ ንስብሖ።"

ትርጓሜ:- "በእነዚህ ከንፈሮች የንግግር ስልት ጠንቅቆ መናገር አይቻልም፤ ከጥንት ስውር የነበረው ዛሬ ግን ለምእመናን የተገለጠ

ሆኗል። እናመሰግነው ዘንድ የምንመካበት ይህ መስቀል በልብ የሚታሰብ ረቂቅ ነው እንጂ በዐይን የሚታይ ግዙፍ ነገር አይደለም።' (ትምህርተ ኅቡአት)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።" ሲል ቅርጽ ያለውን መስቀል ስለመሸከም ሳይሆን የእርሱን መከራና ሞት እያሰብን ስለመኖርና በመከራውም ስለመካፈል የሚያስረዳ ነው። (ማቴ. 16÷24) ይህንንም ሲገልጽ ሐዋርያው " የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን።" ብሏል። (2ቆሮ. 4÷10)

ክርስቶስ የሞተው በመስቀል ላይ በመሆኑ መስቀል የተሰቀለውን ክርስቶስን ስለሚያሳስባቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ክቡር ዓርማቸው አድርገው ይጠቀሙበታል። የቤተ ክርስቲያናችንም እምነት ይኸው ነው። ከዚህ በቀር በፈጠራ ትምህርትና ታሪክ ጌታ ለተሰቀለበት መስቀል በሚል ሽፋን ቅርጻ ቅርጽ ሠሪዎች በተለያየ መጠንና ቅርጽ እየሠሩ ለተጠበቡበት እደ ጥበብ የሚሰጠው የክርስቶስ የአዳኝነት÷ የቤዛነት÷ የመመኪያነት ስፍራ አግባብነት የለውም። (ኢሳ. 42÷8)

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ምድር ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር እየተጓዙ ሳለ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ በማጉረምረማቸው እግዚአብሔር በቅን ፍርዱ ተናዳፊ እባቦችን አስነሥቶ እንዲነደፉ አደረገ። በመቅሠፍቱም ብዙዎች ሞቱ። በሕይወት ተርፈው በመርዙ የተነደፉት ሁሉ በደላቸውን አምነው በመጸጸት በመካከለኛቸው በሙሴ በኩል እግዚአብሔርን በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ እንዲሰቅልና የተነደፉት ወደተሰቀለው እባብ በማየት የሚድኑ መሆኑን ለሙሴ ነገረው። ሙሴም እንዲሁ በማድረጉ በመርዘኛው እባብ የተነደፉት ሁሉ የናሱን እባብ አይተው ዳኑ። (ዘኍ. 21÷4-9)

ይህም ወደፊት የሚሆነውን የክርስቶስን መሰቀልና ዲያብሎስ የገዛቸው ሁሉ የተሰቀለውን በእምነት በማየት የሚድኑ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ነበር። (ዮሐ. 3÷14-15)

በመርዘኛው እባብ የተነደፉት ሁሉ እሱን በማየት ብቻ ድኅነትን ካገኙ በኋላ የናሱ እባብ አገልግሎት አብቅቷል። ሕዝቡ ግን የአገልግሎት ዕድሜውን በገዛ ፈቃዳቸው በመጨመራቸው ትውልድ

ዐልፎ ትውልድ ሲተካ ዘመናትም እንዲሁ በጨመሩ ቁጥር የናሱን እባብ ወደማምለክ ተሸጋገሩ። ይህ አድራጎታቸው ትክክል ባይሆንም ለዚያው ለአንዱ ጊዜ እንኳ ያዳነቸው የናሱ እባብ እንጂ እባቡ የተሰቀለበት ዓላማ (ዕንጨት) አለመሆኑን አስተውለው ነበር። ዛሬም ዓይኖቻቸው በተሰቀለው ክርስቶስ ላይ መሆኑ ቀርቶ በተሰቀለበት መስቀል ላይ ላረፈው ወገኖች ይህ ጥሩ ትምህርት ይሆናል።

ሕዝበ እስራኤል ከጊዜያዊ መቅሰፍት የዳኑበትን የናስ እባብ እንጂ የተሰቀለበትን ዓላማ አልተመለከቱም። የታዘዙትም የናሱን እባብ ብቻ እንዲመለከቱ ነው። (ቁ. 8-9) ይህንን በእርግጥ ተረድተዋል። ከመጀመሪያው ጣዖት ያልነበረውና በቆይታ ግን የሕዝቡ ልብ ወደ ማምለክ ተሸጋግሮ እንደጣዖት በመቆጠሩ ንጉሡ ሕዝቅያስ ሰባብሮ እስካስወገደበት ዘመን ድረስ እንኳ ይዘው የተገኙት የናሱን እባብ ብቻ እንጂ ዓላማውን ጭምር አልነበረም። (2ነገ. 18÷4)

ስማቸው÷ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የገቡበት ትክክለኛ ዓላማ የጣዖት ያልሆነ የኛ አቀባበል÷ አያያዝ÷ አመለካከትና የዘመን ርዝመት መልካቸውን ቀይሮ ጣዖት ያደረጋቸው ስንት ነገሮች ይኖሩብን ይሆን?

በመስቀል የተሰቀለው መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ጊዜ የማይሽረው ዘላለማዊ አዳኝ አምላክ በመሆኑ አንዳች ነገር ሳያግደንና ሳይገድበን ለዘላለም ወደ እርሱ እንመለከታለን። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት እናመልከዋለን። ክብርና ምስጋና አምልኮና ስግደት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለእርሱ ይሁን!

ዛሬ ያ የሕዝበ እስራኤል ታሪክ ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል አቅጣጫ ራሱን መድገሙን ልብ እንበል።

ይህን ስሕተት የሚያራምዱት አፈጮሌዎች ያቆሙትን አምልኮተ መስቀል ትክክለኛ ለማስመሰል ተገን ያደረጉት "እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።" የሚለውን ቃል ሲሆን እንደ ፍላጎታቸው የሚሰጡት ትርጉም ደግሞ "የክርስቶስ እግሮች በምስማር ተቸንክረው ለሦስት ሰዓታት ያህል በመስቀል ላይ ስለቆሙ ለመስቀል ስግደት ይገባል።" የሚል ነው።

በትክክለኛው መንገድ ከተረዳነው ቃሉ በምድር ላይ ለእግዚአብሔር መስገድን ያሳያል። በስፍራ የማይወሰነው አምላካችን

እግዚአብሔር ለእኛ በሚገባን መጠን የራሱን የታላቅነት ቦታ በሰማይና በምድር ወስኖ "ሰማይ ዙፋኔ ኔው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት።" ብሎ እንደተናገረው የእግሩ መረገጫ በሆነችው በምድር ላይ ሰግደን እናከብረዋለን፤ እንገዛለታለን። (ኢሳ. 66÷1)

በብሉይ ዘመን የእግዚአብሔር ከተማና ማደሪያው ኢየሩሳሌም (ጽዮን) ነበረች። (መዝ. 131÷13-14፤ 121÷1) እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን ያለው በተመረጠችው ቅድስት ስፍራ በኢየሩሳሌም ስለመስገድ ነው። ቢኢየሩሳሌም የነበረው መቅደስ የእግሩ መረገጫ ነበር። (ሕዝ. 43÷7) ክርስቶስ ሰው ሆኖ የእግዚአብሔርን በቦታ ሳይወሰን በእውነትና በመንፈስ መመለክ ሳያውጅልን በፊት የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚችው ስፍራ ይሰግድ ነበር። (መዝ. 5÷7፤ 23÷2፤ የሐዋ. ሥራ 8÷27)

ቃሉን እንዲያው ቢቸግራቸው ወይም ሌላ አማራጭ ስላጡ ምንም ቢሆን ስለመስቀል ሊናገርልን ይችላል ብለው ጠቀሱት እንጂ የእነርሱን አሳብ የሚደግፍበት አንድ ነጥብ እንኳን የለውም። በነሱ አተረጓጎም እንሂድ ቢባል እንኳ "እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን" ይላል እንጂ "እግሮቹ ለሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን" አይልም። በሌላ አገላለጽ ለስፍራው ሳይሆን ስፍራው ላይ ለሚቆመው እንሰግዳለን ማለት ነው። እንደ እነርሱ አሳብ እግሮቹ የሚቆሙበት (የቆሙበት) ስፍራ መስቀል ነው ተብሏልና እንግዲህ መስቀሉ ላይ ቆመን መስገድ ሊኖርብን ነው። ይህ ታዲያ ይሆናልን?

ይህ ብቻም አይደለም ሰዎች ስለመስቀል ሌላም ብዙ ፍልስፍና አላቸው። አለቃ አያሌው ታምሩ በጽሑፍ ያስፈሩትን ለአብነት ያህል እንመልከት " . . . በአምላክ ደም የከበረ የቅድስና ተቀባይ አስተላላፊ በይ ቅዱስ መስቀል ነው።" (ምልጃ ዕርቅና ሰላም ገጽ 61)

ሁሉም ይህንን የመሳሰለውን ሥጋዊ ፍልስፍና ትቶ ወደ አእምሮው ተመልሶ ነገሮችን ሁሉ ለማጤን ቢሞክር ጌታ ሲሰቀል በፈሰሰው ክቡር ደም የተነካው መስቀሉ ብቻ ሳይሆን የተቸነከረባቸው ምስማሮች÷ የተወጋበት ጦር÷ የተገረፈባቸው ጅራፎች÷ በራሱ ላይ የደፋው የሾህ አክሊል÷ ደሙ የፈሰሰበት ምድር . . . ወዘተ ቁሳቁሶችና ግዑዛን ነገሮች ሁሉ ናቸው። ታዲያ ለጸጋው አስተላለፊነት መስቀሉ ብቻ እንዴት ታጨ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ከዚህ ተራ ፍልስፍና ይለያል። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠን ጸጋ ወደኛ የሚፈስበት ቦይ የዕንጨት መስቀል ሳይሆን እምነት ነው። (ኤፌ. 2÷10፤ ዕብ. 4÷16)

ስለመስቀል የተሳሳተ አስተምህሮ በቤተ ክርስቲያናችን ይበልጥ የተስፋፋው በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (15ኛው መቶ ክ/ዘ) መሆኑ ይታወቃል። " ወከመዝ ግበሩ" (እንዲህ አድርጋችሁ ሥሩ) ብሏል የሚለው ታሪክ ዘለል የጥራዝ ነጠቆች አጠቃቀስ እንደታቦቱ መስቀልንም ከተለያዩ ነገሮች (ከዕንጨት÷ ከብረትና ከተለያዩ ማዕድናት) በተለያየ መጠን÷ ቅርጽና ዓይነት ለመቅረጽ ያገለገላቸው ይመስላቸዋል። (ዘጸ. 25÷9)

መስቀል ይበልጥ እየተሠራ ቀሳውስት እንዲይዙት ምእመናን እንዲሳለሙት÷ በአንጻረ ቤተ ክርስቲያን በርቀት ተተክሎ እንዲሰግዱለት÷ የድንጋይ ስጦታ እንዲያበረክቱለትና የመሳሰለው የተለየ ክብር ሁሉ እንዲደረግለት የታወጀው በዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ነው።

"ወካዕበ ናስተበቍዕ ለዕፀ ቅዱስ መስቀል ጽኑዐ ሥልጣን ወኃይል" "ጽኑ የሆነ ኃይልና ሥልጣን ያለውን ቅዱስ የዕንጨት መስቀልን ዳግመኛ እነለምነዋለን" ተብሎ በቤተ ክርስቲያናችን ወደ መስቀል መጸለይ የተጀመረው÷ እንደገናም "ለእሉ ክልኤቱ ፍጡራን ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ እስመ ተዐረዩ በክብሮሙ" "ለእነኚህ ለሁለቱ ፍጡራን (ለማርያምና ለመስቀል) የፈጣሪ ክብር ይገባቸዋል። በክብራቸው ከፈጣሪ ጋር ተካክለዋልና" ተብሎ ቅ/ማርያምና የዕንጨት መስቀል እንደፈጣሪ እንዲመለኩ የታወጀው በዚሁ ለማይረባ አእምሮ ተላልፎ በተሰጠው በዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ነው።

ምናልባት እነአልሰሜ "ቤተ ክርስቲያን መስቀልን ታከብረዋለች እንጂ ከፈጣሪ ጋር አስተካክላ አታመልከውም" ብለው ይሉ ይሆናል። ከላይ የተጠቀሰውን ድርሰት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይኸው እስካሁን ድረስ መሻሻል ሳይደረግበት ቤተ ክርስቲያናችን እየተጠቀመችበትና ወደ መስቀል እየጸለየችበት ይገኛል። ታዲያ ይህ መስቀልንም እያመለከች ነው አያሰኛትምን? (መስተበቍዕ ዘመስቀል)

# የቀረልን ዘር

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘር ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን ነበር" (ኢሳ. 1÷9)

ለቅድስት ድንግል ማርያም ተሰጥተው ከተተረጎሙት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች መካከል ይህም ተጠቃሽ ነው።

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የይሁዳ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን እየጨመሩ እግዚአብሔርን ስላሳዘኑት ለከፋ ችግር እንደሚጋለጡ÷ አገራቸውም በጠላቶቻቸው ተቃጥላ እንደምትፈራርስ÷ ባዕዳን ሰዎችም እንደሚጠቀሙባት÷ ሕዝቡም ለምርኮና ለብዝበዛ እንደሚሰጥ ነቢዩ ኢሳይያስ በግልጽ ተናግሯል። (ኢሳ. 1÷2-8፤ 2ነገ. 20÷17-18)

(ቁ. 9) ላይ የተነገረው ትንቢት ለጊዜው ከባቢሎን ምርኮ ስለሚተርፉት ቅሬታዎች ሲሆን (ነህ. 1÷3) ፍጻሜው ደግሞ ክርስቶስ ወደ ወገኖቹ መጥቶ ወገኖቹ ሊቀበሉት ባለመቻላቸው ምክንያት መዳንን ለመውረስ ባይታደሉም በኋለኛው ዘመን የአሕዛብ ሙላት ሲፈጸም የእስራኤል ቅሬታዎች በክርስቶስ አምነው እንደሚድኑ ያሳያል። (ኢሳ. 10÷22-23፤ ሮሜ 11÷25-27)

ይበልጥ ደግሞ ቅ/ጳውሎስ በሮሜ 9÷29 ላይ የኢሳ. 1÷9ን ቃል ጠቅሶ በመናገሩ ትንቢቱ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተነገረበትን ዓላማ በትክክል አስቀምጧልና ከዚህ ያለፈ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም።

ትንቢቱን ያለመልእክቱ ለድንግል ማርያም የሰጡት ክፍሎች "ዘር ባያስቀርልን ኖሮ" የሚለውን "አንቺን ባያስቀርልን ኖሮ" በሚለው ተክተው በድርሰታቸው ውስጥ እናነባለን። "ከመ ሰዶም እም ኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ እግዚአብሔር ኪያኪ እመ ኢያትረፈ ለነ" "እግዚአብሔር አንቺን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን÷ ገሞራንም በመሰልን ነበር።" (ማሕሌተ ጽጌ)

በአተራጓጎማቸው ብንሄድ እንኳ የቀረልን ዘር ብለን ልንጠራው የሚገባ ከእርሷ የተወለደውን ክርስቶስን መሆን ይኖርበታል። እሱ ገና

ከመጀመሪያው "የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል::" ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የሴቲቱ ዘር ነውና። (ዘፍ. 3÷15)

እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ ከድንግል ማርያም እንዲወለድ ሲያደርግ እርሷን ለዚህ ታላቅ እድል መርጦ አንጽቶ ቀድሶ አክብሯታል። ይህን ሁኔታ የምንገልጸው ግን በኢሳ. 1÷9 ሳይሆን በሉቃ. 1÷28 ነው። ኢሳ. 1÷9ን ለእርሷ የሰጡበት ምክንያት እርሷን ከሰው ዘር የተለየች ፍጥረት አድርገው ለመመልከትና ጌታ ለእርሷ ካሣ እንዳልከፈለላት ወይም እንዳልሞተላት ለመግለጽ መሆኑ ይታወቃል።

ለዚህ ግን የሌላውን ምስክርነት ሳንጠቅስ በፊት ራሷ የተናገረችውን ነው የምናስቀድመው፤ "መድኃኒቴ" ብላ ለምን ጠራችው? ጌታ ለእርሷም ጭምር እንደሞተላትና ካሣ እንደከፈለላት ለማመልከት አይደለምን? (ሉቃ. 1÷47)

ቅ/ያሬድ ይህን ሲያስረዳ:-" . . . እስመ በእንቲአሃ ወበእንተ አዝማዲሃ ተሰቀልኩ ዲበ ዕፅ ከመ አድኅኖሙ አዳምሃ ÷ አቤልሃ÷ አብርሃምሃ ÷ ይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ ÷ ወባዕዳነ ነቢያተ እለ ከማሆሙ ዐቀቡ ሕግየ ከመ በላዕሌሆሙ እሰባሕ እስከ ለዓለመ ዓለም"

ትርጓሜ:- "ስለእርሷና (ስለማርያም) ስለወገኖቿ በዕንጨት ላይ ተሰቀልኩ፤ አዳምን÷ አቤልን÷ አብርሃምን÷ ይስሐቅን÷ ያዕቆብን ሌሎችን ነቢያትንና እንደነርሱ ያሉትን ሕጌን የጠበቁትን አድናቸው ዘንድ÷ በእነርሱም እስከ ዘላለም ድረስ እመሰገን ዘንድ::" (የኅዳር ጽዮን ቅንዋት)

"የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ" በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 29 ላይ የሚከተለው ተጽፎአል:- "አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ። ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት::"

## የጽዮን ማንነት

"የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወዳንቺ ይመጣሉ። የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።" (ኢሳ. 60÷14)

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለጽዮን በስፋት የተጻፈውንና ሌላውንም በሴት አንቀጽ የተነገረውን ሁሉ ለማርያም ሰጥቶ መተርጎም በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ ነገር ሆኖ ከመጣ ዘመናት ተቆጥረዋል። እነዚህ ሁሉ በትክክል ለእርሷ የተነገሩ ትንቢቶች ቢሆኑ ኖሮ ሌላው ቀርቶ አንዱ እንኳ በዐዲስ ካዳን መጻሕፍት ውስጥ ተፈጻሚ ሆኖ እናየው ነበር። ለምሳሌ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና አማኑኤልን እንደምትወልድ በነቢዩ በኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት በዐዲስ ኪዳን ተፈጽሞ እንዳየነው ማለት ነው። (ኢሳ. 7÷14፤ ማቴ. 1÷22-23) ስለ ጽዮንና ሌሎቹም በሴት አንቀጽ የተጻፉት ትንቢቶች ግን አንድስ እንኳ ስለእርሷ የተነገረ ነው ተብሎ በዐዲስ ኪዳን የተገለጸበት ስፍራ የለም።

ስለ ጽዮን ከተነገረው መካከል ይስማማል ያሉትንና ባማሩ ቃላት የተቀመጡትን ብቻ በተለመደ ስልታቸው ከመሀል ነጥሎ በማውጣት ስለማርያም የተነገረ ነው ይላሉ እንጂ የመልእክቱን አሳብ ከመጀመሪያው ጀምረው እያስተዋሉ ቢያነቡ ኖሮ ለእርሷ ከመለጠፍ ይታቀቡ ነበር።

ኢሳ. 60÷14 ላይ በተጻፈው የማለሉት ከላይ ከፍ ብለው ቁ. 10ን ቢያስተውሉ "በቁጣዬ ቀስፌ በፍቅሬ ምሬሻለሁና" ይላል። ታዲያ ይህ ለድንግል ማርያም ይስማማልን? ቁ. 10 ላይ እንዲህ የተባለችው ቁ. 14 ላይ "የአስጨናቂዎችሽም ልጆሽ አንገታቸውን ደፍተው ወዳንቺ ይመጣሉ። የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ። የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።" እንደተባለላት መዘንጋት የለብንም።

"ጽዮን ግን እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታም ረስቶኛል አለች" (ኢሳ. 49 ÷16) ይህም ቃል ከድንግል ማርያም ጋር አብሮ አይሄድም መልአኩ የተናገረላትን ቃልም ይቃረናል "ጌታ ካንቺ ጋር ነው" (ሉቃ. 1 ÷28)

በውብ ቃላት የሚደለሉት መተርጉማን ግን ይህን ዘልለው (ኢሳ. 49 ፥16) ቁ. 22-23 ላይ የተጻፈውን ለእርሷ ይጠቅሳሉ። መቼም አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ እውነተኛ መሆን አይቻልም።

ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ስለጽዮን የተነገሩ ነገር ግን ድንግል ማርያምን የማይወክሉ አሉ። ሁሉንም በየክፍሉ መመልከት ነው፤ ጥቂቶቹ (ኢሳ. 54 ፥4፤ 51 ፥21፤ 57 ፥21) ናቸው። በተለይም ኢሳ. 57 ፥11ን ብንመለከት "ሐሰትን የተናገርሽው እኔንም ያላሰብሽው በልብሽም ነገሩን ያላኖርሽው ማንን ሰግተሽ ነው? ማንንንስ ፈርተሽ ነው? እኔ ብዙ ጊዜ ዝም አልሁ። አንቺም አልፈራሽም።" ይላል። ይህ በዐዲስ ኪዳን ተገልጦ የታየውን የቅድስት ማርያምን የአስተዋይነት ባሕርይ ይሽራል። እርሷ ከሐሰት የራቀች፥ ጌታን ሁልጊዜ የምታስብና የምታከብር፥ ነገሮችን ሁሉ አስተውላ በልቧ የምትጠብቅ ናት (ሉቃ. 1፥28፤ 47፤ 2፥19)

ለመሆኑ ጽዮን ማናት? የሰዎቹን ትተን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ስንመጣ ስለጽዮን ሰፋና ጠለቅ ያለ ግልጽና ምስጢራዊ ትርጉም እናገኛለን።

ጽዮን የኢየሩሳሌም ከተማ ከተሠራባቸው ተራራዎች አንዱ ሲሆኑ የቃሉ ትርጉም ደግሞ አምባ (ምሽግ) ማለት ነው።

የጽዮን ተራራ በስተሰሜን አቅጣጫ ይገኛል። (መዝ. 47፥2) ጽዮን በመጀመሪያ የተመሸገችው በኢያቡሳውያን ነበረ። እስከ ዳዊት ዘመነ መንግሥት በኢያቡሳውያን ሥር የነበረችውን የኢየሩሳሌምን ከተማና አምባይቱን የጽዮን ተራራ እነርሱን ድል አድርጎ ዳዊት ከተማዋን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ጽዮንንም ያዘ። (2ሳሙ. 5፥6-10፤ 1ዜና. 11፥4-7)

ዳዊት በአምባይቱ በጽዮን ላይ ድንኳን አስተክሎ የቃል ኪዳኑን ታቦት የጌት ሰው ከሚሆን ከአቢዳራ ቤት አስመጥቷል። (2ሳሙ. 6፥12-15፤ 1ዜና. 15፥25-29፤ 16፥1) በኋላ ጊዜ ዳዊት ከኢያቡሳዊው ኦርና ላይ የገዛውና ለእግዚአብሔር መሠዊያ የሠራበት አውድማ የጽዮን ክፍል እንደሆነ ግልጽ ነው። ጽዮን ደብረ ጽዮን የተባለችው ቀድሞ ሞሪያ፥ ኢያቡስ፥ የኢያበሳዊው የኦርና አውድማ የነበረችውና

ሰሎሞን ቤተመቅደስ የሠራባት ስፍራም ናት። (መዝ. 132÷13-14፤ 77÷68፤ ኣሳ. 4÷5፤ 2ዜና. 3÷1)

ሞሪያ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት ያቀረበበትና የእርሱን ምትክ በግ የሠዋበት ስፍራ እንደነበር ማስተዋል ያሻል። (ዘፍ. 22÷2-10)

የጽዮን ትርጉም በዚህ ሳይወሰን መላውን ኢየሩሳሌም ወክሏል። (2ነገ. 18÷35፤ 19÷21፤ መዝ. 68÷35፤ 146÷12)

ከዚያም ትርጉሙ እየሰፋ ሄዶ መላውን የእስራኤል ሕዝብ ምድራቸውን ባህላቸውን÷ መንግሥታቸውን÷ ሃይማኖታችውን የሚያመለክት ቃል ወደ መሆን አድጓል። ጽዮናውያን ተብሎ የእስራኤልን ሕዝብና መንግሥት ወደማመልከት ደረሰ ማለት ነው። (መዝ. 125÷1፤ 137÷1-4፤ ኢሳ. 49÷10፤ 52÷1)

ይህ የእስካሁኑ የምድራዊቷ ጽዮን ግልጽ ትርጉም ሲሆን ምስጢራዊ አተረጓጎሙ ደግሞ መንፈሳዊት (ሰማያዊት) ጽዮንንና ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል። ሰማያዊቱ ጽዮን በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን ሁሉ አሁን በእምነት የገቡባትንና ወደፊትም በጌታ ዳግም ምጽአት የሚወርሱአትን መንግሥተ ሰማያትን ታመለክታለች። (ገላ. 4÷26፤ ዕብ. 12÷22፤ ራእ. 3÷12፤ 21÷2፤ 10)

ጽዮን በብሉይ ኪዳን መላውን ቤተ እስራኤል ወይም ከቤተ እስራኤል የተመረጠውን መንፈሳዊ ጉባኤ ወክላ እንደምትነገር ሁሉ በዐዲስ ኪዳንም ቤተ ክርስቲያንን ትወክላለች። በተነገረው ጥቅስ ጊዜያዊ ትርጉም ቤተ እስራኤልን ስትገልጽ ፍጻሜዋ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ይሆናል። (ኢሳ. 52፤ 54) ለዚህም እነኚህ ሁለት ምዕራፎች በውስጣቸው በዐዲስ ኪዳን ተስፋ የተሞሉ ናቸውና ሊጠቀሱ ይችላሉ።

እንግዲህ የጽዮን ትርጉም ይህን ሲመስል ከዚህ ውጪ በተናጠል ለማርያም ተሰጥቶ ሊተረጎም አይችልም። ሰዎች ይመስልልናል ብለው ከሚጠቅሷቸው "ሰው እናታችን ጽዮን ይላል። በውስጧም ሰው ተወለደ" የሚለው ይገኝበታል። በአንድምታቸው መሠረት ጽዮን→ድንግል ማርያም÷ እናታችን ጽዮን ብሎ የሚጠራው ሰው→ምእመን÷ በውስጧ ተወለደ የተባለው ሰው→ኢየሱስ ክርስቶስ

ነው ይላሉ። እዚሁ ላይ ብቻ ለቆመ ሰው ነገሩ እውነት ይመስላል። በጽዮን ውስጥ ተወለደ የተባለው ሰው ግን አንድ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ናቸው። ቁ. 6 ና 7ን ስንመለከት ብዙ አለቆች እንደተወለዱ ይናገራልና ለዚህ ደግሞ ምን ትርጉም ይሰጠው ይሆን? ነው ወይስ ሌላ ችግር እንዳያመጣ ተድበስብሶ ይታለፋል?

ቃሉ በጽዮን ከተማ ውስጥ ስለመወለድ እንጂ ጽዮን ከተባለች ሴት መወለድን አያሳይም፤ እንዲያማ ቢሆን "በውስጧም ሰው ተወለደ" በማለት ፈንታ "ከእርሷ ሰው ተወለደ" መባል በተገባው ነበር። ስለዚህ የቃሉ አመልካችነት በምድራዊቷ ጽዮን ከተማ ውስጥ ዜጎቿ መወለዳቸው ሲሆን ከቁ. 3-4 ባለው ክፍል እንደተገለጸው በሰማያዊቷ ጽዮን ውስጥ በዳግም ልደት እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ ረዓባውያን÷ ባቢሎናውያን÷ ፍልስጥኤማውያን÷ ጢሮሳውያን÷ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ታስበው በውስጧ እንደሚወለዱ ጭምር ነው። ሰማያዊቷን ጽዮንንም እናታችን ብለው ይጠራሉ። (ገላ. 4÷26፤ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁ. 12)

በአጠቃላይ መዝ. 86ን አስተውሎ ላነበበው ሰው ስለጽዮን ከተማ እንጂ ስለድንግል ማርያም አይናገርም። እንደዚሁም ሁሉ የኢሳ. 60÷14 ክፍል የሚገልጸው ወደ ባቢሎን የተማረኩት የይሁዳ ሰዎች ከምርኮ በመመለስ የሚጽናኑበት ዘመን እንደሚመጣ÷ የማረኳቸውና አስጨንቀው ለሰባ ዓመታት የገዙአቸው አሕዛብ አንገታቸውን ደፍተው እስራኤላውያንን ወደ ማክበር እንደሚመለሱ÷ ጽዮንም ተመልሳ እንደምትታነጽ የሚገልጽ ነው። (ከቁ. 10 ጀምሮ ተመልከት)

እግዚአብሔር "እጄን ወደ አሕዛብ አነሣለሁ ዓላማዬንም ወደወገኖች አቆማለሁ። ወንዶች ልጆችሽንም በብብታቸው ያመጧቸዋል። ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሟቸዋል።" (ኢሳ. 49÷22) ብሎ እንደተናገረው ከአሕዛብ ወገን የፋርስ ንጉሥ ቂሮስን አስነሥቶ በወገኖቹ ላይ ያቆመውን ወደ ስፍራቸው የመመለስና እንደገና የመሥራት ዓላማውን ተግባራዊ አድርጓል። (ኢሳ. 44÷28፤ 45÷1-3፤ 13፤ ዕዝ. 1÷1-4፤ 7-8)

ይህን እውነት ወደ ጎን ጥሎ ትንቢቱ ድንግል ማርያምን የሚንቁ እንደሚነሡና በይቅርታ ወደ እርሷ እንደሚመለሱ የተነገረ ትንቢት አስመስሎ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም። በመሠረቱ ደግሞ በክርስቶስ አዳኝነት አምኖ እግዚአብሔርን ዐውቃለሁ የሚል ሁሉ

እንኳን አምላክን በሥጋ የወለደችውን ድንግል ማርያምን ይቅርና በሰው ፊት አናሳ የሆነውን ሰው ይንቅ ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል አይፈቅድለትም። (ማቴ. 5÷22፤ 18÷10)

ነገር ግን ለስሕተት ትምህርቶች ሕጋዊነትን ለመስጠት ሲባል ትርጉም እያበላሹ ድንግል ማርያም ያልሆነችውን ሆነች ያልሠራችውን ሠራች ማለት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስለሚቃረን "ይህ ትክክለኛ አይደለም" ብሎ የተሳሳተውን አተረጓጎም መቃወም እሷን እንደመቃወም ተደርጎ መቆጠር የለበትም።

# የመጻተኞችና የጃንደረቦች መታሰቢያ

"እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና :- በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ" (ኢሳ. 56÷4-5)

ቅዱሳንን በተገቢው መንገድ ለማክበር ነው በሚል ሽፋን ወደ አምልኮ ባዕድ እየተጓዘች የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫዋ በመመለስ ፈንታ ለተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች ይህን የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል እንደማስረጃ በማቅረብ የእስካሁኑ እንኳ እንዳይበቃ ሌላ ረጅም ዕድሜ እየተጨመረላቸው ይገኛል።

ለሞቱ ቅዱሳን በመታሰቢያ ስም ብዙ ብዙ ነገሮች እንደተካሄዱና አሁንም እየተካሄዱ እንዳለ ሁሉም ያውቀዋል። ለዚህ እንግዳ ትምህርት ድጋፍ ይሆን ዘንድ የሚጠቀሰው ኢሳ. 56÷4-5 የተነገረው ስለመጻተኞችና ስለጃንደረቦች መሆኑን በቅድሚያ ማወቁ የአንዱን ለሌላ ከመስጠትና በእውነት ስም ቆሞ ሐሰትን ከመናገር ያድናል።

መጻተኛ ማለት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አገሬ የሚለውን ምድር ትቶ በምድረ እስራኤል የሚኖር÷ እስራኤላዊ ዝርያ የሌለው የሌላ አገር ተወላጅ ሲሆን ጃንደረባ ደግሞ የጾታ መለያ አካሉ የተቆረጠበት ወይም የተኰላበት እስራኤላዊ ወይም የእስራኤላዊነት መብት የተሰጠው ማለት ነው። ጃንደረባ ሌላም ሁለተኛ ፍቺ እንዳለው ይታወቃል ይኸውም ከፍ ባለ ማዕረግ የሚገኝ ጠባቂ ማለት ነው። (ዘፍ. 39÷1፤ 8፤ አስቴ. 1÷10) በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ግን በመጀመሪያው ትርጉም የሚገኘውን ጃንደረባ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለነዚህ መጻተኞችና ጃንደረቦች የተደነገጉ ሕገጋት ነበሩ። መጻተኛ የሆነ ሰው ለፋሲካ መታሰቢያ በዓል የሚዘጋጀውን መብል እንዳይበላ ÷ ወደ መቅደስ እንዳይገባ÷ ንጉሥ ሆኖ እንዳይሾም÷ በጋብቻ ከእስራኤል ጋር እንዳይቀላቀል ይከለከል ነበር። (ዘጸ. 12÷43፤ 45፤ ሕዝ. 44÷9፤ ዘዳ. 17÷15፤ 34÷12-16)

ጃንደረባ ደግሞ እንደነውረኛ ተቆጥሮ የተቀደሰን ነገር እንዳያቀርብና ወደ እግዚአብሔር ጉባኤም እንዳይገባ ሕጉ ደንግጓል። (ዘሌዋ. 21፥10፤ ዘዳ. 21፥1)

ነገር ግን እግዚአብሔር መጻተኞች ወደ እርሱ ለመጠጋት ቢፈልጉ÷ ለእስራኤል የቃል ኪዳኑ ምልክት አድርጎ የሰጠውን ሰንበት ቢያከብሩ÷ እግዚአብሔርን ቢወድዱና እርሱን ለማገልገል ራሳቸውን አሳልፈው ቢሰጡት እንዲህ ያሉትን መጻተኞች ሕዝቤ ከሚላቸው ከእስራኤል ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለይቶ እንደማያያቸው÷ በጸሎት ቤቱም ደስ እንደሚያሰኛቸውና የሚያቀርቡለትን መሥዋዕት እንደሚቀበላቸው ቃል ሲገባ በቃሉ ውስጥ ይነበባል። (ቁ. 3፤6-7)

በተመሳሳይ ሁኔታ ስለጃንደረቦችም ሰንበቱን ቢጠብቁና ደስ የሚሰኝበትን ነገር ቢመርጡ በቤቱና በቅጥሩ ውስጥ ለሕዝቡ ከሰጠው ስምና መታሰቢያ የሚበልጥ የዘላለም ስም እንደሚሰጣቸው ተናግሯል። (ቁ. 4-5)

በመሆኑም እግዚአብሔር ለብዙ መጻተኞችና ጃንደረቦች በሕዝቡ መካከልና በቤቱ ውስጥ ዘላለማዊ ስምና መታሰቢያ ሲሰጣቸው እንመለከታለን፤ በምሳሌነት ከመጻተኞች ሩትን ከጃንደረቦች ደግሞ ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን መጥቀስ ይቻላል።

ሩት የገዛ ምድሯን ሞዓብንና ወገኖቿን ሞዓባውያንን ትታ "ወደ ምትሄጂበት እሄዳለሁና÷ በምታድሪበትም አድራለሁና÷ እንድተውሽ ÷ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ÷ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል። በምትሞችበትም ስፍራ እሞታለሁ፤ በዚያም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ፤ እንዲሁም ይጨምርብኝ።" (ሩት 1÷16-17) በማለት አማቷን ኑኃሚንን ተከትላ ወደ እስራኤል አምላክ በመጠጋቷ እሱ ከሕዝቡ ሳይለያት ተቀብሎ በማክበር የንጉሥ ዳዊትን አያት ኢዮቤድን በመውለድ በክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ እስከመግባት የሚያደርስ ክብር በመስጠት ስሟና ታሪኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲሰፍርና ለዘላለም እንድትታሰብ አደረገ። (ሩት 4÷13-22፤ ማቴ. 1÷5)

ጃንደረባው አቤሜሌክም ወደ እስራኤል አምላክና ወደ ሕዝቡ ተጠግቶ በንጉሡ በሴዴቅያስ ቤተ መንግሥት ያገለግል በነበረበት ጊዜ

ለእግዚአብሔር ነቢይ ለኤርምያስ መልካም ነገርን ያደረገ÷ ሕይወቱን ከጥፋት በማዳን የእግዚአብሔርን ሥራ የሠራ የእግዚአብሔር ሰው ነበር። ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ስትጠፋና ሕዝቡ ተማርኮ ለጉስቁልናና ለታላቅ ጥፋት ሲዳረግ አቤሜሌክ ግን እግዚአብሔር በኤርምያስ በኩል በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት ከጥፋቱ ተሰውሮ ነበር። በወቅቱ የነበሩ ብዙ እስራኤላውያን ዝክረ ስማቸው እንኳ እስታዋሽ አጠቶ ሲደመሰስ የአቤሜሌክ ስም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶት እየታሰበ ይኖራል። (ኤር. 38÷7-13፤ 39÷15-18)

ለመጻተኛዋ ሩትና ለጃንደረባው አቤሜሌክ መታሰቢያና ለዘላለም የማይጠፋ ስም የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህን ራሱ ከሚያደርግ በቀር "ፈቃዴን ለሚፈጽሙ መጻተኞችና ጃንደረቦች ለመታሰቢያቸው እንዲሆን ይህንና ያንን በስማቸው አደርጉላቸው" በማለት ማንንም አላዘዘም።

ደግሞም በመጻተኞችና በጃንደረቦች ላይ ተደርጎ የነበረው ሕግ የሚሠራው በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ እንጂ በዐዲስ ኪዳን እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እግዚአብሔር "ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል" (ኢሳ. 56÷7) ባለው መሠረት ምንም ዓይነት የዘር÷ የቀለምና የአካል ልዩነት ሳይደረግ አይሁዳዊውንና አረማዊውን በሙሉ የክርስቶስ አካል በሆነችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን በማጠቃለል በፊት የነበረውን ልዩነት ጨርሶ ደምስሷል። (ኤፌ. 2÷11-22፤ 3÷1-6፤ ገላ. 3÷28)

ቃሉን በትክክል አንብበው ሳያጤኑ ለመናገር የሚቸኩሉና የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን ለግል አመለካከታቸው ደጋፊ እንዲሆን የሚጠቅሱት ወገኖች ይህ የኢሳ. 56 ክፍል ለቅዱሳን ሁሉና በስማቸው የተለያዩ መታሰቢያዎችን እንድናደርግላቸው የሚናገር ነው ሲሉ ጥቂት እንኳን ቅር አይላቸውም።

ቃሉ የሚናገርላቸውን ክፍሎች ይዘን በእነርሱ አተረጓጎም እንሂድ ቢባል እንኳ ከቃሉ አንጻር እስራኤላዊ ዝርያ ያላቸው ቅዱሳን ለምሳሌ:- ድንግል ማርያም÷ ቅ/ጳውሎስና ቅ/ጴጥሮስ በዚህ ውስጥ ተሳታፊነት አይኖራቸውም። እነርሱ መጻተኞች ወይም ጃንደረቦች

አይደሉምና። ታዲያ ለእነርሱ ሁሉ እንደተነገረ አድርገው በጅምላው ለምን ይጠቅሳሉ?

እግዚአብሔር ያዘዘው ስንት ነገር እያለ እሱ ሥሩ ያላለውንና ራሱ የሚሠራውን እኛ ካልሠራን በሚል አጉል ታዛዥ መስሎ መቅረቡ ራስን ማታለል ነውና በሐሰትና በማስመሰል የእግዚአብሔርን ቃል ተገን አድርጎ ተገቢ ያልሆነ ሥራን ለመሥራት ራስን አሳልፎ ከመስጠት ለአፍታም ቢሆን ቆም ማለትና እግዚአብሔር የሚለውን ሰምቶ መታዘዝ በጌታ ፊት ትክክለኛ ነገር ነው። (ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁ. 16)

# የቀደመችው መንገድ

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ በመንገድ ላይ ቁሙ፤ ተመልከቱም። የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርሷም ላይ ሂዱ፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ።" (ኤር. 6÷16)

ይህን ጥቅስ ራስ ወዳዶችና ሌላውን ከራሳቸው አሳንሰው የመመልከት ስሜት ያላቸው ብልጣ ብልጦች ስለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደተነገረ ትንቢት አድርገው ይጠቅሳሉ።

መንገድ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ነገሮች ተገልጸውበታል መንገድ ሰው ወደሚፈልገው ስፍራ ለመድረስ የሚሄድበት (የሚጓዝበት) ነው። ስለዚህ ሰውም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ከፈለገ ወደ እርሱ ሊያደርሰው በሚችል መንገድ ብቻ መጓዝ አለበት።

የመንገድ መንፈሳዊ ትርጉም የተለያየ ሲሆን በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት መኖርን ያመለክታል. (ዘጸ. 32÷ 8፤ ዘዳ. 5÷33)

ወደ ሕይወት የሚያደርስ የእግዚአብሔር መንገድ እንዳለ ሁሉ ወደ ጥፋት የሚወስድ የክፉዎች መንገድ ደግሞ አለ። (መዝ. 1÷1-6፤ ምሳ. 14÷12፤ 16÷25፤ ማቴ. 7÷13-14)

ሌሎች የሕይወት መንገድን ስያሜ የወሰዱትን ሁሉ ሊወክል የሚችል ትክክለኛ መንገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ. 14÷6)

የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም (የክርስትና ሃይማኖት) መንገድ ተብላ ተጠርታለች። (የሐዋ. ሥራ 9÷ 2፤ 19÷ 9፤ 23፤ 22÷ 4)

በኤር. 6÷ 16 መሠረት ሳይሆን በዚህ በመጨረሻው ስያሜ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች መንገድ ልትባል ትችላለች።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ካሳለፈችው የረጅም ዘመናት ጉዞ አንጻር ይዛው የነበረው እውነተኛ ትምህርት ተቀብሮ ከጊዜ በኋላ በተፈጠሩ ብዙ የስሕተት ትምህርቶች ብትጠላለፍም ቤተ ክርስቲያን ሊያሰኙአት የሚችሉትን ነገሮች እየተንገታገተችም ቢሆን ይዛለች። ከሚጠቀሱላት ውስጥ:-

- እግዚአብሔር ሦስትነት ያለው አንድ አምላክ መሆኑን ታምናለች።
- ቃልና ሥጋ የተዋሐዱበትን መንገድ ለማብራራት የተደከመበትና ዋናው የመዳን ምስጢር ያልተተኮረበት ቢሆንም የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆንና አዳኝነቱን (የሌሎችንም አዳኝነት ደምራበት) ታምናለች፤ ታስተምራለች።
- የጥምቀትና የቁርባን ሥርዓት አላት።
- የአተረጎጓም ችግር ቢኖርም መጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች መጻሕፍትን ጨማምራበት ትቀበላለች።

በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አንዳንድ አባላት ዘንድ ግን ጎልቶ ከሚታየው ስሕተቷ አንጻር "ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነች" ከማለት ይልቅ የአይሁድ ምኩራብ ወይም ከክርስትና ውጪ የሆነች ሌላ ሃይማኖታዊ ድርጅት ትመስላቸዋለች፤ ተብላለችም። ይህ ግን ትክክል አይደለም።

መድኅነ ዓለም ክርስቶስ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለእርሷ ራሱን አሳልፎ በመስጠት እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችውን አንዲት ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ቢፈልግም (ኤፌ. 5፡26-27) ቤተ ክርስቲያን ግን ባለፈችባቸው መንፈሳዊ ጉዞዎቹ ውስጥ ጌታ እንደሚፈልገው ብቻ ሆና ከዚህ ደርሳለች ለማለት አይቻልም። በቅድስናና በተጋድሎ ውስጥ እንዳለፈች ሁሉ በብዙ ችግሮችና በርኩሰቶች ውስጥም አልፋለች። በዚህ ጊዜ ጌታ መልእክተኞቹን በመላክ ስሕተቶቿን አስተካክላ እንድትቀደስ ለቤተ ክርስቲያን ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹት የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑት አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለዚህ በቂ ማስረጃ ይሆኑናል።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩባት ችግሮችና ርኩሰቶች መካከል ክርክር፥ መለያየት፥ ሙግትና በአሕዛብ ዘንድ እንኳ ያልተደረገ ዝሙት በዋናነት ይጠቀሳሉ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያቋቋመው ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ መልእክት በመጻፍ ራሷን እንድታስተካክልና በንስሓ እንድትታደስ አድርጓል። (1ቆሮ. 1፥ 11፤ 1፥ 17፤ 6፥ 1፤ 5፥ 1፤ 2ቆሮ. 7፥ 5-16)

የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲሁ ከወንጌልና ከእግዚአብሔር ጸጋ ፈቀቅ ብለው ወደ አሪቱ ሥርዓት በመመለስ ታላቅ ስሕተት ውስጥ ገብተው ነበር። (ገላ. 1፥ 6-9) በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ወደ አሪት ሥርዓት የተመለሱትን እንደገና ወደ ክርስቶስ መልሶ ለማምጣት የማማጥን ያህል አስቸጋሪነት ያለው መሆኑን ሐዋርያው ሳይጠቅስ አላለፈም። (ገላ. 4፥ 19) ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ያለው ከፊል አሪታዊ ሥርዓት የተሰቀለው ክርስቶስ በምእመናን ልብ እንዳይሣል ዕንቅፋት የሆነ ግዙፍ ተራራ ነው። በአንድ ወገን የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትና የኛዋ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተመሳሳይ ገጽታ አላቸው።

በሌላም በኩል በራእየ ዮሐንስ ለተገለጹት ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት የተላለፈው መልእክት የዚያን ዘመን የቤተ ክርስቲያን ደካማና ብርቱ ጎን ያሳያል። ከሰባቱ መካከል ሁለቱ ብቻ ነቀፌታ አልተሰነዘረባቸውም። የተቀሩት አምስቱ ግን የተለያየ አስጸያፊና አስነዋሪ ኃጢአት የተፈጸመባቸው ናቸው። (ራእ. 2፥ 1-3፤ 22)

ለምሳሌ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ታላቁን ነገር ፍቅርን የጣለች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። (ራእ. 2፥ 4) የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሰይጣን ዙፋኑን የዘረጋባት፥ አምልኮተ ጣዖት የተደባለቀባት ሴሰኝነት የተስፋፋባት ነበረች። (ራእ. 2፥ 13-15) የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ነበሩባት። (ራእ. 2፥ 20)

የሚያስደንቀው ግን በፍቅር ጌታ ዘንድ እንዲህ ያለ ርኩሰትን የተሞሉት አብያተ ክርስቲያናት ካልተነቀፉቱ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በእኩል ዐይን የታዩበት ሁኔታ አለ። ሰባቱም ልዩነት ሳይደረግባቸው ጌታ በመካከላቸው የሚመላለስባቸው የወርቅ መቅረዞች ሲሰኙ መላእክቶቻቸውም (መሪዎቻቸውም) በጌታ ቀኝ እጅ የተያዙ ሰባቱ ከዋክብት ተሰኝተዋል። (ራእ. 1፥ 20) ይሁን እንጂ አምስቱ ንስሓ

መግባት ይጠበቅባቸዋል። አሊያ ግን የጌታ ፍርድ ወደ እያንዳንዳቸው ይመጣባቸዋል። (ራእ. 2፥ 5፤ 16፤ 3፥ 19)

ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን ሊያሰኟት የሚችሉትን ነገሮች ያሟሉና ልዩ ልዩ ስሕተቶች ያሉባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሞልተዋል። ሆኖም በመሠረታዊ እውነቶቻቸው ላይ ስሕተቶች ስላሉባቸው ብቻ ቤተ ክርስቲያን መባላቸው አይቀርም፤ ንስሐ ገብተው ካልተስተካከሉ ግን ከፍርድ በታች ይሆናሉ።

ኦርቶዶክስም ቤተ ክርስቲያን ሊያሰኙአት የሚችሉትን መሠረታዊ እውነቶች ይዛ በመገኘቷ ቤተ ክርስቲያን መባሏ ባይቀርም ካሁን በፊት እንዳየነው የምትነቀፍባቸው ብዙ ስሕተቶች አሉባት። ስሕተቶቿን አስተካክላ ወደ ትክክለኛነቷ እንዳትመለስ ግን ከራሷም ከውጪም ብዙ ችግሮች አሉባት።

የራሷ ችግር በቃለ እግዚአብሔር ወልዳ ያሳደገቻቸው ልጆቿ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ላይ ቆመው የተቀበረ እውነቷን ይዘው የምትነቀፍባቸውን ስሕተቶቿን ሊያስተካክሉላት ሲነሡ ሌላ ስም እየለጠፈችባቸው በማሳደድ ብዙ ግፍ ትፈጽምባቸዋለች። እንደያኔዋ ኢየሩሳሌም ለሰላሟ የሚሆነውን አላወቀችም፤ ከዐይኖቿም ተሰውሮአል። (ሉቃ. 19፥ 12)

ከውጪ ያለባት ችግር ደግሞ ከስሕተቷ ሌላ በእምነት ላይ ምንም ችግር የማያመጣውን ባህሏንና ሥርዓቷን መውረርና የወንጌልን እውነት የተረዱ ምእመናንንና አገልጋዮቿን ማፍለስ ጥቂቶቹ ናቸው።

በውስጥ ያሉና ይህን ማንነቷን በዚህ መልክ ያልተረዱ ሰዎች ስሕተቷን ሁሉ እንደትክክለኛ ነገር በመቁጠርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ እንዲኖረው የእግዚአብሔርን ቃል ያለቦታው በመጥቀስ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በስተቀር ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው አድርገው ያስባሉ። ኦርቶዶክስን በፊት አስቀድመው ሌሎቹን ኋላ ለማስቀረት ሲሉ ኤር. 6፥ 16ን እየጠቀሱ:- "የቀደመችውና እግዚአብሔር ሂዳባት ያላት መንገድ ኦርቶዶክስ ብቻ ናት" ይላሉ። እውን በእግዚአብሔር የምትታወቅ ኦርቶዶክስ ብቻ ናትን? ይህ ቤተ ክርስቲያን ከሕንፃ ያለፈ ትርጉም እንዳላት ከማያስቡ ጠባቦች የመነጨ አመለካከት ነው።

እንደ ኦርቶዶክስ ሁሉ ሌሎቹም አብያተ ክርስቲያናት "ኦርቶዶክስን ትክክል አይደለችም፤ በእግዚአብሔርም አትታወቅም፤በእግዚአብሔር የምንታወቅ እኛ ብቻ ነን።" ቢሉ በጣም ስሕተተኞች ናቸው። የትም እንሁን የት እግዚአብሔር እኛን የሚያውቀን በድርጅታችን ስም ሳይሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም አምነን በክርስቶስ ደም ታትመን እንደ ቃሉ በመኖራችን ነው።

ሁሉም የእኔ ከሚለው ዶክትሪንና ሥርዓት ባሻገር አንድ ሊያደርገው የሚችል እውነት ከላይ የተገለጸው ነው። ይህን የሚያምኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አላቸው። እርስ በርሳቸውም ኅብረት ሊኖራቸው ይገባል። (1ዮሐ. 1÷2-4) የእግዚአብሔርን ሦስትነት ጠቅልለው አንድነቱን ከፋፍለው የሚያበላልጡ÷ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና ሰውነት የሚክዱ÷ መንፈስ ቅዱስን ሕፁዕ የሚሉ ግን ከእግዚአብሔርም ሆነ ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረት የላቸውም። (1ዮሐ. 2÷18-25)

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ስብስብ ናት። ይህን ማንነቷን ሲገልጽ ሊቁ ሳዊሮስ:- "ወበስብከቶሙ ለሐዋርያት ይከውኑ ኵሎሙ አብያተ ክርስቲያናት ወኵሎሙ መሃይምናን አሐተ ቤተ ክርስቲያነ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ቅዱሳን እንተ አስተጋብእዋ እምኵሎሙ አሕዛብ ወተቀደሰት በመንፈስ ቅዱስ።"

ትርጓሜ:- "በሐዋርያት ስብከት አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን ሁሉ አንዲት ሐዋርያዊት ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ይሆናሉ። እርስዋ ከአሕዛብ ሁሉ የተሰበሰበች በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰች የቅዱሳን ሐዋርያት ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ናትና።" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 126)

ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ እውነት እንጂ የዕድሜ ርዝማኔ ብቻውን የትክክለኛነት መለኪያ ወይም የጀማሪነት ምልክት ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። ትክክለኛነት በዕድሜ ርዝማኔ የሚለካ ከሆነማ የኤር. 6÷16 የተስፋ ቃል ባለቤት የሆኑት የአይሁድ እምነት ይሁዲነት ይቀድማልና የቀደመችው መንገድ ይሁዲነት ናት ብለን ይሁዲዎች እንሁን ማለት ነው። ነገር ግን ማንም

ይህ ትንቢታዊ ቃል ስለእኔ ሃይማኖት የተነገረ ነው በማለት ራሱን ያሳያል።

የኤር. 6፥16 ትንቢታዊ ቃል ላስተዋለው ከአንድ ሃይማኖታዊ ድርጅት ይልቅ ወደ አብ የሚያደርሰውን መንገድ ያሳያል። (ዮሐ. 14፥6)

እግዚአብሔር ልጁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አስቀድሞ ሁሉ ወደ ራሱ እንዲመጣ ያዘጋጀው ብቸኛ መንገድ ነው። (የሐዋ. ሥራ 3፥19-20) በእርሱ መንገድነት ላይ መሄድ ወደ ዕረፍት ያደርሳል። (ማቴ. 11፥28) እግዚአብሔር ግን ሁሉን አስቀድሞ አይቷልና "እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ" ብሎ እንደተናገረው በእርሱ ለማመን ብዙዎች ፈቃደኞች አልነበሩም፤ ዛሬም አይደሉም። (ዮሐ. 1፥11፤ 12፤ 37-43፤ 15፥18-24)

በወቅቱ ጌታ እንቢተኞች ለሆኑት አይሁድ ". . . ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደኔ ልትመጡ አትወዱም" በማለት ተናግሯል። (ዮሐ. 5፥40)

እንግዲህ ቃሉ በአንድምታ ጋጋታና በራስ ወዳድነት ለሌላ የሚተርፍ ትርጉም የለውም። በውስጡ የተገለጸው ሁሉ አንድ በአንድ የተከናወነበት የቀደመው መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

"ኮነ ወልድ ዕጓለ እመሕያው ዘበአማን ወውእቱ ፍኖት ዘይመርሐነ ኀበ አቡሁ ቅዱስ።"

ትርጓሜ:- "እርሱም በእውነት ሰው የሆነ ወደ ቅዱስ አባቱ የሚመራን መንገድ ነው።" (ሃይ አበ. ም. 49 ክፍል 11 ቁ. 37)

## ፍጻሜን ያገኘው ሕግ

"እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።" (ማቴ. 5÷ 17)

ወደ ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የገባው የአይሁድ ባህልና ሃይማኖታዊ ሥርዓት በክርስትናው ዘመንም ሊቀር ባለመቻሉ የክርስትናውን ውበት ጉራማይሌ አድርጎታል።

ሃይማኖት በሰው አስተሳሰብ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው። ከዚህ የተነሣ ሰው የያዘው ሃይማኖት የተሳሳተ ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር እውነቱን አብርቶ ትክክለኛውን አሳይቶ በጥበቡ ካልመለሰው በቀር ከነከንቱ ሃይማኖቱ ይሞታል። ሌላው ደግሞ ትክክለኛውን የማወቅ ዕድል ቢገጥመውም "ሌላ መስማት አልሻም" በሚል ጠባብነት ስለሚያዝ በልቡ እልከኝነት ይጸናል። (ዕብ. 3÷7-12)

አይሁድ ለዚህ ተጠቃሽ ይሆናሉ። ሃይማኖታቸው በዘመን ርዝማኔ÷ ባሳለፈው ታሪክ÷ ሕዝቡ በተለያዩ ጊዜያት በፈጸሟቸው ስሕተቶች ከደረሰባቸው ምርኮና ፍልሰት አንጻር ቅርጹና ይዘቱ የተለያየ ለመሆን ቢገደድም ምንጩ ግን ከእግዚአብሔር እውነት የፈለቀ ነው።

የሚገርመው ግን የኦሪትን ጊዜያዊነት በመጽሐፋቸው ተጽፎ እያነበቡና ልባቸውም እያወቀው የኦሪት ፍጻሜ የሆነውን ክርስቶስንና እርሱ የመሠረተውን ክርስትና አምኖ መቀበል ሃይማኖትን የመለወጥ ያህል መቁጠራቸው ነው። ስለሆነም ሕጋችንን ሻረ ሃይማኖታችንን ለወጠ በሚል ክስ እስከ ሞት አድርሰውታል። (ሉቃ. 23÷2) ተከታዮቹንም በተመሳሳይ ሁኔታ በመቃወምና ክርስትናንም በመንቀፍ እስከ ሞት ድረስ አሳደዋቸዋል። (የሐዋ. ሥራ 24÷5፤ 14፤ 1ተሰ. 2÷14-16)

አይሁድን የተጠናወታቸው የአክራሪነት መንፈስ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን መዳን እንዳያዩ ልባቸውን አጨልሟልና ዛሬም እነሆ የአገልግሎት ዘመኑ በተፈጸመው የኦሪት ሥርዓት ውስጥ ይገኛሉ።

ቤተ ክርስቲያናችን እንደ አይሁድ ክርስትናን አልቀበልም ሳትል የተቀበለች ብትሆንም ከአይሁድ ሕግና ባህል ጋር በመደባለቅ ነው። ይህም በክርስትና እምነቷ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮባታል። ክርስትናዋ ሲታይም ባለቤት (ባለዘመን) ሳይሆን የኦሪት ጥገኛ ነው የሚመስለው። ሁኔታውም ብዙዎችን አደንዝዞ ሙሉ በሙሉ ወደ ጌታ ዘወር እንዳይሉ መጋረጃ ሆኖ ሸፍኖአቸዋል። (2ቆሮ. 3÷14-16)

ከፊል ሥርዓተ ኦሪቱና ክርስትናው ተቀላቅሎ የሚደረገው መንፈሳዊ ጉዞ ትክክል እንደሆነ የሚያስቡ አልታጡም። ለዚህም እንዲረዳቸው ማቴ. 5÷17ን ይጠቅሳሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 5÷17 የገለጸው በሕግ ማለትም በሙሴ መጻሕፍትና በነቢያት መጻሕፍት የተነገሩትን ትንቢቶችና የተመሰሉትን ምሳሌዎች ለመፈጸም እንጂ ለመሻር እንዳልመጣ ነው። ሕግና ነቢያት ስለክርስቶስ ይመሰክራሉና። (ሉቃ. 24÷25-27፤ 44-47፤ ዮሐ. 5÷39፤ 46፤ የሐዋ. ሥራ 3÷21-24)

በሕግና በነቢያት ከተነገሩት ትንቢቶች መካከል ነገረ ሞቱን ለማስቀረት ጴጥሮስ ". . አይሁንብህ ጌታ ሆይ! ከቶ አይድረስብህ" እያለ ባከላከለው ጊዜ "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል" ሲል ሕግና ነቢያት የተናገሩትን ቃል ለማስተሐቀር ወይም ለመሻር ያቀደውን ጠላት ገሥጾታል። (ማቴ. 16÷ 22-23)

እያንዳንዱ የኦሪት ነገር ሁሉ በተገቢውና በታቀደለት መንገድ በክርስቶስ ፍጻሜን አግኝቷል። ፍጻሜ ማግኘት ማለት ግን የተሻረ መሆን ማለት አይደለም። ለምሳሌ አንድ ባለሥልጣን የተወሰነለትን የአገልግሎት ዘመኑን ሳይፈጽም በመሀል ከሥልጣኑ ቢወገድ ተሻረ እንጂ የሥልጣን ዘመኑን ፈጽሞ በሌላ ተተካ እንደማይባል ሁሉ ኦሪትም በእግዚአብሔር የተወሰነላትን የአገልግሎት ዘመን ሳትፈጽም ስፍራዋን ለዐዲስ ኪዳን አገልግሎት አልለቀቀችም። ይህ ቢሆን ኖሮ ተሻረች ሊባል በተገባ ነበር፤ ስለዚህ አሁን ተፈጸመች እንጂ ተሻረች አትባልም።

በሌላም በኩል አንድ የቀድሞ ባለሥልጣን የሥልጣን ዘመኑን ፈጽሞ ሥልጣኑን ለሌላ ከለቀቀ በኋላ ምንም እንኳ የቀድሞ ባለሥልጣን ቢሆን አሁን በቦታው ሌላ ተተክቷልና የሥልጣን ሥራውን ሊሠራ አይችልም። ሥልጣኑን ለሌላ ካስረከበ በኋላ ሕጋዊ

ስላልሆነ ባለጉዳዮች በቀድሞ ባለሥልጣንነቱ ተመልክተው ጉዳያቸውን ይዘው ወደ እርሱ አይሄዱም። አሁን በሥልጣን ላይ ወዳለው ባለሥልጣን እንጂ።

የኦሪትም የሥልጣን ዘመን እንደዚሁ አብቅቶ በወንጌል ተተክቷል። ስለዚህ አሁን ወደ ኦሪት አገልግሎት መሄድ ማለት ሥልጣኑን ወደ አስረከበ ባለሥልጣን ጉዳይን ይዞ እንደመሄድ ይቆጠራል።

በኦሪት ዘመን የነበሩትን ሕጎችና ሥርዓቶች በዐዲስ ኪዳን አፈጻጸማቸው የጸኑ፥ የተተኩና የተሻሩ (የቀሩ) ተብሎ በሦስት ሊከፈል ይችላል። በምሳሌነት ጥቂቱን እንመልከት:-

ሀ. የጸኑት:- አሥሩና ሌሎችም መሰል ትእዛዛት፤ (ማቴ. 5፥21-37፤ 19፥18-19፤ ሮሜ. 3፥31)
ለ. የተተኩት:- የድንጋይ ጽላት በልብ ጽላት፤ (ኤር. 3፥16፤ 31፥31-34፤ ሕዝ. 11፥19-20፤ 36፥26-27፤ 2ቆሮ. 3፥3፤ ዕብ. 8፥6-13)
- የእንስሳት መሥዋዕት በክርስቶስ መሥዋዕትነት፤ (ዕብ. 9፥11-14፤ 10፥11-14)
- ግዝረት በጥምቀት፤ (ማር. 16፥16፤ ገላ. 5፥6፤ ቈላ. 2፥11-13)
ሐ. የተሻሩት (የቀሩት) ስለመብል "ይህን ብሉ ይህን አትብሉ።" የሚለው፤ (ማር. 7፥18-19፤ ሮሜ. 14፥3፤ 14፤1ቆሮ. 6፥12፤ 10፥23-26፤ ቈላ. 2፥16)
- በቈላ. 2፥16-23 የተጻፉት ስለ በዓላት እንዲሁም አትያዝ፥ አትንካ፥ አትቅመስ . . . የሚሉት ትእዛዛት።

በአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ግራኝ መሐመድ አገሪቱን በወረረ ጊዜ ለእርዳታ ከፖርቱጋል ወታደሮች ጋር አብረው የመጡ ኢየሱሳውያን ሕዝባችን በአምልኮቱና በአኗኗሩ ዙሪያ የሚፈጽማቸውን ኦሪታዊ ሥርዓቶችንና ወጎችን በመመልከት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኦሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም በማለት ለያዙት አቋም ንጉሡ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ እምነት የሚያስረዳ ጽሑፍ አሠራጭተው ነበር። ይህም "የአፄ ገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ" በመባል ይታወቃል። በሃይማኖት ውሳኔው ውስጥ ከተዘረዘሩት መካከል ስለመብል ጉዳይ የተገለጸው እንዲህ ይላል :- ". . . አሳማንም ስለመብላት:- ከመብላት

የተከለከልነው እንደ አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም። የሚበላውንም አንጸየፈውም፤ አናረክሰውም። የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም። አባታችን ጳውሎስ ለሮም ሰዎች እንደጻፈው "የሚበላ የማይበላን አይንቀፈው። እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና። የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው። ለሰው ክፉው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው" (ሮሜ 14÷3፤ 17፤ ቲቶ 2÷15፤ 1ቆሮ. 8÷9-13) ወንጌላዊው ማቴዎስም "ካፉ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክስ የለም። ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል። ይፈሳል። ምግቦችን ሁሉ ያነጻል።" አለ (ማቴ. 15÷11፤ ማር. 7÷19) ይህ አባባሉ ከኦሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስሕተት ሕንፃ ሁሉ አፈረሰው። <u>የኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ በትእዛዜ የሚያስተምሩ አዋቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው። ከወንጌል ትምህርት ከጳውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደግራ አይሉም</u>. . . . ስለእንስሳት ሥጋ መብል በዐዲሲቷ መጽሐፍ ውስጥ (በዐዲስ ኪዳን) ሕግም ቀኖናም የለም።" (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአቡነ ጎርጎርዮስ ገጽ 180 - 181)

መብል ጠቀሜታም ሆነ ጉዳት እንደሌለው ቢታወቅም በዐዲስ ኪዳን የተቀመጠው እውነትና ይህ የሃይማኖት ውሳኔ በቤተ ክርስቲያናችን ተግባራዊ ስላልሆነ መነቃቀፍና መፈራረድ መጸየፍ ይታያል። ይህም ቤተ ክርስቲያንን ዛሬም ከኦሪት ሥርዓት በታች ያለች ያስመስላታል።

በአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት እንደሆነው ዛሬም ኦሪታዊ ቅሬታዎች ጎልተው በሚታዩባት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያነሣ ወገን ቢመጣ ሊሰጥ የሚችለው መልስ ያለውን እውነታ በትክክል የሚያሳይ ሳይሆን ላለማፈር ሲባል የሌለውንና የማይታመንበትን የሚገልጽ ነው።

በመሠረቱ ኦሪት ለኢትዮጵያውያን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ አይደለም። ኦሪት የተሰጠው ለሕዝበ እስራኤል ብቻ ነው። "ቃሉን ለያዕቆብ፥ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል። ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፥ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም።" (መዝ. 147÷8-9)

ስለዚህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየው ኦሪታዊ ሥርዓት በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት

አይሁድ የወረስነው የእነርሱ ብቻ ገንዘብ የሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ሕግ እንጂ ከእግዚአብሔር አልተሰጠንም። ለምሳሌ አሁን በቤተ ክርስቲያናችን ያለው ታቦት የሥጋ ወደሙ መፈተቻ እንጂ ለእስራኤላውያን ከተሰጣቸው ታቦት ጋር ከአሠራሩ ጀምሮ በይዘትም ሆነ በሚሰጠው አገልግሎት ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። ይህንንም አቡነ ጎርጎርዮስ ሲገልጹ የሁለቱንም አገልግሎት ለያይተው አስቀምጠዋል። "የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር። ይህ ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት . . የምሕረት ምሥዋዕ (መሠዊያ) ነው።"

ይህን ልዩነት ጠንቅቀው ያልተረዱ የዋሆች የአንድ ጥቅስ ድጋፍ እንኳ የሌለውን የአሁኑን የቤተ ክርስቲያኒቱን ታቦት ከእስራኤላውያን ታቦት ጋር በሁሉም ረገድ ለማመሳሰል ሲሉ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ እየጠቀሱ ሰውን ሲሞግቱ ምን ያህል የማያስተውሉ እንደሆኑ እግረ መንገዳቸውን እየመሰከሩ ነው።

እ.ኤ.አ በ1970 በእንግሊዝኛ ቋንቋ የታተመው "The Ethiopian Orthodox Church" የተሰኘው የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል "of all the Christian Churches the Ethiopian Orthodox Church as retained most Judaic elements such as the Tabot, Hospitality to strangers, clean and unclean meat, circumcision of a boy eight days after birth, priestly dances with drums . . . and St. Clement show that the Eucharistic service in their day was very similar inform to the Jewish service"

ይህም ማለት "በዓለም ዙሪያ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አያሌ ልዩ ልዩ የአይሁድ አምልኮት ሥርዓቶችን እስከዛሬ ድረስ በእምነቷና ሥርዓቷ ውስጥ አጣምራ በመያዝና በመፈጸም ጎልታ ትታወቃለች። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምትከተላቸውና ከምትፈጽማቸው የአይሁድ የአምልኮ ሥርዓት መካከል የታቦት አምልኮት፥ እንግዳ ተቀባይነት፥ ንጹሕና ርኩስ ሥጋ፥ ሕፃናትን በተወለዱ በ8ኛው ቀን መግረዝ፥ የካህናትን ውዝዋዜና የከበሮ አመታት፥ የሥርዓተ ቍርባንን አፈጻጸም ጨምሮ በቀጥታ ከአይሁድ ሥርዓት ጋር አንድ ናቸው።" (ገጽ 123)

መጽሐፉ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የሚታዩት የአይሁድ ሥርዓቶች ከእግዚአብሔር የተሰጡን አስፈላጊ ነገሮች ሳይሆኑ ከአይሁድ ጋር አብሮ በመኖር የወረስናቸው ልማዶች መሆናቸውን በትክክል ያስቀመጠ ቢሆንም በመጨረሻም ላይ ኦሪት ከወንጌል ጋር አብራ እንደተሰጠችን አስመስሎ "... what Jewish customs exist in Ethiopian Christianity have come through early Christianity" ማለትም "ዛሬ በኢ/ኦ/ተቤ/ክ የሚፈጸሙት የአይሁድ ወግና የአምልኮት ሥርዓት የመጡት በመጀመሪያ የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ነው።" በማለት የተናገረው ግን ለምንም የማይመችና እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ታሪክ ያልተሰማ ተረት ተረት ነው። (ገጽ 124)

ሐሰተኞች ታሪክን ከታሪክ በማጋጨት፥ የእግዚአብሔርን ዕቅዳዊ አሠራር ለማዘበራረቅ በመሞከር ለኦሪት የተዘጋውን በር እንከፍታለን ቢሉም የማይሆን ነገር ነው።

አንዳንድ አባቶችም ነገሩን በትክክል እየተረዱት ማስተካከል ሲገባቸው "ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳን አገር የነበረችው ኢትዮጵያ በክርስትና ጊዜም ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ጠቃሚ ነገሮች በክርስትና መንፈስ እየተረጎመች ትጠቀምባቸዋለች።" የሚል አስተያየት በመስጠት የኦሪት ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖሩን መደገፋቸውና ማበረታታታቸው ያሳዝናል።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ራሱ ሰጥቶ የወሰነላት ዘመን ሲፈጸም በመጨረሻው የማትጠቅም ያደረጋትን እኛ የሚጠቅም ነገር አላት ብለን ከእርሷ የተወሰነውን ወስደን እንጠቀምባት ማለት ከኦሪት የምትሻለውንና በእጅጉ የምትበልጠውን ወንጌልን አቃልሎ ብቁ እንዳይደለች መቁጠር ይሆናል። (ዕብ. 7፥ 18-19፤ 2ቆሮ. 3፥ 10-11፤ ገላ. 4፥ 9)

"ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር። ዐዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል። አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።" (ዕብ. 8፥ 7-10)

እግዚአብሔር በገዛ ሥልጣኑ አሮጌና ውራጅ ብሎ ያፈረሰውን ይጠቅማል ብለን ለማነጽ የምንነሣ ከሆነ የእግዚአብሔርን አሠራር እየተቃወምን እንገኛለን።

ጌታ "በአረጀ ልብስ ዐዲስ እራፊ የሚጥፍ የለም። ቢደረግ ግን ዐዲሱ መጣፊያ አሮጌውን ይቦጭቀዋል። መቀደዱም የባሰ ይሆናል። በአረጀ አቁማዳም ዐዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም። ቢደረግ ግን የወይን ጠጁ አቁማዳውን ያፈነዳል። የወይኑም ጠጅ ይፈሳል። አቁማዳውም ይጠፋል። ዐዲሱን የወይን ጠጅ ግን በዐዲስ አቁማዳ ያኖራሉ" በማለት የተናገረው የኦሪትና የወንጌል ሥርዓቶች አብረው መሄድ እንደማይችሉ አመልካች ነው። ባለአንድምታዎቹ ይህን ሲተረጉሙት ያረጀው ኦሪት ዐዲሱ ደግሞ ወንጌል መሆናቸውን አብራርተዋል። (የማር. 2÷ 21-22ን አንድምታ ወንጌልን ተመልከት)

በእርግጥም ጌታ ኦሪትን ፈጽሞ ዐዲስ ኪዳንን በገዛ ደሙ ሲመሠርት ከኦሪት ሥርዓት ውጪ በሆነ መንገድ ነው። ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ቀን ምሽት ላይ ዐዲስ ኪዳንን ሲመሠርት የኦሪቱን ቤተ መቅደስና በዚያ የነበሩትን የተቀደሱ ዕቃዎች (ንዋያተ ቅዱሳት) ታቦት÷ የዕጣን መሠዊያ (ጽንሐ) ÷ መቅረዝ . . . ወዘተ የመሳሰሉትን አልተጠቀመም። በዚህ ሁሉ ፈንታ በአንድ የተነጠፈ የግለሰብ አዳራሽ ውስጥ ነው ዐዲስ ኪዳንን የመሠረተው። (ሉቃ. 22÷ 8-20)

ለምን እንዲህ አደረገ? ቤተመቅደሱ አልነበረምን? ወይስ ደግሞ ካህናተ ኦሪት ቤተ መቅደሱን ስላልፈቀዱለት ነውን? አይደለም! የዚህ ምስጢሩ በአረጀ ልብስ ዐዲስ እራፊ ማኖር ስለማይገባ ነው።

በክርስቶስና በአይሁድ መካከል መለያየትን የፈጠረው ይህ የኦሪትና የወንጌል አብሮ ያለመሄድ ጉዳይ ነው። ሕጋችንን ሻረ÷ ሃይማኖታችንን ለወጠ አሰኝቶ እርሱን ለመስቀል ሞት ያበቃውም ይኸው ጉዳይ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተመሠረተችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በኦሪቱ ሥርዓት ሳይሆን ክርስቶስ ባቋቋመው ዐዲስ ኪዳን ነበር የተመራችው። አንዳንድ ጊዜ ሐዋርያት የቤተመቅደሱን የጸሎት ጊዜ ጠብቀው ወደመቅደስና ምኩራብ ይወጡ የነበረው ሥርዓተ ኦሪትን ለመፈጸም ሳይሆን እግዚአብሔርን በመንፈስ ለማምለክና ክርስቶስ በየዕለቱ በመቅደስና በምኩራብ እየተገኘ ያስተምር እንደነበረው እነርሱም የወንጌልን መስበኪያ በር ለማግኘት ሲሉ ነው።

በተከፈተላቸውም በር ወንጌልን ሰብከዋል። (የሐዋ. ሥራ 3፥ 1-26፤ 2፥ 46፤ 5፥ 42፤ 9፥ 20፤ 13፥ 14-52፤ ሉቃ. 21፥ 37፤ ማቴ. 26፥ 55)

በተረፈ ግን ቤተ ክርስቲያን ከመቅደስና ከምኩራብ ውጪ በሆነ ስፍራና ሁኔታ ተሰብስባ የራሷን አምልኮ፥ ጸሎት፥ ሥርዓተ ጥምቀትና ቁርባን . . . ወዘተ መንፈሳዊ ሥርዓቶችን በመንፈስና በእውነት ታከናውን ነበር። (የሐዋ . ሥራ 2፥ 46፤ 4፥ 23-31፤ 8፥ 38፤ 12፥ 5፤ 16፥ 13)

## ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ

"በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ÷ መንገዱም ትልቅ ነውና÷ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ÷ መንገዱም የቀጠነ ነውና÷ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" (ማቴ. 7÷ 13)

ከዚህ ገጸ ንባብ የምንረዳው ሰፊውና ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ የሰይጣን ሲሆን እርሱም ዓለማዊ ምኞትንና ሥጋዊ ፈቃድን ሁሉ ያካትታል። ጠባብ ወደ ሕይወት የሚወስድ የተባለው ደግሞ እግዚአብሔር መንገድ ነው። ሰው ሰይጣንን በመከተል ዓለማዊ ምኞ ትንና ሥጋዊ ፈቃድን የሚፈጽም ከሆነ በሰፊው መንገድ ላይ ስለሆነ ወደጥፋት እየተጓዘ ነው። (2ቆሮ. 6÷ 9-10፤ ገላ. 5÷ 19-21) ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ እግዚአብሔርን ቢከተል ወደ ሕይወት ስፍራ በሚወስደው በጠባቡ ደጅ ገብቷል። (ምሳ. 19÷ 23) በአጭር አገላለጽ ሰፊውን ደጅ ትቶ በጠባቡ መግባት ዲያብሎስን በመቃወም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው። (ያዕ. 4÷ 7-8)

በዚህ መንገድ ሊተረጎም የሚገባው ቃል ሌላ የማይስማማ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን። "ሰፊ በር ሰፊ መንገድ ኦሪት ናት" የሚል። (አንድምታውን ተመልከት)

የአንድምታን ተርጓሚዎች በትኩረት ላጤናቸው ብዙ ጊዜ መነሻና የሚመስል አሳብን እንጂ ግብን አይመለከቱም። "ሰፊ በር ኦሪት ናት" ያሉት ከመነሻው መስሏቸው ነው። ሰፊው በር ወዴት እንደሚያደርስ ግቡን ቢመለከቱት ኖሮ ግን እንዲህ ከማለት ይታቀቡ ነበር።

ኦሪት በራሷ የምታጠፋ ሕግ ነበረችን? አይደለችም። ሰው ከሥጋው ደካማነት የተነሣ ሊፈጽማት ባለመቻሉ ጽድቅን አላሰጠችውም። (ሮሜ 8÷3-4) ቢፈጽማት ኖሮ ግን ሊጸድቅባት ይችል ነበር። (ዘሌዋ. 13÷5፤ ሮሜ 2÷13፤ ገላ. 3÷12) ባልፈጸማት ላይም መቅሰፍትን ታመጣለች (ሮሜ 4÷15) ስለዚህ ኦሪት የጥፋት መንገድ አይደለችም። (ሮሜ 7÷12)

እግዚአብሔር እውነተኛውን መዳን በልጁ መገለጥ እስኪያረጋግጥ ድረስ ኦሪት ፍጹም ድኅነትን ባታሰጥም በወንጌል ጥላነቷ ዐዲስ ኪዳንን በርቀት እያመላከተች ኃጢአትን በመከደን ጊዜያዊ ስርየትን ታሰጥ ነበር። (ዕብ. 9÷8-10) ክርስቶስ ሲመጣም ስፍራዋንና አገልግሎቷን ለወንጌል አገልግሎት ለቃለች።

ቅ/ጳውሎስ እንደተናገረው ኦሪት በጊዜዋ የሰጠችው የሞግዚትን አገልግሎት ነው። ሞግዚት ጠብቆና ተንከባክቦ እንዲያሳድግ÷ የተሰጠውን ልጅ እስከተወሰነለት ጊዜ ድረስ አሳድጎ ለባለቤቱ እንደሚያስረክብና ከዚያ በኋላም በልጁ ላይ አንዳች እንደሌለው ሁሉ ኦሪትም ወደ ክርስቶስ ያቀረበች ሞግዚት ናት። እምነት እስኪገለጥ ድረስ ሁሉን በሷ ሥር አድርጋ ትሠራ ትቀጣ ነበርና። አሁን ግን በሥሯ ሆነን የተጠበቅንለት እምነት መጥቷልና ከሞግዚታችን ከኦሪት በታች አይደለንም። (ገላ. 3÷23-25) ይህም ቢሆን ኦሪትን ወደጥፋት የምትወስድ ሰፊ በር ናት አሰኝቶ በተሳሳተ ትርጉም አያስነቅፋትም።

በእጅጉ የሚደንቀው የሚናገሩትና የሚሠሩት የተለያየባቸው የኦሪት ነቃፊዎች እንዲያው ለይስሙላ ኦሪትን የጥፋት በር ይበሏት እንጂ ወደ ጥፋት መውሰዷን ተረድተው ከኦሪት ሥር መቼ ወጡ?

# ራስን ለካህን ማሳየት

"ኢየሱስም ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፤ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ። ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ።" (ማቴ. 8 ÷4)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምጻምነት እንደ ኃጢአት በሚቆጠርበት በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ውስጥ ለነበረው አንድ ለምጻም ሰው የተናገረው ቃል ነው። በኦሪቱ ሥርዓት መሠረት አንድ ሰው በሚሠራው ኃጢአትም ይሁን እንዲሁ ለምጽ ቢወጣበት እንደ ርኩስ ነገር ተቆጥሮ ከማኅበረሰቡ ይገለላል። እንደርሱ ላሉ ለምጻሞች ወደ ተከለለው ስፍራ ሄዶ በዚያ ይኖራል። ለምጹ እስካለቀቀው ድረስ ርኩስ ነው። ለምጹ ሲነጻ ግን ካህኑ አይቶት መንጻቱን ሲያረጋግጥለት ሕጉ እንደሚያዝዘው ስለመንጻቱ ተገቢውን መሥዋዕት ያቀርብና ወደ ማኅበረሰቡ ይቀላቀላል። (ዘሌዋ. 13)

ከጌታ ጋር የተገናኘው ለምጻም ሰው የዚህ ሥርዓት ተገዢ ነበር። ጌታን ባየ ጊዜ በእምነት ቀርቦ ከለምጹ እንዲያነጻው ለመነው። ጌታም አነጻው። ከዚያ በኋላ ይህ ሰው ምንም ማድረግ አያስፈልገውም ነበር። ነገር ግን ዐዲሱ ኪዳን በክርስቶስ ደም እስኪቆም ድረስ በእንስሳት ደም የተመረቀው ብሉይ ኪዳን የአገልግሎት ዘመኑ አላበቃም። ክርስቶስም የመጣው ኦሪትን ያለጊዜው ለመሻር ሳይሆን በጊዜው ለመፈጸም ነውና ስለዚህ ተቀናቃኞቹ የእርሱን ሕግ ፈጻሚነት እንዲያውቁና የነጻውን ሰው ወደ ካህን መላኩ ምስክር እንዲሆንባቸው ሰውዬውን "ሂድ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ።" ብሎ አዘዘው።

የመልእክቱን ፍሬ አሳብ ከመሠረቱ ሳይረዱ "ራስህን ለካህን አሳይ" የሚለውን ቃል ብቻ ከመሀል ነጥለው በማውጣት ዛሬም በዐዲስ ኪዳን ሰው ኃጢአቱን በቤተ ክርስቲያን ላሉ ቀሳውስት ካልተናዘዘ በቀር ስርየተ ኃጢአትን ፈጽሞ አያገኝም የሚለውን ትምህርታቸውን ያራምዱበታል።

ለመሆኑ ጌታ ሰውዬውን የላከው ወደ የትኛው ካህን ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ አያሻማም፤ ወደ ኦሪቱ ካህን ነው። ታዲያ ይህ ክፍል ስለ ዐዲስ ኪዳን ካህናት እንደተነገረ ተደርጎ ለምን ይወሰዳል? እርግጥ ሁኔታው ዐዲስ አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል አሳስተው

የሚተረጉሙ ወገኖች ቤተ ክርስቲያንን በካህን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በብዙ ሁኔታዎች ከኦሪት ሥርዓት በታች እንዳኖሯት ግልጽ ነው።

በብሉይ ኪዳን ለአስታራቂነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚገቡ ከነገደ ሌዊ የሆኑና ከአሮን ወገን የተመረጡ ብዙ ካህናት ነበሩ። (ዘሌዋ. 4÷1-35፤ 5÷4-6፤ ዕብ. 5÷1-2) በዚህ የክህነት አገልግሎት ፍጹም ድኅነት አልተገኘም። (ዕብ. 7÷11) ከዚህም የተነሣ ተደጋጋሚ መሥዋዕትን ማቅረብ አስፈልጓል። (ዕብ. 10÷11) ካህናቱም ሰው ብቻ በመሆናቸው ፍጹምነት ስለሚጎድላቸው ለራሳቸው ኃጢአት መሥዋዕት ያስፈልጋቸዋል። (ዘሌዋ. 9÷7፤ ዕብ. 5÷3) የማስታረቅ አገልግሎታቸውም በሕይወተ ሥጋ እስካሉ ድረስ ብቻ በመሆኑ ከሞቱ በኋላ ክህነታቸው ይቀርና ሌላ በሕይወተ ሥጋ ያለ ካህን ይሾማል። (ዕብ. 7÷23)

በዐዲስ ኪዳን ግን የአሮን ክህነት በክርስቶስ ክህነት ሙሉ በሙሉ ተተክቷል። (ዕብ. 7÷11-19) ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ካህን ብቻ ሳይሆን መሥዋዕትም ጭምር ነውና ፍጹም ድኅነት ማስጠት ያልቻለውን የእንስሳት መሥዋዕትን አስቀርቷል። (ዕብ. 9÷11-12) ክርስቶስ ያቀረበው መሥዋዕት ፍጹምና ሕያው በመሆኑ መደጋገም ሳያስፈልገው ለዘለዓለም ኃጢአትን ለማስተስረይ አንድ ጊዜ የቆመ ሕያው መሥዋዕት ሆኗል። (ዕብ. 9÷25-26፤ 10÷12-14፤ ሮሜ 3÷25) የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት ፈጽሞ የራቀ ጻድቅ በመሆኑ እንደ ኦሪቱ ካህናት ስለራሱ መሥዋዕት ያቀርብ ዘንድ አላስፈለገውም። (ዕብ. 7÷27፤ 4÷15) ክርስቶስ ቢሞትም ሕያው ሆኖ ተነሥቷልና ክህነቱ አይሻርም አይለወጥም፤ በዚህም ምክንያት ሌላ የሚተካው ካህን አላስፈለገውም። (ዕብ. 7÷20-22፤ 24-25) ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ የፍጹምነት መስፈርቶች አሟልቶ የተገኘ ካህንና መሥዋዕት ስለሆነ የኦሪቱን ካህናትና አገልግሎታቸውን መሥዋዕቱንም ጭምር ሙሉ በሙሉ አስቀርቷል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነት አስቀድሞ በግዘፍ፥ በምሳሌ፥ በሚታዩና በሚዳሰሱ ነገሮች እንዲሁም በአንድ ስፍራ ተወስኖ የነበረው አፍአዊ አምልኮና አገልግሎት ሁናቴው ተለውጦ በመንፈስና በእውነት ብቻ በመሆኑ ምክንያት በሱ ያመነን ሁላችን አንድ ጊዜ ባፈሰሰው ደሙ በእምነት ተረጭተንና ታጥበን ተቀድሰን ከኃጢአታችንም ነጽተን ድነናል። (ዮሐ. 4÷19-24፤ ዕብ. 10÷21-22፤ 1ቆሮ. 6÷11፤ ዕብ. 12÷24)

ያነጻን የደሙ መፍሰስና የእኛም ይህን አምኖ መቀበል እንጂ ሌላ በዐይነ ሥጋ የሚታይ አፍአዊ ሥርዓት መፈጸም አለመሆኑን የተረዳው ኤፍሬም ሶሪያዊ:- "በውኂዘ ደሙ ቅዱስ አንጽሖሙ ለመሃይምናን ወለሕዝብ ንጹሐን::" "በክቡር ደሙ መፍሰስ ያመኑትንና ንጹሐን የሆኑትን ወገኖች አነጻቸው::" ብሏል።

ይህን መንፈሳዊ የክህነት አገልግሎት ያከናወነው የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ አስታራቂ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከእርሱ በቀር ይህን ያከናወነ ወይም የሚያከናውን የለም። ጌታ ምድራዊ አገልግሎቱን ፈጽሞ ከሄደ በኋላ ወደ ሰማያዊቱ መቅደስ በዘላለም ቤዛነቱ የገዛ ደሙን ይዞ ስለገባና በዚያው ካህን ስለሆነ የክህነቱን ሥራ ተክቶ በምድር ላይ እንዲያከናውን ኃላፊነትን የተቀበለ፥ ኃጢአትን አስተሰርያለሁ፥ አነጻለሁ፥ እቀድሳለሁ ባይ ሌላ ካህን አልተሾመም ለወደፊቱም አይሾምም።

ታዲያ በዐዲስ ኪዳን ካህናት እነማናቸው? ተብሎ ቢጠየቅ የዘር፥ የቋንቋ የቀለም፥ የእውቀት፥ የሀብትና የመሳሰሉት መስፈርቶች ሳይኖሩ ክርስቶስ በደሙ የቀደሳቸው ምእመናን በሙሉ ናቸው። እነዚህን ጌታ ለአባቱ መንግሥት ካህናት አድርጎ ሾሟቸዋል። (ራእ. 1፥6፤ 5፥10)

በክርስቶስ ሿሚነት ካህናት የተደረጉት ምእመናን እርሱ ብቻ ባቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰው በተሾሙበት ክህነት ሌሎች መንፈሳዊ መሥዋዕቶችን በየዕለቱና በየሰዓቱ በመሠዋት እግዚአብሔርን ያገለግላሉ። (1ጴጥ. 2፥5) በክህነታቸው የሚሠዉአቸው መሥዋዕቶች የራስን ሁለንተና (ሥጋን ነፍስንና መንፈስን) ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ (ሮሜ 12፥1-2)፥ የምስጋናን መሥዋዕት መሠዋት (ዕብ. 13፥15፤ መዝ. 49፥14፤ 23፤ 53፥6)፥ የእርሱን በጎነት መናገር (1ጴጥ. 2፥9) ፥ ነፍሳትን በወንጌል በኩል ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ (ሮሜ. 15፥15-16፤ ኢሳ. 66፥20)፥ ካለው ነገር ላይ ለሌሎች ማካፈል (ዕብ. 13፥16፤ ፊልጵ. 4፥18) ፥ . . . የሚሉት ናቸው።

ነገር ግን የኦሪቱን ክህነት ኮፒ በማንሣት ራሳቸውን ከሌላው የተለዩ ካህናት አድርገው ያስቀመጡ ወገኖች ራስን በራስ የመሾሙ ጉዳይ ተቀባይ እንዳያጣ ለማድረግ ሲሉ አሁን ይዘናል የሚሉት ክህነት ለሐዋርያት ከጌታ የተሰጠና ሲወርድ ሲዋረድ ከእነርሱ የደረሰ መሆኑን

በአጽንዖት ይናገራሉ። ሆኖም ጌታ ለሐዋርያት የተለየ ሥልጣን ክህነትን እንደሰጣቸው የሚናገር አንድም ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ አይገኝም። ከላይ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ለማቅረብ ካህናት ከተሰኙት አማኞች መካከል ቤተክርስቲያንን ለማስተዳደር÷ ለመምራት÷ ለመመገብ አገልጋዮችን ለመሾምና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን ግን ሁሉም አማኞች ሳይሆኑ የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው ጳጳሳት÷ ኤጲስ ቆጶሳት÷ ቀሳውስት÷ ዲያቆናትና ሌሎችም አገልጋዮች ተደርገው ይሾማሉ። ቅዱሳን ሐዋርያትም የተሾሙት በዚህ መንገድ ነው። (1ቆሮ. 12÷27-29፤ የሐዋ. ሥራ 20÷28፤ 1ጢሞ. 3÷1-13፤ 5÷17፤ ቲቶ 1÷5) ይህንንም በሌላ ስፍራ ሲገልጽ ሐዋርያው እንዲህ ብሏል። "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት ÷ ሌሎቹም ነቢያት ÷ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች÷ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።" (ኤፌ. 4÷11) በእነዚህ ሁሉ ውስጥ "ካህናትን ሾመ ወይም ሰጠ" የሚል እንዳልተጻፈ ልብ እንበል። ካህንነት መንፈሳዊ መሥዋዕቶችን ለማቅረብ በጳጳስ ሳይሆን በሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች ሁሉ የሚሾሙት የወል ሹመት ነውና ለተወሰኑት ብቻ ከሚሰጡት ሹመቶች መካከል መጠቀስ አላስፈለገውም።

የሁሉም አማኞች ሹመት የሆነውን ክህነት የግል ንብረታቸው አድርገው የቆጠሩት ወገኖች የሥልጣን መዋቅራቸውን በመዘርጋትና የሥራ ድርሻቸውን በመለየት ራሳቸውን በሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ስፍራ አስቀምጠው እርሱ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ለራሳቸው ደርበው በመውሰድ ኃጢአትን ለቄስ ከመናዘዝ ጋር አቆራኝተው የሥልጣን ወንበራቸውን አደላድለውበታል። (ማቴ. 16÷19፤ 18÷18፤ ዮሐ. 20÷23)

የቤተ ክርስቲያን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን በጉልህ የተብራራበትን የማቴ. 18÷18ን ክፍል እንመልከት:- "በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል። በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።" የሚለው ቃል ኃጢአትን ለቄስ ከመናዘዝና ስርየትን ከማግኘት ጋር ፈጽሞ አይናገኝም። ይህን ለማረጋገጥ ቢያስፈልግ ከቁ. 15 ጀምሮ ያለውን ማንበቡ ተገቢ ነው።

በክርስቲያኖች መካከል በተለያዩ ጉዳዮች የተገናኙ በዳይና ተበዳይ ቢኖሩ ተበዳዩ በአንድ ጊዜ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የበደለውን ለብቻው መውቀስ አለበት። በዳዩ በዚህ ዕድል ተጠቅሞ

ከጥፋቱ ካልተመለሰ ለ2ኛ ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ምስክር አስቀምጦ ሊወቅሰው ይገባል። አሁንም ካልተመለሰ ለመጨረሻ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ፊት (በቤተ ክርስቲያን መሪዎች) እንዲወቀሥና ከበደሉ እንዲመለስ ማድረግ ይገባል። ቤተ ክርስቲያንን አልሰማ ካለ ግን እንዲህ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ከአንድነቷ ትለየዋለች። ይህም በምድር ያሰረችው (የለየቻው) ጉዳይ በሰማይም የጸና ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ይህ ሥልጣን ስለተሰጣት ይህንኑ እንደየሁኔታው ስትጠቀምበት እናያለን። (የሐዋ. ሥራ 5÷1-10፤ 1ቆሮ. 5÷5፤ 1ጢሞ. 1÷20)

ቤተ ክርስቲያን ወይም ሐዋርያት ይህን ሥልጣን ስለዚህ ጉዳይ ብቻ እንጂ ኃጢአትን ለማናዘዝ አልተጠቀሙበትም። ደግሞም እግዚአብሔር ይፍታህ ወይም ይሰርህ ሳይሉ በተሰጣቸው ሥልጣን አሰሩ፥ ፈቱ፥ ፈረዱ። (የላይኛውን ጥቅሶች ተመልከት)

ነገሩ እነርሱ እንደሚሉት ይሁን እንኳ ቢባል አፈጻጸሙ በጣም አስቸጋሪ መሆኑ እርግጥ ነው። ሰው ንስሐ የሚገባው በበደለ ሰዓት በመሆኑ ኃጢአት የሠራው ሰው በበደለ ሰዓት መናዘዝ ቢፈልግ እንኳ ቄሱን የግድ ማግኘት ስለሚኖርበት እሱን ፍለጋ መሄዱ አይቀርም። ከሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣ በወቅቱ ሊያገኘው ባይችል ደግሞ ለንስሓ ቀጠሮ ለመያዝ ይገደዳል። ወይም ደግሞ ቢገናኙ በነሳሒው ልብ ውስጥ ቄሱ እንደሱው ያለ ሰው መሆኑ ስለሚታወቅ የሚናዘዘው ኃጢአቱን በከፊል አሊያም ኃጢአት የሆነውን ትቶ ኃጢአት ያልሆነውን ጉዳይ ነው።

በዚህ ዐይነት ሰው የሆነው ቄስ በሥሩ ከሚገኙት ብዛት ያላቸው የንስሓ ልጆቹ አንጻር ለስንቱ ሊበቃ ነው? ዛሬ ኃጢአትን በመናዘዝ ዙሪያ ያለው የሕዝባችን የልብ ጭንቀት የእነዚህ ሁሉ ችግሮች ድምር ነው። በክርስቶስ ወንጌል ዐይነ ልቡናቸው የበራ ምእመናን ግን በዚህ ሰው ሠራሽ ሥርዓት ስርየተ ኃጢአትን እንደማያገኙ ስለተረዱ የንስሓን የአሁን ዕድሜ አሳልፈው ሌላ ቀን በመቅጠር እንደ እነርሱ ድካም ያለበትን ቄስ ፍለጋ ላይ ታች አይሉም። (ዕብ. 5÷2-3፤ 7÷28) በሰማያት ያለፈው ትልቅ ሊቀ ካህናተ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹምነት ያለውና በድካማቸው የሚራራ መሆኑን በመገንዘብ (ዕብ. 4÷14-15) "ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አበ ነፍስየ አንተ።" "ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አንተ የነፍስ አባቴ ነህ።" (መልክአ ኢየሱስ) ብለው በመጥራት ኃጢአት እንደሠሩ በተረዱ ሰዓት ወዲያው ኃጢአታቸውን ተናዘው በደሙ ታጥበው ስርየትን ይቀበላሉ። (ዮሐ. 1÷7፤ ዕብ. 9÷14)

ሐዋርያው ያዕቆብ "እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ" ሲል እንደተናገረው እርስ በርሳችን እንደ አስፈላጊነቱ አንዱ ለአንዱ መናዘዝ ይገባል። ይህም ቄሱ ወይም ሌላው ምእመን ወንድማችን ኃጢአታችንን እንዲያስተሰርይልን ሳይሆን በጸሎት እንዲያስበንና በመንፈሳዊ ምክር እንዲረዳን፥ እንዲያጽናናን ለማድረግ ነው። (ያዕ. 5÷16)

ከዚሁ ጋር አብሮ የሚታየው በእግዚአብሔር ፊት ለመጸለይና ኃጢአታችንን ተናዝዘን ይቅርታን ለማግኘት ከመቆማችን በፊት የበደልነው ሰው ቢኖር እርሱን የበደልንበትን በደል ለእርሱ ተናዝዘን ይቅርታ ከእርሱ መጠየቅና መቀበል አለብን። (ማቴ. 5÷24፤ ሉቃ. 17÷4)

በአጠቃለይ ግን ኃጢአታችንን ልንናዘዝ የሚገባንና ትክክለኛውን ስርየት የምናገኘው በሰማያት ላለፈው ታላቅ ሊቀ ካህናት ለኢየሱስ ክርስቶስ በመናዘዝ ብቻ ነው። (ዕብ. 4÷14-16) እግዚአብሔር ለእርሱ ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። የክርስቶስም ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል። (ኢሳ. 1÷18፤ 43÷25-26፤ 1ዮሐ. 1÷7-8)

ኃጢአትን ለእግዚአብሔር መናዘዝ እንደሚገባ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ሳይቀር ስለተረዱ ብዙ ጊዜ ኃጢአታቸውን ለእግዚብሔር በቀጥታ ይናዘዙ ነበር። (2ሳሙ. 24÷10፤ ነህ. 1÷6-7፤ ኢዮ. 7÷20-21፤ መዝ. 24÷11፤ 31÷5፤ 37÷18፤ 50÷1፤ 3፤ ኢሳ. 64÷5-6፤ ኤር. 14÷7፤ 9÷20፤ሰቆ.ኤር. 1÷20፤ ዳን. 9÷4፤20)

እውነተኛ ይቅርታን ለማግኘት ኃጢአትን ለሌላ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብቻ መናዘዝ ተገቢ መሆኑን ዮሐንስ አፈወርቅ መስክሯል:- "መፍትው ለነ ናዑቅ አበሳነ አኮ በልሳንነ ባሕቲቱ አላ በኅሊናነሂ ምስለ ገዐር ወክዒወ ልብ እንዘ ናዜክር ኵሎ ኃጢውኢነ በበገጹ ወአኮ ዘእብለከ ከመ ትክሥት ርእሰከ ወኢ ከመ ትሕምያ ለጎበ ካልዓን አላ ተአዘዝ ለነቢይ ዘይቤ "ክሥት ለእግዚአብሔር ፍኖተከ" ወተአመን ባቲ ወኀበ መኰንን አይድዕ ጌጋየከ እንዘ ትስእል ወታስተበቍዕ።"

ትርጓሜ:- "ከጭንቀትና ልብን ከማፍሰስ ጋር ኃጢአታችንን ሁሉ በየሲማው (በየመልኩ) እያሳሰብን በአንደበታችን ብቻ ሳይሆን በመላው አሳባችን በደላችንን እናስታውቅ ዘንድ አግባብ ነው። ይህንም ስልህ ራስህን ለማናቸውም እንድትገልጥ ወይም በሌሎች ዘንድ ነፍስህን ለሐሜት አሳልፌህ እንድትሰጥ ማለቴ አይደለም። ነገር ግን "መንገድህን ለእግዚአብሔር የተገለጸ አድርግ" ለሚለው ለነቢይ ቃል ታዘዝ:- በእርስዋም አምነህ ተዳኝ (ተናዘዝ)። በልመናና በምልጃም በደልህን ለጻድቁ ፈራጅ ተናገር።" (መዝ. 36÷5) (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 157-158)

ይህን ቀና ትምህርት አጣምመው "ለቄስ ካልተናዘዝን በቀር ስርየት የለም" የሚለውን እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አስርገው ያገቡት ሰዎች በእነርሱ ሥርዓት መሠረት ንስሐ ለሚገባ ሰው ቀኖና (ስለኃጢአቱ የሚከፈል ዋጋ ወይም የሚቀጣው ቅጣት ጾም÷ ስግደት . . . ) እንዲኖር ደንብ ደንብተዋል። ክርስቶስ በሊቀ ካህንነቱ የገዛ ደሙን የኃጢአት ማስተስረያ አድርጎ እንዳቆመ እነርሱም ራሳቸውን በእርሱ ስፍራ አስቀምጠዋልና ሌላ የኃጢአት ማስተስረያ መፈለጋቸው ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ሰውስ ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?" ሲል ነፍስን ከኃጢአት አንጽቶ ለማዳን የሚበቃ ዋጋ አለመኖሩን ይመሰክራል። (ማር. 8÷37)

ቄርሎስም ይህንኑ ሲያረጋግጥ:- "ወኢኮነ ክርስቶስ በካልዕ ዘየኀድግ ኀጢአተ ወኢይስእሮ ለሞት ዘእንበለ በደሙ።"

ትርጓሜ:- "ክርስቶስም ኃጢአትን ይቅር የሚለው ሞትንም የሚሽረው በደሙ ነው እንጂ በሌላ አይደለም።" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 156-157)

እውነተኛ መስሎ የተቀመጠው ይህ ሁሉ የስሕተት ትምህርት በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ያልነበረ ሲሆን ከእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ጊዜ የክርስትናው ተከታዮች ቁጥር እየተበራከተ በመምጣቱ አምኖ የተጠመቀውን ክርስቲያን በእምነቱ ለማሳደግና ተገቢውን መንፈሳዊ ክትትል ለማድረግ በየቀበሌው አንዳንድ ቄስ መካሪ እረኛ እንዲሆን ተደርጎ ሲያገለግል ነበር። ይህም ትክክለኛ ነገር

ነበር። እየቆየ ሲመጣ ግን በጊዜ ብዛት መካሪ ሆኖ በየአካባቢው የተመደበው ቄስ "ለነፍስ ጉዳይ የአባት ያህል ይመክራል" ተብሎ "የነፍስ አባት" ወደመባል ተሸጋገረ። በመቀጠልም የቀኖና መጻሐፍት ተዘጋጅተው ቄሶች ስለነፍስ ጉዳይ ኃላፊዎች እንደሆኑ ተቆጥረው የንስሐ አባት ተብለው በመጠራት ይኸው እስካሁን እየተሠራበት ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግን አይደለም።

# የእግዚአብሔርን ቅዱሳን መቀበል

"ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል። ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።" (ማቴ. 10÷41-42)

በብዙዎች ዘንድ ለዚህ ጥቅስ የሚሰጠው ትርጉም እግዚአብሔርን አገልግለው ባንቀላፉት (በሞቱት) ቅዱሳን ስም ዝክር መዘከር÷ ምጽዋት መስጠት የሚል ነው።

ጌታ 12ቱን ሐዋርያት በስማቸው ጠርቶ ርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጥቶ የጠፉ በጎች ወደሆኑት ሕዝበ እስራኤል ላካቸው፤ ሲልካቸውም የተለያዩ መመሪያዎችን ሰጥቷቸው ነበር። በተለይም "ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ" ሲል (ማቴ. 10÷9-10) የነበራቸውን ወይም ሊኖራቸው የሚገባውን በቂ ወይም ትርፍ ነገር ሁሉ የሚያስቀር መመሪያ ሰጣቸው። በዚህ መልኩ የነበራቸውን ነገር ሁሉ አስጥሎ ባዶአቸውን ሲልካቸው "ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና" የሚል ተስፋ በመስጠት ነበር። (ማቴ. 10÷10)

ያለአንዳች ነገር የላካቸውን አገልጋዮቹን ወደ ቤቱ አስገብቶ የሚቀበላቸውና ትምህርታቸውን የሚሰማ ጌታን ይቀበላል። በቤቱ አስፈላጊውን መስተንግዶ ሲያደርግላቸው ደግሞ አገልጋዮቹ በአገልጋይነታቸው ከሚያገኙት ዋጋ ተካፋይ ይሆናል።

በማቴ. 10÷12-15 "ወደ ቤትም ስትገቡ ሰላምታ ስጡ ቤቱም የሚገባው ቢሆን ሰላማችሁ ይድረስለት። ባይገባው ግን ሰላማችሁ ይመለስላችሁ ከማይቀበላችሁም ቃላችሁንም ከማይሰሙ ሁሉ ከዚያ ቤት ወይም ከዚያች ከተማ ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ። እውነት እውነት እላችኋለሁ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ አገር ይቀልላቸዋል።" በማለቱ የቁ. 40-41ን መልእክት ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል። የጌታን አገልጋዮች በመቀበል አንጻር በረከት እንደሚገኝ ሁሉ አገልጋዮችን ባለመቀበልም ፍርድ አለ ማለት ነው።

ቃሉ ግልጽ ነው። ዛሬም ቢሆን ፍቺው ይኸው ነው፤ አይለወጥም። ራስን ሙሉ በሙሉ ሰጥቶ ብዙ በማገልገልና አመርቂ ፍሬን በማፍራት ረገድ ልዩነት ቢኖርም የጌታ አገልጋዮች የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ብቻ አይደሉም። "እስከዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" እንዳለው በዘመናት ሁሉ አገልጋዮች አሉት። ስለዚህ ዛሬ በመካከላችን በሕይወተ ሥጋ ያሉትን እውነተኛ የወንጌል አገልጋዮች ተቀብለን ቃላቸውን ብነሰማና እንደተቻለንና እንደ አስፈላጊነቱ ብንረዳቸው ጌታን እንቀበላለን፤ በረከትንም እንወርሳለን።

ባለአንድምታዎቹ ግን ለአንድ ቃል ዐይን ዐዋጅ የሚሆኑ ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች መስጠት ልማዳቸው በመሆኑ ትክክለኛውን ትርጉም "እውነተኛውን መምህር እውነተኛ መምህር ብሎ የተቀበለ መምህሩ የሚያገኘውን፥ እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል።" በማለት በመጀመሪያ ከሰጡ በኋላ በሞቱ ነቢያትና ቅዱሳን ስም ለድሀ መመጽወትንም እንደሚያመለክት በሌላው ትርጉማቸው ገልጠዋል። (የማቴ. 10፥40-41 አንድምታ ወንጌልን ተመልከት)

ለድሀ ስለመመጽወት በሌሎች ስፍራዎች ተጠቅሷል። (ዘዳ. 15፥11፤ ሉቃ. 16፥9፤ 14፥12-14) ይህ ክፍል የወንጌል አገልጋዮችን ስለመቀበል እንጂ ለድሆች በሞቱ ቅዱሳን ስም ስለመመጽወት ፈጽሞ አያወሳም። እንዲያውም በሌላው ወንጌላዊ አገልጋዮችን በጌታችን ስም ስለመርዳት እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል። "የክርስቶስ ስለሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውሃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እነግራችኋለሁ።" (ማር. 9፥47)

## ምስጢራዊቷ ዕለት ስትታወቅ

"ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም" (ማቴ. 24÷ 36)

በመተርጉማኖቻችን ዘንድ ያለው ሌላው ትልቁ ችግር እግዚአብሔር ሳይገልጥ የሰወረውን ምስጢር ሁሉ እናውቃለን በማለት ለመተርጎም መነሣት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የማያሻቸው ግልጽ መልእክቶችን ይዟል። በመምህራን ሊብራሩ የሚችሉ መልእክቶችም አሉ። ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊተረጉማቸው የማይችሉ መልእክቶችም ይገኛሉ። ስለዚህ ማንኛውም አንባቢ መጽሐፍ ቅዱስን እንዳሻው ለመተርጎም ከመነሣቱ በፊት እነዚህ ነገሮች የተካተቱበት መጽሐፍ መሆኑን ተገንዝቦ ሁሉንም በየፈርጁ ሊያጤነው ይገባል።

ዘላለማዊ ድኅነት የሚገኝበት መልእክት (ወንጌል) ለዘመናት ምስጢር ሆኖ ቢቆይም በጌታ ሰው መሆን ተገልጧል። (ሮሜ 16÷ 25-26፤ 1ቆሮ. 2÷ 17) እግዚአብሔር የሰወረውን በተለይም በትንቢትና በራእይ መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ስውር አሳቦች ስውር ስለሆኑ ማንም በገዛ ራሱ ፈቃድ ሊተረጉም አልተፈቀደም። (2ጴጥ. 1÷ 20-21)

ጌታ በክብር የሚመጣባትን ቀንና ሰዓቲቱንም ጭምር ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊያውቃት እንዳይችል ወስኗል። ያቺ ቀን እንደሌባ አመጣጥ ድንገተኛ ናት። (ማቴ. 24÷ 43) ደቀመዛሙርቱ ቀኒቱ መቼ እንደሆነች ላቀረቡት ጥያቄ እንኳ የቀኒቱን መቅረብ ከሚያመለክቱት ምልክቶች በቀር ቀኒቱን ገልጦ አልተናገረም። (ማቴ. 24÷ 3-16) ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እንደተናገረው ጌታ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ያልተገለጹ የነበሩ ብዙ ምስጢሮችን ገልጾላቸው ሐዋርያት ብዙ ዐዳዲስ ነገሮችን ተናግረዋል። ጽፈዋልም። (ዮሐ. 16÷12-14፤ 1ቆሮ. 15÷51-52፤ 1ተሰ. 4÷15-17፤ 2ጴጥ. 3÷10-13) ይሁን እንጂ የጌታን መምጫ ቀን መንፈስ ቅዱስም ቢሆን ስላልገለጠላቸው ምንም ያሉት ነገር የለም። ጌታ የተናገረውን ብቻ ደግመው ተናግረዋል። (2ጴጥ. 3÷10፤ 1ተሰ. 5÷2)

ሁሉን እናውቃለን ባዮች ግን የጌታን መምጫ ቀንና ሰዓት በዝምታ አላለፉትም። በየትኛው የሒሳብ ስሌት እንደደረሱበት ባይታወቅም ዓመተ ምሕረቱን ብቻ ሳይጠቁሙ:- በዘመነ ዮሐንስ÷ በወርኀ መጋቢት÷ እሁድ ዕለት በመንፈቀ ሌሊት እንደሆነ በአንድምታቸው በእርግጠኝነት ተናግረዋል።

እግዚአብሔር ምስጢር ያደረገውን እንገልጣለን ብለው ወገኖቻችን ከእግዚአብሔር ሥራ ጋር ትንቅንቅ ከሚይዙ÷ በሰውም ዘንድ መጠቋቆሚያ ከሚሆኑ እንደ ሙሴ:- "ምስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው። የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለኛ÷ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።" በማለት ምስጢር የሆነውን ለእግዚአብሔር ትተው ለተገለጸው እውነት ብቻ ሊታዘዙ ይገባል። (ዘዳ. 29÷29)

## ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ

"ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሐ. 14÷ 6)

አንድምታ የተገለጸውን እውነት መልሶ በመቅበር የተጫወተውን ጉልህ ሚና ከሚያስረዱ ክፍሎች መካከል "በኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" ለሚለው ቃል የተሰጠው የተሳሳተ አንድምታ ይገኝበታል። አንድምታቸው "እኔን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም።" የሚል ነው። ይገርማል!

ይህ ቃል ግልጽ ከመሆኑ የተነሣ ምንም ትርጉም አያሻውም። የግእዙ ዐዲስ ኪዳን "ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ" "በኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" በማለት በግልጽ ያስቀምጠዋል።

ሕይወት የሆነውን ቃል በትርጉም ስም አጣምሞ መተርጎም የክርስቶስን መንገድነት ለማጥፋት ከታለመ ክፉ አሳብ የመነጨ ነው። ካሁን በፊት እንዳየነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ የመጣው በእምነት ወደአብ የምንቀርብበት ብቸኛ መንገድ ለመሆን ነው።

ይህን አምላካዊ ዕቅድ አፍርሰው ከክርስቶስ በቀር ሌሎች የመዳኛ መንገዶች አሉ ብለው የሚያምኑና የሚያስተምሩ ቢኖሩ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚነኩ ተረፈ ግኖስቲኮች ናቸው። (ግኖስቲኮች መዳን በማወቅ እንጂ በማመን አይደለም የሚሉ! በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን በልብ ወለድ ፍልስፍና ላይ የተመሠረቱ! ጸረ ክርስትና አቋም ያላቸው ክፍሎች ናቸው።)

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዛሬም ቢሆን በክርስቲያኖች መካከል የግኖስቲኮችን አስተሳሰብ የሚከተሉ መኖራቸውን "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ" በተሰኘው መጽሐፋቸው በገጽ 58 እንዲህ በማለት ጽፈዋል:- "ግኖስቲኮች አሁንም ቢሆን አንዳንድ ጋሻ ጃግሬዎች (ተቀጽላዎች) አሏቸው። በስሕተትም ይሁን በድፍረት ይልቁንም ሠለጠነ በተባለው ዓለም የሚኖሩ ዘመናውያን ነን የሚሉ ሰዎች አንዳንድ የግኖስቲኮችን የመሰለ ሐሳብ ይናገራሉ። ለምሳሌ:- <u>በክርስትና ሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት የጽድቅና የሕይወት መንገድ ክርስቶስ ብቻ ነው</u>። (ዮሐ. 14÷6፤ የሐዋ. ሥራ 4÷12) እነዚህ

ያልናቸው ክርስቲያኖች (የግኖስቲኮችን የመሰለ አስተሳሰብ ያላቸው) በተለይም የፖለቲካ መሪዎች ላገዛዝ እንዲመቻቸው ይሁን ወይም ዐዲስ ፈላስፋዎች ለመባል በየተገኙበት ቦታ ብዙ ሃይማኖቶችን እንደ ወርቅ አንከብለው እንደሸማ ጠቅለው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብዙ መንገዶች አሉ ሁሉም ያስኬዳል እያሉ በድፍረት ሲናገሩ ይሰማሉ። ይህም ዩኒቨርሳሊዝም "UNIVERSALISM" ይባላል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዳቆየን ግን አባባሉ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚነካ ነው። ቤተ ክርስቲያንን ለረጅም ጊዜ የሆድ ሕማም ሆኖ ሲያሰቃይ የኖረ የግኖስቲኮች እርሾ ነው።"

"እኔን ተወላዲ ካለለ አብን ወላዲ የሚለው የለም" የተባለው አርፍተ ነገር በራሱ ትክክለኛ አባባል ሊሆን ቢችልም ለዮሐ. 14÷6 ቃል ግን የሚስማማ አይደለም። ምናልባት "እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል" ከሚለው ቃል ጋር ሊቀራረብ ይችል ይሆናል። (ማቴ. 10÷40) አብሮ ሊሄድ የማይችለውን ነገር አብሮ ለማስኬድ ሲባል ትርጉም መለወጡ ግን ትልቅ ስሕተት ነው። መጽሐፍ እንኳ "በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?" በማለት ይናገራል። (አሞ. 3÷3)

# የቅዱሳን ዕውቀት

"ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን። ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ ዐውቃለሁ። በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ ዐውቃለሁ" (1ቆሮ. 13÷12)

የእግዚአብሔርን ቃል ለተሳሳተ አመለካከታቸው መሸፈኛነት መጥቀስ የለመዱት ወገኖች ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር ለማስተካከል ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱት ይህን ክፍል ሲሆን በዚህ ጥቅስ ሽፋንነት የሚሰበከው ትምህርት ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ ሳሉ ዕውቀታቸው ውሱን እንደሆነና በአፀደ ነፍስ ግን እንደፈጣሪያቸው በሰማይ ሆነው በምድር የሚደረገውን እያንዳንዱን ነገር ያውቃሉ የሚል ነው።

ለዚህ በማስረጃነት የሚያቀርቡት በሉቃ. 16÷19-31 በተጻፈው ታሪክ ውስጥ በላጠጋው ሰው በሕይወተ ሥጋ ያሉት ዘመዶቹ እርሱ ወዳለበት የሲኦል ስቃይ ቦታ እንዳይመጡ በማሰብ አልዓዛርን እንዲልክና እንዲመሰክርላቸው አብርሃም በለመነው ጊዜ አብርሃም የሰጠውን ምላሽ ነው። የአብርሃም ምላሽ :- "ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ።" የሚል ነበር። ስለሆነም አብርሃም የሞተው አስቀድሞ ነውና ከብዙ ዘመናት በኋላ የተነሡትን ሙሴንና ነቢያትን (የሙሴንና የነቢያትን መጻሕፍት) እንዴት ሊያውቃቸው ቻለ? ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ በምድር የሚሠራውን ሁሉ አንድ በአንድ ስለሚያውቁ አይደለምን? " ይላሉ።

በ1ኛ ቆሮ. 13÷12 ለመግለጽ የተፈለገው እነርሱ በዚህ መንገድ ለመግለጽ ሽርጉድ ያሉለትን አመለካከት እንዳልሆነ ከንባቡ መንፈስ ለመረዳት ይቻላል። በዚሁ ምዕራፍ ቁ. 8-10 አሁን የምናውቀው ከፊል ዕውቀት ፍጹም የሆነው ሲመጣ እንደሚቀር ሲያስረዳ ቁ. 12 ላይ ደግሞ ከፊል የሆነውና አሁን በድንግዝግዝ ወይም በመስተዋት እንደማየት የተቆጠረው የዛሬው ዕውቀታችን በዚያን ጊዜ ማለትም ሥጋዊ ሞትን ሞተን ወደጌታ ስንሄድና የጌታችን ክብር ሲገለጽ ከፊልነቱ ተሽሮ ወደ ፍጹም ዕውቀት እንደምንሸጋገር አስረግጦ ይናገራል። ". . . በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን . . . በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ ዐውቃለሁ"

በዚህ ክፍል ዕውቀት የሚለው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኘውን÷ የዚህ ዓለም ጠቢባን ያልደረሱበትንና ወደፊትም

ሊደርሱበት የማይችሉትን መንፈሳዊ ዕውቀት ነው። (1ቆሮ.2፥6-9) ይህን ዕውቀት ሊረዱት የሚችሉት እግዚአብሔርን የሚወዱትና እርሱ የገለጸላቸው ብቻ ናቸው። (ማቴ. 16፥16-17፤ 1ቆሮ. 12፥3)

መንፈሳዊው ዕውቀት እግዚአብሔርን፥ ክብሩን፥ እኛን የመጥራቱን ተስፋ ምንነት፥ በቅዱሳን ዘንድ ያለውን የሰማያዊ ርስት ክብር ባለጠግነትን፥ ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉን ታላቅነትና የብርታቱን ጉልበት፥ የክርስቶስን የትንሣኤ ኃይልና የመሳሰሉትን ረቂቅ ጥበባት ሁሉ ያጠቃልላል። (ኤፌ. 1፥17-21፤ ፊልጵ. 3፥8፤ 10)

ዛሬ በሕይወተ ሥጋ እያለን እነዚህን ነገሮች በእግዚአብሔር ቃልና በእምነት ተደግፈን በተስፋ ብቻ በድንግዝግዝ እናውቃቸዋለን። ምናልባትም የልባችን ዐይኖች ሲበሩ የዕውቀታችን መጠን ሊጨምር ቢችልም ወደ ሙሉ ዕውቀት ተሻገርን ማለት አይሆንም። ምክንያቱም በሥጋ ስንኖር ከመታወቅ የሚያልፉና እናውቃቸው ዘንድ ዘወትር እየቃተትን የምንመኛቸው ብዙ ጥልቅ ነገሮች አሉ። (ኤፌ. 3፥18-19፤ ፊልጵ. 3፥10-11፤ 2ኛ ቆሮ 5፥1-2፤ ሮሜ . 8፥18-25)

አሁን ሁሉም ምን እንደሆነና ምን እንደሚመስል አልተገለጠም። በዚህ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን አንድ ትልቅ ተስፋ አለ እንዲህ የሚል፦ "ወዳጆች ሆይ! አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።" (1ዮሐ. 3፥2) ስለዚህ አሁን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በከፊል ያወቅነውን ወደፊት ሙሉ በሙሉ እናውቅ ዘንድ በተስፋ ለምንጠብቀው ለእኛ የርስቱን መያዣ ቅዱስ መንፈሱን ሰጥቶናል። (2ኛ ቆሮ. 5፥5፤ 1፥22፤ ኤፌ. 1፥13-14) በጥቅሉ ለመናገር የ1ቆሮ. 13፥12 መልእክት እንዲህ ያለውን ጥልቅ ነገር ከማወቅ ጋር የተያያዘ ነው።

አብርሃም በአፀደ ነፍስ ሆኖ እርሱ በሞት ተለይቶ ከዚህ ዓለም ከሄደ በኋላ ብዙ ዓመታት ዐልፈው የተነሡትን ሙሴንና ነቢያትን ማወቁ ግን ከላይ ከተመለከትነው ዕውቀት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ከላይ የተመለከትነውን ጥልቅ ነገር ሊያውቅ የሚችል እግዚአብሔርና እርሱ በመንፈሱ አማካኝነት ሊገልጽለት የወደደው ሰው ብቻ ነው። (1ቆሮ. 2፥10-13)

አብርሃም በአፀደ ነፍስ ሆኖ እንዲያውቅ እግዚአብሔር የገለጸለትን በሙሴና በነቢያት ዘመን የነበሩ ሰዎች ያለአንዳች መንፈሳዊ ብቃትና ቅድስና ሙሴንና ነቢያትን የማወቁ እድል ነበራቸው። የአብርሃምን ማወቅ ድንቅ የሚያሰኘው ከተፈጥሮ ባሕርዩ ውጪ በአፀደ ነፍስ ሳለ በአፀደ ሥጋ ያሉትን÷ በሱ ዘመን ወይም ከእርሱ አስቀድሞ በነበረው ዘመን ያልነበሩትንና የማያውቃቸውን ሙሴንና ነቢያትን ማወቁ ነው። እነደዚህ ያለውን ዕውቀት ለማወቅ ግን የግድ በአፀደ ነፍስ መገኘት አያስፈልግም። ከአብርሃም ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች በአፀደ ሥጋ ሳሉ በተፈጥሮ ባሕርያቸው ማወቅ ከሚገባቸው በላይ የሆነውንና የድርጊቱ ፈጻሚዎች ብቻ የሚያውቁትን ምስጢር በእግዚአብሔር ጸጋ ታግዘው ሲያውቁና የተሰወረውን ሲገልጡ እንመለከታለን።

ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ዘመን የኖረው ነቢዩ ኤልሳዕ የሶሪያ ንጉሥ ሰራዊት አለቃ የነበረውና በለምጽ ደዌ የተመታውን ንዕማንን በዮርዳኖስ ውሃ ታጥቦ እንዲፈወስ ባደረገው ጊዜ የተፈወሰው ንዕማን ለኤልሳዕ የተለያዩ ስጦታዎችን ሊያበረክትለት ወደደ። ኤልሳዕ ግን በእግዚአብሔር ስም ምሎ እንደማይቀበለው ገለጸለት። ንዕማንም ከኤልሳዕ ተለይቶ ከሄደና ራቅ ካለ በኋላ ኤልሳዕ የንዕማንን ስጦታ ባለመቀበሉ የተቆጨው ሎሌው ግያዝ ከኤልሳዕ ተደብቆ ወደ ንዕማን በመሮጥ ከደረሰበት በኋላ ኤልሳዕ እንደላከው ሆኖ በመቅረብ አንዳንድ ነገሮችን ለራሱ ወሰደ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ኤልሳዕ በስፍራው ተገኝቶ አላየም ወይም ደግሞ ሰዎች መጥተው ግያዝ ያደረገውን አላወሩለትም። ተፈጥሮአዊ ባሕርዩም ይህን በራሱ ያውቅ ዘንድ አይፈቅድለትም። ነገር ግን በውስጡ በነበረው ጸጋ እግዚአብሔር ከኤልሳዕ ዕውቀትና ችሎታ በላይ የነበረው ይህ ነገር ተገልጦለት ግያዝ የፈጸመውን ሁሉ አንድ በአንድ ሲዘረዝርና ስለጥፋቱም ሲገሥጸው እንመለከታለን። (2ነገ. 5÷26-27)

በዐዲስ ኪዳን ዘመንም እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አባላት የነበሩትን ባልና ሚስት የሐናንያንና የሰጲራን ድብቅ ሥራ ሲገልጽ እናነባለን። (የሐዋ. ሥራ 5÷1-10)

እንግዲህ ኤልሳዕም ሆነ ጴጥሮስ ከዕውቀታቸው በላይ የሆነውን ይህን ምስጢር ማወቃቸው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን

ጸጋ የሚሰጠው በወቅቱ ሲሠራ ያሰበው ድንቅ ሥራ ስላለው ነው። ስለሆነም ኤልሳዕና ጴጥሮስ ሌሎቹም ቅዱሳን ቢሆኑ ሁልጊዜ እንደዚህ ያለውን ድብቅ ነገር ያውቃሉ ወይም ይገልጣሉ ማለት አይቻልም። ይኸውም ሲታወቅ ኤልሳዕ በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠራ ብዙ ስውር የነበሩና ማንኛውም ሰው ሊያውቃቸው የማይችለውን የተደበቁ ነገሮችን ያወቀ ቢሆንም ከእርሱ የተሰወሩ ነገሮችም ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ሱነማይቱ ሴት ልጅ ሞቶባት ወደ ኤልሳዕ ስትመጣ ኤልሳዕ የሆነውን ነገር እንደወትሮው አላወቀም ነበርና አለማወቁን እንዲህ ሲል ገለጸ:- " . . . እግዚአብሔርም ያንን ከእኔ ሰውሮታል፤ አልነገረኝም።" (2ነገ. 4÷27)

ጴጥሮስንም ብንመለከት እግዚአብሔር ሐናንያና ሰጲራን ለመገሠጽና ክብሩን ለመግለጽ ሲል በራሱ የማያውቀውን ምስጢር ቢገልጽለትም በሌላ ስፍራ ያላወቀበት ሁኔታ አለ። ለቆርኔሌዎስና ለቤተሰቡ ወንጌልን እንዲመሰክር ጌታ ሲልከውና በአይሁዳዊነቱ አሕዛብ የሆኑትን እንዳይጸየፍ በራእይ ሲያሳየው ነገሩ ሁሉ ስላልተገለጠለት ስላየው ራእይ "ምን ይሆን ? " ብሎ ያመነታ ነበር እንጂ የቆርኔሌዎስ መልእክተኞች መጥተው እስኪነግሩት ድረስ የራእዩን ምስጢር አልተረዳውም ነበር። (የሐ. ሥራ 10÷ 17፤ 28) ወደ ቆርኔሌዎስ ከሄደ በኋላም እርሱን የጠሩበትን ምክንያት እንዲያስረዱት "አሁንም በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ? ብዬ እጠይቃችኋለሁ።" የሚል ጥያቄ በማንሣቱ ምንም ያወቀው ነገር አለመኖሩን አስረድቷል። (ቁ. 29)

በሌላ በኩል እግዚአብሔር በእርሷ ታላቅ ነገርን ሊያደርግ ከአንስተ ዓለም የመረጣትና ያከበራት የጌታችን እናት ቅ/ማርያምን ልንመለከት እንችላለን። በመልአኩ ብሥራት እንደተገለጸው ጸጋ የሞላባት ናት። ይህ ማለት ግን እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ትገኛለች ሁሉን ታውቃለች ወደሚል ድምዳሜ አያደርሰንም። መመረጧ ክብሯና ታላቅነቷ በመልአኩ ከተገለጸ በኋላ እንኳ ልጇን በ12 ዓመት ዕድሜው ለበዓል ይዛው ከዮሴፍ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም በወጡ ጊዜ የበዓሉ ቀናት ተፈጽመው ወደ ስፍራቸው ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር:- "ዮሴፍና እናቱም አላወቁም ነበር። ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለመሰላቸው የአንድ ቀን መንገድ ሄዱ። ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቁአቸውም ዘንድ ፈለጉት ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።" ይላል (ሉቃ. 2÷41-51)

እንግዲህ ማርያም ልጇ በኢየሩሳሌም መቅረቱን እንዳላወቀችና ከመንገደኞች ጋር ሊሆን ይችላል ብላ በመሰለኝ ከዮሴፍ ጋር ይጓዙ እንደነበረ ከቃሉ ለመረዳት እንችላለን።

በእርግጥ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለውን የባሕርይና የዕውቀት ልዩነት ካላወቅን ትልቅ ስሕተት ውስጥ እንገባለን። ፍጡራንን ከፈጣሪ ጋር አስተካክለው የሚያዩ ወገኖች ችግርም ይኸው ነው። ሌላውን ሁሉ ትተን በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ሰዎች መካከል በባሕርይና በዕውቀት ደረጃ ብቻ ያለውን መሠረታዊ ልዩነት እንኳ በንጽጽር ብንመለከት ርቀቱ ከሰማይና ከምድር ርቀት የሚልቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ቦታ ተከልሎለት የማይወሰን÷ በስፍራዎች ሁሉ የመገኘት ታላቅነት ያለው (ምሉዕ በኩለሄ) ÷ ስፍራዎች ሁሉ ሊይዙት (ሊወስኑት) የማይችሉ ልዑለ ባሕርይ አምላክ ነው። (ዮሐ. 4÷24፤ ኤር. 23÷2-4፤ ዕብ. 4÷13፤ መዝ. 138÷7-10)

ሰው ግን ግዙፍ÷ በዐይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ አካል ያለው÷ በቦታ የሚወሰን÷ በሁሉ ስፍራ የመገኘት ብቃት የሌለው ፍጡር ነው። ምናልባት የፍጡራን ወሰን ከየት እስከየት እንደሆነ ባልተረዳ አእምሮ በአፀደ ነፍስ ቅዱሳን ስለሚረቁ በሁሉ ቦታ ይገኛሉ ተብሎ ይታሰብ ይሆናል። የቱንም ያህል ቢረቁ እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የመገኘት ብቃት ለማንም የለውም።

በተፈጥሮአቸው ረቂቃን መናፍስት የሆኑትን ቅ/መላእክት እንኳ ያየን እንደሆነ ጽኑዓን÷ ኃያላንና ለተልዕኮ የሚፋጠኑ ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የሚገኝ ባሕርይ ስለሌላቸው በቦታ የተወሰኑ ናቸው። (በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 58 ላይ በፊደል መ ውስጥ የተጠቀሰውን ተመልከት)

ስለዚህ ቅዱሳንም ተፈጥሮአዊ በሕርያቸው ከሚፈቅደው በላይ ያለውንና ለእነርሱ ስውር የሆነውን ነገር የሚያውቁት እግዚአብሔር ሲገልጥላቸው ብቻ ነው። ከዚህ በቀር በአፀደ ነፍስም ቢሆን ሁሉን ማወቅን የራሳቸው ባሕርይ ሊያደርጉ አይችሉም፤ ይወቁም ቢባል

ባሕርያዊ ውሱንነታቸው ይወስናቸዋል፤ ተራራ÷ ገደል÷ የአገር ርቀት . . . ይከለክላቸዋልና አይችሉም።

እንግዲህ አብርሃም ሙሴንና ነቢያትን በአፀደ ነፍስ ሳለ ማወቁ በዚህ መንገድ ስለተገለጸለት ብቻ ነው እንጂ እንደ እግዚአብሔር በምድር የምትሠራዋን ሁሉ አንድ በአንድ ልቅም አድርጎ ስለሚያውቅ ነው ተብሎ በተሳሳተ መንገድ መወሰድ የለበትም። ምክንያቱም በሌላው ስፍራ በአፀደ ነፍስ ባለበት ሁኔታ አብርሃም የማያውቀው ነገርም እንዳለ ተጽፎአልና። (ኢሳ. 63÷16)

## አምስቱ አዕማደ ምስጢር

"ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮ ልናገር እወዳለሁ" (1ቆሮ. 14÷19)

አምስቱ አዕማደ ምስጢር ከጥንት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ስትጠቀም የቆየችበት አስተምህሮዋ ነው። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በምስጢረ ሥላሴ፥ የአምላክን ሰው መሆን በምስጢረ ሥጋዌ፥ ስለጥምቀት በምስጢረ ጥምቀት፥ ስለቅዱስ ቍርባን (ሥጋ ወደሙ) በምስጢረ ቁርባን፥ ስለክርስቶስ ዳግመኛ መምጣትና ስለሙታን መነሣት በምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ስታስተምር ቆይታለች።

ይህ ለተከታዮቿ የመጀመሪያ ሃይማኖታዊ ትምህርት እንዲሆን በራሷ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ቢሆንም ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

በቁጥሮች ላይ የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች "ቁጥሩ ይህን ያህል መሆኑ የዚህ ምሳሌ ነው" ማለትን ልማድ አድርገው ስለያዙት ብዙ ጊዜ ሦስት ቁጥር ካገኙ የሦስትነት፥ አምስት ካገኙ ደግሞ የአምስቱ አዕማደ ምስጢር፥ ሰባት ከሆነ ደግሞ የሰባቱ ምስጢራት ቤተ ክርስቲያን . . . ወዘተ ማለት ይቀናቸዋል።

ሐዋርያው ዛሬም በዘመናችን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ጎልቶ እንደሚታየው ከሥርዓት ውጪ በሆነ መንገድ የልሳንን ጸጋ ይጠቀሙ ለነበሩት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሁሉን ለማነጽ በአግባቡ እንዲጠቀሙና ለሌላውም ዕቅንፋትን እንዳያኖሩ ካስተማረበት የ1ቆሮ. ምዕራፍ 14 ውስጥ "አምስት ቃላትን በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ" ያለው ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢር ለመናገር ፈልጎ መሆኑን አፉቸውን ሞልተው ይናገራሉ። ይህን አተረጓጎም እንደ እነርሱ ያለ ቁጥር አምላኪዎች ያዳንቁላቸዋል።

የአዕማደ ምስጢር ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጣ ነው ቢባልም ትምህርቱ የፈለቀበት ምንጭ ግን 1ቆሮ. 14÷19 አይደለም። ከጥራዝ ተነጥቆ ያለ አንዳች ማንገራገር ለአዕማደ ምስጢር የተለጠፈው ቃል መልእክቱ ሌላ ነው።

እንደሚታወቀው በበዓለ ኀምሳ ዕለት በሐዋርያት ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ሐዋርያት የተናገሩት ልሳን ለተናጋሪዎቹ ሐዋርያት ዐዲስ የሆነና አድማጭ ያገኘ ልሳን ነበር። በመሆኑም የገሊላ ሰዎች እንደሆኑ በአድማጮቻቸው የተመሰከረላቸው ሐዋርያት ካሁን ቀደም በማያውቁት በአድማጮቻቸው የተለያየ ቋንቋ ሲናገሩ የሰሙት አድማጮቻቸው በገዛ ቋንቋቸው የእግዚአብሔርን ድንቅ ነገር ስለሰሙ መደነቅና መገረም ይዟቸው በክርስቶስ ለማመን ምልክት ሆኗቸዋል። እንዲህ ያለው ተደማጭ ልሳን በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውና ለማያምኑ ሰዎች ምልክትም ነው። (የሐዋ. ሥራ 2÷1-21፤ 1ቆሮ. 14÷22)

በሌላ ስፍራ ደግሞ ራስን ለማነጽ ብቻ የሚጠቅም ትርጉሙ ሊታወቅ የማይችልና ሌላው በዚያው ጸጋ ሊተረጉመው የሚችል ልሳን እንዳለም ይታወቃል። (1ቆሮ. 14÷4፤ 13÷1፤ 12÷10-11)

ትርጉሙ የማይታወቅ ልሳን ራስን ከማነጽ ዐልፎ በጉባኤ ላይ ላሉ ምእመናን የሚሰጠው ረብ ባለመኖሩ ይህ ጸጋ የተሰጠው ሰው ቢኖር ትርጉሙን እንዲያውቅ መጸለይ ወይም በተራና በሥርዓት አስተርጓሚ በሚገኝበት መጠቀም÷ አሊያም ደግሞ የሌላውን ሰላም ጠብቆ ራሱ ለእግዚአብሔር ብቻ መናገር አለበት። ይህ ካልሆነም በጉባኤ ላይ ዝም ማለት ይኖርበታል። አሊያ ግን ያልተማሩና የማያምኑ ሰዎች በጉባኤው መካከል ቢገኙ ሥርዓት አልበኞቹን የልሳን ተናጋሪዎች አብደዋል ብለው ሊሰነካከሉባቸው ይችላሉና እንዲህ ያለው የልሳን አጠቃቀም ከሚያንጸው ይልቅ የሚያፈርሰው ይበልጣል። (1ቆሮ. 14)

በዚህ ጉዳይ ላይ ሚዛናዊና በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተደገፈ አመለካከት ሊኖረን ይገባል። በዚህ ዘመን የልሳን ስጦታ አይኖርም ብሎ ተገቢ ያልሆነ ነገር መናገር ወይም ልሳን የሚሰጠው በማስተማር ጊዜ ለአስተማሪዎች (ለሰባኪዎች) ብቻ ነው ማለቱ ቤተ ክርስቲያንን ሊመራ በመንፈሳዊ ስጦታዎቹም እየደገፈ ወደ ክርስቶስ ሙላት ልክ ሊያደርሳት የሚሠራውን ጌታ መንፈስ ቅዱስን መቃወም÷ እንዳይሠራም መገደብ ይሆንብናልና እንዲህ ስናደርግ እንዳንገኝና ስርየት ወደሌለው ኃጢአት እንዳንገባ ልንጠነቀቅ ይገባናል። (ማቴ. 12÷32፤ 1ዮሐ. 5÷16) መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን ቆመው ለሚሰብኩ ብቻ ሳይሆን ተቀምጠው ለሚሰሙትም ሁሉ ራሳቸውን ያንጹበት ዘንድ

ሲያፈስ እጅንም በመጫን ሲቀጣጠል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እናነባለንና። (የሐዋ. ሥራ 10÷44-47፤ 19÷6፤ 2ጢሞ. 1÷6)

በሌላም በኩል ዛሬም ጸጋው እንዳለና እንደሚሰጥ የሚናገረውን ጫፍ ይዞ ከሌላው በመኮረጅና በልምምድ ወይም ከማን አንሼ በሚል ፉክክር በልሳን ለመናገር መሞከሩ አደገኛ ሁኔታ አለው። ምናልባትም በዚህ ውስጥ የሰይጣን መጠቀሚያ መሆንም አለ። ልሳን በራሱ ነጻ ስጦታ እንጂ የመንፈሳዊ እድገታችን ወይም ብቃታችን መለኪያ አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰጠን ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሠራው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ በልሳን እንናገር። ካልሰጠን ደግሞ በተሰጠን በሌላው ጸጋ እግዚአብሔርን እናገልግል ለሁሉ የልሳን ስጦታ አይሰጥምና። (1ቆሮ. 12÷4-11፤ 30)

ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም ቆመን ተገቢ ያልሆነ ነገርን በማስመሰል እያደረግን ራሳችንን አናታልል። ሌሎችንም በዚህ አገልግሎት እያሰናከልን ወደ እውነት እንዳይመጡና ስርየት የሌለውን ኃጢአት በመሥራት መንፈስ ቅዱስን እንዲያሳዝኑ ዕንቅፋት አናኑር።

ቤተ ክርስቲያናችን ከአብና ከወልድ ጋር አስተካክላ በአምልኮት ስሙን ብትጠራም በመንፈስ ቅዱስና በጸጋዎቹ ላይ ያላት ግንዛቤ በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። ወይም ደግሞ ከንግግር ያላለፈ ነው። ይልቁንም የልሳንን ስጦታ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የ1ኛ ቆሮ. 14ን ሥርዓት ባልተከተለና ከሥርዓት ውጪ በሆነ መንገድ ስለሚጠቀሙበት የልሳንን ስጦታና ሌላውንም የመንፈስ ቅዱስ በረከት አቃልላ እንድትመለከተው አድርጓታል።

በልሳን የመናገርን ጉዳይ ሌሎቹን ስትተችና ስትነቅፍ ራሷ ግን አብዛኛው አምልኮዋን ቋንቋውን ጠንቅቀው ያልተማሩ (የማያውቁ) በርካታ አገልጋዮችና አብዛኞቹ ምእመናን በማይሰሙት ቋንቋ በግእዝ ነው የምታከናውነው።

የግእዝ ቋንቋ እንዳይጠፋ በትምህርት ቋንቋነቱና በተጻፉት መጻሕፍት አማካኝነት እስካሁን ይዛው መገኘቷ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ ያስመሰግናታል። ለወደፊቱም ቢሆን ቋንቋውን በአገር ቅርስነቱ መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ግእዝ በቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ስፍራ ያለው ቋንቋ ወይም የቤተ ክርስቲያናችን መገለገያ ቋንቋ በመሆኑ

መምህራንና ሌሎችም ተራ አገልጋዮች በየደረሱበት የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሰው ለመናገር ሲፈልጉ በግእዝ ቋንቋ ጥቅስ ጠቅሰው "እንዲህ ይላል" ማለትን ለምደው ስላስለመዱ ግእዝ የእኛ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም የመጀመሪያ ቋንቋ ተደርጎ በብዙዎች ልብ እንዲታሰብ ማድረጋቸው አስገራሚ ነገር ነው።

ይሁን እንጂ ግእዙ በዚህ ዘመን በትምህርት ሊገኝ የሚችል ቋንቋ በመሆኑ (በተለይም በቤተ ክርስቲያን እየሰጠ ካለው አገልግሎት አንጻር) በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ልሳን (ቋንቋ) ሊባል ባይችልም ትርጉሙን በማያውቁት ቋንቋ መጸለዩና ማምለኩ እንደተባለው አእምሮን ያለፍሬ ያስቀራል፤ (1ቆሮ. 14÷14-17) ቤተ ክርስቲያናችንንም "ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ" ያሰኛታልና ሊታሰብበት ይገባል።

ማኅበሩን በማነጽ ረገድ ትርጉሙ ከማይታወቅ ልሳን ይልቅ ሁሉም በሚግባባበት ቋንቋ ማስተማር÷ መጸለይ÷ መዘመር÷ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ስለዚህም ቅ/ጳውሎስ "ሌሎችን አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላትን በልሳን (ብዙ ነገሮችን ትርጉሙ ባልታወቀ ቋንቋ) ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ (ጥቂት ነገሮችን ትርጉሙ በሚታወቅ ቋንቋ) ልናገር እወዳለሁ።" አለ።

ይህ ቃል በምንም መንገድ ቢተረጎም ለአምስቱ አዕማደ ምስጢር ሊሆን አይችልም። አምስቱ አዕማደ ምስጢርን በተመለከተ ሁሉን ባያካትትም ዕብ. 6÷1-2 ያለው የተወሰኑትን ሊደግፍ ይችላል። "በእግዚአብሔር እምነት" የሚለው ምስጢረ ሥላሴን "ስለጥምቀቶች" የሚለው ምስጢረ ጥምቀትን "ስለሙታን ትንሣኤ÷ ስለዘላለም ፍርድ ትምህርት" የሚለው ደግሞ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታንን ያመለክታል። የተቀሩትን ምስጢረ ሥጋዌን (ዮሐ. 1÷14) ÷ ምስጢረ ቍርባንን ደግሞ (ማቴ. 26÷26-29፤ ሉቃ. 22÷17-20፤ 1ኛቆሮ. 10÷16-17፤ 11÷23-32) ያመለክታል።

# እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት

"በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌ. 1÷3፤ 1ቆሮ. 1÷3፤ 1ጴጥ. 1÷3፤ ራእ. 1÷6)

የተዋሐዶን ትክክለኛ ምስጢር ካለመገንዘብና የኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነቱ ክብር እንዳይዋረድ በሚል ሰበብ "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" የሚለውን ብዙዎች አይቀበሉትም በ1980 ዓ/ም በታተመውና "ሰማኒያ አንዱ" እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይህን በማስተካከል "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ይባረክ" በሚለው ተክተውታል (ኤፌ. 1÷3፤ 1ጴጥ. 1÷3ን ከሰማኒያ ወአሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት) የግእዙ ዐዲስ ኪዳንም 2ቆሮ. 1÷3ን ጨምሮ እንዲሁ ነው የሚለው።

ይሁን እንጂ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለማርያም መግደላዊት ተገልጾ "ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደአባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው።" (ዮሐ. 20÷17) ብሎ የተናገረውን የግእዙም ዐዲስ ኪዳን አይለውጥም። ቃሉ የተነገረበት ጊዜም ብዙዎች አሁን ሰው መሆኑ ቀርቷል ብለው ከሚያስቡበት ከትንሣኤው በኋላ መሆኑ ዕቅዳቸውን ሁሉ አፍርሶ ያፈረሱትን ደግመው እንዲያንጹ የሚያስገድድ ነው። ለአምላክነቱ ሲጠነቀቁ ለሰውነቱ ግን ደንታ ቢስ መሆናቸው በእጅጉ ያሳዝናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ብቻ አይደለም ፍጹም ሰውም ነው። ስለዚህ ጌታ ራሱ እግዚአብሔርን "አምላኬ" ቢል÷ ሐዋርያውም "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ" ቢል ሰው መሆኑን እንረዳለን እንጂ አምላክነቱን ማዋረድ አይሆንብንም። ወይም ወደ ተረፈ አርዮሳውያን "ወልድ ፍጡር በመለኮቱ" ወደሚለው ክሕደት አይመራንም።

ደግሞም "አባቴ" ቢል "የኢየሱስ ክርስቶስ አባት" ቢባልም አምላክነቱን ያስረዳናል እንጂ ሰውነቱን አያስክደንም። ለአይሁድ ጌታችን "አባቴ እስከዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ" ብሎ ሲናገር እግዚአብሔርን "አባቴ" ብሎ በመጥራቱ አይሁድ የተገነዘቡት መበላለጥን ሳይሆን ከአብ ጋር ራሱን ማስተካከሉን ነው። (ዮሐ. 5÷17-18)

እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት የተባለበትን መሠረታዊ ምክንያት ሲገልጽ ኤጲፋንዮስ እንዲህ ብሏል:- "እግዘአብሔር አብ ውእቱ አቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በህላዌ መለኮቱ . . . እግዚአብሔር አብ አምላኩ ለወልድ ውእቱ በእንተ ትስብእቱ::"

ትርጓሜ:- "እግዚአብሔር አብ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርየ መለኮቱ አባቱ ነው:: . . . ሰው ስለሆነ ለወልድ እግዚአብሔር አብ አምላኩ ነው::" (ሃይ. አበ ም. 54 ክ. 1 ቁ. 9)

ከዚህ የአባቶች ሃይማኖት ወጥተው ለአምላክነቱ ብቻ በማድላት የሰውነቱን ነገር አጣጥለው የሚሰብኩትን "መለኮት ሥጋን ዋጠው፤ መጠጠው::" ብሎ ኑፋቄ ካመጣው ከአውጣኬ ለይተን አናያቸውም::

## የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ

"ከሕፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝ በትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ:- ልብንም ለማቅናት:- በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" (2ጢሞ. 3÷15-17)

ይህን ጥቅስ ብዙ ጊዜ ለአዋልድ መጻሕፍት ሕጋዊ ማረጋገጫ ስለመስጠት ይጠቅሱታል። "ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ።" (ዮሐ. 20÷30) የሚለውን አክለው አሳባቸውን ያዳብሩበታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈው በአዋልድ መጻሕፍት ተጽፎ ይገኛል ለማለት። እነዚህን ጥቅሶች በዚህ መንገድ በመረዳቱ ምክንያት አስተሳሰቡ የጠዘው ሕዝባችን ለአዋልድ መጻሕፍት ከፍተኛ ስፍራ በመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን እንደ 2ኛ መጽሐፍ ወይም በራሱ ያልተሟላ ጎዶሎ መጽሐፍ አድርጎ ነው የሚመለከተው። አሁን አሁንማ "መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ የሚያደርጉት አዋልድ መጻሕፍት ናቸው" የሚሉ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያናችን መመሸጋቸው እየታወቀ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ውስጥ "ከሕፃንነትህ ጀምረህ አውቀሃል" በማለት የሚናገርላቸው መጻሕፍት አዋልድን ሳይሆን የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ነው። ይህ መልእክት ለጢሞቴዎስ በጻፈበት ዘመን ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በቀር እንኳን ትናንት የመጡት አዋልድ መጻሕፍት ይቅርና ዐዲስ ኪዳንም ተሟልቶ አልተጻፈም።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለኢየሱስ ክርስቶስ በሚመሰክሩ የተስፋ ቃላት ስለተሞሉ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መዳን የሚገኝ በትን ጥበብ በውስጣቸው ይዘዋል። (ዮሐ. 5÷39፤ ሉቃ. 24÷27፤ 44)

ጌታና ሐዋርያቱም ጭምር ወንጌልን ሲሰብኩ የተስፋውን መሙላት የትንቢቱን መፈጸም ለማብሠር መሠረት ያደረጉት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ነው። (ሉቃ. 4÷17-19፤ የሐዋ. ሥራ 10÷43)

በወንጌል ለማመን ፈቃደኛ ሆነው የተገኙ አይሁድ እንኳ የተሰበከላቸውን የመዳን ወንጌል ትክክለኛነት ያረጋገጡት መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ከሚሰጡት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በማመሰካከር ነበር። ይህም መዳን የሚገኝበት ጥበብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (የሐዋ. ሥራ 17÷11፤ ቆላ. 2÷2-3፤ 1ቆሮ. 2÷6-8)

ስለዚህ በአጠቃላይ ዐዲስ ኪዳን ክፍል "ቅዱሳት መጻሕፍት" የሚለው ውክልናው ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው። (ሮሜ 1÷4፤ 16፥26)

የመጻሕፍቶቹ መልእክት ዘላለማዊ በመሆኑ ጊዜ አይሽራቸውም። በዘመናት ሁሉ ለትምህርት÷ ለተግሣጽ÷ ልብንም ለማቅናት÷ በጽድቅም ላለው ምክር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። (2ጢሞ. 3÷15-17፤ ሮሜ 15÷4፤1ቆሮ. 10÷11)

የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅም ቄርሎስ በግጻዌ ድርሳኑ ሲገልጽ ይህን ተናግሯል:- "ለትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት ግሙራ አልቦ ዘይጸግቦ ወኢመኑሂ ወፈድፋደሰ እለ ይኄልዩ ጥበበ ወአጥረዩ አእምሮ ማኀየዌ ውስተ አልባቢሆሙ እስመ ጽሑፍ እኮ በኅብስት ዘየሐዩ ሰብእ አላ በኩሉ ነገር ዘይወጽእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር ሲሲተ ልብ ቃሉ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወኅብስት መንፈሳዊ ዘያጸንዕ ኃይለ ሰብእ።"

ትርጓሜ:- "የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ማናቸውም ቢሆን ከቶ የሚጠግባቸው የለም። ይልቁንም ጥበብን ለሚሹና በልባቸው ውስጥ ማኀየዊ አእምሮን ለተገነዘቡ፤ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ እንዳይድን ተጽፎአልና። የልቡና ምግብ ሰውንም የሚያበረታ መንፈሳዊ ኅብስት የእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 48-49)

እንግዲህ አዋልድ መጻሕፍትን ለማንገሥ የተፈለገው ይህን የመጽሐፍ ቅዱስን ክቡር ስፍራ ለመስጠት በመሞከር ነው። ከታሪክ እንደምንረዳው አዋልድ መጻሕፍት እንደ አሸን የፈሉት ይበልጥ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ነው። ይህ እየታወቀ አንዳንዶች "አዋልድ" ማለት ሴቶች ልጆች ማለት ነውና አዋልድ መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ ናቸው ከማለት ደርሰዋል። ውስጣቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ለፈተሸ ሰው ግን መወለዱ ቀርቶ የቀረበ ዝምድናም የላቸውም። የጥቅስ ሐረግ መዝዘው በ2ጢሞ. 3÷15-17 በኩል እናዛምድ÷

ከሆነልንም እናዋልድ ቢሉም አዋልድ መጻሕፍቱ ከተመረጠላቸው ጥቅስ ጋር ስምምነት የላቸውም። ለሰው መዳን የሚገኝበትን ትክክለኛ ጥበብ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚሰጡ ይልቅ የኛ የሚሉትን ሌላ የማዳኛ ጥበባቸውን ይሰብካሉ። ስብከታቸው የክርስቶስን ጸጋ የሚያስጥልና በምትኩ "ይህን የሚያደርግ እስከዚህ ትውልድ ይማራል÷ . . . " እያለ ጽድቅን በሥራ ለማስጠት የቆመ ነው። ከዚህ ስብከታቸው የተነሣ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መምህራን "እንደ ወንጌል ማን ጸድቆ እንደ ገድልና ድርሳን ማን ተኮንኖ!" ሲሉላቸው ይደመጣሉ።

ጥንታውያን የኦርቶዶክስ አባቶች እነርሱ ተቀብለው ለእኛ ያስተላለፉልን መልእክት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ባዕድ ቃል እንዳንሰማ ያዝዛል። ለምሳሌ ዮሐንስ አፈወርቅ "ይደልወነ ናጽምዕ ቃላተ መለኮት ከመ ኢይባእ ውስተ አልባቢነ ቃል ነኪር።" "ባዕድ ቃል ወደልባችን እንዳይገባ የመለኮትን ቃላት ማድመጥ ይገባናል።" ብሏል። (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 48)

የመለኮትን ቃላት የያዘውን መጽሐፍ ቅዱስን ሊተካ የሚችል ሌላ ምንም ዓይነት መጽሐፍ የለም። የዚህ ትልቁ ምስጢር መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ የራሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ነው። የሚያስተውል ቢኖር የስሕተት ትምህርቶችን ሁሉ ትክክለኛ ለማስመሰል አንድ ቃል ተፈልጎ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ የግድ መሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃልነት የሚያስረዳ በቂ ምስክር ነው። ስለዚህም ሳዊሮስ ዘእስሙናይን:- "መጻሕፍት አምላካውያት እስትንፋስ አፉሁ ለእግዚአብሔር ነዮን። ወዓዲ ይቤ እስመ መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ ለእግዚአብሔር ፈጣሪ ወውእቱ ክቡር ወየዓቢ አምልኮ ዘፍጡር።"

ትርጓሜ:- "መጻሕፍት አምላካውያት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ናቸው። እንዲሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉን የፈጠረ የእግዚአብሔር ቃል ነውና፤ እርሱም ክቡር ከፍጡር ሐሳብም ከፍ ያለ ነው።" (ዕብ. 4÷12፤ ኤር. 23÷29፤ ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 48)

አዋልድ መጻሕፍት በአብዛኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይስማሙም እንጂ ቢስማሙ ሊጠቅሙ ይችሉ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስን ፊት ለፊት ተቃርነው ስለሚገኙ ግን ተቀባይነት የላቸውም። ይህንንም የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ በግልጽ ይናገራል።

"ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ኃይለ ቃል ያላቸውን መጻሕፍተ ታሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላለች አንልም። ከአሁን ቀደም አልተቀበለችም። ወደፊትም አትቀበልም እንላለን። ከወንጌል ቃል የተለየ አስተያየት (ሥርዋጽ) ያለውንና ያልተስማማውን ንባብና ልብ ወለድ ኃይለ ቃል አስፍረው የተገኙ መጻሕፍት ቢኖሩም እንኳ በበር በኩል ያልገቡ አንዳንድ ጉህልያዎች (ቀጣፊዎች) የሰነቀሩአቸው ናቸው ብለን እንሰርዛቸዋለን እንጂ አሜን ብለን አንቀበላቸውም። ለምሳሌ አንዳንድ ገድሎችና ድርሳኖች እግዚአብሔርን ክደው ጻድቃንን ወይም እመቤታችንን የተማጸኑትን ሰዎች አማልደው አስማሯቸው ሲሉ ቢገኙ ተቀባይ የላቸውም።" (መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 156)

# ለቅዱሳን የሚደረግ አገልግሎት

"እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ÷ እስከ አሁንም ስለምታገለግሏቸው÷ ያደረጋችሁትን ሥራ÷ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።" (ዕብ. 6÷10)

በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ቅዱሳንን ማገልገል" የሚለውን ቃል ይዘው የራሳቸውን አሳብ የተከተሉና የጠፉ ብዙዎች ናቸው። በእነርሱ አመለካከት "ቅዱሳንን ማገልገል" ማለት በሞቱት ቅዱሳን ስም የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ማለት ነው።

ቅድስና በግል ጥረት የሚገኝ ሕይወት ስለሚመስላቸው "ቅዱሳን" ብለው የሚጠሩት ጌታን አገልግለው ያለፉትን ቅዱሳን ብቻ ነው። ቅድስናቸውም በግል ብቃት እንደተገኘ ያስባሉ። ግን ተሳስተዋል።

ያለ አንዳች ልዩነት በክርስቶስ አምነው ዳግመኛ የተወለዱ ሁሉ ቅዱሳን ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክታቱ ውስጥ ክርስቲያኖችን ቅዱሳን እያለ ይጠራቸዋል። (ኤፌ. 1÷1፤ ፊልጵ. 1÷1)

በእርግጥ ቅድስና ክርስቶስን በማመንና በእርሱ በመኖር የሚገኝ እግዚአብሔር የሚደሰትበት ከእርሱ በእርሱና ለእርሱ የሆነ መልካም ኑሮ ነው። (ፊልጵ. 2÷13፤ ዕብ. 13÷21 ሮሜ. 11÷37)

የቀደሙትና አሁን በሕይወተ ሥጋ የሌሉት ቅዱሳንም ቢሆኑ ከዚህ ውጪ በሌላ መንገድ ቅድስናን አላገኙም። በክርስቶስ አምኖ በክርስቶስ በመኖር መልካሙን የእምነት ገድል የተጋደለው ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ሲመሰክር:- "ብቃታችን ከእግዚብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም።" 2ቆሮ. 3÷5 እንዲሁም ". . . ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፤ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።" (1ቆሮ. 5÷10) በማለት የመብቃትና የቅድስና ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ የሰው ጥረት አለመሆኑን ተናግሯል።

ቅድስና በዚህ መሠረት ብቻ የሚገኝ ሕይወት መሆኑን ከተረዳን በዕብራውያን መልእክት ". . . ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ÷ እስካሁንም

ስለምታገለግሏቸው . . . " የሚለው ምን ዐይነት ማገልገል እንደሆነ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንመልከት።

በቅዱሳን ክርስቲያኖች መካከል ድሆች ቅዱሳን ነበሩና ጥሪት ያለቸው ቅዱሳን ድሆቹን ቅዱሳን ይረዱአቸው ነበር። (የሐዋ. ሥራ 4÷32-35፤ 11÷29-30) ይህ እርዳታቸው ቅዱሳንን ማገልገል ተብሏል። (ሮሜ. 15÷25-27)

በተለይም ቅ/ጳውሎስ አዕማድ መስለው የሚታዩት ሐዋርያት ድሆችን ያስብ ዘንድ ብቻ በለመኑት መሠረት ይህንኑ ለማድረግ ይተጋ ነበር። (ገላ. 2÷9-10) በመሆኑም በሱ ስብከት ያቋቋማቸውን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እያስተባበረ ገንዘብ በመሰብሰብ ድሆች ቅዱሳንን አገልግሏል። ሌሎቹም ይህን እንዲያደርጉ አስተምሯል። (1ቆሮ. 16÷1-4፤ 2ቆሮ. 9÷1-15)

ይህ በጎ ተግባር በእግዚአብሔር ዘንድ የማይረሳና ዋጋ የሚያሰጥ ነው። (ዕብ. 6÷10) የተቸገሩትን ሁሉ እንደተቻለ መርዳት ክርስቲያናዊ ተግባር ቢሆንም ቅድሚያ የሚሰጠው ግን ለቅዱሳን ክርስቲያኖች ነው። (ገላ. 6÷10፤ ሮሜ 12÷13) ከዚህ ውጪ ቅዱሳንን የምናገለግልበት አንዳንድ መንገዶች ቢኖሩም ልናገለግላቸው የምንችለው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ ነው። ከሞቱ በኋላማ የማንም ድጋፍና እርዳታ ወደ ማያስፈልግበት÷ ሁሉ ወደተሟላበት ዓለም ነው የሚሄዱት። (ራእ. 7÷16-17)

# ፀሐይን የተጐናጸፈችው ሴት

በራእ. 12÷1-17 ስለ ክርስቶስና ስለእናቱ ስደት ይናገራል የሚል አንድምታዊ ትርጉም ይሰጣል።

ስለስደት በማቴ. 2÷13-15 ተጽፎአል። ራእ. 12 ውስጥ ከስደት ታሪክ ጋር ተመሳሳይ የሚመስል ጥቂት ነገር ያለ ቢመስልም በምዕራፉ ውስጥ የተገለጸው አብዛኛው ሁኔታ ግን ከስደት ታሪክ ጋር ሊመሳሰል ይቅርና ቅርርብም የለውም።

ለምሳሌ ፀሐይን ተጐናጽፋ÷ ጨረቃን ተጫምታ÷ የ12 ከዋክብት አክሊልን የደፋችው ሴት ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ብትባል ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም። የነዚህን ብርሃናት ፈጣሪ ለመውለድ የተመረጠች ናትና።

በ2ኛ ደረጃ ሴቲቱ የወለደችው ወንድ ልጅ ማንነት ". . . አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛ ዘንድ ያለው" መባሉ (ቁ. 5) እንዲሁም ሴቲቱ ወደ በረሃ ሸሽታ የቆየችበት ዘመን በቀናት 1260 ወደ ወራት ሲለወጥ 42 ወራት መሆኑና ቁ. 14 ላይ "ዘመን ዘመናትም የዘመንም እኩሌታ" የሚለው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት የጌታና የእናቱ ስደት ለ3 ዓመት ከ6 ወር ነው ከሚለው ጋር መስማማቱ ይመስላሉ ሊባሉ የሚችሉ ገጽታዎች ናቸው። የማይመስሉትን ደግሞ ቀጥሎ እንመልከት:-

"ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች" (ቁ. 2) የሚለው ቤተ ክርስተያኒቱ "ወጽአ ቃል እምኀበ አብ ዘእንበለ ድካም ወእምድንግል ተወለደ ዘእንበለ ሕማም" "ቃል ከአብ ያለ ድካም ወጣ ከድንግልም ያለ ሕማም ተወለደ" ብላ ከምታስተምረው ትምህርቷ ጋር ይጣላል። (ውዳሴ ማርያም)

(ቁ. 5) "ልጅዋ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ ሴቲቱም በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሃ ሸሸች።" የሚለው በማቴ. 2÷13 የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ነግሮት ዮሴፍ ሕፃኑንና እናቱን በአንድነት ይዞ ወደ ግብጽ መሸሹን ከሚናገረው ክፍል ጋር ይለያያል። በራእይ ክፍል ሴቲቱ ወደ በረሃ ሸሸች ልጁ ደግሞ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ የሚለው ሁለቱም ተለያይተው ወደተለያየ ስፍራ መሄዳቸውን ያሳያል።

ይህን ክፍል ለቀደመው ለጌታና ለእናቱ ስደት ሰጥተው የተረጎሙት ዘንዶውን ስደት አስነሥቶ ለነበረው ለሄሮድስ ምሳሌ አድርገው አቅርበዋል። በክፍሉ ወስጥ የተገለጸውን የዘንዶውን ድርጊትና ሁኔታ ስንመለከት ግን ዘንዶው ሄሮድስ ሊሆን በፍጹም አይችልም። ሄሮድስ ነው! አይደለም! ወደሚል አተካሮ ውስጥ እንዳንገባ ቁ. 9 ላይ ዘንዶው "ዲያብሎስ" ተብሎ ተተርጉሟል።

ዲያብሎስ የተባለው ዘንዶ ከሚካኤልና ከመላእክቱ ጋር ተዋግቶ መሸነፉና ከመላእክቱ ጋር ወደ ምድር መጣሉ በስደት ሰዓት ያልተከናወነ ድርጊት በመሆኑ ራእዩ የቀደመውን ስደት አያሳይም።

ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃን ተጫምታ 12 የከዋክብት አክሊል ተቀዳጅታ የታየችው ሴት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ከመሸጡ አስቀድሞ በሕልሙ ሲሰግዱለት ያያቸውን የፀሐይና ጨረቃ የ11 ከዋክብትን (12ኛው ራሱ ሆኖ) ታሪክ ያስታውሰናልና ሴቲቱ የምትወክለው ምናልባት ቤተ እስራኤልን ነው። ምክንያቱም የአሕዛብ ሙላት እስኪፈጸም በድንዛዜ የቆዩት የእስራኤል ቅሬታዎች በመጨረሻው ጊዜ አምነው እንደሚድኑ ተነግሯልና። (ሮሜ 11÷25-27)

ትንቢት ወይም ራእይ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር እንጂ ያለፈ ድርጊት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው። አንዳንድ አደናጋሪዎች በእንግሊዘኛ "Vision" ማለት ራእይ ነው። ይህም የወደፊቱ ብቻ ሳይሆን ያለፈው ድርጊትም የሚታይበት መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ ቴሌቪዥን ትናንት የተቀረጸውን ዛሬ ወይም ነገ ሊያሳይ እንደሚችል በራእይም ያለፈው ድርጊት በወደፊቱ ድርጊት ውስጥ ይታያል ሱሉ ይደመጣሉ። ይህም የወደፊቱን ራእይ ላለፈው የስደት ታሪክ ሰጥተው ለመተርጎም የፈጠሩት መላ ነው።

ለሁኔታዎች መግለጫነትና ለንጽጽር እንዲያገለግሉ ተብሎ ያለፉ የታሪክ ገጽታዎችና ስሞች ተጠቅሰው ቢገኙም ዮሐንስ የተመለከተው ራእይ ሙሉ በሙሉ ወደፊት የሚሆን እንጂ ካሁን ቀደም የተፈጸመ አይደለም። ለዚህም፡- "ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር . . . ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ" የሚለው ብቻ እንኳ በቂ ማስረጃ ነው። (ራእ. 1÷1)

በግልጽ እስካልተቀመጠ ድረስ የራእይንና የትንቢትን ክፍል በቀላሉ ለመረዳት አይቻልም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት

እንደተረዱት መጠን የግል አመለካከታቸውን ቢሰነዝሩ እንኳ እርግጠኛው ይህ ነው ብሎ ለመናገር ይከብዳል። ትንቢት ከቶውንም በሰው ፈቃድ ስላልመጣ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትም። (2ጴጥ. 1፥20)

የትንቢትንና የራእይን ምስጢር ልናውቅ የምንችለው በጊዜው ተፈጽሞ ስናይ ብቻ ነው። ራእይ 12 ወደፊት የሚፈጸም ትንቢት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህን ሽምጥጥ አድርጎ ከዶ ያለፈ ድርጊት የታወሰበት ክፍል ነው ማለቱ ራስን ማታለል ይሆናል።

# ከሞት በኋላ ያለው የቅዱሳን ተግባር

"ከሰማይም:- ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ አዎን! ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።" (ራእ. 14፥13)

ከዚህ ጥቅስ ውስጥ "ሥራቸውም ይከተላቸዋል" የሚለው ቃል ትኩረታቸውን የሳበው የዘመናችን ወጣት ሰባኪያን ዐዲስ ምስጢር አገኘን ብለው ለሰሚው አስቂኝም አስገራሚም የሆነ እንግዳ ትምህርት እያስፋፉ ነው።

በዚህ ቃል ርእስነት የተዋቀረው ትምህርታቸው አጠቃላይ መልእክት ቅዱሳን በዚህ ምድር ያከናውኑ የነበረው መንፈሳዊ ሥራቸው በሰማይም ተከትሎአቸው ሄዶ ያንኑ ሥራቸውን ደግመው በሰማይ እንደሚያከናውኑ ያትታል። ለዚህም በምሳሌነት ከሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች መካከል "አብርሃም በምድር ላይ እንግዳ ተቀባይ ስለነበረ ይኸው ሥራው ተከትሎት ሄዶ በሰማይም እንግዳ ተቀባይ ሆኗል።" በማለት የአልዓዛርን በአብርሃም እቅፍ መቀመጥ ይጠቅሳሉ። (ሉቃ. 16፥22)

በተጨማሪም ሙሴ የቀድሞ ተግባሩ በመገናኛው ድንኳን እየተገኘ እግዚአብሔርን ማነጋገር ነበር። ስለሆነም ጌታ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ተራራ ላይ ከኤልያስ ጋር ተገልጾ ጌታን አነጋገረ የሚለው ሌላው ማስረጃቸው ነው። (ማቴ. 17፥3)

በዚህ አሳባቸው በመንደርደር ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ያማልዱ ነበር። ስለዚህ ይኸው የማማለድ ሥራቸው ተከትሏቸው በአፀደ ነፍስም አሁን በሰማይም ያማልዳሉ ወደሚለው የዓላማቸው ግብ ይደርሳሉ።

በቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ያማልዳሉ በሚለው ትምህርት ላይ አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት እንደሌለ ይታወቃል። ከላይ የተመለከትናቸውና የዚህ አስተምህሮ ደጋፊዎች የሆኑ ብዙ ክፍሎችና ተከታዮቻቸው በአፀደ ነፍስ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ቆመው በማማለድ ላይ እንደሚገኙ ሲያምኑ፤ ይህን የማይቀበሉ ወገኖች ደግሞ "በአፀደ ነፍስ አሁን አያማልዱም፤ ነገር ግን የቀደመውና በሕይወተ

ሥጋ ሳሉ የነበረው ልመናቸውና የተገባላቸው ቃል ኪዳን ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው።" ይላሉ።

መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት የተሰኘው መጽሐፍ የመጀመሪያውን አመለካከት ውድቅ በማድረግ ሁለተኛውን ደግፎ እንዲህ ይላል :- "ቅዱሳን ጻድቃን ያማልዳሉ ስለተባለ ግን እላይ እንዳልነው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔርን አገልግለው የተቀበሉት ቃል ኪዳናቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው እንጂ እንደገና በአካለ ነፍስ መውጣት፥ መውረድ፥ መስገድ፥ መጸለይ፥ መለመን አለባቸው ማለት አይደለም። . . . ሊቃውንትም "ሰአሊ ለነ ቅድስት" ያለውን ንባብ ሲተረጉሙ በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለሆነ ነው ይላሉ። ቃል ኪዳን ማለትም "መሐልኩ በርእስየ ሕያው አነ" ያለው ቃሉ ሕያው ሆኖ ከእነርሱ በኋላ ለሚነሡ ትውልዶች የሚያደርገው ይቅርታና ቸርነት በመሐላው እንዳጸናላቸው ይሆናል ማለት ነው እንጂ ከሞቱ በኋላ ሲያማልዱ ይኖራሉ ማለት አይደለም።" ገጽ 125፥126)

እዚህ ላይ በቀደመው ልመናቸው ያስምራሉ የሚለው የክርስቶስ አንድ ጊዜ ለዘላለም ከሆነው የማስታረቅ አገልግሎት ተገልብጦ የተወሰደ መሆኑን ልብ ይሏል።

እንግዲህ ይህ አንድ አቋም ያልተያዘበት ትምህርት በዚች መጽሐፍ ውስጥ "ቃል ኪዳን" በሚለው ክፍል ስለቃል ኪዳን ምንነት በተገለጸው እውነት መሠረት ፈራሽ ይሆናል። አሁንም ደግመን የምናረጋግጠው እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባውን የምሕረት ቃል ኪዳን (ኪዳነ ምሕረት) ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ የገባው በክርስቶስ በኩል በተፈጸመው ብቻ ነው። እኛም የዚህ ኪዳን ልጆች ነን። (የሐዋ. ሥራ 3፥25-16)

ወደ አስቂኙ አገላለጻቸው ስንመለስ ቅዱሳን የምድር ላይ ሥራቸው ተከትሎአቸው በሰማይም ያንኑ እያከናወኑ ይኖራሉ በማለት የተናገሩት ቅዱሳን ከሞት በኋላ የሚጠብቃቸውን ዐዲስና ታላቅ ነገር ሰማያዊውንም ሕይወት የሚያቃልል ነው። ቅዱሳን በክርስቶስ ሆነው የደከሙት በምድር የሠሩትን በሰማይ ደግመው ለመሥራት ሳይሆን ከክብር ወደ ክብር ለመሸጋገር፥ በምድር የነበሩበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተለውጦ ወደ ዐዲስ ሕይወት ለመግባት . . . ወዘተ ነው። (ፊልጵ.

1፥23፤ ራእ. 7፥16-17) እዚያው ላይ ደግሞ "ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ" በማለቱ ምድራዊው የድካም ሥራቸው እንደሚቀር ያሳያል።

በሉቃ. 16፥22 የተገለጸው አብርሃም በምድር እንደነበረው ሁሉ በሰማይም እንግዳ ተቀባይ መሆኑን የሚገልጽ አይደለም። አብርሃም በእምነቱ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ በመሆኑ የእምነቱን ፍለጋ ለሚከተሉት ታዛዥ ልጆች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አባት ሆኗል። (ሮሜ 4፥12፤ 16-17) እግዚአብሔርም የእርሱና የልጆቹ ሁሉ አምላክ ተብሎ ሊጠራ አላፈረበትም። (ዕብ. 11፥16፤ ማቴ. 22፥31-32)

አብርሃም መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ እየጠበቀ በተስፋ ያመነው በእምነት ከመሰሉት ጋር ሰማያዊቷን ርስት ሊወርስ ነው። (ዕብ. 11፥8-10) ስለሆነም የእምነት ልጆቹ አብርሃም በአባትነት በተጠራባት ርስት ውስጥ ከእርሱ ጋር እንደሚቀመጡ ተነገረ። (ማቴ. 8፥11) በአልዓዛርም የታየው ይኸው ነው።

በሕይወተ ሥጋ እያለ አብርሃም ምልጃ እንዳቀረበ ተጽፎአል። (ዘፍ. 18፥22-23፤ 20፥7፤ 17) እርሱ ከሞተ በኋላ በሙሴ ዘመን ሕዝበ እስራኤልን ከኃጢአታቸው የተነሣ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው እንዳቀደ ለሙሴ በተናገረው ጊዜ ሙሴ ዘራችሁን አበዛዋለሁ ብሎ የማለላቸውን አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብን እንዲያስብና እንዲራራ ሲለምን፥ እግዚአብሔርም ራርቶ መዓቱን በምሕረት ቁጣውን በትእግሥት ሲመልስ ይታያል። (ዘጸ። 32፥7-14) ይህም እግዚአብሔር በምድር ላይ ዘራቸውን እንደሰማይ ከዋክብት ስለማብዛትና ከነዓንን ስለማስውረስ በመሐላ በተናገረው ነገር ለገባው ቃል ኪዳን ያለውን ታማኝነት ያሳይል። በዚህ ውስጥ ነፍስን የሚያስምርና መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ቃል ኪዳን አልሰጠም፤ እኛም በዚያ ቃል ኪዳን መሠረት ለመዳን ይህንና ያንን አድርጉ ተብለን አልታዘዝንም። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ባሪያዎችህን እነአብርሃምንና የገባህላቸውን ቃል አስብ ማለቱ ቃል ኪዳኑ በሕይወተ ሥጋ ከመኖርና ከነዓንን ከመውረስ ጋር ብቻ የተያያዘ መሆኑን ያሳያል።

አንዳንድ ቀጣፊዎች እንደሚሉት ሙሴ የጸለየው ወደሞቱት ቅዱሳን አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ ሳይሆን መሐላውን ወደሚያስብ ወደ እግዚአብሔር ነው። ይህን ያነሣነው በመጽሐፈ ዚቅ "ሰአለ ሙሴ በእንተ ዘስሕቱ ሕዝብ ኀበ አቡነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ።" "ሙሴ

ስለበደሉት ሕዝብ ወደ አባታችን አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ለመነ።" የሚል ጽሑፍ ስላለ ነው። (የሐምሌ ሥላሴ ዚቅ)

በሉቃ. 16፥19-31 የተገለጸው ታሪክም የሚያሳየን አብርሃም ለነፍስ ጉዳይ የተቀበለው ቃል ኪዳን አለመኖሩን ነው። በታሪኩ ውስጥ የተገለጸው ባለጠጋ በሲኦል ስቃይ ውስጥ ሳለ አልዓዛርን በሕፅነ አብርሃም በዕረፍት ቦታ በማየቱ ጮኸ ከስቃይ እንዲያሳርፈውና ለዚህም አልዓዛርን እንዲልክለት አብርሃምን ተማጸነ። አብርሃም ግን ሁለቱም ባለጠጋውና አልዓዛር በሥጋቸው ሳሉ የዘሩትን በነፍሳቸው እንዳጨዱ ከመግለጹም ሌላ ሰው ሞቶ ከተፈረደበት በኋላ የተለያዩ ደግባኖችን ጠይቆ ከሲኦል ወደገነት ሊወጣ እንደማይችል፥ በዕረፍት ቦታ ያሉ የቅዱሳን ነፍሳትም ወደ ሲኦል ሄደው ምሕረት እየሻቱ የሚጮሁትን የኃጥአን ነፍሳት ሊረዱ ወይም ከስቃዩ ሊያሳርፉ እንደማይችሉ ". . . ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደኛ እንዳይሻገሩ፥ በኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል።" ሲል ገልጾለታል። ምንም እንኳን ባለጠጋውና አብርሃም በአፀደ ነፍስ ባሉበት ሁኔታ መነጋገር እንደ ቻሉ ብናነብም አብርሃም የባለጠጋውን የምሕረት ልመና ተቀብሎ ወደ እግዚአብሔር ምልጃ አላቀረበም። ለምን? ቢባል በአፀደ ነፍስ ቅዱሳን ይህን ሁሉ ማድረግ የለባቸውም።

በሲኦል በአፀደ ነፍስ ላሉት ብቻም ሳይሆን በአፀደ ሥጋ ላሉትም ጭምር በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን ምልጃ ማቅረብ የሌለባቸው መሆኑን ባለጠጋው በሥጋ ስላሉት ዘመዶቹ በማሰብ "እንኪያስ አባት ሆይ! ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ። አምስት ወንድሞች አሉኝና እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ስቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው።" በማለት ላቀረበው ሌላ ጥያቄ የአብርሃም ምላሽ ማስረጃ ይሆናል። ምላሹ "ስለእነርሱ አታስብ መጽሐፈ ሄኖክ ሕያዋን ለሙታን ይጸልያሉ፤ ሙታንም ለሕያዋን ይለምናሉ ይላልና ለሕያዋኑ ዘመዶችህ እኔ እማልድላቸዋለሁ።" (ሄኖ. 12፥34) የሚል ሳይሆን ለእነርሱ እንደነርሱ በሕይወተ ሥጋ አብረዋቸው የሚገኙትን ሙሴንና ነቢያትን (መጻሕፍቶቻቸውንም ሊሆን ይችላል) ይስሙ የሚል ነው።

ወደ ሙሴም ነገር ስንመለስ በዚያ ተራራ ላይ ከኤልያስ ጋር ጌታን ሲያነጋግር መታየቱ የቀድሞው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ቆሞ እግዚአብሔርን ስለሕዝቡ የማነጋገር ሥራው ተከትሎት አይደለም። ሕግን ወክሎ ሙሴ፥ ነቢያትን ወክሎ ደግሞ ኤልያስ

መገኘታቸው ክርስቶስ በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት መሲሕ መሆኑ ይገለጽና በእነጴጥሮስ ዘንድም ይኸው ይረጋገጥ ዘንድ ነው። (ሮሜ. 3፥21፤ ሉቃ. 24፥27)

ሙሴ በሕይወተ ሥጋ ሳለ እግዚአብሔርና ሕዝቡን ለማገናኘት በመካከል የቆመ መካከለኛ ነበር። (መዝ. 105፥23፤ ዮሐ 1፥17) ከሞተ በኋላ መካከለኛነቱ ተከትሎት ሄዶ ቢሆን ኖሮ ሌላ መካከለኛ ኢያሱ መሾም ባላስፈለገው ነበር። ነገር ግን ከሞተ በኋላ ሙሴ መካከለኛ ሊሆን የማይችል በመሆኑ ኢያሱን በምትኩ በመሾም ያኔ ከሙሴ ጋር እንደነበረ አሁን ደግሞ ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ሲናገር እናያለን። (ኢያ. 1፥5) ከኢያሱም በኋላ አንዱ ሲሞት ሌላው እየተተካ ብዙዎች መካከለኛ ሆነዋል።

በዘመኑ ፍጻሜ ግን የማይሞት ሕያው በመሆኑ የሚተካው ሌላ ሳያስፈልግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ መካከለኛ ሆኗል። (ዕብ. 7፥24-25፤ 9፥15፤ 12፥24፤ 1ጢሞ. 2፥5)

በአጠቃላይ ከምስጋና በቀር ቅዱሳን የሠሩትን ሥራ በሰማይም ያከናውናሉ ማለት አላዋቂነት ነው። በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ጋብቻን አስመልክቶ ቀርቦ ለነበረው የተሳሳተ ጥያቄ መልስ በመስጠት የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር "እንደ መላእክት ይሆናሉ" ነው የሚለው። (ማቴ. 22፥30) ስለዚህ ቅዱሳን በሰማይ ምድራዊ ተግባራቸውን ሳይሆን እንደ መላእክት ሆነው እግዚአብሔርን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመስገንና በማምለክ ሰማያዊውን ሥራ ይሠራሉ። (ራእ. 7፥15)

ሌላ ትርጉም የተሰጠው የራእ. 14፥13 ቃል ትክክለኛ መልእክት ምንድነው? የተነገረውስ ለየትኞቹ ቅዱሳን ነው? የሚለውን ለመረዳት ከቁ 9 ጀምሮ እንመልከት:- ስሙ ባልተገለጸው በ3ኛው መልአክ የተገለጸው ራእይ ወደፊት በሚገለጠው በአውሬው ዘመን የሚከናወነውን ሁኔታ ያሳያል። በዚያ ዘመን ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድና በግምባሩ ወይም በእጁ የአውሬውን ምልክት የሚቀበል ሁሉ የሚደርስበት ዕረፍት የለሽ ዘላለማዊ ስቃይ መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል። በአንጻሩ ደግሞ አውሬውንና ምልክቱን ያልተቀበሉ ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየጠበቁ ኢየሱስን በማመን ጸንተው በጌታ ስለሚሞቱ ብፁዓን ናቸው። መንፈስ ቅዱስም ሲመሰክርላቸው "ከድካማቸውም ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል" አለ። እርግጥ ሁሉም የእግዚአብሔር ቅዱሳን በጌታ አምነው በመሞታቸው ከዚህ

ዓለም ድካም ስለሚያርፉ ተመሳሳይ ገጽታ አላቸው። ይህ ቃል ግን የሚወክለው በአውሬው ዘመን የሚኖሩትን ቅዱሳን ብቻ እንጂ ሌሎቹን ሁሉ አይደለም።

ስለዚህ "ሥራቸው ይከተላቸዋል" የሚለው በክርስቶስ ኖረው የሠሩት መልካም ሥራቸው ዋጋ ስለሚያስጣቸው አይረሳም፤ አይዘነጋም፤ ተከትሏቸው ይሄዳል ማለት ነው።

# ጽድቅ በሥራ ወይስ በእምነት

"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከኔ ጋር አለ።" (ራእ. 22፥12)

በዚህና በመሰል ጥቅሶች እየታገዙ ጽድቅ በሥራ እንደሚገኝ የሚሰብኩ ብዙዎች ናቸው። ጌታ ለፍርድ ሲመጣ ጻድቃንንም ሆነ ኃጥአንን የሚጠይቀው የእምነት ጉዳይ ሳይሆን ሥራን ነውና ስለዚህ ጽድቅ በሥራ ይገኛል ብለው ያምናሉ። (ማቴ. 25፥34-46)

ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ አመለካከት መጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ በሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሚገኝ የተናገረውን ያፈርሳል።

በብሉይ ኪዳን ሰው ጽድቅን በሥራ ለማግኘት ይደክም ነበር። ጻድቅ መሆን ግን አልተቻለውም። ምክንያቱም ጻድቅ ለመሆን አንድም ሳይቀር ሕግን ሁሉ መፈጸም ይጠበቅበታል። ሕግን ሁሉ ጠብቆ በአንዱ በደለኛ ሆኖ ቢገኝ ግን በደለኛ እንጂ ጻድቅ ሊባል ፈጽሞ አይችልም። (ያዕ. 2፥10)

ሰውም በውስጡ ኃጢአተኛ ባሕርይ በመኖሩ ምክንያት ሕግን ሁሉ መፈጸምና በእግዚአብሔር ፊት መጸደቅ ተስኖታል። (ሮሜ 3፥20፤ ገላ. 3፥11፤ 2፥16፤ 2ጢሞ. 1፥9፤ ቲቶ 3፥5)

ሰው በሥራው ለመጽደቅ እንደማይችል የተረዳው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በሙሉ የራሱ የሆነውን ጽድቅ ከሥራ በተለየ መንገድ አዘጋጀለት። (ሮሜ 3፥21-22) ይህም የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ኢሳ. 46፥12-13፤ ኤር. 23፥6፤ 33፥5-6፤ ሮሜ 10፥3-4)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የተዘጋጀ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሲሆን በጻድቅነቱ አንጻር ከኃጢአት ፈጽሞ የተለየና የራቀ ነው። ራሱ ኃጢአተኛ ሆኖ ሌላውን ሊያጸድቅ የሚችል የለምና። (ዕብ. 4፥15፤ 1ጴጥ. 2፥22፤ ዮሐ. 8፥46) ይህም ሲሆን በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ለሰው ያቃተውን ነገር (ሕግ መፈጸምን) ፈጽሞአል። (ሮሜ 10፥4፤ ዮሐ. 17፥4፤ ማቴ. 3፥15) በዚሁ ሁሉ የተደገፈው የእርሱ የጽድቅ ሥራ የሚያምንበትን ኃጢአተኛ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለማጽደቅ በቂ ሆነ። (ኤፌ. 2፥18፤ 3፥12፤ 1፥5፤ ኢሳ. 53፥11፤ 26፥12፤ ሮሜ 5፥19)

ይህ ጽድቅ በኛ ድካም የሚገኝ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነውና ለእኛ ተቆጥሮልን የምንጸድቅበት በእምነት ብቻ ነው። ስለሆነም ወደፊት ሳይሆን ሰው ባመነበት ቅጽበት መጽደቁን ያረጋግጣል። ጽድቅ በሥራችን የሚገኝ ቢሆን ግን አሁን ሊረጋገጥ አይችልም። በእምነት ብቻ በመሆኑ አሁን ተረጋግጦአል። (ኤፌ. 2፥8፤ ዮሐ. 3፥18፤ ሮሜ 5፥1፤ 8፥1፤ 1ቆሮ. 6፥11፤ ሮሜ 4፥5፤ 23-25)

የእግዚአብሔር ጽድቅ ነጻ ስጦታ እንጂ የድካም ዋጋ (ደመወዝ) ባለመሆኑ በሥራ ላይ ተመሥርቶ የነበረውን ጽድቅና ከንቱ ትምክሕት መና አስቀርቷል። (ሮሜ 3፥27-28)

እግዚአብሔር ያፈረሰውን እንደገና አንጾ ጽድቅን በእምነት ሳይሆን በሥራ ለማግኘት መጣር እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ጽድቅ ካለማድረሱም በላይ ከጸጋው ለይቶ ይጥላል። (ሮሜ 9፥30-33፤ ገላ. 5፥4)

ቄርሎስ ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚገኝ መሆኑን ሲያስረዳ:- "እመ ፍጻሜሁ ክርስቶስ ለኦሪት ውእቱ ጽድቅኒ ወያጸድቅኒ በሃይማኖት ባሕቲቱ፤ እስመ ዘዚአሁ ውእቱ ክሂል ለአጽድቆ ዘእምእግዚአብሔር።"

ትርጓሜ:- "ክርስቶስ ለኦሪት ፍጻሜው ከሆነ እርሱ ጻድቅ ነውና በሃይማኖት (በእምነት) ብቻም ያጸድቃል። ከእግዚአብሔር የሚሆን የማጽደቅ ችሎታ የእርሱ ገንዘብ ነውና።" ብሏል (ሰምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 94)

ጽድቅ የእኛ አንዳች አስተዋጽኦ የሌለበት የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ከሆነ በእምነት ከጸደቅን በኋላ ኃጢአት ፈጽመን ብንገኝ እንኳ ከጽድቅ ተለይተን አንኮነንም፤ ስለኃጢአታችን በተለያዩ ቅጣቶች እንገሠጻለን እንጂ። (1ቆሮ. 11፥32፤ 3፥15፤ 5፥5)

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ያገኘነው ጽድቅ ኃጢአት ስንሠራ የሚወስድብን፥ ጽድቅ ስናደርግ ደግሞ የሚመልስልን አድርገን ከቆጠርን የድካማችን ወይም የጥረታችን ውጤት እንጂ ነጻ ስጦታ መሆኑ ይቀራል።

ነገር ግን እንዲህ ሲባል ጽድቅ በእምነት ብቻ ነው የሚገኘው ብለን ሁልጊዜ በኃጢአት እንድንኖር ለማደፋፈር አይደለም። (ሮሜ 6፡1-2) እግዚአብሔር ለምን ከእኛ ባልሆነ ነገር አጸደቀን? ብለን ስንጠይቅ ፍሬ ሳናፈራ እንዲሁ በቅጠል ብቻ እንድንታይ አለመሆኑን መረዳት አለብን። እርግጥ በትክክል በእምነት ከእግዚአብሔር ዳግመኛ የተወለደ ሰው የእግዚአብሔር ጻድቅ ዘር በውስጡ ስለሚኖር ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም። (1ጴጥ. 1፡23፤ ዮሐ. 1፡13፤ 1ዮሐ. 3፡9) አዳማዊው አሮጌ ሰው በእምነት ተሰቀለ እንጂ ሙሉ በሙሉ ገና ከውስጡ ስላልተወገደና ከዐዲሱ ሰው ጋር ስለሚቀዋወም በዚህ መሀል ኃጢአትን ቢያደርግ እንኳ በእውነተኛ ንስሓ ኃጢአቱን ከእርሱ ያርቃል። (1ዮሐ. 1፡8-9)

ከዚህ ውጪ ግን በእምነት ጸድቄአለሁና አልኮነንም እያለ ሁልጊዜ ኃጢአትን በተደጋጋሚ የሚፈጽም ክርስቲያን ጸድቄአለሁ በማለት ራሱን ከሚሸነግል አለመጽደቁን ሊያጤነው ይገባል። (1ዮሐ. 3፡4-6፤ ማቴ 7፡21-23)

ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ መሆኑን ተመልክተናል። <u>ይህ እምነት ምን ዓይነት እምነት ነው? ቢባል በፍቅር ሆኖ የሚሠራ ወይም በሥራ የሚገለጽ መሆን ይኖርበታል።</u> (ገላ. 5፡6፤ ያዕ. 2፡20-26) እምነታችን የሚሠራ እምነት ሊሆን የሚችለው ደግሞ በአመንበት ቅጽበት በክርስቶስ የወይን ግንድነት ላይ የተጣበቅን ቅርንጫፎች ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው። የዚህን ጊዜ ሕግን ሁሉ የምንፈጽምበት ጸጋ እግዚአብሔር በወይኑ ግንድ በክርስቶስ በኩል ወደ ቅርንጫሮቹ ወደኛ ስለሚተላለፍ እምነታችን እግዚአብሔር የሚከበርበት የሥራ ፍሬ ይታይበታል።

በክርስቶስ የማይኖር ክርስቶስም የማይኖርበት አማኝ ግን የሥራ ፍሬ አይኖረውም። አለኝ ቢል እንኳ እግዚአብሔር የማይደሰትበት ይሆናል። (ዮሐ. 15፡5-8)

ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬን ማፍራት እንደማይችል ሁሉ ሰውም ያለክርስቶስ መራራ ዛፍ ነውና መልካም ፍሬን ሊያፈራ አይችልም። በሥራ የማይገለጽ እምነት የሞተ እንደሆነ ሁሉ ያለክርስቶስ በራሳችን ጥረት እንሠራለን የምንለው ሥራም የሞተ ነው። (ማቴ. 7፡17፤ 12፡33-34፤ ዕብ. 9፡14)

አባታችን አብርሃም ጽድቅን በእምነት ካገኘ በኋላ ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ እምነቱን በሥራ ገልጿል። (ሮሜ 4፥3፤ ያዕ. 2፥21-23)

ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ እንደሆነ ሁሉ በሥራ ፍሬ ደግሞ የጽድቅና የሕይወት አክሊል (ሽልማት) ይገኛል። በክርስቶስ ያመኑ ቅዱሳን በእርሱ ኖረው እስከሞት ድረስ በታማኝነት የተጋደሉት ለዚሁ ሽልማት እንጂ በሥራቸው ለመጽደቅ ብለው አልነበረም። በሌላ አነጋገር ስለጸደቁ መልካም ፍሬን አፈሩ እንጂ ለመጽደቅ ብለው አይደለም። (2ጢሞ. 4፥6-8፤ ራእ. 2፥10፤ 1ቆሮ. 9፥24-27፤ 1ጴጥ. 5፥4)

ይህም በራእ. 22፥16 እንደተገለጸው እያንዳንዱ በክርስቶስ ኖሮ እንዳፈራው የሥራ ፍሬ መጠን የሚከፈል ደመወዝ ነው።

የመልካም ሥራ ስልቱና ዐይነቱ ብዙ ቢሆንም ሌላውን ሁሉ አጠቃልለው የሚይዙት የራስን ሕይወት በነገር ሁሉ ከኃጢአት ለይቶ በቅድስና መምራትና ለሰዎች ወንጌልን መስክሮ ሰዎችን ከሚመጣው ጥፋት መታደግ ነው። እነዚህ የሕይወት አክሊልን ያስጡናል። (1ተሰ. 4፥4-5፤ 1ቆሮ. 5፥0፤ ፊልጵ. 1፥23፤ 4፥1፤ 1ተሰ. 2፥19፤ 2ቆሮ. 9፥17)

አንዳንዶቸ ቅ/ጳውሎስ "ጽድቅ በእምነት ይገኛል" ያለው ቅ/ያዕቆብ "እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው" ካለው ጋር ይምታታባቸዋል። የሁለቱ አሳብ ግን ተስማሚ ነው። ያዕቆብ "እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው" ማለቱ በሥራ ጽድቅ እንደሚገኝ ለማመልከት ሳይሆን ትክክለኛ እምነት የሚሠራ እምነት መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህም ከጳውሎስ መልእክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። (ገላ. 5፥6)

ስለዚህ ከዚህ መንገድ ውጪ ጽድቅ በሥራ ይገኛል የሚሉትን ሳንሰማ በክርስቶስ የጽድቅና የቤዛነት ሥራ ብቻ በማመን እንደጸደቅን ቆጥረን በክርስቶስ በመኖር መልካም ሥራን እየሠራን ሙሉ ደመወዝን ለመቀበል ከፊት ይልቅ እንትጋ! (2ዮሐ .10)

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ፤
እናመልከው ዘንድ እኛን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን፤
አሜን

ተፈጸመ